


ይድረስ
ለኢሕዴግዬ !
ጉዳዩ፤ እየመሸ
መሆኑን
ስለማሳወቅ !

አቤ ቶኪቻው



አዲሱ ፀዋጅና
ያልተሰሙ
የዜጎች
ድምፆች

ኑብዩ ሲራክ



ጠቅላይ
ሚኒስትሩ
አልዋሹም ¡

ወሰንሰገድ ገ/ኪዳን


በሀሳብ ልዕልና እናምናለን!

# አዲስ ገጽ

ቅፅ 1 ቁ 04 ታህሳስ 23/2008 ዓ.ም ዋጋ 12 ብር


<<በኢትዮጵያ
ምሁራን ዘንድ በጣም
የአድርባይነት መንፈስ
አለ>>

አቶ በቀለ ገርባ /የኦፌኮ ምክትል ሊቀመንበር/

## <<የኦሮሞ ሕዝብ በአንድነትና በቅንጅት መብቱን ለማስከበር በመንቀሳቀሱ እኮራበታለሁ>>



<<ሕወሓት ያነን ኮንዶሚኒየም
ንዶት ወደ ትልቅ እስርቤት
ቀይሮታል። ጣሪያው ላይ እነአባይ
ፀሐዬ እና ቡድናቸው ተኮፍሰው
በሩን ደግሞ ኦሕዴድ እና ብአዴን
በዘብኞነት ተቀጥረው እየተናቁ እና
እየተገላመጡ ቆሽታቸው እያረረ ጊዜ
እየጠበቁ ያለበት ሁኔታ ይታየኛል>>

አቶ ጃዋር ማሐመድ



ሐሳብን የመግለጽ
ነጻነት እስከ
ማበሳጨት

በፍቃዱ ዘ ኃይሉ



<<ለሕጋዊ>>
ሕግ አልባ
ምላሽ !

ይድነቃቸው ከበደ



የ<<መባ>>
ፊልም አፍራሽ
ስጦታዎች

ዩሐንስ ሞላ

# የመጀመሪያ ዕትማችን



አዲስ ገጽ

ቅጽ 01 ቁ 01 ሀዳር 2008 ዓ.ም

በጀንሆይ መንገድ

<<የኢሕአዴግ የፍትሕ ሥርዓት አስመሳይ ስለሆነ፤ በውስጡ ላሉት ሁሉ አስጨናቂ ነው>>

<<የኢትዮጵያን የፍትሕ ሥርዓት ያስተረው፤ የሙስሊሙ ፍጹም አርቃትን ያስተለጠበር ኢሕመድ እንቅስቃሴና የእንአስጠበር ኢሕመድ መልክ አንቅስቃሴ በፍ/ቤት እና በሕጋዊ መልኩ ያደርጉት አንቅስቃሴ መሆኑን አምናለሁ>>

ተማም አባቡልጉ /ጠበቃ/

አዲሁዝ አበካላ ድረስ መሪባችን ይቀጥላል!

NEWS

World

Drought takes terrible toll in Ethiopia

ያልተገረሁ የመሪዎቻችን አንደበቶች

የኢትዮጵያውያንን ሐሳብ ለማፈን የሚፈፀሙ ደባዎች

የጠ/ሚ ኃይለማርያም ንግግር እና ሀገርን ሊውጥ ያቆበቀበው ኔትወርክ

የለውጥ አዋጅ...... የለውጥ ዐይነቱ! አንዲህያም ያለ ነገር ይገባም!

## ማውጫ


አዲሱ ዕዋጅና ያልተነገረው የዜጎች ድምፅ 11





የኢትዮ-ሱዳን ድንበር ጉዳይ 6

ብሔርንትና ዜግነት 9

የተረሳው መንገድ 10

የቻን ቢ መንገድ 12

የንጻነት አሜኬላ 21

የራስ መድኃኒት ሽጠ ... 24

የአገዛዙ የበቀል ጅራፍ 29

ክፍት የሥራ ቦታ ... 30

ሰባራ ታሪክ፤ ሰባራ ትወና ... 31

ዝምታ ሰላም አይደለም፤ ... 32

# ርዕስ አንቀፅ

## የጅምላ እስርና የተቀናጀ ድራማ /Orchestrated Drama/ መፍትሔ አይደለም!

በሀገራችን የተከሰተውን የሰሞኑን ቀውስ ተከትሎ በርካታ ዜጎች ለእስር እየተዳረጉ ነው። ከፖለቲካ ፓርቲዎች በኩልም የኦፌኮ እና የሰማያዊ ፓርቲ አመራሮች እንዲሁም አባላቶች ወደ ወህኒ ወርደዋል። ከነዚህ በተጨማሪም የሰማያዊ ፓርቲ ልሳን «ነገረ-ኢትዮጵያ» ዋና አዘጋጅ የሆነው ጋዜጠኛ ጌታቸው ሽፈራውም በቅርቡ መታሰሩ ይታወቃል። በሀገሪቷ የተለያዩ ክፍሎች የሚገኙ በርካታ ዜጎች (ተማሪዎች፣ መምህራን፣ ጋዜጠኞች፣ ድምፃዊያን፣ የሀገር ሽማግሌዎች...) በገፍ ለእስር እየተዳረጉ እንደሚገኙ እየገለጸ ይገኛል።

ነገር ግን፣ ይህ የጅምላ እስርና ውክቢያ ከመፍትሔነቱ ይልቅ የችግሩን ምንጭ ደብዛ ለማጥፋት የሚደረግ ከንቱ ሙከራ እንደሆነ በግልፅ ይታያል። አግባቡ ሰላማዊ ዜጎችን በግፍ የገደሉና አካል ያጎደሉ፣ ተመጣጣኝ ያልሆነ የአፀፋ እርምጃ የወሰዱና ያስወሰዱ የጦር ሰራዊት አዛዦችና አባላትን ተጠያቂ ማድረግ ሲገባው፣ ተጠቂ የሆኑትን ንጹሃን ሰለባዎችን ወደማሳደድ ገብቷል። ይህም የችግሩን ምንጭ ለማድበስበስና ከተጠያቂነት ለማምለጥ የሚደረግ ውጤት አልባ ሙከራ ነው።

ይህን አይነቱን የአፀፋ እርምጃ ከ20 በላይ ለሆኑ ዓመታት ስናስተውለው የነበረ ነው። ይሁን እንጂ ያው የተለመደ አካሄድ አዲስ ውጤት ያመጣል ብሎ የሚጠብቅ የለም። «አሮጌ ወይን በአዲስ አቁማዳ» እንዲሉ ዛሬ በኃላፊነት ላይ የተቀመጡ ሰዎች ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝን ጨምሮ በ1997ቱ የድሕረ-ምርጫ ቀውስ የተወሰደውን አይነት ተመሳሳይ ኢ-ሰብዓዊ እርምጃ በ2007ቱ ምርጫ ማግስት ወስደዋል። ይህም አግባቡ ችግሮችን ለመፍታት የጠመንጃ አፈሙዝን እንደብቸኛ አማራጭ አድርጎ መውሰዱን ያመለክታል።

ነገር ግን፣ ይህ አካሄድ ችግሮችን የበለጠ ሲያወሳስብና ለጊዜው ሲያዳፍን እንጂ፣ ችግሩን ከስረ-መሰረቱ ሲቀርፍ አልታየም። አግባቡ ለሚነሳበት ተቃውሞ የሚሰጠው የመልስ-ምት የተለደመና ለችግሩ እልባት የሚሆን እንዳልሆነም በግልፅ ታይቷል። ይህ አይነቱ የተለመደ አካሄድ ወይም ታክቲክ ደግሞ ችግሩን ካለመቅረፉ በተጨማሪም፣ ሀገሪቷን ወደ ባሰ ቀውስ እንድታመራ የሚያደርግ ነው።

በሀገራችን ውስጥ ቀውስ በተከሰተ ቁጥር ወደ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና በፖለቲካው ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ወደሚያደርጉ ዜጎች ነገሩን ማዞርና ማላከክ ተለምዷል። ይህም እየሆነ ያለው፦ በየደረጃው ያሉ ካድሬዎች በሚጠሯቸው የይስሙላ ስብሰባዎች ላይ የተጠኑ ዲስኩሮችን በሚያሰሙ 'አንዳንድ ኗሪ' ተብዬዎች ነው። ይህ ግን ተጠያቂነትን ከራሳቸው ላይ ለማውረድ በሚውተረተሩ ብልሹ የአግባቡ ካድሬዎች የሚከወን የተቀናጀ ድራማ/Orchestrated Drama/ ነው። በመሆኑም ይህን አድሚ ልካችንን ስናየው የኖርነውን ያረጀ ታክቲክ እንድንቀበል መመኘት በራሱ በትልቁ መሞኘት ነው።

አግባቡ በሀገራችን ውስጥ የተከሰተው ቀውስ የእውነት ካሳሰበው፣ በግፍ የገደላቸውን ዜጎች ቤተሰቦች በይፋ ይቅርታ በመጠየቅና ወንጀሉን የፈፀሙትንም በየደረጃው ለፍርድ በማቅረብ ለፍትሕ መቆሙን ለሕዝብ በግልፅ ሊያሳይ ይገባል። «ብሔራዊ ቀውሱንም» በጠረጴዛ ዙሪያ ተነጋግሮ መፍታት መቻል የአንድ ኃላፊነት የሚሰማው መንግስት መገለጫ ነው። በመሆኑም ይህ አይነቱ «መንግስት እና የበሰለ አመራር» ካለ ይህን ችግር ወደ ዜጎች ከማላከክ ይልቅ አሁኑኑ ወደ ራሱ በመመልከት ተግባራዊ ቆራጥ እርምጃ መውሰድ አለበት ሲል የ«አዲስ-ገጽ» ዝግጅት ክፍል በፅኑ ያሳስባል!

አዲስ ገጽ

በኢድፋይ ህትመትና ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግል ማኅበር በፖለቲካ ፣ በኢኮኖሚ፣በማኅበራዊና በኪነ-ጥበብ ጉዳዮች ላይ በማተኮር በየ15 ቀኑ ለህትመት የምትበቃ መጽሄት

ዋና አዘጋጅ፦
ኤልያስ ገብሩ
Elias.geberu@addisgets.com
የካ ክ/ከተማ
ወረዳ11፣የቤ.ቁጥር አዲስ
ሞባይል፦251-912 064882

አምደኞች
በቃሉ አጥናፉ ታዬ (ዶ/ር)
ኢድመን ተስፋዬ
ኤፍሬም ስዩም
ሀብታሙ ተሰማ ጂ.
ደረጀ ታደሠ
ዳንኤል ቢ.
ፍርድያውቃል ንጉሤ
ኢዩኤል ፍስሃ
ምስክር አወል
መስከረም ያረጋል
ሃና ረጋሳ
አብርሃም ፈቃደ

የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ
ወረዳ 02፣የቤት.ቁ አዲስ
ስልክ፦ 25-111 8898912
ሞባይል፦251-911634307
ድረ-ገጽ፦www.addisgets.com
ፌስ ቡክ፦facebook.com/addisgets
ኢ-ሜይል፦ info@addisgets.com

ግራፊክስ ዲዛይነር፦ሃናሲምስ አቢ

አታሚ፦
ናታን ማተሚያ ቤት
አራዳ ክ/ከተማ
ወረዳ 03 የቤት.ቁ 1062





# እውነትታችንን እንጋፈጥ!



ኤልያስ ገብሩ

እውነት በሰው ልጆች ልብ እና አንደበት አርሳ የምትገኝ ሀልው ናት። ቃሏ በመንፈሳዊ እና በምድራዊ እሳቤ እና ዕውቀት ተተርጉማ በተለያዩ መንገዶች ትገለጻለች። እውነት በሰው ልጆች እና በተፈጥሮ ሀልወና ውስጥ ተገልማም ሆነ ተደብቃ ትገኛለች ብሎ ማሰብ እንደሚቻል እረዳለሁ።

የሰው ልጅ ከፍጥረት ታሪኩ ጀምሮ፣ እውነቱ! ሳሰው ነገር በዕምነት ሲወድቅ ሲነሳ፣ ሲደማ ሲቆስል፣ ሲታሰር ሲፈታ፣ ሲገድል ሲገደል፣ ሲያዝን ሲደሰት፣ ኖሯል። አሁንም እየኖረ ይገኛል። እውነትን እያወቀት ሸፍነው ወይም አዳፍነው የኖሩ እና የሞቱ የሰው ልጆች ነበሩ፣ አሉ፣ ይኖራሉም። ሰዎች በግልም ሆነ በቡድን «እውነቴ!» ወይም «እውነታችን!» የሚሏቸውን ነገሮች የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ። አያንዳንዳችን የሰው ልጆች ስንፈጠር ጀምሮ በልባችን ውስጥ የተቀመጠ እውነት አለ ብዬ መረዳት የሚቻል ይመስለኛል። ያን እውነት፣ ማወቅ አለማወቅ፣ መፈለግ አለመፈለግ፣ መገንዘብ አለመገንዘብ፣ ማውጣት አለማውጣት፣ ማመን አለማመንና ማኖት አለማኖት በግለሰቡ የሚወሰን ይሆናል።

በሕይወት በመኖቻው የተፈጠሩለትን እውነት አውቀው በመኖር፣ ለራሳቸው፣ ለቤተሰቦቻቸው፣ ለወገኖቻቸው፣ ለሀገራቸውና ለዓለም ታላቅ አበርክቶት የሰጡ ሰዎች አሉ። እነኚህ ክብር ይገባቸዋል። ከእነኚህ መሀከል ተገቢውን ክብር ያገኙ እንዳሉ ሁሉ፣ ክብር የተነፈጉም በርካቶች ናቸው። ለነገሩ፣ ለእውነት የሚኖረውና የሚሰራው ክብር ለማግኘት በሚል ስሞቂ ቀመር መሆን የለበትም። የተፈጠሩለትን እውነት አውቀው ለበጎ ዓላማ ሊሰሩ አቅደው ከመንገዳቸው በተለያዩ ምክንያቶች የተሰናከሉም ይኖራሉ። ተፈጥሯዊ እውነታቸውን ለጥቅም ብለው (ሳያምኑበት) ለሌሎች አሳልፈው የሰጡም ቁጥራቸው ቀላል ላይሆን ይችላል።

ለዚህ ጽሑፍ መንደርደሪያ ይሄን ካልኩኝ በኋላ፣ ሰዎች እውነቱ በምንላቸው ነገሮች ላይ ይበልጥ ትኩረት መስጠት እንደሚገባን ለማስገንዘብ ነው ትልቁ መሻቱ! የግል እውነታችንን ያወቅን ኢትዮጵያኖች፣ በወትሮ ሀቃችን ላይ እንቁም! እውነታችንን ያለወቅን ደግሞ ለራሳችን ጥሬት ያለው ጊዜ ሰጥተን፣ ውስጣችንን በመመርመር ውስጣዊ እውነታችንን ለይተን እንወቀው። ከእኛነታችን ውጪ ያሉ ነገሮችን ለማወቅ በወትሮ እንደምንሻ ሁሉ፣ በቅድሚያ የእኛነታችንን ቁልፍ እውነታም እንወቀው። ይሄንን ስናውቅ፣ የተደበላለቀ ስሜት ሊሰማን ይችል ይሆናል። በዚህ ጊዜ አለመደንገጥ ወሳኝነት አለው። እውነታችን ከእኛነታችን ውጪ ተሻግር ለሌሎች የሰው ልጆች መልካም ጥቅም እንዲውል መሺታችን አይቀርም ይሆናል።ከለመድነው ውጪ አዲስ ህይወትን ለመኖር ስናስብ፣ አዕምሯችን ከለመደው ውጪ አዲስ ነገርን ለመከወን ሲያስብ፣ ከዚህ ቀደም ወደለመድነው ተግባር እንድንመለስ ሊሰበን ወይም ሊጎትተን ይችላል። ሆኖም መሳሳቡ የሚገጥም ነውና በተቻለ አቅም ውስጣዊ ሀይልን አሰባስቦ አዲሱ ለውጥ ላይ የትኩረት አቅጣጫን ማድረግ አስፈላጊ ነው።

ውስጣዊ እውነተኛ ሀይል «መሻትህን አድርግ! አትፍራ! ለእውነትህ ኑር!» የሚል ድምጽ ሲያሰማ አዕምሮህ «በመሻትህ መንገድ ላይ ችግር አለ። አስቸጋሪ ነገር ይገጥምሃል፣

> "ከፈታኙ እና ከአስቸጋሪው የችግር ወላፈን፣ ወጀብ ማዕበልና ነውጥ በኋላ ጸጥ ያለ ሰላም መኖሩም እውነት ነው። በዚህ ሰላም ውስጥ በረዥሙ ተንፍሶ ያለፋትን ከባድ ጊዜያቶች በአፍታ ትውስታ ወደኋላ ተመልሶ በአይን ሀሊና መቃኘትም ሰውን ይሆናል። የተቀላቀሉ የደስታና የሀዘን፣ የሙሉነትና የውድቀት ስሜቶች ይስተናገዳሉ። ከደስታው ጋር አብሮ የመደሰት፣ በችግሮች ሰለባ የሆኑትን በማሰብ ከውድ ወገኖች ጋር አብሮ ማዘንም አንዱ የድል ማግስት እውነታ መሆኑ አይቀሬ ነው።

ተጠው! ...» ወዘተ. የሚሉ አፍራሽ እና ሀይልህን የሚያዳክሙ መልዕቶችን ይመለሰልሃል።

በአዲሱ የእውነት መንገድ መንቀሳቀስ ስትጀምር ከጠበቅኸው ባሻገር ያልጠበቅኸው ተግዳሮቶች ሊገጥሙህ ይችላሉ። ይሄንን ካወክ ተግዳሮቶቹን ታልፋቸዋለህ። በመንገድህ ከዚህ ቀደም ያላስተዋልካቸው የተለያዩ ነገሮች እየተገለጡልህ ይመጣሉ። ውስጥህም በተለያዩ መልክም ነገሮች እየሞላ እና እየጠነከረ ይሄዳል።ይህ ውጤት በራስህ እና በሥራህ ላይ ያለውን እምነት ይጨምራል።

የራስህን እውነት ማንም ሊኖርልህ አይችልምና በእውነትህ መንገድ ላይ ያሉት ሁሉ በቅድሚያ ያንተው መሆናቸውን እመን።

በእውነተኛ መንገድ ላይ መሆን አለመሆንህን ለማረጋገጥ ሊኖሽህ የማይችለውን እውነተኛ የስነስት ውስጣዊ ስሜትህን አዳምጠው። ቀልብህንም ተከተለው። በራስህ እውነት ስትቆም ውስጣዊ እርጋታ፣ የሀሳብ ስከነት፣ የስሜት መስተካከል፣ የዓላማ የጥሬት ዕይታ፣ የማሸነፍ ወኔ፣ የድል አድራጊነት ጽናትና የርዕይ ቁርጠኝነት ይኖርሃል።

...በአንድ ሉዓላዊ ሀገር ውስጥ የሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች፣ የተለያዩ ዓይነት ለውጦችን ይሻሉ። የሚመርጡትን ለውጥ መሻት አግባብ ነው። ለውጡ የሚጠይቀውን ተግባራዊ ክንውን ለማድረግ ማቀድ እና ተግባራቱን መፈጸም ለውጥ ከሚሹ ግለሰቦች እና ቡድኖች ይጠበቃል። የምትሻው ለውጥ ከራስህ ጀምሮ እስከሀገርህ ብሎም መላው ዓለም ድረስ ሊዘልቅ ሊሆን ይችላል። የምትሻው ግላዊ ወይም ሀገራዊ ለውጥ መሆን አለመሆኑን የምታውቀው አንተው ነህ! የለውጥ መሻትህ ተሳክቶልህ ከሆነ አሰየው! ሰው ነህና ሌላም መልካም ለውጥን እሻ! ለውጡንም ዕውን አድርግ።

«የምትፈልገውን ነገር ለማግኘት ከልብህ መሻቱ ሊኖርህ ይገባል። ካለዚያ መልሱ ሁሌም የለም/አይሆንም ነው። ወደፊት ካለተራመድክ ካለህበት ስፍራ ፈቀቅ አትልም» አሊሻ መሃመድ ነሐሴ 08 ቀን 2007 ዓ.ም

በራስ ቡክ ገጹ ማስፈሩን አስታውሳለሁ። የዚህ ግለሰብ ሃሳብ እውነትነት አለው።

እውነትን ተከትለው ለለውጥ መራመድ ሲጀምሩ፣ ወደውድቀት የሚያንደረድር ተግዳሮት ሊገጥምም ይችላል። ነገር ግን፣ ከውድቀት ሂደት እና ከውድቀት ጠል ላይ ሳለመገኘት በአንክሮ ማሰላሰል ቀዳማይ መፍትሄ አድርጎ መውሰድ ብልህነት ነው። የትኛውም ችግር የራሱ እቻ መፍትሄ እንዳለው ማመንም ያሻል። የውድቀት ቁልቁለቱን ካየነው፣ ቁልቁለቱም እንደርድሮ ወደጥልቁ እንደሚያስገባን ከተረዳንና ውድቀቱን መቆጣጠር ተስኖን ሃይላችን ገለሎ ከሰኛን፣ ፍጻሜው ሕልውና አልባ ሞት መሆኑ እሙን ነው። በመሆኑም የውድቀቱን መንገድ የሚቀለብስ አካሄድ አውቆና ሰይቶ በመምረጥ በተግባር እንቅስቃሴ ውስጥ መገኘት ታላቅ እርምጃ ነው።

የሚገጥሙንን ችግር እና ከባድ ወጀቦች ፊት ለፊት፣ መሰመርን ሳይለቁ መጋፈጥ እንደአንድ መፍትሄ ልንወስደው እንችላለን። ወደችግሮቹ ወጀብ ስንገባ፣ ወጀቡ አይሎ ሲመጣ (መምጫው አይቀርም) በተወሰነ ደረጃ ገቶ ብሎ የሚደኛውን ወጀብ፣ ነውጥና ማዕበል በማሳለፍ ውስጣዊ እንቅስቃሴን ጠንክሮ አለማድረግ ጥሩ ብልሃት ነው። ፈታኝና ጎታች ሁነቶች ጠልፈው እንዳይጥሉንና የውድቀት ጠል ላይ እንዳያሳርፉን እጅግ መጠንቀቅ፣ ሀይልን መሰብሰብና በመንፈስ ብርታት መጠንከር ይገባናል። በተጨማሪም የወጀቡን ሀይል በተግባር በመለየት ወደታች ገቶ ሳይሉ የማዕበሉን ግፊትና ምት ለመገዳደር መምከርና ጥረት ማድረግ የሚያፈልግበት ጊዜም ይኖራል።

የችግሩ ግዝፈት ካየለ ደግሞ ወደውስጥ ይበልጥ ገባ ብሎ ሚዛንን በጥንቃቄ በመጠበቅና በዝምታ ውስጥ ለተወሰኑ ጊዜያቶች በመቆየት ዳግም ወደላይ ቀና ብሎ በብልሃት ችግርን ማለፍ ጀግንነትም ጭምር ነው። ተግዳሮትን ተቋቁሞ ወደእውነታችን መገኘ ትልቅ ቁርጠኝነት የሚጠይቅ ተግባር መሆኑ ሀቅ ነው። ይሄ የሥነልቦና ጥንካሬን መፈተኑ አይቀርም። በቀመሰት መስመር ላይ ጸኑ የመሆን ደረጃን ለመለየትም ይረዳል። በመኖር እና ባለመኖር መካከል ያለውን ቀጭን ክር ከጊዜ ትንፍ አስወጥቶ በግልጽ የሚሳይ መንጽርም ነው።

ከፈታኙ እና ከአስቸጋሪው የችግር ወላፈን፣ ወጀብ ማዕበልና ነውጥ በኋላ ጸጥ ያለ ሰላም መኖሩም እውነት ነው። በዚህ ሰላም ውስጥ በረዥሙ ተንፍሶ ያለፋትን ከባድ ጊዜያቶች በአፍታ ትውስታ ወደኋላ ተመልሶ በአይን ሀሊና መቃኘትም ሰውን ይሆናል። የተቀላቀሉ የደስታና የሀዘን፣ የሙሉነትና የውድቀት ስሜቶች ይስተናገዳሉ። ከደስታው ጋር አብሮ የመደሰት፣ በችግሮች ሰለባ የሆኑትን በማሰብ ከውድ ወገኖች ጋር አብሮ ማዘንም አንዱ የድል ማግስት እውነታ መሆኑ አይቀሬ ነው።

እዚህ የማሸነፍና የድል አድራጊነት ሀልው ላይ ለመገኘት ለዓላማ መጽናት እና እውነትን በድፍረት መጋፈጥ ትልቁን ሥፍራ ይይዛሉ። ለምን? ቢባል አቅምን፣ ሞራልን፣ ስብዕናን፣ የዓላማ ጽናትን፣ ርዕይን አለመሳትን፣ ለችግሮች አለመሸነፍንና የሚፈታተኑን ቁርጠኝነትን ስለሚጠይቅ።

ቸር እንሰንብት!

# ጠቅላይ ሚኒስትሩ አልዋሹም ¡



ወሰንሰገድ ገ/ኪዳን

እንደ መግቢያ

ለዚህ ጽሑፍ የመረጥኩት ርዕስ ብዙዎችን ሊያስደንቅ ይችላል። ነገር ግን የሚያስደንቅ አይደለም። ቢያንስ ቢያንጂ በ«አንድ» ጉዳይ ላይ ግን አልዋሹም፤ ያ ጉዳይ ምንድነው? ላስታውሳችሁ።

ትዝ ይላችሁ እንደ ሆነ፣ በወርሃ ጥቅምት 2008 ዓ.ም መጨረሻ፣ ከወሩም የመጨረሻ ሳምንት፣ ጠቅላያችን ከቱባ ባለሥልጣኖቻቸው ጋር በጽሕፈት ቤታቸው «ለየት» ያለ ስብሰባ አካሂደው ነበር። ያ ስብሰባ በሀገሪቱ እጅግ የሰፋውና የተንሰራፋው የሙስናና የመልካም አስተዳደር ችግር ነበር ማጠንጠኛው። ለስብሰባቸው መነሻ ይሆን ዘንድም የችግሩን ግዝፈትና ጥልቀት የሚያሳይ «ጥናት» ቀርቦላቸው ነበር። በዚህ መሠረት ያደረጉትን ውይይት በቴሌቪዥን መስኮት አይተቻኋል/አይተናል።

ጠ/ሚኒስትር ኃይለማርያምና ባለሥልጣኖቻቸው በስብሰባቸው በሀገሪቱ የተንሰራፋው ሌብነት ልክ እና ለከት ማጣቱን ደግመው ደጋግመው ነበር የነገሩን። የችግሩ ግዝፈትና ጥልቀት በ«ኔትወርክ» የተሳሰረ መሆኑን፤ በይሉኝታ-የለሽ ዝርፊያ ውስጥም «ደላሎች» መሰግሰጋቸውን ነበር የደሰኮሩልን። በመጨረሻም ችግሩን ከሥሩ ነቅለን እንጥላለን፤ ይህንን ማድረግም «የሞት የሽረት» ጉዳይ ነው ነበር ያሉን።

ከዚህ በኋላ ነው የመጨረሻው መጨረሻ፣ የስብሰባው ማሳረጊያ የሆነው፣ ጠ/ሚኒስትር ኃይለማርያም «ያልዋሹበት» ንግግር ተፈልቅቆ የወጣው። «አልዋሹም» ያሰኘኝም ይኸው ንግግራቸው ነው፤ «እዚህ ሀገር ትልቅ ፈተና የሚሆነው…» አሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ «… እዚህ እናወራለን እንጂ ከዚህ ከወጣን በኋላ የራሳችንን ኔትዎርክ እንክላከላለን።» አሉ ኮምጨጭ፣ ኮስተር ብለው።

እውነታቸውን ነው። እዚያው ከቱባ ባለሥልጣኖቻቸው ጋር አውሩ እንጂ፣ ከስብሰባው ከወጡ በኋላ ምንም የሆነ ነገር የለም፤ ምንም አልተደረገም። ታዲያ ከዚህ በላይ «መራር እውነት» አለ? የለም። ምክንያቱም ከጠቅላይ ሚኒስትሩም ሆነ ከቱባ ባለሥልጣኖቻቸው ዲስኩር ባሻገር፤ እንዳችም ጠብ ያለ ነገር የለም። ይኸው ወራቶች ተቆጠሩ። የሚታይ፣ የሚጨበጥ የተወሰደ እርምጃ የለም። ጠብ የሚል ነገር ያለም አይመስልም። ምናልባት ጠብ የሚል ነገር አለ ከተባለ፣ ለፖለቲካ ጨዋታቸው ይጠቅማቸው ዘንድ በሕዝቡ አፍ ላይ ያስቀመጧቸው «ኔትዎርክ» እና «ደላሎች» የሚሉ ቃላቶች ናቸው። እነዚህ ቃላቶች ደግሞ አስደንጋጩን ታሪክ ነው ያስታወሱኝ፤ «የኮርፖሬቶክራሲው ቅጥረኞች» የሚለውን ታሪክ።

> ❝ ከጠቅላይ ሚኒስትሩም ሆነ ከቱባ ባለሥልጣኖቻቸው ዲስኩር ባሻገር፤ እንዳችም ጠብ ያለ ነገር የለም። ይኸው ወራቶች ተቆጠሩ። የሚታይ፣ የሚጨበጥ የተወሰደ እርምጃ የለም። ጠብ የሚል ነገር ያለም አይመስልም። ምናልባት ጠብ የሚል ነገር አለ ከተባለ፣ ለፖለቲካ ጨዋታቸው ይጠቅማቸው ዘንድ በሕዝቡ አፍ ላይ ያስቀመጧቸው <<ኔትዎርክ>> እና <<ደላሎች>> የሚሉ ቃላቶች ናቸው

## «ቅጥረኞቹ»

«የኮርፖሬቶክራሲው ቅጥረኞች» ታሪክ ዓለምን ያስደነገጠ ድንበር ዘለል የኢኮኖሚ ውድመት ፈጻሚዎችን ምስጢራዊ ተግባር ያጋለጠ ነው። ለበርካታ ዓመታት ከቅጥረኞቹ አንዱ ሆኖ ወንጀሉን ሲፈጽም የነበረው ፐርኪንስ፣ «Confessions of an Economic Hit Man» በሚል ርዕስ ለሕትመት ባበቃው መጽሐፍ ነው አስደንጋጩን የኢኮኖሚ ደባ ያጋለጠው።

ይህንን አስደንጋጭ ታሪክ የሚያትተውን መጽሐፍ አቶ አያሌው ምትኩ ብሩ «የኮርፖሬቶክራሲው ቅጥረኛ ኑዛዜ» በሚል ርዕስ ወደ አማርኛ መልሰው ለአንባቢያን ጀባ ብለዋል። መጽሐፉ ዓለም-አቀፍ ስምና ዝና ያተረፉ የኃያል ሀገራት ኮርፖሬቶች፣ ድንበር ተሻግረውና ባሕር አቋርጠው የታዳጊ ሀገራትን ሀብት (ኢኮኖሚ) ለመዝረፍ የሚጠቀሙበትን ሥልት አንድ በአንድ ይዘረዝራል። ዓሬኛ ተግባራቸው ምን ምን እንደ ሆነና እስከ ምን ድረስ ሊዘልቅ እንደሚችል ወዘተ. በጥልቀት ይተነትናል። የእነዚህ ድንበር ዘለል የጥፋት መልዕክተኞች ዓሬኛ ተግባርን በአጭሩ እንዲህ ሲል ይገልጸዋል፦

«የኢኮኖሚ አውዳሚ (ኮርፖሬቶክራሲ) ቅጥረኞች፣ በዓለም ዙሪያ ያሉ ሀገሮችን በትሪሊዮን ዶላር የሚቆጠር [ገንዘብ] የሚያጭበረብሩ፣ ከፍተኛ ክፍያ የሚያገኙ ፕሮፌሽናሎች ናቸው። ይህንን ለማከናወን የሚጠቀሙባቸው መሣሪያዎች የሐሰት ፋይናንስ ሪፖርቶችን ማቅረብ፣ የተጭበረበሩ ምርጫዎችን ማከናወን፣ ሰዎች አንዳች ችግር እንዲደርስባቸው ወይም ባለጉዳዩ (ኮርፖሬቶክራሲ) በሚፈልገው ሁኔታ መጥፎና በክህደት የታጀበ ጥፋት እንዲያከናውኑ ገንዘብ መክፈል፣ ኃይልን ወይም ማስፈራራትን በመጠቀም የሀገርን መረጃ ማግኘት፣ የወሲብና የግድያ ወንጀሎችን መፈጸም ወዘተ. ናቸው።»

ይህ ዓለም-አቀፍ ስምና ዝና ያላቸው ኮርፖሬቶች በተጠና ሁኔታ ድንበር ዘለል ወንጀል የሚፈጽሙበት ሥልት ነው። እርግጥ ነው እነዚህ ኮርፖሬቶች ኢትዮጵያ ውስጥ ገብተው የኢኮኖሚ ወንጀል (ውድመት) ፈጽመዋል ማለት የሚያስችል መረጃ የለንም። ይሁን እንጂ «በእኛዎቹ ሰዎች» በተመሳሳይ መልኩ ወንጀሉ አልተፈጸመም ማለት አንችልም። ተፈጽሟልም። ምክንያቱም በሀገሪቱ ሥር የሰደደው እና እጅግ የተንሰራፋው የሙስና ወንጀል፣ ልክና ለከት ያጣው በ«ኔትዎርክ» በመደገፉ እንደ ሆነ በይፋ ተነግሮናል። «ደላሎች»ም ያሉበት መሆኑ የታመነ ጉዳይ ሆኗል። በእኔ ዕይታ እነዚህ «ደላሎች» የኮርፖሬቶቹን ቅጥረኞች ሚና የሚወክሉ ይመስሉኛል።

የእኛዎቹ «ቅጥረኞች» በሙስና መረባቸው ተጠቅመው ጉቦ ይቀበላሉ፤ ጉቦ ያቀብላሉ፤ መሬት ይሸጣሉ፤ መሬት ያሻሽጣሉ፤ ለተባባሪት ሙሰኛ ባለሥልጣን ይላላካሉ፤ ጉዳይ ያስፈጽማሉ፤ የወሲብ ጥማታቸውን የሚያረኩላቸውን ሴቶች እስከ ማቅረብ ድረስ ወዘተ. የከፋ ተግባር ያከናውናሉ ቢባል የሚታብል ሊሆን አይችልም። እነዚህ ቅጥረኞች (ደላሎች) ይህን መሰል ተግባር ሲፈጽሙ እንቅፋት የሚፈጥሩባቸውን ሰው በፈቀቀ መንገድ ከሥራቸው እንዲፈናቀሉ (እንዲገለሉ) ያደርጋሉ፤ ያስደርጋሉ። ሌላም፤ ሌላም፤ ሌላም። እዚህ ላይ ይህን «መሰል ተግባር የሚፈጽሙት እነማን ናቸው?» የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል። ወይም መነሣቱ አይቀርም። ካልተነሣም መነሣት አለበት።

## «ቅጥረኞቹ» እነማን ናቸው?

በዚህ ጽሑፍ «ቅጥረኞቹ» ወይም «ደላሎቹ» እነ እከሌ፣ እነ እከሌ ናቸው ማለት አይቻልም። ምክንያቱም የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሉችን የሚወክሉ ናቸው። «ቅጥረኞቹ» የመንግሥት ቢሮ ኃላፊዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ኢንቬስተሮች ሊሆኑ ይችላሉ። ተራ ነጋዴም ሊሆኑ ይችላሉ። የማስታወቂያ ሥራ ድርጅት ባለቤቶችም ሊሆኑ ይችላሉ። ታዋቂ የሚባሉ የኪነ-ጥበብ ሰዎችም ሊሆኑ ይችላሉ። ሌላም፤ ሌላም ሊሆኑ ይችላሉ። ምንም ይሁኑ ምን፤ ማንንም ይወክሉ ማንንም፤ ከላይ የተጠቀሱትን ዓሬኛ ድርጊቶች የመፈጸምና የማስፈጸም ኃይል ያላቸው ናቸው። ይህን «ኃይል» ከየት እና እንዴት ሊያገኙት ቻሉ የሚለው ጥያቄ ነው መመለስ ያለበት።

ለዚህ ጥያቄ ምላሽ መስጠት ያስችለን ዘንድ በማስታወቂያ ሥራ የተሰማሩ ሰዎችን ወይም የኪነ-ጥበብ ሥራዎች ባለሙያዎችን እንደ አብነት መውሰድ እንችላለን። እንደሚታወቀው በነዚህ የሥራ ዘርፎች የተሰማሩ ሰዎች በሙያቸው የተነሣ ለብዙኃኑ ሕዝብ በጣም ቅርብ ናቸው። ይኼ እንዳለ ሆኖ፣ «ኮርፖሬቱ» የበለጠ ለሕዝብ ቅርብና ገናና የመሆን «ዕድል» እንዲያገኙ ያደርጋቸዋል። (በዚህ ጽሑፍ «ኮርፖሬት» የምለው የኢኮኖሚ ወንጀል ለመፈጸም የሚያደባውን ነው)።





> ❝ ጠ/ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝና ቀንጮዎቹ ባለስልጣኖቻችን በጉዳዩ ላይ ቁርጠኝነታቸውን በተግባር ከማሳየት ይልቅ ማድረግ የመረጡት ጉዳዩን መልሶ ወደ ሕዝብ መወርወር ነው፤ ቀድመው የተናገሩት ነገር <<በአፍ ይጠፉ በለፈለፉ>> ነው የሆነባቸው። ስለዚህ መሪሩን እውነት በተናገሩበት አፋቸው <<ከመጥፋት/ከመጠፋፋት>> ይልቅ <<የሕዝብ ንቅናቄ>> የሚል ፈሊጥ ፈጥረው ማፈግፈግን ነው የመረጡት።

የበለጠ ለሕዝብ ቅርብ እንዲሆኑና ገናና ስም ወይም ዝና እንዲያገኙ ያደርጋል ስንል፣ በተደጋጋሚና በተከታታይ በመገናኛ ብዙኃን (ቴሌቪዥን፣ ሬድዮ፣ ሕትመት) የመቅረብ ሰፊ ዕድል እንዲኖራቸው መንገዱን ያመቻችላቸዋል ለማለት ነው። በዚህ መልኩ ቀድሞ ከነበራቸው ዝና በላይ ባለዝና እና ገናና እንዲሆኑ ይደረጋል። ከዚህ በኋላ «ዕዳው ገብስ» ነው። ጉዳዩን እንዲፈጽሙለት እነኚህን «ታዋቂ» ሰዎች በሚፈልገው አቅጣጫ ወደሚፈልገው አካል ይልካቸዋል። አበቃ! በአጭሩ፣ ከአጭሩም በአጭሩ፣ እንዲህ በተጠና መልኩ የተቀነበረ የኢኮኖሚ ወንጀል ሊፈጸም ይችላል።

ምሳሌው «ኔትዎርክ» እና «ድለላ» የተሰኙትን የባለሥልጣኖቻችንን ዲስኩር በሚገባ የሚገልፅ ይመስለኛል። ለዚህም ይመስለኛል ጠ/ሚኒስትር ኃይለማርያም «… እዚህ ሀገር ትልቅ ፈተና የሚሆነው፣ ከዚህ ስንወጣ የራሳችንን ኔትዎርክ እንከላከላለን። … » ሲሉ ልባቸው የሚያውቀውን መራር እውነት ፍርጥ አድርገው ለመናገር የተገደዱት። ለዚህም ይመስለኛል ቀንጮዎቹ ባለሥልጣኖቻችን፣ «ችግሩን ለመቅረፍ ቆርጠናል፤ ይኼ የሞት የሽረት ጉዳይ ነው!» ብለው ፎክረው፣ አቅራርተው፣ ሸልለው ሲያበቁ ለወሬት ምንም ማድረግ ያልቻሉት። ለዚህም ይመስለኛል የሚታይና የሚዳሰስ ተግባራዊ እርምጃ ለመውሰድ ያልፈለጉት።

ጠ/ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝና ቀንጮዎቹ ባለስልጣኖቻችን በጉዳዩ ላይ ቁርጠኝነታቸውን በተግባር ከማሳየት ይልቅ ማድረግ የመረጡት ጉዳዩን መልሶ ወደ ሕዝብ መወርወር ነው፤ ቀድመው የተናገሩት ነገር «በአፍ ይጠፉ በለፈለፉ» ነው የሆነባቸው። ስለዚህ መሪሩን እውነት በተናገሩበት አፋቸው «ከመጥፋት/ከመጠፋፋት» ይልቅ «የሕዝብ ንቅናቄ» የሚል ፈሊጥ ፈጥረው ማፈግፈግን ነው የመረጡት።

## ወዴት? ወዴት?

ጠ/ሚኒስትር ኃይለማርያምና ባለሥልጣኖቻቸው ከመነሻትም ወደ መከርፋት የሄደውን የሙስናና የመልካም አስተዳደር ችግር በተመለከተ በቴሌቪዥን ቀርበው በራሳቸው አንደበት ከነገሩን በኋላ፣ «ችግሩን መቅረፍ የሞት የሽረት ጉዳይ ነው» ካሉን በኋላ ስንብተው ስንብብተው፣ ከርመው ከራርመው፣ «የሕዝብ ንቅናቄ» የሚል ፈሊጥ ይዘው ብቅ ማለታቸው እንደ ኢሊ ጭንቅላታቸውን ራሳቸው ውስጥ መደበቃቸውን፣ ወይም ከነገሩ መሸሸ መምረጣቸውን ነው የሚያመላክተው።

ወዴት፣ ወዴት? ከማን ይሸሻል? ለምን ይሸሻል? እንዴት ይሸሻል? መቼም በኢትዮጵያውያን ነባራዊ ታሪክ፣ ነባራዊ እምነትና አመለካከት ሽሽት «የቁርጠኝነት» ምልክት ሊሆን አይችልም፤ አይደለምም። የሽሽት ወይም ሬስን የመቅበር ምንጭ ፍርሃት ነው። በኢትዮጵያውያን ነባራዊ ታሪክ እና አመለካከት ደግሞ መሪ (ከመሪር) አያፈገፍግም። አሕአዴግና አሕአዴጋውያን ይህን እውነት ያጡታል ብዬ አልገምትም።

ምንም እንኳ የአገራችን ታሪክ የጦርነት ቢሆንም፣ ከዚሁ የበርካታ ዘመናት የጦርነት ታሪካችን ውስጥ ጎልቶ ነጥሮ ከሚወጣው ነገር አንዱ የመሪዎች የወሳኝነት ሚና የጎላ መሆኑ ነው። በታሪካችን በቀውጢ ጦርነት መሀል የተሰለፈው ሠራዊታቸው ማጥቃት ወይ መመከት አቅቶት በሚያፈገፍግበት ጊዜ ፈረሱን ከልክሉ፣ ደረቱን ነፍቶ፣ ጦሩን ሰብቆ ወደ ፊት የሚገሰግሰው መሪው ራሱ ነው። ያኔ ነው በድንገም የነበረው፣ ሲያፈገፍግ የነበረው ሰራዊታቸው እንደገና ብርታት የሚያገኘው። ያኔ ነው «ከመሪዬ ጋር ልሙት!» ብሎ ተመልሶ ውጊያውን የሚቀላቀለውና እንደገና ድል የሚቀዳጀው። ለዚህም ነው ሽንፈት ቢመጣ እንኳ «መሪ አያፈገፍግም» የምለው።

## የለየለት ስላቅ!

አዎ! መሪ አያፈገፍግም! በሀገሪቱ ቅጥ ያጣውን ሙስና «የሕዝብ ንቅናቄ» የሚል ፈሊጥ ፈጥሮ መልሶ እንደገና ወደ ሕዝብ መወርወር ማፈግፈግ ነው። ሕዝብን «የራስህ ጉዳይ!» ብሎ ለጅብ አሳልፎ እንደመስጠት ያለ ምፀት ነው - ለእኔ።

ለመሆኑ ሕዝብ ምን ያድርግ? ሕዝብማ ምሬቱን ተናግሮ፤ «አቤ! አቤ! ያገር ያለህ» ብሎ ጮኾ ጮኾ ደከመ። አቅም አጣ። አሁን አቅሙም ብርታቱም ያለው፣ እርምጃ መውሰድ የሚገባው፣ አመራሩ ነው። አበቃ! እርምጃ መውሰድ ያለበት አመራሩ ነው ስንል፣ እርምጃውን በውስጡ ካሉት የንቀዙ ባለሥልጣናት መጀመር አለበት ማለታችን ነው። ከራሱ መጀመር አለበት ማለታችን ነው።

መንግሥት ይህን ማድረግ ይችላል፤ ወሳኙ ከንግግር ያለፈ እውነተኛ ቁርጠኝነት መኖሩ ነው። ማን ምን እንዳደረገ፣ ማን እጁ እንደ ቆሸሸ፣ ማን ከማን ጋር በኔትዎርክ እንደ ተሳሰረ፣ ማን ለማን ምን እንደ ደለለ መንግሥት በሚገባ ያውቃል። ሙስናን መዋጋት የሞት የሽረት ጉዳይ ነው ሲሉን ያየናቸው ቱባ ቱባ ባለሥልጣናት ማን እጁ በሙስና ጭቃ እንደ ተጨማለቀ በሚገባ ያውቃሉ። ቢያንስ ቢያንስ ስለጉዳዩ «ጥናት» ተብሎ የቀረበላቸው 800 ገጽ ውስጥ የተጠቀሱትን የወንጀሉ ተዋንያኖች ይታወቃሉ። እንኳንስ የጥናት ሠነዱ የቀረበላቸው ባለሥልጣናት፣ እኛ ውይይታቸውን በቴሌቪዥን የተከታተልን ማን ምን እንዳደረገ ውስን እውቀት አለን።

ለምሳሌ ውይይቱ በቴሌቪዥን በሚተላለፍበት ወቅት፣ በተሰጠው የኢንቨስትመንት መብት ተጠቅሞ መርከብ ሙሉ ብረት ወደ ሀገር ያስገባ፣ በዚህ የንግድ ዘርፍ የተሰማሩ ነጋዴዎችን ለኪሳራ የዳረገ እንዳለ ተነግሯል። ይህን አሻጥር የተባለ ሰው የተሰጠውን መብት ላልተገባ ጥቅም ሲያውል ማንም አልተባበረውም ማለት አይቻልም። ይህን ሁሉ ድርጊት ሲፈጽም ማንም ከለላ አልሆነውም ቢባል ሹፈት ነው። በ800 ገጽ «ጥናት» ውስጥ በዚህ መልኩ እጃቸው የቆሸሸ ወገኖች እንዳሉ የአደባባይ ምስጢር ነው። እንዲህ «በጥናት» የተደረሰባቸው አካላት ላይ እርምጃ ሳይወሰድ፣ «የሕዝብ ንቅናቄ» በሚል ጉዳዩን መልሶ ወደ ሕዝብ መወርወር የለየለት ስላቅ ነው። ስለዚህ ከሁሉ አስቀድሞ እርምጃ መውሰድ የሚገባው ከላይ ነው - «ከአናቱ»።

## «ጥሙቱ ከአናቱ…»

የኢትዮጵያ ትልቁና ዋነኛ ችግር የሚመስለኝ «የአናቱ መቆሸሽ» ነው። ይህም እውነታ ከሕዝብ የተሰወረ አይደለም፤ ተደጋግሞም ተነግሯል። የሩቁን ትተን ከቅርብ ዓመታት በፊት የአገሪቱ ጠ/ሚኒስትር የነበሩት መለስ ዜናዊ (ነፍስ ይማር) በፓርላማ የተናገሩትን ማስታወስ ይበቃል፤ «ይህ መንግሥት በመንግሥት ሌቦች እና በሕዝብ ሌቦች አንድ እጁን ታስሮ እየታገለ ነው እየሠራ ያለው…» ነበር ያሉት አቶ መለስ። የአቶ መለስ አባባል ቃል በቃል የተጠቀሰ ባይሆንም፣ ንግግራቸው የመንግሥት ሥልጣን ላይ ያሉ ወገኖች በሙስና ተግባር ውስጥ መሳተፋቸውን የሚያረጋግጥ ነበር። ይህ ንግግራቸው ስሟ የማይታወቀውን የወሎዋን ገበሬ ሥነ-ቃል ነበር ያስታወሰኝ። ገበሬዋ፦ « … ፈትዬ እንዳልበላው እምቢ አለኝ እንዝርቱ፤ ለካ ካናቱ ነው የቋንጫው ጥሙቱ። …» ነበር ያለችው።

ልክ እንደዛው ሁሉ አሁንም «ጥሙቱ ከአናቱ» መሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው። መቼም ምክንያቱም አቶ መለስ «የመንግሥት ሌቦች … » ሲሉ የገለጿቸው አሁን የሉም አይባልም። እንዲያውም ሌብነቱ ብሶ ተባብሶ መግዘፉን ነው ከእሁኑ መሪዎቻችን «ኔትዎርክ» ይሉት አግላለኝ የምንረዳው። ይህም ብቻ አይደለ፣ ሙስናን ይዋጋል ተብሎ የተቋቋመው የፌ-ሙስና ኮሚሽንም ያረጋግጠልን ይህንኑ የዝፈ ሙስና መቅረፍ አለመቻሉን ነው። ለዚህ እውነታ አብነት ይሆነን ዘንድ የፌ-ሙስና ኮሚሽን መስከረም 20 ቀን 2008 ዓ.ም በሂልተን ሆቴል ያደረገውን ስብሰባ መጥቀስ ይበቃል። «ሙስና በአዲስ አበባ በኔትዎርክ በመደገፉ ከኢሕአዴግ በቀር የሚፈታው እንደሌለ» ነበር በዚያ ስብሰባ የገለጸው። ይህንኑ ዜና ሪፖርተር ጋዜጣ ለንባብ አብቅቶታል።

ሌላም አስረጂ መጥቀስ ይቻላል፤ የፌዴራል የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር በዚሁ ወር በሰጡት ቃለ-ምልልስ ላይ፣ «መንግሥት አመራሩ በሙሉ ሙስና በሰፈጸመ ስብሰብ አድርጋችሁ የምታደርጉትን ሁሉ አድርጉ የሚል መልዕክት አልደረሰኝም። … » ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል። የኮሚሽነሩ ምላሽ ፈገግ የሚያሰኝ ነው። ግን ችግሩም ሆነ ችግራቸው ምን እንደ ሆነ ለማወቅ ነቢይ መሆን አያስፈልግም። ኮሚሽነሩ መስከረም 07 በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ፣ «ገዢው ፓርቲ ኢሕአዴግ በስብሰባው ሙስና ላይ ቁርጠኛ አመራር እስመስጠቱንና አስመታገሉን ቢገልጽም፣ አጊሌ ሙሰኛ ነው ብሎ ማስረጃም ባለማቅረቡ፣ ወደ ሕግ መሄድ አይቻልም። …» የሚል ምላሻቸውን ብቻ መጥቀስ ይበቃል።

እንደኔ እንደኔ፣ ይህ የኮሚሽነሩ ምላሽ የሚነግረን፣ ዋናው ችግር «ከአናቱ» መሆኑን ነው። ከዚያ በኋላ «ችግሩን ለመቅረፍ ቆርጠኛ ነን፣ የሞት ሽረት ጉዳይ ነው» ያሉን መሪዎቻችን፣ አንዳች እርምጃ ይወስዳሉ ተብለው ሲጠበቁ፣ «የሕዝብ ንቅናቄ» የሚል ፈሊጥ ይዘው ብቅ ማለታቸው «ጥሙቱ ከአናቱ» መሆኑን ነው የሚያሳየው፤ ሕዝብ የሚጠብቀው መንግሥት ከንግግር ባለፈ ተግባራዊ እርምጃ መውሰድ ሲጀምር ነውና። አሊያ ሹፈት ነው የሚሆነው። ሕዝብን በንግግር አያደናገሩ ሙሰኞች አደብ ተው ፀያፍ ግብራቸውን እንዲተዉ እንደ መፍቀድ ነው የሚቆጠረው።

ሌላው ሌላው ቢቀር እንኳ፣ እውነት መንግሥት ሙስናን ለመታገል ቁርጠኝነት ካለው፣ «ጥናት» ተብሎ የቀረበለትን 800 ገጽ ሠነድ ለሕዝብ ይፋ ባደረገ ነበር። ቢያንስ ሕዝብ ዘራፊዎቹን በይፋ ቢያውቃቸው አንድ ነገር ነበር። ጥናቱን ለምን ይፋ እንዳላደረገ ባይገባኝም፣ ችግሩን «የሕዝብ ንቅናቄ» በሚል መልሶ ወደ ሕዝብ መወርወሩ ግን የቁርጠኝነቱን አጠያያቂነት ነው የሚያመላክተው ባይ ነኝ።

በመጨረሻ የምለው፣ ተግባራዊው እርምጃ «ከላይ ከአናቱ» ይጀመር ነው። «ጥሙቱን» ማስተካከል በእጁ ካለው ጥናት ይጀመር ነው የምለው። አሊያ … !

አበቃሁ!

# የኢትዮ - ሱዳን ድንበር ጉዳይ



ብሩክ ሲሳይ

የኢትዮ-ሱዳን ድንበር ጉዳይ ሰሞኑን እንደገና መወያያ ሆኗል። ጉዳዩ በ2000 ዓ.ም የጀርመን እና የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮኖች በኢትዮጵያና በሱዳን መንግሥቶች መካከል በምስጢር ድንበር የማካለል ስምምነት እየተካሄደ እንደ ሆነ ከተገለፀ በኋላ፣ ላለፉት ዓመታት ብቅ እያለ የሚጠፋ አጀንዳ ሆኖ ቆይቷል። ከሰሞኑም ዳግም መነጋገሪያ አጀንዳ ሆኗል። ብሩክ ሲሳይ፣ የጉዳዩን ታሪካዊ አውድ እያየ፣ ይህን ጽሑፍ አቋድሶናል።

የኢትዮ-ሱዳን ድንበርና አካባቢ ሽፍን ተሰዋቶች የተመዘገበው ታሪክ የሚገኘው ከዐፄ ፋሲል ዘመነ-መንግሥት ጀምሮ ባሉት ነገሥታት ዜና መዋዕል ውስጥ ነው። ይህ ማለት ግን ከዚያ በፊቱ ታሪካችን ውስጥ አልተካተተም ወይም አልተጻፈም ማለት አይደለም። እንዲውም «ትብያ» እንጂ የኢትዮጵያ የግዛት ክፍል እንደ ነበረች የጥንት መዛግብት ያስረዳሉ። የጎንደር ነገሥታት ለአካባቢው ከመቅረባቸው አንጻር በዜና መዋዕላቸው ውስጥ ትኩረት ሰጥተው በሚገባ የጻፉት መሆኑም ይስመርበት። እና ከዚያ ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ያለውን ሁኔታ በአጭሩ በዳሰሳ መልክ ማስቀመጡ ከላይ የተነሱትን ጥያቄዎች በቀላሉ ለመመለስ ይረዳል።

የዐፄ ፋሲል ታሪክ-ነገስት፣ ንጉሡ በኢትዮጵያ ምዕራብ - ዛሬ የሱዳን ግዛት - በሆነው አገር ሰናርን ኑብያን እንዳስተዳደሩ ይገልፃል። በኑብያም በእርሳቸው ሥር የሚተዳደር ሂዮርጊስ የሚባል የአካባቢ ንጉሥ እንደነበረ (እስከ የግብጽ ወሰን ጠረፍ ድረስ) እንዳስተዳደሩ እና የፈረሰቻቸውም መታሰሪያና መቀመጫ ሰናር እንደ ነበር ያትታል። ታሪክ-ነገሥቱ እያደር፣ ከዐፄ ፋሲል በፊት የነበሩ ነገሥታ ኑብያን እና ሰናርን አስገብረው ቢመለሱ እንጂ እንደ እርሳቸው እንዳስተዳደሯቸው ገልፆ፣ አዝማሪያም እንዲህ ሲል እንዳዜመ ያስታውሰናል፦

ጎንደር ቢያንቀጠቅጥ ፋሲል ፈረስህ፣

ኑብያና ሰናር ወርቁን ጫኑልህ።

ማሩን ተጠየፈ የፋሲል ፈረሱ፣

ከምር የሱዳን ወርቅ ገፈራው ነው ለእሱ።

ዐፄ ኢያሱ (አድያም ሰገድ) ወይም ታላቁ ኢያሱ በአያታቸው በዐፄ ፋሲል እየተዳደረ ሲገበር የነበረውንና ኋላ መገበር ያቆመውን ከከሰላ እስከ ሰናር ያለውን መሬት ጭፍሮቻቸውን ልከው እንዲያቀኑ አድርገው የአካባቢው መሣፍንቶች ያቋረጡትን ግብር እንዲገብሩ አስገግዋል። የዐፄ ኢያሱ (አድያም ሰገድ) የሰሜን ምዕራብ ግዛት ወሰንም ከምዕራብ እስከ ሰናር፣ ከሰሜን የከረንን፣ የሐባብን ሀገር ሁሉ ይዞ፣ እስከ ሳይኖው ባርካ ወንዝ ድረስ ያካተተ ነበር።

የዐፄ በካፋ እና የቋረኛዋ እቴጌ ምንትዋብ ልጅ የሆኑት ቋረኛ ኢያሱ (ብርሃን ሰገድ) ዛሬ የሱዳን ግዛት እስከሆነው መሬት ድረስ ግዛታቸውን በማስፋፋትና አስተዳደራቸውን በመዘርጋት ግብር እንዳስገበሩ የራሳቸው ታሪክ-ነገሥት ያስረዳል። ግዛታቸውም በዐፄ ኃይለሥላሴ ጊዜ እንደ ወሰን የሚታየውን «አትባራ»ን አልፎ፣ «ሰናር» የሚባለውን ከተማ ሁሉ ያካትት ነበር። በጊዜው የሰናር ባላባት የነበሩት ባዲ ኢብን ሻሉክ፣ እልፎ እልፎ ለንጉሡ አልገብርም እያሉ ያስቸግሩ፣ ያምፁ ነበር። ቋረኛው ንጉሥም ወታደሮቹን እያዘመቱ፣ የሚቀጣውን እየቀጡ የሚሰማውን ተነጋግሮ እያሳመነ ያስገብር፣ አካባቢውን ያስተዳድር ነበር። ከዚያ በኋላ ዘመነ-መሣፍንት ገባ፤ ነገሮችም እንዳልነበሩ ሆኑ።

የታሪክ ምሁሩ ተክለጻዲቅ መኩሪያ እንደሚያወሱት፣ ዛሬ ላይ ሱዳን የራሷ ይዞታ ያደረገችው ጋላባትና ዙሪያውን ያለው መሬት፣ በዘመነ መሣፍንት ማብቂያ ወቅት ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ጭፍሮቻቸውን አስከትለው የሸፈቱበት፣ የተንቀሳቀሱበት ስፍራ ነበር። ዐፄ ቴዎድሮስም የዘመነ መሣፍንት የአካባቢ ገዢዎችን ተራ በተራ በመውጋት ሁሉንም አሸንፈው ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ እንዲባሉ ከፍተኛውን ድርሻ ያበረከተው፣ ከዚሁ ከጋላባት እና ቋራ አካባቢ የተውጣጣው ሠራዊታቸው ነበር። ንጉሠ ነገሥት ከተሰኙ በኋላም ስፍራው በእርሳቸው ቁጥጥር ሥር የነበረ ሲሆን፣ በአስተዳዳሪነትም የሸመት የአካባቢው ተወላጅ የሆነውን እና የሸፍትነት ዓይኖቻቸውን፣ የልብ ወዳጆቻቸውን - አንድረሰን ነበር።

ከዐፄ ዮሐንስ ዘመነ-መንግሥት ማብቂያ እንስቶ ኢትዮጵያን በወሰን የሚያካልሏት አገራት እንደሆኑ በተወላጆቻቸው የሚመሩ አልነበሩም፣ እነርሱን በቅኝ ለመግዛት በዘርሊን ኮንፍረንስ ስምምነት የተከፋፈሏቸው እንግሊዝ፣ ጣሊያን እና ፈረንሳይ እንጂ። ዐፄ ምኒልክም ከአድዋ ድል በኋላ የወሰን ክልል የተዋዋሉት ከእነዚሁ የአውሮፓ መንግሥታት ጋር ነበር።

እንግሊዝ በሱዳን በኩል ለላው ወሰን ሌተና ኮሎኔል ገርሆን ሐረንግተን በእንግሊዝ ንጉሥ በኤድዋርድ ሰባተኛ ስም፣ በኢትዮጵያ በኩል ዐፄ ምኒልክ በራሳቸው ስም ግንቦት 15 ቀን 1902 (እ.ኤ) በአምስት አንቀፅ የተከፈለ ውል ተዋውለዋል። ይህ የዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ውል አሁን ያለው የኢትዮጵያ መንግሥትና እንዳንድ የመንግሥት ደጋፊዎች እንደሚሉት መተማን፣ ቋራን፣ ከፊል ሁመራን፣ የቤንሻንጉል ጠረፍ አካባቢዎችን የሱዳን ይዞታ ያደረገ አይደለም። የድንበር አወሳሰኑ በካርታ ላይ እንጂ በመሬት ላይ የተከናወነ አልነበረም። የዚህ የድንበር ጉዳይ ሲነሣ የሆነራቱ የድንበር ይዘኛል መነሻ ተብሎ በተደጋጋሚ የምንሰማው ሽሌቃ ጉዌን የተባለ የቅኝ ገዢዋ እንግሊዝ ወታደር ያሰመረው መስመር ነው።

እንጋፋው የመብቶች ተሟጋች ፕሮፌሰር መሥፍን ወልደማርያም በአንድ ወቅት በዚህ ጉዳይ ላይ ለአሜሪካ ድምፅ ሬድዮ በሰጡት ማብራሪያ እንዳስረዱት፣ ከወደብ ከተማዋ ጋላባት በስተደቡብ ያለው የጉዌን መስመር ችግር የሌለበት ሲሆን፣ ከጋላባት ወደ ሰሜን የሚሄደው መስመር ግን ችግር አለበት ብለዋል። ምክንያቱ፡ - ከጋላባት ወደ ሰሜን በኩል ያለው መስመር መንታ መሆኑ ነው። አንደ ፕ/ር መሥፍን ገለጻ ከሆነ አንደኛው የጉዌን መስመር ወደ ምዕራብ ገባ ያለና የኢትዮጵያን ጥቅም የሚያስጠብቅ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ወደ ምሥራቅ ገባ ብሎ፣ የኢትዮጵያን ድንበር የሚያሳንስ ነው። ሁለተኛውን መስመር አስመልክቶ ንጉሥ ኃይለሥላሴ በ1964 ሊፈርሙ የነበረበት አቅርበውት የነበረ ሲሆን፣ ከእንደራሴዎቻቸውም ጠንከር ያለ ተቃውሞ ገጥሟቸው ነበር። በአጠቃላይ በንጉሥ ኃይለሥላሴ እና በሱዳን መንግሥት መካከል ይሁንታን ያገኘ ምንም ዓይነት ስምምነት አልነበረም።

የቀድሞ የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ፣ ግንቦት 13 ቀን 2000 ዓ.ም በዚህ ወሳኝ ጉዳይ ዙሪያ እርሱ በርሱ የሚቃረን ንግግር ሲያደርጉ እናደርገው ነበር። በወቅቱ እንዳሉት፣ በዚያ አካባቢ በነበሩ የኢትዮጵያ አርሶ አደሮችና በሱዳን ወታደሮች መካከል ግጭት በመነሳቱ ምክንያት የኢትዮጵያ ሠራዊት በ1995/96 በወሰደው እርምጃ መሬቱ በእጃችን ሊገባ የቻለ፣ የእኛ ያልሆነ፣ የእኛ አርሶ አደሮችም ያርሱት የነበረው መሬት ያለአግባብ የተገኘ የአንርሱ መሬት እንደ ሆነ ተናረው ነበር። በፓርላማው ውስጥ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ምንም እንኳ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ቢሆኑም፣ በሰዐቱ ያሰሙት ዲስኩር የሱዳን አስመስሏቸው ነበር። እንዳውም ሱዳን የተስፋፊዎቹን የኢትዮጵያን ጠቅ-ሜሪነት ችላ በትዕግሥት እና በሰላም መሬቷን መጠየቋ የሚያስመሰግናት፣ ካሳም ሊከፈላት የሚገባ... ዓይነት መልእክት አስተላልፈው ነበር።

ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝም በ2006 ዓ.ም ከዚሁ የኢትዮ-ሱዳን ድንበር ጉዳይ ጋር በተያያዘ ባደረጉት ንግግር፣ «እኛ ለሱዳን የሰጠነው አንድም አዲስ መሬት የለም፣ የድንበር ማካለል የምናደርገው በዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ፣ በቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ እና በሻለቃ ደርግ መንግሥታት የተደረጉ ውሎችን መሠረት በማድረግ ነው» ብለው ነበር። በዚያው ሰሞን በጉዳዩ ዙሪያ ኮሉኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ለአንድ የመገናኛ ብዙኃን በሰጡት ቃል እንደ ገለጹት፣ ከሱዳን ጋር እርሳቸውም ሆኑ ከእርሳቸውም በፊት የነበረው የዐፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት ከሱዳን ጋር ምንም ዓይነት የድንበር ስምምነት አላደረገም።

የአካባቢው ሰዎች በቁጭት ሲናገሩ እንደሚደመጡት፣ ለሱዳን ሊሰጣት ነው የሚባለው ምድር ቋረኛዋ እቴጌ ምንትዋብ (የዐፄ በካፋ ባለቤት)፣ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ (ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ) የተወለዱበትን የቋራ ግዛት በከፊል፣ ዐፄ ዮሐንስ አራተኛ የተሰዉበትን መተማ በከፊል፣ የማኅበረ-ሥላሴ ገዳምን ወሰን በከፊል፣ ሞፈር ውሃ የሚባለውን ቦታ ሁሉ የሚሸፍን ሲሆን፣ በዚህ አካባቢ አሁን ድረስ አንድም የሱዳን ዜጋ አይኖርበትም። ይህን መሬት እያረሱና እየተጠቀሙ የሚገኙት ቋረኞችና ከ1992 ዓ.ም ጀምሮ ድርቅ ከሚያጠቃቸው የአማራ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች እየተነሡ በሰፈራ ፕሮግራም ወደዚሁ መሬት የሰፈሩ ኢትዮጵያውያን ናቸው። ከእነርሱም በተጓዳኝ በኢንቨስትመንት ስም ሰፋፊ መሬት ወስደው የሚያርሱና ከሥርዓቱ ጋር እጅና ጓንት የሆኑ አካላት ናቸው።

ኢትዮጵያና ሱዳን በተለይ አፍሪካ ቀንድ ወሳኝ ሚና ያላቸው ታላላቅ አገሮች ናቸው። ይህ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ግን በሁለቱም አገሮች መካከል የሚገነባው የወዳጅነት ትስስር በሁለቱ አገራት ሕዝቦች በላቂ ጥቅምና ሰላም ላይ መመሥረት ይኖርበታል። በአገሮቹ መንግሥታትና መሪዎች ወዳጅነት ላይ የተመሠረተ መሆን የለበትም። የሥልጣን ፍላጎትን ለማርካት ተብሎ የአገርን ሉዓላዊነት ለድርድር በማቅረብና ሰባዕዳን በመስጠት ኢሕአዴግ በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያው አግባቢ ሊሆን ከጫፍ ደርሷል።

ከዓመት በፊት በድንበሩ አካባቢ ሞንግሶበው አደጋ ከሰላ ያቀ የአካባቢው ነዋሪዎች ወደ ጎንደርና ሁመራ ተፈናቅለዋል፣ ያልተፈናቀሉትም ከሱዳን ታጣቂዎች ጋር ጉርር ለጉርር ተናንቀው እስከ ዛሬ ድረስ ያለ መንግሥት ድጋፍ በዚያው በአካባቢያቸው ይኖራሉ። ወደ ፊትም ቢሆን የቋራ ገበሬ የተለየ አስቸጋሪ ነገር ካልገጠመው በቀር በቀላሉ መሬቱን ይለቃል ማለት አይታሰብም።

# ሐሳብን የመግለጽ ነጻነት እስከ ማበሳጨት



በፍቃዱ ዘ ኃይሉ

*"ሐሳብን የመግለጽ ነጻነት ምንድን ነው? ማበሳጨትን ካላካተተ፣ ሕልውና የለውም።" ~ ሰልማን ሩሽዲ*

## ፩ - ማበሳጨት

«በመስከረም ወር 1997፣ ዝርላንድስ ፖስተን የተባለ የዴንማርክ ጋዜጣ ነብዩ መሐመድ ላይ የሚሳለቁ ካርቱኖችን ይዞ ወጣ። የዚህ ሕትመት ዜና በመላው ዓለም እንደተሰማ በየቦታው ያሉ ሙስሊሞች ቁጣቸውን በአደባባይ መግለጽ ጀመሩ።የተቃዋሚዎቹ ምክንያቶቻቸው ሁለት ናቸው፣ አንደኛ፣ ነብዩ መሐመድን በምስል መግለጽ በእስልምና ኃይማኖት አይፈቀድም የሚልና፣ ሁለተኛ፣ ካርቱኖቹ በጥቅሉ እስልምናን እና ሙስሊሞችን ከሽብር ጋር አቆራኝተው ይገልጻሉ የሚል ናቸው። ሠላማዊ ሰልፎችና ሕገወጥ ተቃውሞዎች ቢጋለጡው አዚጋጆች እና በዴንማርክ መንግሥት ላይ ተሰነዘሩ። ከዚህ ውስጥ አንዳንዶቹ ሕይወት እስከመቅጠፍ የበለቀ አመጽ የተቀላቀለባቸው የተቃውሞ ሰልፎች ነበሩ። ካርቱኖቹ ግን በመላው ዓለም በሚገኙ በሌሎች ጋዜጦች ላይ ለዝርላንድስ ፖስተን ጋዜጠኞች የሞራል አጋርነት ለማሳየት በሚል ሰበብ ደጋግሚ ታትመው ይበልጥ ተሰራጩ።» (Paul Sturges, 2006)

ሌላ ምሳሌ እንውሰድ። አንድ ወንድ "ሴቶችን ማስተማር የአገርን ሀብት ማባከን ነው፣ ስለዚህ ሴቶችን ማስተማር ካለብን የቤት አያያዝ፣ ምግብ ማብሰል እና ልጅ አስተዳደግ እናስተምር እንጂ ሌላ ብዙም ክሒታ ሥራ የሚያሰጠዝ ትምህርት ማስተማር የለብንም" የሚል አስተያየት ሲሰጥ በቴሌቪዥን ተላለፈ። ይህን ተከትሎ የተነሣው ሴቶች የተቃውሞ ሰልፍ አደረጉ። ወንድ አሽከርካሪዎች የሚነዷቸውን መኪኖች ሰበሩ። ወንዶችን አምልዷ ደበደቡ።" በዚህ የፈጠራ ታሪክ ውስጥ የአስተያየት ሰጪው ሐሳብ ሴቶችን አበሳጭቷቸው ይሆናል። ነገር ግን ለአመጹ እነርሱን እንዳስቷቸዋል ብሎ መደምደም ከባድ ይሆናል። አሚጺዎቹ ሴቶች ስሜታቸውን መቆጣጠርና ሐሳብን በሐሳብ መመከት ካልቻሉ ድክመቱ የነርሱ የራሳቸው ይሆናል።

የዴንማርክ ፍርድቤት የፈረደውም፣ እኔ በሳይኖው አንቀጽ አመጿኞቹ ሴቶች ላይ የሰጠሁትን ዓይነት ብይን ነው። "እርግጥ ነው ስዕሎቹ የተወሰኑ ሙስሊሞችን ማበሳጨታቸው አይካድም፣ ነገር ግን የካርቱኖቹ ዓላማ ሙስሊሞችን ማንቋሰስ አልነበረም" ብሎ ፍርዱ። ሲያብራራውም፣ "ስዕሎቹን አመጽ ወይም የንብ የመዉርወር ድርጊት በእስልምና ሥም እየተደረገ ነው፣" በሚል መረዳት የካርቱኖቹ ተመልካቾች ደርሻ ነበር ብሏል። የዴንማርክ ፍርድ ቤት ብይን ለካርቱኒስቶቹ ያደላ ቢመስልም ካርቱኒስቶች ራሳቸው ላይ ትድመ ምርመራ እንዲያደርጉ ከሰተቱ አስገድዷቸዋል። ነገር ግን የአንድ ሐሳብ (expression) አግባቢ፣ ተመልካች ወይም አድማጭ የራሱን ስሜት መቆጣጠር ድርሻ የራሱ መሆን ካልቻለ ቢያንስ የሆን ሰውን የማያበሳጭ ሐሳብ ማፍለቅ በጣም አስቸጋሪ ስለሚሆን፣ ብንጹ ቀርቶ ሐሳብን መግለጽ የሚባለው ጉዳይ ራሱ አይኖርም።

እምና የፈረንሳዩ ቬርሎ ሆብዶ መጽሔት ባወጣቸው ካርቶኖች ተበሳጭተው ጋዜጠኞችን፣ ካርቱኒስቶችን እና ፖሊሶችን የገደሉ ሰንፎ-ኃይማኖተኞች ጉዳይም ሊታይ የሚችለው በዚሁ ዓይን ነው። ሰንፎኞቹ የእነርሱን እሴት ያስከፉ፣ በእነርሱ እሴት መሠረት መቀጣት አለበት የሚል እርምጃ ነው የወሰዱት። ከሱተቱ ሌላሳብ ነጻነት አራማጆች መርዶ ነው። ኢጋጣሚውን ተከትሉ ተቀማጭነሉ የመጣውም ወይይት ሰዎች ራሳቸውን በራሳቸው ሳንሱር እንዲያደርጉ የሚያበረታታ ነው። ይሁን እንጂ ኢጋጣሚው የኢትዮጵያውን ጨምሮ ለአምባገነን (authoritarian) መንግሥታት ፕሮፓጋንዳ ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል። ሐሳብ እንዴት መገደብ እንዳለበት ከሰተቱን አስታክከው ያስተረዳሉ።እነዚህ መንግሥታት ሊያስተውሉት ያልፈለጉት ነገር ቢኖር ከዴንማርክ እስከ ፓሪስ የተከሰተው ነገር ጋዜጠኞች ሐሳባቸውን በነጻነት ሲገልጹ የመንግሥት ከለላ እንደሚያስፈልጋቸው እንጂ ሐሳባቸውን በነጻነት ከመግለጽ እንዲቆጠቡ የሚመክራቸው አልነበረም።

ሌሎችን ማበሳጨት የተወሰኑ የማኅበረሰብ ክፍሎች ላይ ወይም ግለሰቦች ላይ ሲከሰት ከሞላ ጎደል ከባይ ባንነው ሁኔታ ሊያልፍ ይችላል። ችግሩ የተበሳጨው አምባገነን መንግሥት (የመንግሥት ባለሥልጣናት) ሲሆን ነው። እነ ኢልያስ ገብሩ (አምሳሉ ገብረኪዳን) ዕንቁ መጽሔት ላይ መጋቢት ወር 2006 የጻፉውን ጽሑፍ ተከትሉ ጀማ የኽርሲቲ አካባቢ በተነሳው የተቃውሞ ብጥብጥ ሳቢያ) የተከሰሱባቸው የአመጽ ማነሳሳት ክስ መቃቶት የሚኖርበት በዚህ ዓይን ነው። መንግሥት ጸሐፊዎቹንም፣ ለጸሐፊዎቹ የጸሐፍ ምሳሌ በመሰጠቱት ፈንታ በኃይል የጸሐፊውን ሐሳብን የመግለጽ ነጻነት የተቃወሙትን፣ ሁሉቱንም በስበ በማስተናገድ ጉዳዩን ለመፍታት አየሚር፣ ጉዳዩ እስካሁን በእንጥልጥል ነው። ተመስገን ደሳለኝ ሦስት ዓመት የተፈረደበት የመንግሥት ባለሥልጣናትን የማያስደስት አልፎም የሚያበሳጭ ጽሑፍ ስለጻፈ ነው። የዚህ ጽሑፍ ጸሐፊ ክሱ ከሽብር ወደ «በጽሑፍ አመጽ ማነሳሳት» የተቀየረው በተመሳሳይ ምክንያት ነው። ተጠያቂነት የሌለባቸው የመንግሥት ባለሥልጣናት በሐሳብ ሲበሳጩ ውጤቱ የከፋ ይሆናል።

## ፪ - የጥላቻ ንግግር እና አመጽ ማነሳሳት

በ1987 ሩዋንዳ በዓለማችን የቅርብ ጊዜ ታሪክ ውስጥ ለትግባጭ የሆነውን ዘር ለካስም አርድታለች። በ100 ቀናት ውስጥ 800 ሺሕ ያህል ሰዎች ተጨፍጭፈዋል። በጭፍጨፋው 70 በመቶ ቱትሲዎች (ወይም 20 በመቶ ሩዋንዳውያን አልቀዋል)። የጭፍጨፋው መነሻ ላይ የታሪክ ባለሙያዎች ሙሉ ለሙሉ ባይስማሙም በጉን ሰም አመጽ እንዲቀጣጠል ያደረገው ግን የሚዲያ የጥላቻ ንግግር እንደሆነ ብዙዎቹ ይስማማሉ። ከዘር ጭፍጨፋው ዓመት ቀድሞ የተቋቋመው ሬዲዮ-ቴሌቪዥን ሊብሬ ደስ ሚል ኮሊንስ (አር.ቲ.ኤል.ኤም.ሲ) ዋነኛ ሚና ተጫውቷል። አንዳንድ ጥናቶች በዘር ጭፍጨፋው የዚህን ሚዲያ ተቋም ሚና እስከ 10 በመቶ ያደርሱታል። ሬዲዮው በጣም ተወዳጅ ከመሆኑ የተነሳ ከዜናዎቹ ጋር በአጭር ጊዜ ለመዋሃድ በቅቷል። ይህ ሬዲዮ ነበር ቱትሲዎችን "በረሮ" ብሎ መጥራት የጀመረው። "በረሮዎችን ደግሞ ማስወገድ አስፈላጊ ነበር።" አለበለዚያ ችግር ያስከትላሉ። ሬዲዮው በተጨማሪም "በረሮ" ብሎ የጠራቸውን ዜጎች ማስወገድ ስለሚገባለት ብቻ ሳይሆን እንዴት መወገድ እንዳለባቸው ጭምር ተንትኗል። የጭፍጨፋው ፈፃሚዎች በአንድ እጃቸው ቆንጨራ፣ በሌላኛው ሬዲዮ ይዘው እንደነበር ሪፖርት ተደርጓል።

በሩዋንዳ ጭፍጨፋ የነበረው ሬዲዮ ብቻ አልነበረም። ጋዜጣም የበኩሉን ተጫውቷል። ካንጉራ የተባለ ሳምንታዊ ጋዜጣ ብሁቱ በሥርቱ ትዕዛዛት፣ የተሰኘ ተወዳጅ ጋዜጣ ነበረው። ጋዜጣው በይፋ ሁቱዎች ከቱትሲዎች ጋር ምንም ወዳጅነት እንደሌላቸው አውጇል። ሐላት ናቸው በሚል ሚስቶች በቡሎቻቸው፣ ንግዶች በንግዱ ላይ በዚህ የማንነት ጠላትነት ላይ ተመሥርተው እንዲነሱ አድርጓል።

የሩዋንዳ ሚዲያዎች የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ እና ዘመቻ ውጤቱ እልቂት ሆኗል። ሚዲያዎቹ ወደዘር ጭፍጨፋ የደረሱት በሦስት ደረጃዎች ነው፣ መንግሥት ሚዲያውን በተሳሳተ መንገድ ተጠቅሞባቸዋል - በጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ለዘር ጭፍጨፋ ማዘጋጃ አድርጓታል (1)፣ በጭፍጨፋው ወቅት አመፁን አቀጣጥሏል (2)፣ ከዚያም የጥፋቱ መጠን በትክክል ለሕዝብ እንዳይደርስ አድርጓል (3)።

አሁን የሩዋንዳ መንግሥት ያንን መጥፎ ጠባሳ የሚያበትን ታሪክ ለማጥፋት በማሰብ የሁለቱንም ጎሳዎች ማንነት ከልሏል። በሩዋንዳ አንዱ ሌላውን የእሱ ጎሳ አባል ነው ብሎ በይፋ መናገር አይፈቀድለትም። ይህን የዘር ጭፍጨፋን በማፈን ፈንታ ሐሳብን የመግለጽ ነጻነትን ያፈነ እርምጃ እንደሆነ አጥኚዎች ይከራከራሉ። (Yakaré-Oulé (Nani) Jansen, 2014) ለሩዋንዳ መንግሥት ግን ጉዳዩ ግራ ኢጋቢ ነው። ለሩዋንዳ መንግሥት ብቻ ሳይሆን ለብዙዎች ሌሎችን እስከ ማበሳጨት በሚደርሰው ሐሳብን የመግለጽ ነጻነት፣ በጥላቻ ንግግር እና በአመጽ ቅስቀሳ መካከል ያለውን ልዩነት መረዳት አስቸጋሪ ፈተና ይሆንባቸዋል።

ኢትዮጵያም ጭምር የፈረመችው የሲቪል እና ፖለቲካዊ መብቶች ዓለምአቀፍ ቃልኪዳን እንደሚለው "ማንኛውም ዓይነት በዜግነት፣ በዘር፣ ወይም ኃይማኖት ላይ የተመሠረተ የማግለል፣ ጠላትነት ወይም አመጽ የሚያነሳሳ መልዕክት በሕግ መከልከል አለበት።" ሆኖም አንድ ንግግር ወይም መልዕክት የጥላቻ ሊባል የሚችለው የትኛው ደረጃ ላይ ሲደርስ እንደሆነ መግባባት የለም።

አስቀድመን ባየናቸው ምሳሌዎች የሚዲያ እና አመጽን ግንኙነት ስንመለከት፣ አበሳጭ የተባሉ ይዘቶችን ይዘው የወጡ የሕትመት ውጤቶች፣ አመጽ አልቀሰቀሱም። ይልቁንም የተቃውሞ አመጽ ተቀስቅሶባቸዋል። የሩዋንዳው የዘር ጭፍጨፋ ደግሞ በተቃራኒው አመጹ የተካሄደው በሚዲያዎቹ የጥላቻና ጥፋት ስብከት መሪነት ነው። በነዚህ ሁለት ምሳሌዎች መካከል ያለውን ልዩነት መረዳት ከባድ ላይሆን ይችላል። የአመጽ ቅስቀሳ ከመደረጉ በፊት ለመከላከል ያንን ዓይነት አዝማሚያ ያለውን የሚዲያ ተቋም ቀድሞ መቆጣጠር ግን ከባድ ይሆናል። የሚያደርገል ግን አይደለም። ይህን የሚያደርግ የመንግሥት ሥራ ክፍተት የሚፈጹ አምባገነኖች ሚዲያን (ወይም ሐሳብን የመግለጽ ነጻነትን) ለማፈኛ እንደምክንያት ይጠቀሙበታል፣ እየተጠቀሙበትም ነው።

ኢትዮጵያ ወሰዋ ያለው መንግሥት በዜቤር ላይ ያብሎ አንዱን የሚያበረሽ፣ ሌላውን ተበዳይ የሚያደርጉ የቁርሾ ታሪኮችን እንዲያውም በቡሉ ሲመለከቷቸውና ሲታዩቸው ይታያል። የፖሊው ፓርቲ ከመመሥረቱም ሆነ ከዛም የቤቤር በደል-ተበዳይ ግንኙነትን አጠናክሮ በሚል ሥም ስለሆነ እነዚህ ዓይነቶቹ ትረካዎች የተሰሚነት ይመስላል። ነገር ግን መንግሥት ለእነዚህ አደገኛ አዝማሚያ ጓዳቸው ሐሳቦች/ጽሑፎች ያለውን ትዕግሥት ትንግሥ ታክለ እንኳን ሰርጎቶን ለሚተችት የለውም። ይህም የሚያስገነዝበው መንግሥት ለሐሳብ ነጻነትም፣ ይሁን ሕዝቦች ላይ ለሚደርሰው አመጽ እንደማይጨነቅ፣ ይልቁንም ለሥልጣኑ ብቻ እንደሚሳሳ ነው። ሐሳብን በመግለጽ ነጻነት እና አመጽ በመቀስቀስ መካከል ያለው ልዩነት ጠርቶ በሕግና መመሪያ እንዲደነገግ የማይፈልገውም ለዚያው ነው።

"ማንም ከብስጭት የመጠበቅ መብት የለውም። ይህ መብት እስካሬ ባሰበቢቻቸው ድንጋጌዎች ሁሉ ላይ የለም። ከተበሳጫችሁ፣ የራሳችሁ ችግር ነው፣ እንደእውነቱ ብዙ ነገሮች ብዙ ሰዎችን ያበሳጫቸዋል።" – አሕመድ ሰልማን ሩሽዲ

# ‹‹ለሕጋዊ›› ሕግ አልባ ምላሽ!



ይድነቃቸው ከበደ

> ‹‹ ማንኛውም ዜጋ በሰላማዊ መንገድ ተቃውሞውን መግለጽ ይችላል፤ ሕጋዊ መብቱ ነው፤ በእኛ ሀገር ግን ለዚህ የሚሰጠው ምላሽ ሕግ-አልባ የሆነ፣ በገዢው ግንባር ፍላጎትና ፍቃድ ላይ የተመሠረተ ሕገ-ወጥ አፈና ነው



ተቃውሞ የዴሞክራሲ መገለጫ ነው፤ የመንግሥት አስተዳደር ጤናማነት መለኪያም ጭምር ነው። ዴሞክራሲ በራሱ እጅ እግር ኖሮት የሚንቀሳቀስ ፍጡር አይደለም፤ ዴሞክራሲ በሐሳብና በተግባሩ በሰዎች የሚገለፀን ነው። ከመብቶች መካከል ደግሞ መቃወም አንዱ ነው።

ተቃውሞ በግለሰብ፣ በቡድን እና በተቋም ደረጃ ሊከናወን ይችላል፤ የሚቻለውን ነገር ለማድረግ የአመለካከት ነጻነት በቅድሚያ መኖር አለበት። የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥትም በአንቀጽ 29 ንዑስ-አንቀፅ 1 ይህንኑ ይደግፋል፤ «ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት የመሰለውን አመለካከት ለመያዝ ይችላል።»

ድንጋጌው ግን ለኢሕአዴግ አስተዳደር እቀበት እንደ መውጣት ነው። በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ የሠራተኞች መገምገሚያ አንዱ አባባ «አመለካከት» ነው። ከተሰጠ የሥራ አፈጻጸም በላይ፤ የፖለቲካ አመለካከት የደሞዝና የደረጃ ዕድገት ያስገኛል/ያሳጣል። የትኛውም ሠራተኛ በተመደበበት መደብ የቁንጅ ያህል ችሎታና ብቃት ቢኖረው «አመለካከቱ» በሚዛናው መሠረት ዝቅተኛ ከሆነ ዋጋ የለውም። ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት የመሰለውን አመለካከት የመያዝ መብቱ በራሱ በኢሕአዴግ አስተዳደር ይደፈጠጣል።

ለዴሞክራሲ ዕድገትና ሞት ንጽጽሩ ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ማክበር ወይም አለማክበር ነው። ከዚህ ውጭ ሌላ አማራጭ የለም። ተግባራዊነቱ እንደ ተጠበቀ ሆኖ፤ የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት አንቀፅ 29 ንዑስ-አንቀፅ 2፤ «ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሐሳቡን የመግለጽ ነጻነት አለው።» ይህ ነጻነት የማይተ ወሰን የለውም፤ በማንኛውም የማሰራጫ ዘዴ ሐሳብን ማሰራጨት ይቻላል።

ሐሳብን ከመግለጽ ጋር በተያያዘ የሰማሁት አንድ ነገር ትዝ ይለኛል፤ ነገሩ የተከሰተው በአንድ የመንግሥት መ/ቤት ውስጥ ነው። እና በመሥሪያ ቤቱ በተደረገ ግምገማ ላይ - ነው አሉ - አንዱ ሠራተኛ ተራው ይደርስና ‹አመለካከቱን› ይገልጻል፤ ቢጋላ በእርሱና በገምጋሚዎቹ መካከል ‹ሰፊ ክርክር› ተደረገ፤ ክርክሩ፤ ተገምጋሚው ያልገለጸውን አመለካከት፤ ለመግለጽ አስቦ በሚል የነገ ነበር አሉ፤ ይህች ቁም-ነገር ያዘለች ቀልድ/ጨዋታ፤ ኢሕአዴግ አይደለም ሐሳብ ተገልጾ፤ ያልተገለጸ ሐሳብ እንኳ ምንኛ ‹እንደሚያሸብረው› የምትጠቁም ነች። («አዎ፤ ሐሳቡን አስቤአለሁ፤» የሚለው የቀልዷ ማሳረጊያ ነች፤ «ተጸጽቻለሁ፤ ግለ-ሒሴን አውርጃለው» ነው እንጂ!)

ሐሳብ መግለጽ ይቅርና፤ ሐሳብን ማሰብ በራሱ ሐሳብ የሆነብን እኛው ነን! በእኛ አገር ሐሳብን በነጻነት መግለፅ ለእስር፣ ሞት፣ አገር ጥሎ ለመሰደድ በቂ ምክንያት ነው። ለዜጎች የሚሆንን ነገር በግድ የሚመርጥልን፤ ማሰብ ያለብንን ሐሳብ ‹እዚህ እንዲህ› መሆን አለበት የሚልን መንግሥት ለእኛ ምናችን ነው? ምንም! ሁሉም ማለት በሚቻል መልኩ የሐሳብ ማሰራጫ ተቋማት በእጁ ናቸው! ለመረጣቸው ‹ጋዜጠኞች› ‹ይሄን አድርጉ! እንዲህ በሉ› እያለ እንዳሻው የመዘወር ‹ሥልጣን› በእጁ ነው! ‹እነዚህ፤ እነዚህ› ሚዲያዎች ‹በሬ-ሰላም›፤ ‹በሬ-ልማት›፤ በሬ-ምናምን... ናቸው እያለ የመፈረጅ ‹ሥልጣን› የእርሱ! ‹አንተ አሸባሪ! እሱ አሸባሪ!› የማለት ‹ሥልጣን› ያለው በእጁ! ታዲያ እንዲህ ያለ መንግሥታዊ አስተዳደር ለእኛ ምናችን ነው?! ምናችንም አይደለም!

በአንድ ጤናማ ዴሞክራሲያዊ ሒደት ውስጥ፤ ማንኛውም ሰው በራሱ አመለካከቱ ለደረሰበት ድምዳሜ መሠረት ሕጋዊ ተቃውሞውንም ሆነ ድጋፉን ያለማንም ጣልቃ ገብነት የመግለፅ መብቱ በእኛ አገር ሕግ ላይ ብቻ ሳይሆን፤ በሌሎች ዓለም አቀፍ ሕጎችም ተቀባይነት ያለው ዴሞክራሲያዊ መብት ነው። ለዚህም ነው መብቱ በሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌ የተቀመጠው። በኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት የመሰብሰብ፤ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነጻነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት የተጠበቀ ነው። በዚህም መሠረት መቃወም የተቃወሙትን ነገር በሰልፍም ሆነ በስብሰባ መግለፅ የሕግ ከለላ አለው።

መንግሥት የሕዝብ መብት ለመጠበቅ የቆመ የሕዝብ አገልጋይ ነው! ሕዝብ በመንግሥት ቅር ከተሰኘ የምርጫን ዘመን ጠብቆ ኃላፊነት ከመስጠትና ከመንፈግ ባሻገር፤ በማንኛውም ጊዜና ቦታ በሕጋዊ መንገድ በመንግሥት ላይ ያለውን ተቃውሞ እና አቤቱታ ማቅረብ ይችላል። የሕወሓት/ኢሕአዴግ የመንግሥት፤ ለአቅመ ትችትና ተቃውሞ ያልደረሰ ነው እንደሚባለው፤ የእውነትም ‹ድንክዬ› መንግሥት ነው።

የአገዛዙን ሥርዓት ለመደገፍ የሕዝብ ሀብት ከሆኑ ንብረቶች ጀምሮ፤ እስከ ማሰብ ደረጃ የውዴታ ግዴታ እንዲገዙ በማድረግ፤ በሚያስፈልጋቸው ቦታና በወደዱት ሰዓት ካሰኙላቸው የተፈለገው ነገር ሁሉ ይደረጋል። ደስ ካላቸውም በመገናኛ ብዙኃን የቀጥታ ስርጭት ሊያስተላልፉ ይችላሉ። የሚገርመው ነገር የአገዛዙን ሥርዓት በመቃወም የተጠራ ሰልፍ ወይም ስብሰባ ካለ፤ በሕዝብ ሀብት በሚተዳደሩ የመንግሥት የመገናኛ ብዙኃን ‹ሰልፉ/ስብሰባው እውቅና ያልተሰጠው ስለሆነ ማንም እንዳይሳተፍ፤ ለመሳተፍ በሚሞክሩት ላይ ፖሊስ ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል› በማለት ያስፈራራል።

ማንኛውም ዜጋ በሰላማዊ መንገድ ተቃውሞውን መግለጽ ይችላል፤ ሕጋዊ መብቱ ነው! በእኛ ሀገር ግን ለዚህ የሚሰጠው ምላሽ ሕግ-አልባ የሆነ፤ በገዢው ግንባር ፍላጎትና ፍቃድ ላይ የተመሠረተ ሕገ-ወጥ አፈና ነው። የዚህ ዓይነቱ ሥርዓት መገለጫ የአስተዳደር አቅም ማነስን ያሳያል። በሕዝብ ትከሻ ላይ ተቀምጦ የሕዝብ ቅሬታን ለመቀበል ፍቃደኛ የአለመሆን ውጤት «የሰሁብትም!... የለሁብትም!...› እንዳይሆን!

‹ዴሞክራሲ ማለት ምን ማለት ነው?› ከሚለው መጽሐፍ የቀነጨብኩት አስፍሬ ጽሑፌን እቋጫለሁ፤

‹በመራጩ ሕዝብ ስምምነት ላይ የተመሠረተ መንግሥት በሙሉ ልቡና የመናገር እና የመጠበን ሥልጣንና ኃይል ይኖረዋል። ይህ ልበ-ሙሉነት በወታደራዊ ኃይል ለተጨበጠ ሥልጣን እና በሕዝብ ላልተመረጠ መንግሥት በቀላሉ የሚገኝ አይደለም።›





# ብሔርነትና ዜግነት



ደሳለኝ ስዩም
desalegnseyoum@yahoo.com

**ለጽሑፌ መነሻ የሆነኝ፤ ከቤቴ የተልከሰከሱ ወረቀቶች ሳስተካክል ከመካከላቸው ያገኘኋቸው ጥቂት ገጾች የሚያወሩት ቁም-ነገር ነው። ወረቀቶቹ የሆነ ኮርስ የተማርኩባቸው ናቸው። የሆኖ ሆኖ የጽሑፌ መሠረታዊ ትኩረት በሦስት ሊመዘዝ ይችላል፤ - በብሔር ምንነት፤ በብሔሮች ሥነ-ልቦና እና አማራ የት ነው? በሚሉ። አሳሬ የመጣልኝን ብቻ ጽፍና ወደ ፊት - ወኔው ቢኖር - በርዕስ-ጉዳዩ ላይ ቀጥላለሁ።**

## አንድ

ርዕስ ያደረግኹትን ሐረግ የወሰድኩት ከዶክተር ዳኛቸው አሰፋ ነው። ዶክተሩ ሐረጉን የተጠቀሙት ‹ብሔር ጎሳና፤ ዜግነት ኢትዮጵያዊነት ለሚሉት ፅንሰ-ሐሳቦች ማመሳከሪያ ነው።እና ሰው ሲተዋወቅ አስቀድመው፤ ‹ብሔር ነህ? ዜጋ ነህ?› ብለው እንደሚጠይቁ ይናገራሉ።

## ወረቀቱና የ‹‹ብሔር›› ትርጓሜ

<<An ethnic group is defined here as a collectivity within a large society having real or putative common ancestry, memories of a shared historical past, and cultural focus on one or more symbolic elements defined as the epitome of their people hood. Examples of such symbolic elements are: kinship patterns, physical contiguity (as in localism or sectionalism), religious affiliation, language or dialect forms, tribal affiliation, nationality, phenotypical features, or any combination of these. A necessary accompaniment is some consciousness of kind among members of the group.>>

‹‹ብሔር›› ስንል በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ሐሳባዊ ወይም ተጨባጭ የወል ማንነት ያለው ስብስብ ነው። ይህም ሲባል የጋራ ታሪክ፤ ለሰዎቹ ማንነት አንድ ወይም ብዙ የወል ዕሴት፤ እንደ ምሳሌያም የዝምድና፤ የቅርርብ፤ የሃይማኖት፤ የቋንቋና የዘር፤ የጎሳና የዜግነት፤ ሌላም እንዲህ ያሉ የማንነት ማስተንተኛ፤ እንዲሁም ስለጉዳዩ እውቀታዊ ንቃት ሊኖር ማለታችን ነው። (ሐሳቡ Shchermerhorn የተባሉ ጸሐፊ ስለመሆኑ ተገልጿል።)

ከላይ የተገለጸው ሐሳብ የጎሳን ትርጓሜ እንጂ፤ የሀገራችን መንግሥት እንደሚጠቀምበት የሀገርን (ብሔርን) ትርጓሜ የሚያሳይ አይደለም። በጥቅሉም የአንድን ክልል አካባቢ ሁነት የሚያብራራ እንጂ፤ በአንድ ትልቅ ሀገር ውስጥ ያለን የጋራ ማዘሬት ብሉም ዜግነት የሚያሳይ አይደለም። (ወይስ ገልብጠን እንረዳው - የሀገር (ብሔር) ትርጉም ነው ብለን?) ያስተማረኛችን ማስታወሻ ከላይ የተገለጸውን መሠረት አድርጎ ይቀጥላል። ወደ እናት ሀገር ጉዳይ ሲገባም፤

‹‹It [Ethiopian people] is also the people who truly characterize the diversity. Numerically, it hosts a number of ethnic groups which are not yet precisely known but frequently estimated as just over 80.

‹‹Currently, only sixty-nine nations, nationalities and peoples of Ethiopia are represented in the upper of House of Federation (the Secretariat of House of Federation, 2007). Others are represented in the House of Nationalities of the Southern Nations, Nationalities and Peoples Regional State; and hence their total number is under eighty as represented in both Houses.››

‹‹የኢትዮጵያ ህዝብ እውነተኛውን ብዝኃነት የሚያሳይ የብዙ ‹‹ብሔሮች›› ስብስብ ነው። የብሔሮችን ቁጥር አስረግጦ ለመናገር ቢያስቸግርም ከሰማኒያ በላይ እንደሚሆኑ ይገመታል። ይሁንና የፌዴሬሽን ም/ቤት ጽ/ቤት በ2007 እንዳስታወቀው ስልሳ ዘጠኝ ብሔሮች በምክር ቤቱ ሲወከሉ በደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ህዝቦች ክልል የብሔረሰቦች ምክር ቤት የተወከሉትን ሌሎችን ጨምሮ ሰማኒያ የሚደርስ ቁጥር አልተመዘገበም።››

እንዲህ ቁልጭ ብሎ በማይታየውና የሚመስለኝም ምክር ቤት እንኳ በትክክል ይህን ያህል ብዛት ያለው ‹ብሔር› አለ ብሎ መናገር ባልቻለበት በዚህ ጊዜ፤ ነገሮችን ሥር እየሰደደ ነው። በተቃውሞ ጎራ ያሉ (ኅብረ-ብሔራዊ ነን የሚሉ) አብዝተው የሚያሰሙት ድምፅ፤ ይህ የጎሰኝነት ስሜት ሀገሪቱን ችግር ላይ ሊጥል እንደሚችል የሚወተውት ነው።

ከሀገር በፊት የክልል ባንዲራ የሚያስቀድሙ፤ ከሙያ ብቃት በፊት አካባቢያዊነትን የሚቀጥሩ፤ ከስፋት ይልቅ ጥበትን የሚመኩ፤ ሁሉም ነገር እኔ ጋር፤ ከኔ በላይ ሀገር የለኝም የሚሉ ...ድምፆች እየተሰሙ እንዳልሆኑ የሚከራከር ይኖር ይሆን? ይሄን ጊዜ ነው የዶክተር ዳኛቸው አሰፋ ጥያቄ የሚነሳው፤ ብሔር ነህ ዜጋ ነህ?

እዚህ ጋር አንድ ነገር ልብ ማለት ይቻላል፤ እዚህ ድረስ ደርሰን የሰውን ማንነት ለማወቅ ብሔርንትና ዜግነትን እንደ ማጣሪያ ለመጠቀም የተገደድነበት እንዳች አስገዳጅ ኃይል እየገፋን እንደ ሆነ፤ ለእኔ እንደዚህ ይሰማኛል። ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ፤ ከሰሜን እስከ ደቡብ ያለው ሰው ስለሆነ አንድ ዓይነት አመለካከት ያልያዘበት፤ ማንነት ለአንዳንዱ ‹ብሔር› ለሌላው ‹ዜግነት› የሆነበት ምክንያት ምንድን ነው?

## ሁለት

ጥናት ስለመሆኑ መረጃ ባይኖረኝም፤ በተደጋጋሚ ሲባል የምሰማው አንድ ነገር፤ አማራ ‹አማራ› ተብሎ መጠራት አይፈልግም። ጎሰኝነት ስለማይመቸው፤ ይልቁን ብሔር የሚለው ቃል ሀገርን ይጠቅሳልና የአማራ ተወላጆች ‹ብሔርህ?› ሲባል ‹ኢትዮጵያዊ› ማለት ይቀናቸዋል። በዚህ ውስጥ አንድ ትልቅ ሐሳብ አለ። ይኸውም ሀገር ነው!

በርግጥ ቅርብ ጊዜ የታተመው ‹‹አንቀጽ 39›› የተባለ መጽሐፍ እድምቶ እንደሚገልጸው፤ በሰው-ልጆች ማኅበራዊ አካባቢ ሁነት መገራት የሰው ልጅ ዕጣ ፈንታ ነውና ሌሎች ጎሳቸውን ስለስቀደሙ አማሮች (አዲስ አበቤዎችም) ሀገራቸውን ስለስቀደሙ ‹‹እኛ ጥፋተኛ፤ እነሱ ልማተኛ ነው›› ለማለት ያስቸግራል። ይሁንና ይሄ የጎሰኝነት አስተሳሰብ ፊደል የቆጠሩና ብዙ በሥርት ዕድሜ የጠገቡትም ላይ ነግሦ መታየቱ ግን ጥያቄ ማጫሩ አይቀርም። ወደ ነበርንበት እንመለስ!

የፖለቲካና የብዙኃን መገናኛ ሰዎች አብዝተው ሲሉትና ሲጽፉት የማየው ነገር አለ፤ አማራ ‹አማራ› የሚለውን ስያሜ ያለውድ በግድ ከኢትዮጵያዊነት እንዲያስቀድመው እየተገደደ እንደሚገኝ። በዚህም የተነሳ የአማራ ተወላጆች የሥራና የመኖር መብት እየተነፈጋቸው ከልዩ ልዩ የሀገሪቱ ክልሎች ሲፈናቀሉ ይስተዋላል፤ ሲገደሉ፤ ቤታቸው ሲቃጠልና ንብረታቸው ሲዘረፍም ጭምር።

በዚህም ውስጥ አንድ ትልቅ ነገር አለ፤ ላይ እንደ ተመለከተው፤ ‹ብሔር ለእኔ ኢትዮጵያዊነት ነው› ብሎ የሚያምንን አንድ ማኅበረሰብ ከሀገር በፊት ብሔርን (እንደ ብዙኃኑ) ማስቀደም እንዲለምድ፤ ቋንቋና ዘሩን እየለየ ግፍ ቢፈጸምበት የጎሰኝነት ስሜትን ሊያዳብር ይችላል የሚለው። ሐሳቡን በሳይንስ መርህዎች ለማስረዳት ጠጠር የሚል ቢሆንም፤ ከእሙክንዮ ግን የወጣ አይመስለኝም።

ይህንን ለመመልከት አማራ ክልልን እያስተዳደረ የሚገኘው ብአዴን ከሰሩት በፊት ልደቱን ሲደግስ በተሰይ የአማራ ቴሌቭዥንን አጨናንቀው ከነበሩ ስብካዎች ‹የአማራ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ብሔርተኝነትን ሊያዳብር ይገባል› ያለውን እናገኛለን። ይህን የምጠቅሰው ኢትዮጵያዊነትን የሚያቀነቅነው ኢሕአፓ አባል የነበሩት እና ቆይተው ኢሕአዴግን የመሠረቱት ሰዎች እውን ብሔርተኝነት ይጠቅማል ብለው አስበው ተናገሩ ለማለት አይደለም። አይመስለኝምም።

ለምን እንዲሉ መሰላችሁ ንግግሩን ሳስተምጥ እችላለሁ፤ የአራት ድርጅቶች ውህድ የሆነው ኢሕአዴግ ለግምገማ ሲቀመጥ ምናልባት የብአዴን አመራሮችን ‹ሕዝባችሁን ከዜግነት ወደ ብሔርነት መቀየር አልቻላችሁም› ብሎ ስለተመሙባቸው ይሆናል፤ ወይም ብአዴን ክልሉን እያስተዳደረ ስለሆነ የክልሉ ባለውለታ ለማደታዊ ፓርቲ መሆኑን መስበክ ፈልጎ ይሆናል፤ ወይም በዘማት ኅብረ-ብሔራዊ ተቃዋሚዎች መካከል ወይም ጥግ የሚያደርጉት አማራውን ስለሆነ እኒህን ፓርቲዎች ለመደቆስ - ዘር ከልዣም ይዞ ለገን መዝለን - ስብእናን አቅጭ ሆና ሊሆን ይችላል።

እንደሚ ሐሳቡን ነጥለን ለማየት ብንችል ዴሞክራሲያዊ ብሔርተኝነት ምን ማለት ነው? ለመሆኑስ ብሔርተኝነት ከዴሞክራሲ ጋር ምን ዝምድና አለው? ያው አብዮታዊ ዴሞክራሲ እንደሚለው መገዘብ ቃላት ላይ ተፈልጎ የማይደገኝ ጽንሰ ሐሳብ ይመስላል።

በሌላ በኩል በሚዘለው ዓይነቱን የሚቀያይር የመብት ረገጣ አማራ ናቸው በተባሉ ሰዎች ላይ ሲደጋገም እናያለን። ይሄን ማየት ከተቻለ የብአዴንን ዴሞክራሲያዊ ብሔርተኝነት የጎንዮሽ በላይ ስሜት መሆኑን መረዳት አያዳግትም።

እነዚህን ሁለት ዓይነት የጎጂና የተጎጂ ወገን ይዘን ወደ ፊልሙ ብንዘልቅ ምስቅልቅሉ የወጣ፤ መስመሩ የማይለይ የጨለማት መንገድ እናያለን። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ፊልሙን ካየው ከስቀደሰ ርዕሰ-ጉዳዮች መካከል ‹አማራ ራሱን ማስከበር አለበት!›፤ ‹አማራ ሌላሱ መደራጀት አለበት!›፤ ‹አማራ የራሱን ነጻ ሀገር መመሥረት አለበት!› የሚሉት ይገኙበታል። ይህ የዴሞክራሲያዊ ብሔርተኝነት ሰበክ ያመጣው ይሆን?

በዚህ ውስጥ አንድ ልንመለከተው የምንችለው ነጥብ አለ። ይኸውም ለአንድ ወይም ለሌላ ዓላማ በሌሎች ብሔሮች ላይ ሲደርስ የማይታይ በደል በአማራ ላይ በመድረሱ ምክንያት ሆዱ እየሻከረ ያለ ስለመኖሩ። ለምሳሌ ከደቡብም ይሁን ከቤንሻንጉል የተፈናቀሉ አማሮች ብቻ እንጂ ሌሎች በስመሮቹው ሲወሩ የሰማነው ነገር የለም። ባለፈው የኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በደል ሲፈጸም የኖረ ብቸኛ ብሔር ተደርጎ የሚተረከው አማራ ነው። የሀገርን ታሪክ እንደ ሀገር ሌሎችም ብሔሮች ሊጋሩት አልቻሉም።

# የተረሳው መንገድ


ተማም አባቡልጉ

ብዙውን ጊዜ የኢህአዴግ አባላትና ባለሥልጣናት ከነሱ ውጪም ይሁን በነሱ ውስጥ የመብትና የነፃነት ጥያቄ የሚያነሳን ዜጋ ጥያቄው የእሱ ሳይሆን የሌሎች ፀረ-ምናምን አካላት እንደሆነ አድርገው በማቅረብ ከማሸማቀቅ በተጨማሪም የጥያቄውን አቀራረብ በሚመለከት ከአንደበታቸው የማይጠፋው «በሕጋዊና ሠላማዊ መንገድ መቅረብ አለበት» የሚል ሆኖ እስከአሁን ድረስ «በሕጋዊና ሠላማዊ መንገድ ቀረበ» የተባለ ወይም «እንዲህ መቅረብ ነበረበት» ያልተባለ አንድም የመብት ጥያቄ የለም። በኢህአዴግ ላይ የቀረቡት የመብት ጥያቄዎች በሙሉ በሠላማዊና ሕጋዊ መንገድ መቅረብ ነበረባቸው እንጂ አንዳቸውም በሠላማዊና ሕጋዊ መንገድ ቀርበዋል ተብለው ያለማወቃቸው ከምን የመጣ ነው ብለው ያለማወቃቸው ለምንድን ነው?

ኢህአዴግ ማንኛውም ጥያቄ «በሕጋዊና በሠላማዊ መንገድ መቅረብ አለበት» ሲል «ማናችሁም (ሁሉም ዜጋ ወይም ሠው) የምትኖሩበትም የመብትና የነፃነት ጥያቄ መሰማት ስለማልሻ እንድታነሷቸውም ሆነ እንድታቀርቡ አልፈልግም ወይም የቱንም የመብት (የነፃነት ጥያቄዎችን ማንሳት(ማቅረብ) የተከለከለ ነው» ማለቱ ነው።

ይህን ለማለት ያስቻለኝ ምክንያት ሠላማዊ መንገድ ማለት ሕጋዊ መንገድ ማለት ስለሆነና ሕግ ደግሞ በተግባር ሥራ ላይ መዋል ያለበት ወይም የሚውለው ነውና ኢህአዴግ በሀግ ላይ በተወሰነ ደረጃ ቢፈቅድም ሁለቱንም ሠላማዊ (ሕጋዊ) የቅሬታ ማቅረቢያ መንገዶችን በተግባር እንዳይቻሉ (እንዳይኖሩ) ስለደረገ (ማድረጉ) ነው።

አንደኛው ሕጋዊ (ሠላማዊ) የቅሬታ ማቅረቢያ መንገድ ቅሬታን በሠላማዊ ሰልፍ ወይም በሕዝባዊ ስብሰባ ወዘተ... መግለፅ ሲሆን፣ ሠዎች (ፓርቲዎች) ስለዚህ በሕጉ የተጣለባቸውን የማሣወቅ ግዴታ ለመወጣት ሠልፍ (ስብሰባ) የሚያደርጉ መሆኑን መንግስት ለሆነው ኢህአዴግ ሲያሳውቁት በሕጉ በተጣለበት ግዴታ መሠረት ለሠልፉ ጥበቃ ፖሊስ መመደብ ይቅርና (ይተውና) በሕጉ ላይ የሌሉ ምክንያቶችን እየደረደረ በሕጉ በሌለው ሥልጣን ተጠቅሞ ሠልፉን መከልከሉን ይገልፅና ጠያቂዎቹ «ያማ ያንተ ሥልጣን አይደለም (ሥልጣኑ መፍቀድ መከልከል ሣይሆን ዕውቅና ሠጥቶ ጥበቃ የማድረግ ነው) እና የማሳወቀ ዓላማ ለጠያቂዎች ደህንነት ጭምር ነበርና) ማሳወቂ ለኛ ጥበቃ እንድታደርግ ነበርና ባትጠብቀንም ሰልፍ በማድረግ እንቀጥላለን» ብለው ሠልፉን ሲያደርጉ ፖሊስ አምጥቶ ይደበድባቸዋል፣ ያስራቸዋል።

ሁለተኛው አቤቱታ በሕጋዊ / ሠላማዊ/ መንገድ የሚቀርብባቸውን እንደ ፍርድ ቤት ያሉ አካላትን ያደራጃቸው ለሁሉም እንዲሆኑ ሳይሆን ለራሱ እንጂ ለሌሎቹ እንዳይወስኑ ለማስቻል አድሏዊና ነፃና ገለልተኛ ያልሆኑ አድርጎ መሆኑ ነው። እንደፖሊስ፣ ፍ/ቤት፣ ምርጫ ቦርድ ያሉና ነፃና ገለልተኛ መሆን ያለባቸው ተቋማት በሀገሪቷ ስለሌሉና ኢህአዴግ በተግባር እንዳይኖሩ ስላደረጋቸው ስለራሱ በሱ ላይ የሚቀርብ ክስም ሆነ በሱ ላይ በሠላማዊ ሰልፍ ተቃውሞ ለማሰማት የዕውቅና ጥያቄ የሚቀርበው ለራሱ ለኢህአዴግ ስለሆን እሱን ዴሞክራሲያዊ አስመስሎ ግን ምንም ጉዳት ለማያመጣበት ሠልፍ ዕውቅና ሰጥቶ ሌላውን ይከለክላል (ይህኛውን ማስመሠል እንኳን ዛሬ ላይ ሙሉ በሙሉ ትቷታል)። ይህንንም ሁኔታ «አባቱ ዳኛ፣ ልጁ ቀማኛ» በማለት ልናጠቃልለው እንችላለን።

በተጨማሪም የሚያውሳቸው ሕጎች እሱን ብቻ መጥቀም ብቻ ሣይሆን ሌሎችን እንዲጎዱ ተደርገው የሚወጡ ስለሆንና የቱንም ያህል ሠላማዊ ቢሆን የመብት ጥያቄ ባነሱ የትኞቹም ዜጎች ላይ የኃይል እርምጃ ሳይወስድ ቀርቶ ስለማያውቅ ነው። ለምሣሌ የሙስሊም የመብት ጥያቄ አቀራረቡ ሠላማዊ ቢሆንም መንግስት መሪዎቹን ተቀብሎ ቢያነጋግርም እነዚህም ሆኑ እነሱን መርጠው የላኩት መብት ጠያቂዎች በመንግስት የደህንነት፣ የፖሊስና፣ የጦር ሠራዊት አባላት ከመታሠር፣ ከመገደል፣ ከመደብደብ፣ ከሀገር ከመባረርና ከመዋረድ አላመለጡም። በኦሮሚያ ክልል ባሉ እጃቸውን ሠልፍ የወጡት ልጆች ከተመሳሳይ የመንግስት ጡጫ አልተረፉም።

የአንድነትና የሠማያዊ ፓርቲ አባላት በምርጫ ቦርድ ለሁለት የተከፈለው አንድነት ያለአግባብ ከምርጫ ተወዳዳሪነት ስለመሠረዛቸውና ስለቦርዱ ሕገን ያልተከተለ አሠራር ለፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ታይቶ መወሰን ይቅርና መዝገቡ የተዘጉት ተከሳሽ የተደረጉት የመንግስት አካላት ተጠርተው መልስ እንዲሠጡ ሳይደረግ ነው። ከዚያ ቀደም ሲል አንድነት ፓርቲ ስለሠላማዊ ሠልፍ ትንክሳኛ በቅስቀሳ ላይ የነበሩትን አባላት አስራትና ልቃ መውሰድ ወዘተ በአዲስ አበባ ፖሊስ በአ/አበባ ከተማ መስተዳድርና ከንቲባ ላይ ያቀረበውም ክስ ክርክር ተደርጎ ሲያበቃ «የመከሰስ መብት የላችሁም» በሚል ብይን ተዘግቷል። እንአስተዳበር አህመድ በጅዛዊ ሃረካት ፊልም ስበብ በፖሊስ በደህንነት በቴሌቪዥን በፍ/ቤትና በፍ/ቤት ፕሬዚዳንት ላይ ያቀረቡት ክስ ተመሳሳይ ዕጣፈንታ ነው የገጠመው። የተቃዋሚ ፓርቲ ሕዝብን ጠርቶ ማወያየት፣ ሠልፍ ጠርቶ በሕጋዊ መንገድ የማይቀበለውን አሠራርና ሕግ መቃወም ወይም ይህንኑ አስመልክቶ ለፍ/ቤት ክስ አቅርቦ ማሸር ወይም ለማስቀረት መሞከር ሕጉ-ወጥና በራ-ሠላምነት ሆኖ ይህን በማይችልበት ሀገር (ሁኔታ) ይህንን ያደረጉ ዜጎች በሽብርተኝነት በሚከሰሱበት፣ በአደባባይ በሚደበደቡበትና በሚታሠሩበት ሁኔታ ሥር ይህንን ያደረጉ የመንግስት ባለሥልጣናት በሕግ በማይጠየቁበት ሁኔታ ሥር የትኛው እንዴትና በምን መልኩ የቀረበ ጥያቄ ነው? በሠላማዊና በሕጋዊ መንገድ ቀረበ የሚባለው ኢህአዴግ ያለውን ያልተቀበለ ሁሉ ሕጉ-ወጥና ሠላማዊ ያልሆነ በሚባልበት ሁኔታ ሕግም ሠላምም እሱ ያለውን መቀበል ነው ማለት ይሆናል።

ስለሆነም ኢሕአዴግ «ሕጋዊና ሠላማዊ መንገድ» የሚለው አባባል «እኔ ያልኩትን ዝም ብላችሁ እየተቀበላችሁ ኑሩ።እኔን ለመደገፍ ብቻ ሠልፍ ውጡ፣ ተሰብሰቡሁ የእኔን ድል አድንቁ» ከማለት የተለየ አይደለም።ሊሆንም አይችልም። ለኢሕአዴግ «ሠላማዊና ሕጋዊ» ተብሎ ወይም «የፀረ-ሠላምና የፀረ-ልማት እጅ ያለበት» ሳይባል ቀርቶ የሚያውቀው የራሱ የአባላቱና የደጋፊዎቹ ስብሰባና ሠልፍ ብቻ ነው። ይህ ማለት ሕጋዊና ሠላማዊ የሚባለው ሠው የኢሕአዴግ አባል ወይም ደጋፊ ብቻ ሲሆን ሠላማዊና ሕጋዊ ድርጊትም በዚህ የሚደረገው ብቻ ነው ማለት ይሆናል።

«መሬታችን አይነጠቅ!» በሚል የተቃወሙና በዚህም በአረመኔያዊ መንገድ የተገደሉ የኢትዮጵያ ልጆችን የገደሉትን ነፍሰ ገዳዮች በቀጥጥር ሥር ያላደረገው ኢሕአዴግ እተ በቀለ ገርባን ጥጋቸኛ ጎረምሶችን ልኮ ያስፈራራል። የተቃዋሚ ፓርቲ ሚና ግን ምንድን ነው ብሎ ያምናል? ኢህአዴግ የሠራውን የልማት ሥራ በማድነቅና ማዳነቅ አድርጎ ነው የተቃዋሚዎችን ሚና የሚቀበለው። ይህም ሠላማዊነትና ሕጋዊነት እሱን (የሱ አባልና ደጋፊ) መሆን አድርጎ ከመቀበሉ የመጣ ነው።ከአጠቃላይ ለኢህአዴግ ሠላማዊና ሕጋዊ መንገድ (ሃገር) እሱን መደገፍ፣ ማድነቅ፣ ማገዝ፣ ማዳነቅና ማምለክ ብቻና ብቻ ነው። በዚህ አጋጣሚ ለሁሉም ኢትዮጵያዊ የማስተላልፈው መልዕክት ሁሉም እንደየእምነቱ እስከዛሬ ልጆቻችንን ያሠሩትን የደበደቡትን ወይም የገደሉትን ሁሉ እንዲረግም ሲሆን ይህንን ባቀዱ፣ ባዘዙና ባስፈፀሙት ሁሉ ላይ ልጆቻቸው የሞቱባቸው አባቶችና እናቶች የደረሰባቸውን ዓይነት መራር ሐዘን፣ በአደባባይ የተደበደቡ እናቶች፣ አባቶች፣ ሕፃናትና አካውንት፣ አህቶች፣ ወዘተ... ያገኛቸውን ዓይነት ስቃይና ውርደት በቅርቡ ደርሶባቸው ወይም እነሱንም አግኝቷቸው እንዲያሳየን ፈጣሪውን እንዲለምን ነው። ይህንን ስንፈልም በውስጣችን እኛም ያንን ስቃይ እንደየእምነቱ ሁሉም ኢትዮጵያዊ «ይህንን ካሳለፈኝ አውነትም አንተ አይደለሁም የለሁም» ብሎ ከልቡ ፈጣሪውን እንዲማጣተው ነው። ወደፈጣሪው እንዲያለቅስ ነው።

እነዚህ ልጆቻቸው የሞቱባቸውን አባቶች/እናቶች በተግባር አጠገባቸው ባንቆም ወይም ፈጥሚዎችን በአደባባይ ተቃውመን ባንሞግት ሁላችንም በየጓዳችን ይህንን ለፈጣሪያችን ማድረስ ሊያቅተን አይችልም። የደረሰባቸውን ስቃይና ውርደት (በደን) በዓይኑ-ሕሊናችን እያየን መቀበል አቅቶተንም ይህንን ያለማድረጋችን አይገባም ቢያንስ ቢያንስ በዚህ ብቻ የየዳተኞችነት ስሜታችንን ማጠብ መቻላችን እንደሁኔታው ሊሆንም ላይሆንም ቢችልም ለራሳችን ይቅር ለማለት ማሳመኛ ሊሆንን ይችላል። ለራሱ ይቅር የማይል ደግሞ ለምንም በተላሉ አይበቃምና ይህ ስለሆነም ይህ ለወገኖቻችን (ለራሳችን) እንደለውና እንደዚጋ ልናደርግላቸው ግድ ነው። የሚገባው ዝቅተኛው ነገር ስለሆነ ማንም ኢትዮጵያዊ በቤቱ ወይም በየትኛውም የዐሉት መድረክ (ቦታ) መስጊድ ወይም ቤተክርስቲያን ወይም ሌላ ቦታ በግልም ይሁን በቡድን፣ መብታቸውን ስለጠየቁ የታሠሩትን የተደበደቡትን፣ የተዋረዱትን፣ የሞቱትን፣ የተሰደዱትን ወዘተ በሰሙቱ እንዲያስታውሳቸውና ፍትሕ እንዲያገኙ እንዲፀልይላቸውና ይህንን የፈፀሙ አካላት በሌሎቹ ላይ ያደረጉት በነሱም ላይ በፍጥነት እንዲደርስባቸውና የእጃቸውን እንዲያገኙ ለዚህ ያበቃቸውን ሁሀት፣ ስልጣን፣ ጉልበት፣ ብልሃትና ብልጠት ፈጣሪ እንዲነሣቸውና እነዚህ ሁሉ ወደነሱ እንዳይሠሩና እንዳይጠቅሟቸው (እንዲጎዷቸው) እንዲያደርግባቸው አልቅሶ ከልቡ ፈጣሪውን እንዲመሀላቸው እንዲጠይቅላቸው ሁላችሁንም በምታምኑት ሁሉ ይገፍ እጠይቃችኋለሁ። የጠየቃችሁት ሆኖ በተግባር ተፈፅሞ እስከምናየው ድረስ በሙታችሁን በትጋት፣ በፅናትና በፅሎቱ

ወደ ገጽ 25 ዞሯል





# አዲሱ ዐዋጅና ያልተሰሙ የዜጎች ድምፆች


ነቢዩ ሲራክ

ታኅሣሥ 19 ቀን 2008 ዓ.ም ለዓመት ተኩል ገደማ ሲያዋልለን የባጀው አዲሱ የውጭ ሀገራት የስራ ስምሪት አዋጅ መጽደቅ ዜና በፋና ብሮድካስቲንግ ተነግሮናል። አዋጁን ያጸደቀው የኢፌዴሪ የተወካዮች ምክር ቤት መሆኑን ያረዳን የመንግስት መገናኛ ብዙሃን ስለጸደቀው አዋጅ አንኳር ስለተባሉት የመብት ማስጠበቅ ጉዳዮች ዝርዝር መረጃ ባያቀርብም «ጉዳዩ ውስብስብ በመሆኑ በሁለት ሳምንት ይከፈታል የተባለው ስምሪት እስካሁን መዘግየቱ በተሳሳፈው መረጃ ተጠቁሟል።

ምንም እንኳ ሕጉ ቢጸድቅም በርካታ ዜጎችን የምትቀበለው የሳኡዲ ዐረቢያ መንግሥት፣ የኢትዮጵያን ሠራተኞች ለመቀበል እስካሁን ስምምነት ላይ አልተደረሰም። ከሁሉም የሚያስገርመው እኛ መረጃ እያጠቀስን ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት አልመከሩበትም ብንልም፣ መንግስት ጠቃሚ ምክክር መደረጉን ይናገራል። የአዋጁን መጽደቅ ተከትሎ በጅዳ የኢትዮጵያ ቆንስል «አዲሱ የውጭ ሀገራት የስራ ስምሪት አዋጅ ፀደቀ» ሲል ባሰራጨው መረጃ ስር፣ «በአዲሱ አዋጅ መሰረት በሳኪና ተቀባይ ሀገራት መካከል ባሉ ኤጀንሲዎች መካከል ስምምነት ቢደረግም፣ በዋናነት የስራ ስምሪቱ ተግባራዊ የሚሆነው ግን በኢትዮጵያና በሌላኛው ተቀባይ ሀገር መካከል የጋራ ስምምነት ሲኖርወን ብቻ» መሆኑ ተገልጿል። ዳሩ ግን በተቀባይ ሀገራት መካከል ባሉ ሀገራት ሠራተኛ አቅራቢ ኤጀንሲዎች ስምምነት ስለመደረጉ ቆንስል መስሪያ ቤቱ ቢገልጽም፣ ስምምነቱ የት፣ መቼና በምን ሁኔታ እንደተደረገ እስካሁን የተሰጠ መግለጫም ሆነ መረጃ ከዚህ ቀደም አላየንም አልሰማንም።

ልክ የዛሬ አመት ታኅሣሥ 27 ቀን 2007 ዓ.ም ለኛ በማለዳ ያገኘኋቸው ሁለት መረጃዎች የወጡት በሁለቱ እንጋፋ የሳኡዲ ጋዜጦች በዐረብ ኒውስ (Arab News) እና በሳኡዲ ጋዜጣ (Saudi Gazett)e ነው። ቢጋዜጦቹ የወጣው መረጃ የአፈ-ጉባኤ አባ ዱላን ስምንኛ የሳኡዲ ጉብኝት ያመላከተ ነበር። የተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ በሳኡዲ ዐረቢያ ጉብኝት ሲያደርጉ የሰራተኛ ሚኒስትር አድል ፋቂን ጨምሮ በርካታ የመንግስት ኃላፊዎች አግኝተው አነጋግረዋል። አፈ-ጉባኤ አባ ዱላ ገመዳ ከሳኡዲ ባለሥልጣናት ጋር በአዲስ ረቂቅ ሕግ ዙሪያ ከሳኡዲዎች ጋር ሲመክሩ፣ ሳኡዲዎች ቅድመ-ዝግጅት ያልተደረገበትን የሠራተኛ አቅርቦት እንደማይቀበሉ በአጽንኦት መናገራቸውን የሳኡዲ መገናኛ ብዙኃን በማስወጣት ተመልክቷል።

አባ ዱላ ገመዳ በሪያድና በጅዳ ጉብኝታቸው እኔና እኔን መሰሎች ሲትተቀን ስለምንናገረው፣ በቂ ዝግጅት ሳይደረግ ስለተላኩ የእኛ ዜጎች መናገራቸው እውነት ነው። ያኔ አባ ዱላ በሪያድ፣ በጅዳ ጉብኝታቸው በኢንባሲና በቆንስል ኃላፊዎች ከተመረጡ «የተከበሩ ምርጥ» ዜጎች፣ ከኢህአዴግ የድርጅትና ከተለያዩ ጥሪ ከተደረገላቸው የማህበር አባላት ጋር ሲመክሩ፣ አዲሱ ስምምነት በተግቢ ጥናት ካልተደረገ አደገኛነት በገደምዳሜም ቢሆን ነግረዋቸው ነበር። ይህ ሲሆን አፈ-ጉባኤውና ልዑካኑ በማህበራዊ ኑሮው፣ በመብት ጥበቃው፣ በኮንትራት ሰራተኞች የሰቆቃ ብሶት የመረረ እውነት ተመልክቶና ገፈት ቀማሽ የሆነውን ነዋሪ ለአፈ-ጉባኤውና ለልኡካኑን ሊያነጋገራቸው ባይፈቀድም፣ ወደ ስብሰባው ሄደው በሆድ-አደር ኢጋፋሪዎች የተከለከሉ ነዋሪዎች ድምፅ አልተሰማም።

ነገሩ እንዲህ ሆኖና ነዋሪ ዜጋው እንዲህ ተገፍቶ የሀገሪቱ የበላይ ህግ አውጭ የሆነው የተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ሳያዩትና ሳያነጋግሩት ሄደዋል። አፈ-ጉባኤ አባ ዱላን ማግኘት እና ብሶቱን ማሰማት የፈለገው ነዋሪ ጉጉት ምን ይሆን ብዬ ጠያይቄ ነበር። ያገኘሁት ምላሽ ነዋሪው ማቀሚያ ስለጠፋው የኮንትራት ሰራተኞች አበሳ ለመናገር እንጂ መፍትሔ ከባለስልጣኑ ይገኛል ብሎ አለመሆኑን ተረድቻለሁ። እውነት ነው አባቶች «ድሃ በሀልሙ ቅቤ ባይጠግብ... » እንደሚሉት ሆነና፣ ነዋሪው ሆዱ ብሶቱን ማሰማቱ ሀመሙን ያቀልለት መስሎት ለመሆኑ መናገር ይቻላል! ነዋሪው ይህን የማለቱ እንድምታ ፕሬዝደንትና ጠቅላይ ሚኒስትሩን ጨምሮ እስካሁን ሳኡዲ ለመጡት ከፍተኛ ባለስልጣኖች ጥያቄ አቅርቦ መልስ እንዳልተገኘ አሳምሮ የሚያውቀው ነዋሪ፣ በዚህና በዚያ ተስፋ ቆርጧል። ግን ተስፋ ቆርጦም መናገር መተንፈስ ይፈልጋል!

ከምንሰማው ከምናየው የዜጎች አበሳ ጋር ሁነኛ የመብት አስከባሪ የበላይና የበታች ሹማምንት እጥተን በስቃይ ላይ ለመሆናችን ምስክሮች የምናቀርባቸው መረጃዎች ናቸው። በሳኡዲ 350 ሽን የኮንትራት ሰራተኛ እንዳለ በመንግስት ተረጋግጦ እየተነገረን፣ የተብተኑት መብት ሳይጠበቅ አዳዲስ መከረኞችን እምጥተን ልንደፋ ዝግጅቱ የተጠናቀቀ እንደ ሆነ አመልካች ነበር። የሠራተኛ ስምሪቱ በተቀናጀ ጥናት፣ በበቂ ዝግጅት፣ በበጎል አመራር ካልተመራ ሌላ አደጋ እሰው እያልን ጮኸናል። መከራ ብሶቱን፣ እስከፊ ምስሉን እያሳየን «ኧረ ያገር ያለህ!» እያልን እጮሀን ነው! ሰሚ ሆን አውጪኒና ሆን አስፈጻሚ ግን የለም! ሰሚ ያጣው ጨኸታችን ሰሚ እስኪያገኝ ግን ዝም አንልም፣ እያነባን እንጮኻለን!

የአስፈሪው ቀን መቅረብ ምልክቶች

በሳኡዲ መንግሥት የተዘጋው የኮንትራት ሰራተኞች ይጀመራል ተብሎ በሞና ሞና ደላሎች ወሬው ከተነዛ ወዲህ በመንግስት በኩል የረቂቅ ደንቡ መውጣቱን ሰምተን ልክ በአመቱ የአስፈሪው ቀን መቅረብ ምልክት የሆነው አዋጁ ጸድቋል። ይህ ሁሉ ሲደረግ ባለድርሻው የሳውዲ ነዋሪ ሳይመክርበት የውጭ ሰራተኛ ስምሪት አዋጅ ላይ ውይይት ያደረጉት ሰራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ነበሩ። በዚህ ዙሪያ መረጃ ያቀበለው አዲስ አድማስ «ወደ አረብ አገራት የሚሄዱ ሰራተኞች ላይ የሚደርሰውን ችግርና እንግልት ለማስቀረት በሚል ከአንድ ዓመት በላይ ተቋርጦ የቆየውን አሰራር ለማስጀመርና ለመቆጣጠር የተዘጋጀው ረቂቅ አዋጅ ውዝግብ አስነሳ።» በሚል ርዕስ ስር ውይይቱን ትንትኖት ተመልክተናል። ውይይት ተደረገበት የተባለውን ዝርዝር መረጃ ስንቃኝ፣ በዋናነት መታየት ያለበት እንኳ የሰራተኞቹ ደህንነት እና የመብት ጥበቃ ጉዳይ በዝምታ ላይ አልተካተተም። ይህም ይሁን ብለን የቀረበውን መረጃ ስንቃኝ፣ ከዚህ ቀደም በነጻ ያገኙትን ቪዛ በደላላ በየገጠር ከተሞች ሰብስበው እህቶቻችንን ከመላካቸው አስቀድሞ ፈቃድ ሲያወጡ ለመንግስት ያቀረቡት የገንዘብ መያዣ በደል ደርሶባቸው ለሚመለሱ ዜጎች ካሳ ሲከፈል አላየንም አልሰማንም።

በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ሰራተኞችን የሚልኩ ኤጀንሲዎች ያስመዘገቡት ቅሬታ የስራ ፈቃድ ለማግኘት «ከአንድ ሚሊዮን እስከ አምስት ሚሊዮን ብር ካፒታል ሊኖረው ይገባል» መባሉና «ለሰራተኛው መብትና ደህንነት ዋስትና ማስከበሪያ የሚውል 100 ሺህ ዶላር (ከሁለት ሚሊዮን ብር በላይ) በዝግ ሒሳብ የማስቀመጥ ግዴታ አለበት» የሚለውን ተቃውመውታል። ከሃምሳ ሚሊዮን የማያንስ ዜጎች በደል ደርሶባቸው ሲፈናቀሉና በደል ሲደርስባቸው ኢንሹራንስ ሳይቀር ገንዘብ አስከፍለው የላኳቸው ኤጀንሲዎች በደል ሲደርስባቸው ለጉዳታቸው ካሳም ሆነ ለክፈሉት ኢንሹራንስ ተጠቃሚ ያለመሆናቸው ምስጢር በውይይቱ አልተጠየቀም።

ኤጀንሲዎች የሰራተኞችን መብት አሟልተው ስራ ለማሰማራት ውል ገብተው በወሰዱት ፈቃድ ልክ ውል ሲያፈርሱ ከሕግ አስፈጻሚ አካላት በኩል በዝምታ የታለፉት የእኛ ሥራና ሠራተኛ አገናኝ «ኤጀንሲዎች» በአዲሱ ረቂቅ ያነሱት ተቃውሞ «ቅድመ-ሁኔታዎች አያሠሩንም» የሚል ተልእኮ ምክንያት ሆኖ ረቂቁን መቃወማቸው ተሰምቷል። ኤጀንሲዎች ይህን መሰሉ ረቂቅ ሕግ እንደማያሰራቸው እንዲያውም «በውጭ ሀገር ሥራ ለማሰማራት የሚፈልጉትን ዜጎች እድል ያጠብባል፣ ሕገ-ወጥነትንም የሚያባብስ ነው» ሲሉ ሕመሙን የመከረኞቹ ሕመም በማድረግ የአዞ እንባ የማንባት አይነት ቅሬታ ያሰሙት ኤጀንሲዎች፣ ረቂቁን ህግ በውይይቱ የተቃወሙበትና ያልደገፉበት ዋንኛ ምክንያታቸው የተደነገገው ቅድመ ሁኔታ ማሟላት የሚከብዳቸው በመሆኑ እንደ ሆነ ሰምተናል።

ዳግም እንዳናነባ!

ከአንድ አመት በፊት ዩናይትድ ዐረብ ኢሚሬትስን የጎበኙት ፕሬዝዳንት ዶ/ር ሙላቱ እና የኢምሬትስ አምባሳደር አቶ አብድልቃድር የተዘጋውን የዐረብ መንገድ መቼ እንደሚከፈት ተጠይቀው ሕግ/መመሪያ እየወጣ እደ ሆነ ጠቁመው ነበር። ከዚህ ጋር በማያያዝ በስጡት መግለጫም፣ ካሁን ቀደም ከዐረብ ሀገራት ጋር ያልነበረው የሁለትዮሽ ስምምነት በቀጣይ መከወን እንዳለበት ገልጸው ነበር። ይህ መግለጫ በተነገረ ማግስት፣ በቢሻው ጉዳድ ተሰማርተው ከገጠር እስከ ከተማ ከሃምሳ ሚሊዮን በላይ እህቶቻችን ለሳኡዲ ‹ገዢ› ያቀረቡ ደላሎች፣ ጅዳና ሪያድ በመምጣት መረባቸውን እያጠናከሩ መዘጋጀታቸው ይጠቀሳል።

ከዚህ ቀደም በነበረው ሕግ በቂ ዝግጅት ሳይደረግበት፣ በሳኡዲ ብቻ ከሃምሳ ሚሊዮን የሚበልጡ ዜጎች፣ ቤት ሽፋን ሕጋዊ ፈቃድ ባላቸው ኤጀንሲዎች በየገጠር ከተሞች ተበታትነዋል። ዛሬ በኮንትራት የመጡት ያሉበት ደህታ እንዲህ ነው ብሎ መረጃ መስጠት ቀርቶ፣ የትና በምን ሁኔታ እንደሚገኙ የሚያውቁ ኤጀንሲዎችም ሆኑ የመንግስት ተወካዮች የሉንም፣ ይህንንም የምለው በእርግጠኝነት ነው። በተደጋጋሚ ከሚደርሱኝ መረጃዎች መረዳት እንደ ቻልኩት፣ በአሁኑ ሰዓት መግቢያ መውጫ ጠፍቷቸው በደልን እያስተናገዱ የሚንገላቱ በርካታ እህቶች በየቤቱ አሉ። በዚህ መሰሉ የተወሳሰበ ችግር ዜጎች እየተሰቃዩ፣ መብታቸውን የሚያስጠብቅ በሌለበት ሁኔታ፣ ሌላ እንባ ልናነባ የተቃረብን ይመስላል!

የኮንትራ ሠራተኞች አበሳ በቃላት ብቻ አይገለጽም። የሚሠራው ታስቦና ተጠንቶ አይደለም፣ መብታችንን የሚያስጠብቅልን ስለጠፋ ተዋርደናል። አሁን ድረስ በዚህ ዙሪያ ያገባናል ብለን ስንጽፍና ስንናገረው እንደ ተቃዋሚ እየታየንም ቢሆን ግፍ ሰቆቃና ስቃዩን ሊያስለቅ በሚችል ሰፋትና ጥልቀት ጽፈነዋል፣

ወደ ገጽ 25 ዞሯል

# የቫን ቢ መንገድ



አብርሃም ፈቃደ

**የቫን ቢ መሳይ ፕሮፖጋንዳዎች አገራችን ላይ ምን ያህል ጊዜ ተከስተዋል? የየዕለት ተግባራችን ለምን ሆኑ? ጆሯችን በመስማት ስለማይሞላ ነውን? በቴሌቪዥንና በሬድዮ የተነገረውን ሁሉ ኢትዮጵያውያን እንደሚያምኑ በጥናት ያረጋገጠ ይኖር ይሆን? ኢትዮጵያዊው ሁሉ እንዲህ እንዳች ማመዛዘን ተስኖት፣ <በአወገዙ> እና <በአወደሱ> ፕሮፖጋንዳ ይጠለፋል ያለው ማነው?**

ቬት ኮንግ (Viet Cong) በሰሜን ቬትናም የሚደገፍ የሽምቅ ተዋጊ ቡድን መጠሪያ ስም ነው። ቡድኑ በ1960ዎቹ አሜሪካንንና ደቡብ ቬትናምን ያጠቃ ነበር። በአንድ ወቅት ወጣቱ ወታደራቸው ቫን ቢ ለተልዕኮ በተሰማራበት ቦታ ይሞታል። የሽምቅ ቡድኑ ከዚህ በኋላ የቫን ቢን ታሪክ መተረክ ይጀምራል። «ተማርኬ ግርፋትና ስቃይ ከሚደርስብኝ» በማለት አጠገቡ ከሚገኝ የጠላት ታንክ ላይ 10 ኪሎ የሚመዝን ቦንብ በእጆቹ ጨብጦ ከፍ አድርጎ ወደ ላይ በማንሳት፣ «ረዥም ዕድሜ ለብሔራዊ የነጻነት ግንባር! ሞት ለኢምፔሪያሊስቷ አሜሪካ» እያለ በመፎከር፣ 69 አሜሪካውያንንና ሌሎች ቬትናሞችን ገድሎ እሱም ገድሎ ፈጸመ የሚል ዜና በመላው ቬትናም እንዲናኝ አደረገ።

ለአድናቆት ወራት ለወጣቱ ጀግና ቫን ቢ ስንኞች ተሰደሩ፣ የመዝሙር ድምፅ ሰሜን ቬትናምን ናጣት። በሚሊዮን የሚቆጠር በራሪ ወረቀቶች፣ በሙቀ ሺኅዎች የሚቆጠሩ ፖስተሮች፣ ፎቶግራፎችና ለእርሱ ብቻ ሽፋናቸውን የሰጡ ጋዜጦች ታተሙ። ቴሌቪዥኑ፣ ሬድዮኑ፣ ፊልሙ ሁሉ በቫን ቢ ተጥለቀለቀ። ትግሉን እንዴት ታጋዮች ልብ ውስጥ ማኖር እንደሚቻል መጽሔቶች ተጻፉ። በተጻፉበት ልክ ለሌቹ ሽምቅ ታዋጊ ወታደሮችም ሥልጠና ተሰጠ። የሽምቅ ቡድኑ ገና በሊጋቱ ወደ ትግል ተቀላቅሎ በጀግንነት የተሰዋውን ወጣት አርአያነት እንዲከተሉ ለቬትናም ወጣቶች በዓለም ላይ የሚቻለውን ሁሉ አደረገ።

ከሶስት ወሀል ታሪኩን የሚቀይር ዱብዳ ተከሰተ። ሟቹ ቫን ቢ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጠ፣ እንዲህም ሆኑ፦ «ሰሜን ቬትናም እንደሞትኩ በማስታወቅ በሰማዕትነት የተቀበለችኝ ቫን ቢን እኔ ነኝ። አሁኑ አልሞትኩም» አለ («I am Nguyen Van Be and the government of North Vietnam claims I died a martyr, but I am alive in south Vietnam»)። መጨረሻ ላይም በተልዕኮ ላይ ሳለ በደቡብ ቬትናሞች በምርኮ ተይዞ ለማምለጥ ሞክሮ እንዳልተሳካለት፣ እንዲትም ጥይት እንዳልተኮሰ ተናገረ።

የቫን ቢ መሳይ ፕሮፖጋንዳዎች አገራችን ላይ ምን ያህል ጊዜ ተከስተዋል? የየዕለት ተግባራችን ለምን ሆኑ? ጆሯችን በመስማት ስለማይሞላ ነውን? በቴሌቪዥንና በሬድዮ የተነገረውን ሁሉ ኢትዮጵያውያን እንደሚያምኑ በጥናት ያረጋገጠ ይኖር ይሆን? ኢትዮጵያዊው ሁሉ እንዲህ እንዳች ማመዛዘን ተስኖት፣ «በአወገዙ» እና «በአወደሱ» ፕሮፖጋንዳ ይጠለፋል ያለው ማነው? ቃል በቃል ባይሆንም የቀየውንም የቅርቡንም እናስታውሰው፦

«በጦር ሜዳ ያስመዘገብነውን ድል በዓለም-አቀፍ ፍርድ ቤት በዜግ በድጋሚ አሸንፈናል። መላው የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሆይ! እንኳን ደስ አላችሁ!» ነበር ያሉት የተከበሩ ሚኒስትር ሥዩም መስፍን። ነገር ግን ሰባ ሺኅ ወጣቶች ያለቁበት ባድመ እንደ ውጫሌ ውል በትርጉም ስሕተት የተፈጠረ ሳይሆን ልክ እንደ ቫን ቢ የፕሮፖጋንዳ ሰለባ በመሆኑ ነበር። ሰምኑን ማስተር ፕላኑን ተከትሎ በተነሳው ጥያቄ ጠ/ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ በቴሌቪዥን መስኮት ብቅ ብለው መግለጫ ሲሰጡ የተረዳሁት አንድ ነገር ቢኖር፣ ቅጥ አምባሩ በጠፋ የፕሮፖጋንዳ አያያዝ ምክንያት የኢትዮጵያዊው ዋጋ ምን ያህል እንደ ሆነ ነው።

«100 ፐርሰንት መርጦናል» ያሉት ሕዝብ በወታደሮች ጥይት ሞቶ ሳለ ስለወደመ ንብረት ሰፊ ሽፋን መስጠታቸው አንዱ ነው። በርግጥ ንብረትም ቢሆን መውደም የለበትም። ነገር ግን ልንመልሰው የማንችለውን እስትንፋስ መሳድ ነውር ነው። የሚቻቹ ቁጥር መብዛትም ማንሰም ታባቢን ቁጭ ብድግ አያሰኘውም። ለምን ቢባል፣ አጥጋቢ ባልሆነ ምክንያት ግማሽ የሚባል ሰው ኖሮ እርሱ ቢገደል እንኳ፣ ተጨማሪ 10 ሺኅ ሰው ተገድሏል ብሎ እንዲያምን ሰፊ መንገድ ይከፍታልና። እናም የመንግሥት ኃላፊዎች መግለጫ መራራት የሚባል ስሜቱ ከስም በምትኩ ግብዝነት ተጠናውቶታል። የመንበሩና የውጤት ጉዳይ ሳያሳስበው ሕዝብ፣ በትራፊክ አደጋ የሞቱትን ብቻ ሳይሆን፣ በወታደሮች ጥይት ያለቁትን ዜጎች ትክክለኛ ቁጥር ጭምር የማወቅ ሕገ-መንግሥታዊ መብት አለው። በፕሮፖጋንዳ መረብ ተጠምዶ በዝምታ መሰልቀጥ የለበትም። ልክ እንደ ቫን ቢ በድንገት ማንነቱን እስከሚገልፅ መጠበቅ የለበትም።

በድጋሚ ወደ ኋላ ሄደን ስናስታውስ፣ ሟቹ ጠቅላይ ሚኒስትር ሰማሊያ ውስጥ ስለሞቱ ወታደሮች ቁጥር ተጠይቀው ሲመልሱ፣ በጉዳዩ ላይ ምላሽ የመስጠት ግዴታ እንደሌለባቸው ነበር ለአገሪቱ ፓርላማ የተናገሩት። የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹሙ መልስ መስጠት አልገደደም ቢሉም፣ በሌላ መልኩ ወታደሩ ግልጽና አደገኛ ነበር ያሉትን ሥጋት እንደ ደመሰሰ ገልጠዋል። ታዲያ ይህ ጠላታችንን ደመሰሰ፣ ስጋታችንን አስወገደ የተባለውና ልናከብረው የሚገባው ወታደር ድሉ'ንጂ ሞቱ አይመለከታችሁም የተባልነው በምን ምክንያት ነው? እንግዲህ ከተመታት በኋላም ስለሟች ወታደሮች ቁጥር የተሰጠ ይፋዊ መረጃ አልደረሰንም!

**“ ምክር ቤቱ (ስሙ ደስ ይለኛል) እሀል በአንዳንድ ወረዳዎች በእጣ እየታደለ እንደሚገኝ ሪፖርት አቅርቧል። ከወራት በፊት ግን ረሃቡ ፍጹም ከመንግሥት ቁጥጥር ውጭ እንዳልሆነ በልበ-ሙሉነት ሲተረክልን ነበር**

ሌላው፣ ልማታዊ ጋዜጠኝነት በሚል አገር ትርጉሙ የፕሮፖጋንዳ ከበሮ እየደለቁ የሚዘፍኑትን ማጀብ ሆኗል። ታዲያ በዚህ ዓመት በተደጋጋሚ የምንሰማው ድምፅ «በኤል ኒኖ አማካኝነት በተከሰተው ድርቅ ...» የሚለው አገማች ነው። ‹ሕልንግዲህ አይመለስም። ታሪክ ነው።› ተብሎ ፖስተር የለጠፍንለት፣ በጠ/ሚኒስትር ደረጃ ለልማታዊ አርሶ አደሮች በቴሌቪዥንና ከፍ የደመቀ የሽልማት ሥነ-ሥርዓት የተካሄደበት፣ በዓለም-አቀፍ ደረጃ መዝገብ ቃላት የተፋቀበት በጉዳዩ ላይ ተጨማሪ ሥልጠናዎች እና ሴሚናሮች የተካሄዱበትን ታሪክ ገልብጦ በየዕለቱ አልሞትኩም'ን አለው ይለናል። በማን ምክንያት? በኤልኒኖ ምክንያት! ልብ አድርጉ! ኃላፊነት የሚወስደው ሌት ተቀን ተጠያቂ የሚሆነው በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ ኃላፊነት እና ተጠያቂነት የሌለበት አካል ነው።

ከላይ ካነሣሁት ጉዳይ ብዙም ሳንርቅ ምክር ቤቱ (ስሙ ደስ ይለኛል) እሀል በአንዳንድ ወረዳዎች በእጣ እየታደለ እንደሚገኝ ሪፖርት አቅርቧል። ከወራት በፊት ግን ረሃቡ ፍጹም ከመንግሥት ቁጥጥር ውጭ እንዳልሆነ በልበ-ሙሉነት ሲተረክልን ነበር። በተቃራኒው አደጋው ከአቅም በላይ ነው የሚል ሰው ሲገኝ ከመቅጽበት ከፀረ-ሰላም ጎራ ይመደባል። ምን ዓይነት የመቻል አቅም እንዳለ እየተተነተነና አዲሱ ባቡር ለመጀመሪያ ጊዜ የእርዳታ እሀል ጭኖ እንደ ገባ በደምቃሚ በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ ዓይነት ፕሮፖጋንዳ ይደሰኮራል። እያለ እያለ ይቀጥላል።

በመጨረሻም እነ ቢ.ፒ.አር፣ እነ ቢ.ፒ.ኤስ፣ እነ ካይዘንና ሌሎች ምን ያህል በራሪ ወረቀት ይሆን የታተመላቸው? ምን ያህል ሰው ነው ወደ ውጭ ተልኮ የተሰለጠነላቸው? ከፌደራል እስከ ወረዳ ምን ያህል ስብሰባና ሴሚናር ተካሄደ፣ ስንት ሚሊዮን አበል ተበላባቸው? ስንት መጽሔቶች ተጻፉ? ስንት ሚሊዮን ሕዝብ ሠልጥኖ በኢትዮጵያ ላይ ምን ዓይነት ተጨባጭ ለውጥ አመጣ?

«ድህነትን ድል እናደርጋለን» ተብለው የመጡ አስተሳሰቦች እንደ ቫን ቢ እስከ ጥግ ደረሰ ለአንድ ሰሞን አንዝፍንላቸውና በደቡብ ቬትናም በኩል ደግሞ ፕሮፖጋንዳ እንደ ነበሩና ወንብ አይደለም፣ እንዲትም ድህነትን የሚያሸንፍ ጥይት እንዳልተኮሱ እንሰማለን። እነዚህ ሁሉ ጉዳዮች የፕሮፖጋንዳ አዙሪት ጠልፎ የጣላቸው የአስተሳሰብ ሽለፈቶች ናቸው።

ቫን ቢ ሆይ! መንፈስህ ለዘለዓለም ይኑር!





# ይድረስ ለኢሕዴግዬ! ጉዳዩ፤ እየመሸ መሆኑን ስለማሳወቅ!



አቤ ቶኪቻው
(abetokichaw@gmail.com)

ይሄንን ደብዳቤ ልጽፍልሽ ከመጀመሬ በፊት አንድ የቴሌቪዥን ፕሮግራም እየተመለከትኩ ነበር። ያዲሳባ ሴቶች መደዳውን ተደርድረው አንድ ጎረምሳ በፍቅር ያሳቹው ዘንድ በዜማና በሌሎችም ጥቅማጥቅሞች ሲለማመጡትና ‹እኔ እሻል እኔ› ሲፎካከሩበት አየሁ። ‹እጅብ ያለሬ ቴሌቪዥን ጣቢያዎች፣ ስንት ርዕሰ-ጉዳዮች ባሉባት ሀገር ውስጥ ለቀናጆት ጎረምሳ በመምረጥ ይጠመዱ!? ሥልጣኔው እንዴት ዘልቆ ቢገባቸው ነው!› ስል አደንቅኳቸው።

ይህ ዓይነቱ የቴሌቪዥን መሰናዶ እዚህ እኛ የምንኖርበት ሀገርም አለ ...እኔ አሜሪካም ያደርጉታል፣ ልክ ባለፈው ጊዜ አቶ ኃይለማርያም፣ «ድርቅ ብርቅ አይደለም፣ ኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ካሊፎርኒያም በአሁኑ ሰዓት በድርቅ እየተሰቃየ ነው» እንዳሉት በይው! ታድያ ጊዜው የግሎባላይዜሽን ነውና፣ እዚህ እኔ ያለሁበት እንግሊዝና አሜሪካ ያለው ነገር ሁሉ ኢትዮጵያ መኖሩም ብዙም ባይደንቅም፣ ነገር ግን ‹እነርሱጋ ለምን ኖረ? እኛጋስ ለምን ያስፈልጋል?› ብሎ መጠየቅም የቴሌቪዥን ዝግጅት አቅራቢዎቹ ሥራ ነበር። እነ ድርቅንስ እግዜሩ ከላይ አስፋፍቶ ነው... ድርቅናውን ግን ራሳችን እንዳመጣልን ከነርሱ የኮረጅነው ነው። ልብ አድርጊልኝ! ኢሕአዴግዬ! ቆንጆቶች መድረክ ላይ ተከልኩለው «ቆርሰሀ እንቀላል ፍርፍር፣ ራትህን ቋንጣ ፍርፍር እንዳዘላህ፣ በዜፈን እያሞካሹው እንዳባበሉህ እኔን ውሰደኝ እኔን ውሰደኝ» ሲሉ ማየት ከዝ ድርቅና አይደለም ትያለሽ? እንኳሚዎቹ እንግሊዝ እንዲህ ያለውን ዝግጅት በቴሌቪዥናቸው የሚያቀርቡት ማኅበረሰቡ እርስ በእርሱ በቅጡ የማይቀራረብ፣ ሁሉም የየራሱን ከበብ ከቦ «አትድረሱብኝ፣ አልደርስባችሁም» ያሰመረ ዓይነት ስለሆነ፣ የመገናኛ መድረክ ለመፍጠር አስበው ነው ...እኛ ሀገር እውቶብስ ፌርማታው ...ታክሲ ግፊያው ወፍጮ ቤቱ ሳይቀር የፍቅር መድረክ በሆነበት፣ ቆንጆቶች በቴሌቪዥን መስኮት አደባባይ ወጥተው አንዱን ወንድ፣ ‹እኔን ውሰደኝ እኔን...› ሲሽሙበት ማየት በእውኑ እንግዳ ነገር ነው!

አንዳንድ ወዳጆችማ እንደሚጠረጥሩት «ይሄ አይነቱ ዝግጅት ኢህአዴግዬ ጎረምሳውን ሁሉ አስሬ፣ አስሬ ሃገሩ ላይ የወንዶች እጥረት እንዲከሰት በማድረጓ የመጣ ነው» ቢሉ... «የለም... በዚህ እንኳ እኔ አልስማማም፣ ነውር አይደለም እንዴ!? ኢህአዴግዬ እንዲህ አይነት እድሉ አታውቅም። የጾታ እኩልነት በተረጋገጠበት በዚህ ወቅት፣ ወንድ ወንዱን ሰይታ አታስርም። ይሄ ስም ማጥፋት ነው፣ ሁሉንም ነው የምታስረው፣ እንጂ ‹ወንድ ወንዱን ለትማ አስሬ የወንድ እጥረት ተከሰተ› ብሎ ማለት ተራ ስም ማጥፋት ነው ብዬ ተከራከርኩልሽ!

ነገርን ነገር ያነሳዋል። አፈር ስሆን በጨጥና ሰባት ዓመት ምህረት የሆነውን ልንገርሽ... ምነው እንኳ ያኔ «ከንግዲህ ጣቱን የቀሰረ ጣቱ ይቆረጣል» አዋጅ የታወጀ ጊዜ... አንቺኮ ትረሽኛለሽ ደግነቱ እኛ አለንልሽ፣ መዝግበን የያዝን ሰዎች እናስታውስሻለን! እናልሽ ያኔ ጎረምሳው ሁሉ በአደባባይ ወኔ አዋጅ ተለትሞ እስር ቤት ሲገባ አንዱ «አደገኛ ቦዘኔ» ወዳጃችን በዛ በቀውጢ ሰዓት አንዷን አፍቅሮአል ወየታት፣ የፍቅር አጋሩ ሆኚ ... ብሎ ቢላት ጊዜ ምን አለችው መሰለሽ ... «ኔ ጌታ በዚህ ሰዓት ካንተጋ ፍቅር ጀምሬ ካሁን አሁን ታሰረ አልታሰረ እያልኩ የምጨነቅበትና የምሳቀቅበት ምክንያት የለም፣ ግርግሩ ሲያልፍ ካሰብ ያኔ ጠይቀኝ!» አለችው።

የኔ ነገር... ይሄንን ሁሉ ያነሳሁት በምን መሰለሽ ...ላንቺ ይሄንን ደብዳቤ ከመጻፌ በፊት አየሁት ባልኩሽ ፕሮግራም ላይ እንዲ ከረዳ በግድግዳ ተከልሎ ላለየችው ጎረምሳ የዘፈኑለትን ዘፈን፣ እኔ ላንቺ ላጣጥምኪት ኢህአዴግዬ ‹ለምን አልዘፍንላትም?› ስል ባሰብ ጊዜ ዝግጅቱ ትውስ ብሎኝ ይሄንን ሁሉ መዘብዘቤ፣ ‹እስቲ ልቤን አትስቀለው ተሎ ዘፈንልኝ ...› ብለሽ ችኩል ስትይ ታየኝ። አንቺኮ ችኩል ነሽ! እንደው ጥድፍ-ጥድፍ ማለት ትወጃለሽ! ‹ችኩል ብላ ካደረገች በኋላ እንዴት ላድርገው ብላ የምታማክር፣ ከገደለች በኋላ ቁም፣ ብላ የምታስወንችት ችኩል› እያለ ሃገሩ ሲያማሽ መቼም ጆሮ ሰባለቤቱ ባዳ ነውና አልሰማሽም፣ እኔ አለሁልሽ አይደል እንዴ ታድያ ይሄው ነገርኩሽ (ማስታወሻሽን ያዢ ብቻ እንቺ) እና እዚያማት እዚያማት ያሉኝ ምን የሚለውን ዘፈን መሰለሽ...

**"ገዳይ ነሽ ገዳይ ነሽ በፍቅር ገዳይ ነሽ...**

**ገዳይ ነሽ ገዳይ ነሽ በመውደድ ገዳይ ነሽ"**

ምነው ሳትሽ መጣ፣ እውነቱን ነው ገዳይ ነሽ› ...ካላመንሽኝ ያለፉትን ሳምንታት ዜናዎች ዘወር ብለሽ ተመልከቺ ...(በትንፍም፣ «ዞር መመልከት ብቻል መቼ ገዳይ እሆን ነበር» ካልሽኝ አደንቅሻለሁ!) ሰው አንድ ይገድላል፣ ሁለትም - እሺ ይሁን። ሰይጣን ካሳሳተው ምን ይደረጋል፣ አንቺኮ በአንድ ሳምንት ብቻ አንድም ሳይሆን አስርም ሳይሆን መቶ ገዳይ መሆንሽን አለም የመዘገበልሽ ተዓምረኛ ነሽ! ደፍተር ያለው በደፍተሩ ልብ ያለው በልቡ ሁሉንም ጣፎልሻል...

ሰይጣን ብል ጊዜ ምን ትዝ አለኝ ...(ስል መቼም ራስሽው ሚኒስትር ጌታቸው ረዳ ‹ሳትይኝ አትቀሪም።) በትክክል መልሰሻል! እኔ የምልሽ ኢህአዴግዬ? እንደው እንዴት እንዴት አይነቱን ታበቅይ ጀመር ባክሽ ...? የኛ ሀገር ሰው ሰራሱ እንኳን እንዲህ በምሬታ ሰደበሽውና እንዲሁም ‹ምን ለማለት ፈልጋ ነው?› ብሎ ይጠምድሻል። ጭራሽ ባለስልጣኖችሽ የገዛ ህዝብሽን ‹ሰይጣኖች፣ አጋንንቶች፣ ጠንቋዮች!...› እያሉ ሲሳደቡ ዝም ትያለሽ እንዴ! እንዴ ....ማኅበረሰቡ፣ ‹ድርም ሰው የውሉውን ነው የሚያውቀው› ብሉ በሌላ በሌላ እየጠረጠረሽ ነው...!?

ኢህአዴግዬ! ለመሆኑ እንዴት አለሽልኝ? ጤና እንዴት ይዞሻል? ‹ጤና መንሳት እንዴት ይዞሻል?› አላልኩም። የገዛ ጤናሽን ነው የምጠይቅሽ፣ ስብሰባው፣ ግምገማው እንዴት እያደረገሽ ነው? እውነቱን ነው የምልሽ፣ አንዳንዴ ብርቱ የለም፣ ትዝ ይለኛል ከአስር ይሁን አስራ ምናምን አመት በፊት፣ ‹የመበስበስ አደጋ አጋጠመኝ› ተብለሽ? ...ምነው እንኳ የገዛ አባትሽ አቶ መለስ ዜናዊ ነበሩ፣ ‹ኢህአዴግ የመበስበስ አደጋ ላይ ናት› ብለው ባደባባይ የተናገሩት? ...ታዲ የመበስበስ አደጋ ድነሽ ስንቱን ለአደጋ ዳረግሽው? ...ልልሽ ነበር፣ ግን እንዲህ አይባልም!

ይሄው ዛሬም ቃል በቃል መበስበስ ባይባልም፣ ትልቅ የሆነ የመልካም አስተዳደር ችግር ውስጥ እንዳለሽ ቁባ ቁባ ባለስልጣኖችሽ ተሰብስበው ሲናገሩ ሰማን። እኔምልሽ!? አንዳንዴኮ አስማተኛ ነው የምትመስይኝ፣ ...ብዙ ችግር ውስጥ ሆነሽ ‹አለተሳተ ቢታ!› ስትባይ አንቺቴ አፈርሽን ረገፍ ረገፍ አድርገሽ ተነስተሽ ነፍስ ዘርተሽ ዳግም እናታችን ላይ ጉብ ስትይ ... የምርም አስማት የምትችዪ ነው የሚመስለኝ ...

የሆነስ ሆነና፣ ኢህአዴግዬ ዛሬ ዋናው ደብዳቤ ልጽፍለሽ ያነሳሳኝ ጉዳይ እየመሸ መሆኑን ልነግርሽ ፈልጌ ነው ...

ጊዜው እንዴት እንደሚሮጥ ልብ ብለሻል!? እንደ ዋዛ ሃያ አምስት አመት ሞላሽ!? ... ትዝ ይለኛል፣ አስራ ስምንት አመት የሞላሽ ጊዜ፣ ‹ኢህአዴግ እስካሁን ሳጠፋችው ልጅነት ይሏት ነው› ብለን እንምራታለን፣ ከንግዲህ ግን አስራ ስምንት አመት ሞልቷታልና ኃላፊነቱን ትወስዳለች› ብለን ከነደኞቻችን ጋር ስናወራ ነበር... ይሄው ዛሬ ይሄንን ደብዳቤ ስጽፍልሽ ሩብ ምዕተ አመት ሆኖሻል ...ይሄ እድሜ ታድያ ምሬት ጥጥ የምታደርጊበት ብቻ ሳይሆን፣ ያጠፋሽውን፣ የበደልሽውን ሁሉ ተናዝዘሽ ሂሳብሽን ጥጥ ምታደርጊበት እድሜ ይመስለኛል!

እውነቱን ነው የምልሽ ኢህአዴግዬ! እየመሸብሽ ነው ...እንደው ዝም ብሎ ደመና ነው ብለሽ እንዳትታለዪ ...ደም-መና ሆኖ አይቀርም ...(ብዬ ልተኝብሽ እንዴ....) የምሬን ነው እየመሸ ነው... ልብ ብለሽ ብትመለከቺ ሰማዩ ጠቆሯል። ጊዜው እየመሸብሽ ነው...

እና ምን ይጠበስ ...? ያልሽኝ እንደሆን ግን እንደሚከተለው እነግርሻለሁ... እኔ እንደሌላው መሸተብሽልና ወደምትሄጂበት ሄጂ አላልሽም። እኔ እንደማምነው አንቺም ሌላ ሀገር፣ ሌላ ቤት የለሽም። የትም የምትሄጂበት አይኖርሽም... እና ዝም ብለሽ እረፍት አድርጊ ....ጋደም በይ ኢህአዴግዬ! እረፍ በይ...! ቆመሽ አታቁሚን... ጋደም በይ እና እረፊሽ አሳርፊን እንጂ!

ዘንድሮ ምን ልብ አለኝ እንዳትይኝ እንጂ ልብ ብለሽ እንደሆነ፣ ቀድሞ ሰላማዊ ታጋይ የነበሩ ሁሉ በሰላማዊ ትግሉ ተስፋ ቆርጠው የትጥቅ ትግል አማራጭን መጠቀማቸው የመምሸቱ ምልክት ነው ...በየቦታው የህዝብ ሆድ ብሶት አደባባይ መውጣቱ በኦሮሚያ እና በጎንደር እንደሚታየው የሚሆነው ሁሉ የመምሸቱ ምልክት ነው.... አንቺም ብትሆኚ ለጥያቄዎቹ ሁሉ ደምሽ ቶሎ ቶሎ እያለ ተኩሽ ተኩሽ የሚያሰኝሽ የመምሸቱ ምልክት ነው ... እና ግዴየለሽም እረፊ! መሸቶ ሳይመሽ እረፍ በይ!

ታድያ እንዲያም ስልሽ እንደ ንጉስ ሚካኤል ስዑል ተኝተሽ ምሪን አይደለም። ‹መሬውን ተረከቡኝ ልተኛበት... ልረፍበት› ብለሽ ጥሪ አድርጊ! አንቺስ ብትሆኚ ምን በወጣሽ ሃያ አምስት አመት ሙሉ ስትመሪና ሲታማርሪ ትኖሪያለሽ! አሰበላ ምሽቱ እየገፋ አንቺም አርጅናው እየተጫጫነሽ መጥቶ በድቅድቁ ጨለማ ከወደቅሽ ለመነሳት ከባድ ነው ...እና መሸቶ ሳይመሽ ጨለማው ሳይበረታ እረፍ በይ ኢህአዴግዬ!

አክባሪሽ፣

ከሰላምታ ጋር!

# ሙስና በኢሕአዴግ



ደረጀ መላኩ (tilahungesses@gmail.com)

በ<<አዲስ ገጽ>> የታኅሣሥ 9 ቀን 2008 ዓ.ም ዕትም ላይ <<ሙስና ትላንትና ዛሬ>> በሚል ርዕስ በሀገሪቱ ኃይለሥላሴ እና በደርግ መንግሥቶች ስለነበረው የሙስና ባሕርይ የወፍ-በረር ቅኝት አድርጌአለሁ። ዛሬ ደግሞ ሙስና በኢሕአዴግ መንግሥት ያለውን ባሕርይ ለማብራራት የተቻለኝን ያህል እሞክራለሁ።

የኢሕአዴግ ዘመን ሙስና በተቋም ደረጃ ብቻ የተዋቀረ አይደለም፤ ለሙስና ፖለቲካዊ እና ሞራላዊ መከላከያ ለማበጀትም የሞከረ ነው። የዘመኑ ሙስና በዓይነቱም በስፋቱም ከዚህ ቀደሞቹ ዘመነ-መንግሥቶች የላቀና የጠለቀ ነው። የኢሕአዴ ዘመን ሙስና መቋጠሪያ ያለበት ስፍራ የአምባገነንነት ፖለቲካ ሥልጣን ላይ ነው።

ግንባሩ ሥልጣን ከጨበጠበት ጊዜ አንስቶ የሀገሪቱን ሀብት ያግበሰበሰ በመመዝበር ትላላቅ ኩባንያዎችን በግል ባለቤትነት እቁቁሟል የሚል የግል ዕምነት አለኝ። በሀገሪቱ ውስጥ የሚንቀሳቀሱትን ትላልቅ የምርት፣ የግንባታ፣ የትራንስፖርት፣ የጅምላና ችርቻሮ ንግድ እንቅስቃሴዎችን በሙሉ በተቆጣጣሪነት የሚመሩትና የሚቆጣጠሩት እነዚህ የአንባሡ ኩባንያዎች ናቸው። እንደ እውነቱ ከሆነ የአገባቡ የኢኮኖሚ አቅም በእነዚህ ኩባንያዎች ከልል ብቻ የተወሰነ አይደለም። እነዚህ ኩባንያዎች አገባቡ በቀጥታ በስሙ እስመዝግቦ የሚያንቀሳቅሳቸው ናቸው። ከእነዚህ ውጭ በአገባቡ ጥገኛ ግለሰቦች ስም - አፍቃሬ ኢሕአዴጎች - ተመዝግበው የሚንቀሳቀሱ ብዙ መለስተኛ እና ትናንሽ የንግድ ድርጅቶች ስለመኖራቸው አያጠራጥርም።

በሌላ በኩል ከራሱ ከአገባቡ የፖለቲካ ድርጅት አባላት እነሀን መሰል ድርጅቶች በመምራት ተግባር ሲሰማሩ፤ ቀሪዎቹ በመንግሥት ከፍተኛ ኃላፊነቶች ላይ ተመድበው እንደሚሰሩ የታወቀ ነው። በሌሎች የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥም አድርባዮች እና አወ-ባዮች ቁልፍ ቁልፍ የሆኑ የሥልጣን ስፍራ እንዲይዙ ተደርገዋል። እነዚህ ባለሥልጣናት የተመረጡበት መስፈርያ ደግሞ የፖለቲካ ታማኝነት እና ለአገባቡ ቅን ታማኝ መሆን ብቻ ነው።

የአገባቡ ሙስና የተዋቀረው እነሀን የኢሕአዴግ እና የመንግሥት ባለሥልጣናት በማስተሳሰርና በማቀላለፍ ነበር። ከላይ እንደተጠቀመው የኢሕአዴግ ሙስና ከቀደሞቹ የሚለይበት ዋና ጉዳይ ለሚፈጸመው ብልግና የሞራል ሽፋን ለመስጠት መሞከሩ ነው። ይህ ከላይ የኢኮኖሚ ዘርፉን አስመልክቶ የተጠቀሰው ሁኔታ በብዙ መንግሥታዊ ተቋማት የሚደጋገም ነው። ኢሕአዴግ ይህን መሰል ጥልቀትና ስፋት ያለው የሙስና ሥርዓት በሀገሪቱ ላይ በመዘርጋቱ የሀገሪቱን ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሕይወት አሉታዊ በሆነ መንገድ ተጭኖታል። የቀድሞ የአገሪቱ ጠ/ሚኒስትር የነበሩት አቶ መለስ ዜናዊ በሸንጎ መንግሥቱ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት አቶ ታምራት ላይኔ በቅሌት ከሥልጣን በተባረሩ ወቅት በመንግሥታቸው ውስጥ ሙስና ቤቱን እንደ ሠራ ተናግረው ነበር። ማስታወስ ከቻልኩ ጠ/ሚኒስትሩ ታምራት ላይኔን «ብዙ ጊዜ መክሬው ነበር» ሲሉ ነበር የተናገሩት።

ኢሕአዴግ በዚህ ዓይነት መንገድ ያዋቀረው ሙስና አምባገነናዊውን ሥርዓት ለማፈርጠም ጠቅሟል። አገባቡ የትላልቅ ኩባንያዎች ባለቤት በመሆኑና የተለያዩ ማኅበራዊ ተቋማትን አመራር አባላት በፖለቲካ ድርጅቱ አማካይነት ለመቆጣጠር በመቻሉ የአብዛኛውን ኢትዮጵያዊ ሕይወት ለመቆጣጠር አስችሎታል። የገበሬውን ሕይወት በዚህ መዋቅር አማካይነት መቆጣጠር ዋነኛ የኢሕአዴግ ሥልጣን የሕይወት ዋስትና

> በሦስትዮሽ ማእዘናት ቅንጅቱ አማካኝነት ብዙውን የሀገሪቱን ሕዝብና ተቋማት በእይታው ውስጥ ከትቶታል። ተቀጣሪውን የመንግሥት ሠራተኛ በተለያዩ መንገዶች፤ በደም-ወዙ፣ በሥራ ዋስትናው፣ በደረጃ ዕድገቱ… ሊቆጣጠረው ይሞክራል።

ነው። ለይስሙላ እንደ ተካሄዱ በሚነገርላቸው ምርጫዎች (ከግንቦት 97ቱ ምርጫ ውጭ) «99.6 እና 100 በመቶ አሸነፈ» የተባለው በዚህ ቁጥጥር መሣሪያነት ነው። መሬት የመንግሥት በመሆኑ የገበሬ ማኅበራትና ቀበሌዎች አስተዳደር በአጠቃላይ በኢሕአዴግ አባላት/ደጋፊዎች እጅ እንዲወድቅ አድርጓል። ገበሬው የኢሕአዴግን ትእዛዝ ከመቀበልና ከማክፈልም ውጭ መፈናፈኛ አጣ፤ ቀጥሎ ያደረገው ጉዳይ ከላይ የተጠቀሱትን በሙስና ድጋፍ የደረጁ የንግድና ኢኮኖሚ ተቋማትን እንቅስቃሴ ከዚህ መዋቅር ጋር ማቀናጀት ነበር። ሥልጣን ለብቻቸው ካለተቆጣጣሪ ይዘው የሚገኙት ኢሕአዴጎች ስለነበሩ ይህም በቀላሉ የተከናወነ ጉዳይ ነበር።

እንግዲህ የኢሕአዴግን የሙስና ሥርዓት በሦስትዮሽ ማእዘናት - የኢሕአዴግ የንግድ ኩባንያዎች፣ የመንግሥት ባለሥልጣናት እና የኢሕአዴግ ጥገኞች (በገጠር የገበሬ ማኅበራት መሪዎችና በከተማ በአጭር ጊዜ ውስጥ በትክክል ሳይሰሩ ሚሊየነር የሆኑ ሰዎች) - የሚደረግ ትብብሩሽ አድርጎ መመልከት ይቻላል። ይህ ትብብሩሽ ልእልናውን የሚቀዳጀው በ100 ፐርሰንት የፓርላማ ወንበር መቀመጫ ብልጫ ነው። ኢሕአዴግ የፓርላማውን ቁጥጥር በዚህ ዓይነት መንገድ ካደረገ በኋላ «ሙስናን እየተዋጋንው ነው» የሚሉ የሽንገላ ቃላቶች ይኽንዳጎዳሉ። ሥርዓቱ ያልገባው ነገር፤ መሠረት በሌለው ሕንፃ ላይ አብነ-በረድ ቢቀመጥ ድንጋዩ ሽበም እንጂ ጌጥ ሊሆን አለመቻሉን ነው። ገብቶት ሌላውን ለማታለል ከሆነም እእምሮ ያለው ሰው ሊሰተው አይችልም።

ኢሕአዴግ ውስጣዊ በሆነው አምባገነናዊ ቀመሩው ከቁጥጥሩ ውጭ እንዲሆን የሚፈቅደለት የኅብረተሰብ ክፍል የለም። ከላይ እንደ ተመለከተው በሦስትዮሽ ማእዘናት ቅንጅቱ አማካኝነት ብዙውን የሀገሪቱን ሕዝብና ተቋማት በእይታው ውስጥ ከትቶታል። ተቀጣሪውን የመንግሥት ሠራተኛ በተለያዩ መንገዶች፤ በደም-ወዙ፣ በሥራ ዋስትናው፣ በደረጃ ዕድገቱ… ሊቆጣጠረው ይሞክራል። ሊያጠቃ የፈለገውን ሌላ የግል ድርጅት ተቀጣሪን ደግሞ ቀጣሪውን በማስፈራራት እና በቀጣሪው መሥሪያ ቤት ላይ የተለያዩ መንግሥታዊ ጫናዎችን ወይም የግል ኩባንያዎቹን ተጽእኖ በማሳረፍ ሊቆጣጠረው ይሞክራል። በእንዲህ ዓይነት ምድብ ውስጥ ሊገባ የማይችለውን የግል ተዳዳሪና ሥራ አጥ ዜጋ ደግሞ በቀጥታ አስተዳደራዊ መላዎች ሊቆጣጠረው ይሞክራል።

እነዚህ እይታዎች በመነሣት በኢሕአዴግ ዘመን ያለው የሙስና ሥርዓት ምን ያህል አስፈሪ እንደ ሆነ መገንዘብ የሚያዳግት አይሆንም። የኢሕአዴግ ሙስና በገንዘብ ዝርፊያ ብቻ የተወሰነ አይደለም፤ ሥልጣንን በማጠናከርና ንቫውን እካል በመጠጋት የተደራጀ ነው። ስለዚህ የኢሕአዴግ ሙስና በሙሉ ገጽታው ለመረዳት የዚህን ሙስና ሥርዓት ከላይ እስከ ታች በዝርዝር መመርመር ያስፈልጋል።

የአገባቡ ሙስና ለሀገር ዕድገት ቁልፍ ሚና ሊጫወቱ በሚችሉ የፖለቲካ ልሂቃን ላይ ያሳደረው ተጽእኖ ቀላል አይደለም። ልሂቃኑን በተለይ ያነሳሁት ሀገሪቱን ከምትገኝበት ድህነት ለማምለጥ ወሳኙ ጉዳይ አግዛዝነት ያለው የፖለቲካ አመራር ማግኘት በመሆኑ ነው። በአገባቡ የተፈጠረው ሁኔታ ከሁሉም ቀድሞ ያገኛል ማለት የነበረበት የኅብረተሰብ ክፍል ተስፋ እንዲቆርጥ ወይም በፍራቻ ከፖለቲካ ተሳፎ ራሱን እንዲያገል የሚያደርግ ነው።

አገባቡ በተቋም ደረጃ የሚያከናውነው የሙስና ተግባር የኅብረተሰቡን ሕይወት የዘለቀበት ደረጃ በጣም ጥልቅና ሰፊ ነው። የተባባ ፍትሕ አብዛኛውን ማኅበራዊ ሕይወት አዳርሷል። በፊት ከሚታወቀው ማኅበረሰባዊ ግንኙነት በስተጀርባ ሌላ መሪብ በዘረኛነትና በየደረጃው ተፈጥሯል። ለሀገር ኅልውና እንደ መታያ የሚያገለግሉ ተቋማት ሁሉ የተከፈለ ተገለ-ሰውነትን ተላብሰዋል። ከእነርሱም አንዱ ሀገር የተባለ ደባብ ራሱ ነው። ስለዚህ የኢሕአዴግ ሙስና ሀገር የሚባለውን ሸማ እየበተነው እንደሚገኝ መናገር ማጋነን አይሆንም።





# እምባማደሩ ሚኒስትር ፫



አፍሬም ስዩም

አብዛኛውን ጊዜ የእረፍት ቀኑን የሚያሳልፈው እዚህ ነው። ከብቸኛ ሚስቱ እና ከሁለት ሴት ልጆቹ ጋር በመሆን። እዚህ ሁሉመናው ውሸት ከሆነ ወሰሉ አረንጓዴ መሃሉ አበባ ጥጉ በውሃ ከታጠረ ገነት የመሠለ መናፈሻ ውስጥ። ውበትና አየር ለዓይንና ለመንፈስ ምግብ ከሆነበት ሥፍራ። የመናፈሻው ሥፋት በደካማ ግምት በሃገሩ ዋና ከተማ ውስጥ ከሚገኙ ክፍለ ከተሞች፤ የአንዱን ክፍለ ከተማ መጠን ያህላል። የቀድሞው የባህል ሚኒስትር የአሁኑ እምባማደር ዛሬ በዚህ መናፈሻ ውስጥ ብቻውን ይገኛል። እንደሁልጊዜው በውበት እየተደነቀ …በሚያስተውለው እየተገረመ … ለሃገሩ እየተቆጨ …

ሴቶቹ ራቁታቸውን ናቸው ማለት ይቻላል። ነገር ግን ቆዳቸው ከእናንታቸው እስኪላቀቅ ለምኖት የሚዳራቸው የንዘቦች ዓይን በዚህ የለም። እንኳን የሚያስደፍ ለክፉም አይሞክርም። ምክንያቱም …ማንም የሌላውን መብት ሳይነካ እርሱ መኖር እንደፈተደው እንዲኖር የሥልጡን ህዝብ ባህል ስለሚፈቅድና …ሁለተኛው ደግሞ በሥልጡን ህዝብ የተረቀቀው የሴቶችን እና የህፃናትን መብት የሚጠብቀው ሕግ እጅግ ጠንካራ ስለሆነ። …

በልቦናው ለራሱ እንዲህ ተናገረ፤ እውቀት ባለው ሕዝብ መሃል የሚደነገግ ህግ ህያው እና ተግባራዊ ሲሆን፤ ድህነትና ተስፋ መቁረጥ በበረቱበት ህዝብ መሃል የሚደነገግ ሕግ ካለመኖር እኩል ነው። ሲል…

ዘመናቸው የተፈፀመ …ጉልበታቸው የተቀፈፈ …ቆዳቸው የተንዘረፈፈ ሽማግሌዎችና አሮጊቶች በዚህ መናፈሻ ሥፍራ በዝተው ይታያሉ። ወልደዋል ልጆች ግን የሏቸውም …ልጆች ለወላጆቻቸው የሚሆን ጊዜ እንዳይኖራቸው የሥልጡን ህዝብ ሕግ አይፈቅድምና። …እነውንቶቹ በምግቢት እጅ የወደቁ ለልጆቻቸው በዓመት አንዴ ለገና የሚላኩ ብርቅዬዎች ሆነዋል። …

በዚህ በኩል ሃገሩ ክብረ ሙሉ እና መንፈሡ ሕያው እንደሆነች ታሠበችው። … ምንም እንኳ ድህነት የበረታባት ብትሆንም ሃገሩ የመንፈስ ልዕልናዋ ሰማይን ይጠቅሳል፡ የሃገሩ ሰዎች እንደ ሰውነታቸው ይራባሉ-ይጠማሉ-ይታረዛሉ እንጂ የህይወት መንገዳቸው ግን

ከንፀርያም ከመሳዕከት የተቀዳ ነው። …

እባቶች ለልጆቻቸው ብቻ ሳይሆን … የልጆቻቸው መጠን በሆኑ ሁሉ የተከበሩ ናቸው። …በዘጠና ዓመቱ የታመመ እባትን ሥራዎን ጥሎ …ልጆቿን ለጎረቤት አደራ ብላ ጠበል ወይም ሆስፒታል ይዛ የምትሄድ ልጅ በዚህ አለች። …

በእዛውንቱ ሀገር ላይ ሽበት በዝቶባታልና የተቀመጠበትን ወንበር ለእርሱ የሚለቅ ትልማግ በዚህ አለ። በእርሱ ሃገር …

በዚያ በርሱ ሃገር ምናልባት ሥፍራ የሚሰጠውለወጣቶች ይሆናልእንጂለአረጋውያንና ለባልቴቶች ክብርና ሥፍራ ብዙ ነው።

በሃገሩ ልጆች የሌሏቸው አረጋውያን ልጆች አሏቸው። ይህም ምስክር ይሆን ዘንድ በየሠንበቱና በየበዓሉ ዘመን ያስረጃቸውንና አቅም የሌላቸውን ለመዘከር የሚደረገውን ማሠብ ብቻ በቂ ነበር። …

ልባዊ ሙቀት ለውስጡ ተሠማው።ሃገሩ ምንም እንኳ ሠማይ ጠቀስ ፎቆች ባይኖራትም …ረሃብተኛ ብትሆንም …ድህነት ክንዶቿን ያላት ወገቧን ያደቀቃት ብትሆንም …እናናፆ ግን እንደ መሳዕከት ነው። ለማኝ ለለማኝ የሚወፅውትባት ሃገር አለችው። …ወደላ ለብሰው ለምንው ለተቸገሩ የሚሰጡ ፍፁማን አሉባት። ሃገሩ ይሉኝታ በሚባል ቅድስና ራሱን ጎድቶ ለዚያኛው መሆንን የሚሉ ህዝቦች ያሉባት ናትና። ፈገግ አለ። …ከዚህ ህዝብ መሃል ስለወጣም በልቡ ተደሠተ። …በወቅቱ በቀድሞው የባህል ሚኒስትር በአሁኑ እምባማደር ፊት ላይ የነበረው ፈገግታ በመናፈሻው ውስጥ ከነበሩት እበቦች የተዋበ ነበር። …ልክ መልኩ-ጥፉ ከሆነ የባለፀጋ ልጅ አጠገብ እንደቆመች ቆንጆዬ የለማኝ ልጅ …

ጉዳውን ሥልጡን ህዝብ መናፈሻ ውስጥ አስቀምጦ መንፈሱን ወደ ሃገሩ ላከ-ከሃገሩም ወደ እደገበት መንደር …እእርሱ ቤት በና ሲፈላ ሄደህ ጎረቤትን በና ጥራ ሲባል ይሆላቸው ነበር። ምክንያቱም ብዙ ጎረቤቶችን ይጠራ ስለነበር። …በትንሿ ቤታቸው ውስጥ ከዘጠኝ ያላነሠ ሰው ይሰበሰብ ነበርና። የመንደራቸው

መንፈስ ግለኝነትን አይፈቅድም። እቤታቸው በርበሬ ተፈጭቶ ድልህ በሥጊ እየተቀሰሰ በየቤቱ አድርስ ሲባል ምን ያህል ሰልችቶት እንደነበረ አስታወሰ። ያኔ የሰለቸው ሃገሩን ያለ መምረያ የፀበቀ መልዓካዊ ህይወት መሆኑ ተገለፀለት። ስለዚህም የዓመቱ ያፈታውያን በተከላቸው እበቦች መሃል በሮርጌው ተንጋሎ አንሩን ናፈቀ።…

ፊት ለፊ ተቀምጠው የነበሩት ጥንዶች ሃሳቡን ከሃገሩ ወደ እንርሱ መለሰት ለየብቻቸው የተቀመጠ የየራሳቸው የምግብ ምርጫ … በወንዱ በኩል ተበልቶ ያለቀ … በሴቷ በኩል ደግሞ ሩብ የተረፈ እና የተጋበደፉ ኮሳዎች እና ሌሎች ልብ ያላላቸው ነገሮች …

ለአስተናጋጁ ሂሣብ ሊከፍሉ ሁለቱም ወደየፊናቸው ተጓዙ። ሴቲቱ ከትልቁ ቦርሣዋ መሃል ትንሽ ቦርሣ አውጥታ ብር መዘዘች። ወንድየው ከኋላ ኪሱ መጠነኛ ቦርሣ መዞ … ብር ይፈልግ ጀመር።

እነዚህ ሁለት ጥንዶች እምባማደሩ እዚያ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ የነበሩ ሲሆን ጥሩ ሲሣሣቁና ሲጫወቱ ያመሹ ናቸው። …ጥያቄው ግን እንዴት ፍቅረኛሞች የምግባቸውን ሂሣብ ይከፍላሉ? የሚል ነበር።

ያውም እህል መጫወቻ በሆነበት ከእስር ዶላር ለማያበልጥ ሂሣብ። ሃገሩ የኢኮኖሚ መሣይ ከታላላቆቹ ሃገራት ተርታ ቢሆን የድሆች ሃገራትን እዳ እኔ ካልከፈልኩ ብላ ቡራ ከረዩ እንደምትል እርግጠኛ ነበር። ተንስቶ የጥንዶቹን ሂሣብ መክፈል አማረው። ግን ሃገሩ ኢትዮጵያ አልነበረም። አሁን ያለበት ሃገር ሠዎች እንደ ሠው ብቻ የሚኖሩበት የመንፈሥ ልዕልና የከሠመበት ግለኝነት የነገሠበት ሃገር ነው። እዚህ መልካም ለመሆንም ምክንያት ያስፈልጋል።

ከተቀመጠበት ተነስቶ ወደ ቤቱ ሊሄድ ወደ መኪናው እያመራ እያለ አንድ ቆንጆ ጫማ የተጫማ …ቆንጆ ጅንስና ምርጥ ቲ-ሸርት የለበሠ፤ ማክዶናልድ እየጉመጠ ለብቻው የሚያወራ ሠው በአጠገቡ አለፈ …

በልቡም የሠወፍው ችግር ሠው ብቻ እንደሆን እያሠበ … «ይሄ ነጭ ኢትዮጵያ ቢሳክ ኀብሩና ጠግ በመሃል ብቻ የሚታከም ነበር» አለ።

# ዜና

## ፍ/ቤቱ በ<<እነ ከድር መሃመድ>> ላይ ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጠ

በፌደራል እቃቤ ሕግ «በ2001 ዓ.ም የወጣውን የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀፅ 7/1/ ሥር የተመለከተውን በመተላለፍ» የሚል ክስ የተሪሰባቸው «እነ ከድር መሃመድ» በተከታታይ ሁለት ቀናት፣ ሰኞ ታህሳስ 18 ቀን 2008 ዓ.ም እና ማክሰኞ ታህሳስ 19 ቀን 2008 ዓ.ም በፌደራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት 14ኛ ወንጀል ችሎት ቀርበው የነበረ ቢሆንም፣ በተከሳሾቹ ላይ የአቃቤ ሕግ ምስክሮች ሳይደመጡ ቀርተዋል።

ሰኞ ታህሳስ 18 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት አቃቤ ሕግ በችሎት ሊገኝ ባለመቻሉ የተሰየመ ፍ/ቤቱ የአቃቤ ሕግ ምስክሮችን ለመስማት ለታህሳስ 19 ቀን 2008 ዓ.ም ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቷል። ታህሳስ 19 ቀን 2008 ዓ.ም ከሰዓት በኋላ በተሰየመው ችሎት ቀጥራቸው በርካታ የሆኑ የተከሳሾቹ ወዳጆች፣ ዘመዶች፣ ቤተሰቦች …ችሎቱን ለመታደም የተገኙ ቢሆንም «ችሎቱ ሞልቷል» በሚል ችሎቱን እንዳይታደሙ ተደርጓል። አቃቤ ሕግ በዚህ ቀን ቢገኝም በችሎቱ የተሰየሙት ዳኛ ፍ/ቤቱ ባጋጠመው «እክል» ምክንያት መቅረብ ድምፅ ሊያሟላ ስላልቻለ ተለዋጭ ቀጠሮ ለመስጠት እንደሚገደዱ ገልፀዋል። ዳኛው ተለዋጭ ቀጠሮ ከመስጠታቸው በፊት ተከሳሾች አቤቱታቸውን አሰምተዋል።

ከተከሳሾቹ መሃል የቀድሞ በላል ፊዳዮ ዜጋዉ ካሊድ መሃመድ ለፍ/ቤቱ ባሰሙት አቤቱታ እንዲህ ሲሉ ተደምጠዋል።

«በተደጋጋሚ ይህ ምክንያት እየቀረበልን ነው። እኛም ሆን ቤተሰቦቻችን ከፍተኛ እንግልት እየደረሰብን ይገኛል። ይህ ችሎት የአቃቤ ሕግ ምስክሮችን ለመስማት በተደጋጋሚ ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቷል። ነገም ተመሳሳይ ምክንያት እንደማይቀርብልን ዋስትና የለንም። ፍ/ቤቱ ይህን ቢያደርግ በእኛም ሆነ በቤተሰቦቻችን ላይ እንግልት እያደረሰ እንደሚገኝ ከግምት ሊገባ ይገባል»

በሌላ በኩል በዚህ መዝገብ ሥር ተከሳሽ የሆኑት አቶ ሙጂብ አሚኖም ለፍ/ቤቱ አቤቱታቸውን አሰምተዋል። አቶ ሙጂብ አቤቱታ አሰኝ ካሉ በኋላ በስሜት ተውጠው ተከታዩን ንግግር አድርገዋል።

«ይሄን ድራማ በተከታታይ እያየነዋል። እኛ ከዚህ ችሎት ፍትሕ አንጠብቅም። ልክ እንደኛ በተመሳሳይ መልኩ የተከሰሱት «እነ አብቡክር አሕመድ ሆነ እነ ኢልያስ ከድር» ላይ የተሰራውን ድራማ አይተናል። ምስክር ሳይደመጥብን ጥፋተኛ ተብሉ እንዲወሰንብን ነው የምንጠይቀው። ወንድሞቻችን የሆኑት እነ ኢልያስ ከድር ጥፋተኛ ተብለዋል። እኛም ከዚህ የተለየ ውሳኔ አንጠብቅም፡ ‹ከዚህ ፍ/ቤት ፍትሕ አናገኝም! ሊገኝ አላህ› በማለት ለፍ/ቤቱ አቤቱታውን አሰምቷል።

ፍ/ቤቱ፤ አቃቤ ሕግ ቀሪ ምስክሮችን በሚቀጥለው ቀጉ-ቀጠሮ አሟልቶ እንዲያቀርብ አሳስቧል። አቃቤ ሕግ በዘኩሉ ካዘጋጃቸው 24 ምስክሮች መሃል ስድስቱን በችሎት ያቀረበ ሲሆን፣ ስድስቱም የአቃቤ ሕግ ምስክሮች በችሎት እንዲገኙ በተደረገበት ጊዜ ፊታቸውን ወደ ፍ/ቤቱ ሳይሆን ወደ አቃቤ ሕግ ሲያዞሩ ተስተውሏል። አቃቤ ሕግ ቀሪ 18 መከላከያ ምስክሮቹን እንደሚያቀርብ ገልፆ ስለት ያህል ምስክሮቹ ታስረው እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱን ጠይቋል። አቃቤ ሕግ 1ኛ፣ 2ኛ፣ 8ኛ፣ 6ኛ፣ 3ኛ፣ 25ኛ እና 24ኛ ምስክሮቹ በቀጣይ ቀጠሮ ታስረው እንዲቀርቡለት «ትዕዛዝ ይሰጥልኝ» ሲል አመልክቷል።

በችሎቱ የተሰየሙት ዳኛ በቀጣይ ቀጠሮ የችሎቱ ዳኝነት መቅረብ-ድምፅ እንዲያሟላ በተጨማሪነትም የተከሳሾች ቤተሰብ ችሎት እንዲታደሙ ሌላ ሰፊ አዳራሽ እንዲያዘጋጅ ትዕዛዝ ሰጥተዋል። የአቃቤ ሕግ ምስክሮችም በተከታታይ ሁለት ቀናት እንደሚደመጡ የገለጹት ዳኛ ተለዋጭ ቀጠሮ ለጥር 24 እና 25 ቀን 2008 ዓ.ም ሰጥተዋል።

# <<የኦሮሞ ሕዝብ በአንድነትና በቅንጅት መብቱን ለማስከበር በመንቀሳቀሱ እኮራበታለሁ>>

አቶ ጃዋር መሐመድ

**አቶ ጃዋር መሐመድ በአሜሪካን ሀገር የሚገኘው የኦሮሚያ ሚዲያ ኔትወርክ (OMN) የቴሌቭዥን ጣቢያ ሥራ አስፈጻሚ እና የፖለቲካ ተንታኝ የሆኑት አቶ ጃዋር መሐመድ የዚህ ዕትም የ<<አዲስ ገጽ>> እንግዳችን ናቸው። ኢሊያስ ገብሩ በቅርቡ ትልቅ ተቃውሞ አስነስቶ ስለነበረው የአዲስ አበባ ማስተር ፕላን ዕቅድ እና በሌሎች ሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ከአቶ ጃዋር መሐመድ ጋር ያደረገውን አጠር ያለ ቃለ-ምልልስ እንዲህ ቀርቧል።**



**ጠቅለል ባለ መልኩ ከአዲስ አበባ ማስተር ፕላን ጋር በተገናኘ በኦሮሚያ ክልል በበርካታ ቦታዎች ስለተነሳው ህዝባዊ ተቃውሞ፣ የንጹሃን ሞት፣ ድብደባ፣ እንግልት፣ የትምህርት ማቆም ችግር … ምን ተሰማዎት?**

በሁለት ምክንያቶች አዝናለሁ፤ በሌሎች ምክንያቶች ደግሞ እጽናናለሁ። በግፍ ለተገደሉት፤ ለቆሰሉት እና በየቦታው ታስረው ለሚማቅቁት እህቶቼ እና ወንድሞቼ፤ ለወዳጅ ዘመዶቻቸው አዝናለሁ። በዚህ ዘመንም የህዝብን የመብት ጥያቄ በሰላም ከመፍታት ይልቅ መግደልን የሚመርጥ፤ በሂደቱም ወደጠባርነት እየመለሰን ያለ የሹመቶች መንግስት በመኖሩ አዝናለሁ። ከዚያ በተረፈ ግን የኦሮሞ ህዝብ ከዳር እስከ ዳር በአንድነት እና በተቀናጀ መልኩ መብቱን ለማስከበር በመንቀሳቀሱ እኮራበታለሁ። በተጨማሪም ይህንን የመሰለ መጠነ ሰፊ ንቅናቄ ሲያደርግ ከሌላው ህዝብ ጋር የአንድነቷ ግጭት ማስወገዱ እና የሥርዓቱን መሰሪ ስልቶች ማክሸፉ ያኮራኛል።

**የትግሉ ምንጭ ማን እና ምንድን ነው? ከማስተር ፕላኑ ጀርባ ድብቅ አጀንዳ ይኖር ይሆን? ካለስ ምንድን ነው? ለምን? ከማስተር ፕላኑ በስተጀርባ ድብቅ አጀንዳ አለ?**

ሰምን አለ። ይህም አጀንዳ ህወሃት የኦሮሞን ገበሬ አፈናቅሎ መሬቱን ለራሱ ሰዎች ሸንሽኖ በአዲስ አበባ እና ዙሪያዋ የትግራይን ሰዎች የበላይነት መገንባት ነው። ይህ እነሱ ድብቅ የሚመስላቸው ሴራ ለኦሮሞ ህዝብ ግልጽ ስለሆነ ነው በነቂስ ወጥቶ ህይወቱን ገብሮ የተቃወመው።

**ቁጣው በተለያዩ የኦሮሚያ ክልሎች በፍጥነት መዳረሱና የሌሎች ክልል ተወላጆች ማስተር ፕላኑን አለመቃወም የደረሰበትን አውንታ እንዴት ገመገሙት?**

በማስተር ፕላኑ ስም የተከፈተው ሴራ ገበሬውን እንዴት እንጠራራ ሀብቱን ማለትም መሬትን ለማሳጣት ያለመ መሆኑን ሁሉም በደንብ ስለተገነዘበው እና ጥቃቱን በአስቸኳይ ማስቆም ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ ስለሆነ ነው በፍጥነት ተቃውሞው የተቀጣጠለው።

**ከአብዛኛው ህዝብ ፍላጎት ውጪ ህወሃት/ኢህአዴግ ዕቅዱን ወደመተግበር ቢያመራ ምን ሊፈጠር ይችላል? ለተፈጠረው ችግር እውነተኛ መፍትሄውስ ምንድነው ይላሉ?**

የገበሬውን መሬት መዝረፍ ካላቆመ ህወሃት መቀበሪያውን እየቆፈረ ነው። በዚህ ዙር መቃብሩን በደምብ ጠለቅ አድርጎ አውቆታል። በዚሁ ከቀጠለ የሚቀረው መገፍተር ብቻ ነው።

ከማስተርፕላኑ ጉዳይ እንዉጣና፦ በውጭም ሀገር ይሁን በሀገር ውስጥ ባሉ የኢትዮጵያ ልሂቃች መካከል፤ ያለፈ ሁኔታ ይሁን የወደፊት ዕጣ ፈንታ ወይም ሀገሪቷ አሁን ያለችበትን ሁኔታ ምንነት አለመልከቶ፤ ያላግባባቸው ነገር ወይም መሠረታዊ የአቋም ልዩነት አለ? ካለ የዚህ ልዩነት ምንጭ፤ ምክንያትና መፍትሄው ምንድን ነው? ማን ምን ማድረግ /ሊለማድረግ አለበት?

በዚህ ዙሪያ ውይይቶች እና ድርድሮች እየተካሄዱ ነው። ወደ መፍትሄም ያመራሉ የሚል ተስፋ አለ። አሁን ሁሉም ያሉትን አቋሞች፤ የልዩነት እንዲሁም የጋራ አቋሞችን ተረድተዋል።





እናም ዘላቂ መፍትሄ ለማምጣት የሚቻል ይመስለኛል። በሰፊት በሌላ ጊዜ እንወያይበታለን።

**በአሁኑ ወቅት በሀገሪቷ ኢሊቶችና የፖለቲካ ሀይሎች መካከል ስለምን ትብብር ያስፈልጋል?**

ይህ ግዴታ ነው፤ ይቻላልም። ይህ የሚያስፈልገው ሥርዓቱን ለማስወገድ ብቻ አይደለም። አዲስ ለሚመሰረተው ሰላማዊ፤ ዴሞክራሲያዊና የሰከነ ፖለቲካዊ ሥርዓት መሰረቱ የልሂቃን መግባባት እና በህዝብ ተቀባይነት ማግኘት ነው።

**ይህ ልዩነት እያለስ ትብብር መፍጠር ይቻላል/አይቻልም? ለምን? ልዩነት መኖሩ ጤናማ ነው /አይደለም ይላሉ?**

ልዩነት ሁሌም ይኖራል። እነዚያን ልዩነቶች አጥርቶና አውቆ መስማማት በሚቻለው ላይ መስማማት፤ በማይቻለውም ላይ እንዴት መስተናገድ እንዳለበት የጋራ ስልት ማበጀት ይቻላል።

**በታሪክ ንባብ እና አረዳድ ላይ የአቋም ልዩነት መፍጠሩ፣ ዛሬ ባለው የሀገሪቷ የፖለቲካ ሀይሎች ላይ ምን ዓይነት ተጽዕኖ ፈጥሯል? ይህንንስ ዓይነት ተጽዕኖ መፈጠር ነበረበት ይላሉ? የፈጠረው ተጽዕኖ ጤናማ ካልሆነ ምንጭና መፍትሄውስ ምንድን ነው? በዚህ የተጠቀመው ወይም የተጎዳው ማን ነው ይላሉ? ለምን?**

ትላንት ዛሬ እና ነገ ተነጣጥለው የሚገኙ አይደሉም። ዛሬ የትላንት ውጤት ነው፤ ነገ ደግሞ የዛሬው። ይህ ማለት ግን ትላንት የነበረ ችግር ዛሬን ጥፍሮ ማንቆ አለበት ማለት አይደለም። እንዲያውም ዛሬ ትላንት ለነበሩ እና እስካሁን ሊፈቱ ያልቻሉ ችግሮች መፍትሄ ለመፍጠር ሊረዳ ይችላል። ከትላንት ለወረስናቸው ውስብስብ ችግሮች መፍትሄ ለማግኘት መነሻው ትላንትን አለመካድ እንዲሁም ከልክ በላይ አለማጋነን ነው። ነገሮችን ከሁኔታዎች አንፃር ተመልክቶ የጋራ ግንዛቤ መፍጠር ይቻላል።

**ለኦሮሞ ነጻነት፣ እኩልነት፣ ፍትሃዊነትና አንድነት ማለት በሀገርና ህዝብ ደረጃ ምንን ያመለክታል? <<ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እና የሕግ የበላይነት ተፈጠረ>> የሚባለው ምን ሲሆን እና ሳይሆን ሲቀር ነው? እነዚህንስ ማሟላትና መፍጠር የማን ግዴታ ነው? በኢትዮጵያ ባለፉት ጊዜያትና ዛሬ እነዚህን በተመለከተ የነበሩትና መሟላት አለባቸው የሚሏቸው ምንድን ነው/ ናቸው?**

ዜጎች በራሳቸው ቀዬ ላይ ንትሥ እነሱ ብቻ ሲሆኑ፤ የማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎች ህዝብ ከአብራኩ በመረጣቸው ግለሰቦች ሲነደፉና ስራ ላይ ሲውሉ፤ እነዚህን የህዝብ ተወካዮች ደግሞ ነጻ እና አፎካካሪ (competitive) በሆነ የምርጫ ሂደት ሲመረጡ፤ እንዲህ አይነት ፖለቲካዊ ሥርዓት መገንባት የሁላችንም ኃላፊነት ነው።

**አንድ ሰው <<የአንድ ሀገር ዜጋ ነው>> የሚባለው ምን ሲሆን ነው? የኢትዮጵያ ዜጎችስ እነማን ናቸው? በዜጎች መካከል ልዩነት የሚፈጠረው እንዴትና በማን ነው? መፍትሄውስ?**

ዜጋ ማለት፤ በአንድ ሀገር ውስጥ መብት እና ግዴታ ያለው ያን ግዴታ ደግሞ እሱም በአግባቡ የሚወጣ፤ መንግስትም (state) መብቱን የሚያከብርለት ጥቅሙን የሚያሟላለት ማለት ነው። መንግስት መብቱን የማያከብርለት እና ጥቅሙን የሚነፍለት ግን ተገዢ (subject) ነው። በአንድ ሀገር ውስጥ ሁለቱም አብረው ሊታዩ ይችላሉ። በኮሎኒያሊዝም ዘመን ሰፋሪ አውሮፓዊያን ዜጋ ነበሩ፤ ሀገሬው (native) ደግሞ ተገዢ ነበር። አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ ትግሬዎች (ሁሉንም አይደለም) ዜጋ፤ ሌላው ተገዢ (subject) ናቸው ብንል የተሳሳትን አይመስለኝም።

ዜጎች በራሳቸው ቀዬ ላይ ንትሥ እነሱ ብቻ ሲሆኑ፤ የማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎች ህዝብ ከአብራኩ በመረጣቸው ግለሰቦች ሲነደፉና ስራ ላይ ሲውሉ፤ እነዚህን የህዝብ ተወካዮች ደግሞ ነጻ እና አፎካካሪ (competitive) በሆነ የምርጫ ሂደት ሲመረጡ፤ እንዲህ አይነት ፖለቲካዊ ሥርዓት መገንባት የሁላችንም ኃላፊነት ነው።

**አስከዛሬ በዚህች ሀገር የደረሰ ጥፋትና በሆነት ካሉ አርሰዎ ተጠያቂ የሚያደርጉት ማንን ነው? ለምን? ይህስ በማንና በምን ይካካሳል ይላሉ?**

ተጠያቂው ሀገር የማስተዳደር ኃላፊነትን በጉድም ይሁን በውድ የተረከበ ግለሰብ ቡድን ነው። ያንን የማስተዳደር ኃላፊነት ለግል ወይም ለቡድናዊ ፍላጎት ሲል መድሎአዊ ሥርዓት የገነቡት ናቸው ጥፋተኞች። መፍትሄው እነሱን በማስወገድ፤ እነሱ የፈጠሩት ያጋደለ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ክሥተት በማስተካከል ነው የሚፈታው።

**የዚህች ሀገር አንድ ብሄር ለምሳሌ፣ አማራ ወይም ኦሮሞ ዕጣ ፈንታ ከሌሎች የኢትዮጵያ ብሔሮች ዕታ ፈንታ በተለየ ሊወሰን ይችላልን? እንዴትና ለምን?**

ሁለት ሂደቶች አብረው መሄድ አለባቸው፤ ይችላሉም። ይህ ማለት አንድ ህዝብ የራሱም እድል በራሱ የመወሰን መብት ሊጎናጸፍ ይገባል። እንዲሁም ደግሞ ከሌሎች ጋር በሚያቀራርበው የጋራ ጉዳዮች ላይ አብሮ በጋራ መወሰን፤ መሸትና መቻል አለበት። እነዚህ ተጻራሪ ጉዳዮች ይምሰሉ እንጂ አይደሉም። በዓለም ላይ ያሉ ሀገሮች ሁሉ ህብረ-ብሄራዊ ናቸው። ድርብርብ ማንነቶች፤ ተፎካካሪና ተመጋጋቢ ፍላጎቶች በአንድ ላይ አቅፈው ነው የተፈጠሩት። መፍትሔን በጥምና የቀየሱ በሰላም እና ዴሞክራሲ ይኖራሉ። ሌላውን መንገድ የተከተሉ ሰጭቆና፤ ብጥንት እና መፈራረስ ይጋለጣሉ።

**እስከዛሬ በሀገሪቷ ውስጥ ጭቆና እንዲቀጥል እኩልነት፣ ነጻነትና የመብት መከበር እንዳይፈጠር ያደረገው አመለካከት አለ? የቱ ነው? ይህንንስ ለመለወጥ ማን ምን ማድረግ ይጠበቅበታል?**

ቀበሌ ባለ መልኩ ሲቀመጥ መልኩ ‹‹እኔ ስለሳ አንተ ቀላውጥ፤ እኔ ጌታ አንተ ሎሌ ሁን የሚል›› አባዜ ነው። ከዚህ በፊት የነበሩትንና የአሁኖቹም ገዢዎች በዚህ አመለካከት ነው የሚመሩት። ይህን ችግር ለመፍታት ለዚህ አይነት ግብዝነት የማያመች አመለካከት እና ፖለቲካዊ እውነታ መፍጠር ያስፈልጋል። የሲቪል ማኅበራት መጠናከር፤ የአንድ ህዝቦችን አቅም ማጠንከር፤ የሚዲያው ማደግ ወሳኝ ሚና አላቸው።

**ኢትዮጵያ የዛሬ 5፣ 10ና 20 ዓመት ምን ትመስለለች ይላሉ?**

ይህንን በርግጠኝነት ለመተንበይ እኔ ጠንቋይ አይደለሁም፤ የፖሊቲካ ተንታኝ እንጂ። ከትንታኔ አኳያ ካየነው፤ ህወሃት በሥልጣን ላይ ከቆየ ይህቺ አሁን ገደል አፋፍ ላይ ያደረሷትን ሀገር ወደገደል መክተታቸው አይቀሬ ነው። (ታላቅ ወንድሜ ዶ/ር መረራ ጉዲና አሁንም መስቀለኛ ላይ ነው ብለው ተስፋ ያደርጋሉ፤ ግን እኔ ገደል አፋፍ ላይ ተንጠልጥላ ነው የማያት)። ነገር ግን ህዝቡ አሁን በጀመረው መንገድ ህወሃቶችን ከመኪናው (ሀገር) ነጥሎ ገደል ከከተተ ሀገርን እና እራሱን ማዳን ይችላል።

**ከሰላት ዓመት በፊት ዕንቁ መጽሔት ላይ ከእርስዎ ጋር ባደረግነው ሰፊ ቃለ ምልልስ <<ኢትዮጵያን እንደኮንዶሚኒየም ቤት ነው የምመለከታት (በጋራ የሚኖርባት)>> ብለውን ነበር። ዛሬስ?**

ህወሃት ያንን ኮንዶሚኒየም ንዶት ወደ ትልቅ እስርቤት ቀይሮታል። ጣሪያው ላይ እንአባይ ጸሃዬ እና ቡድናቸው ተኮፍሰው በሩን ደግሞ አህዴድ እና ብአዴን በዘብኝነት ተቀጥረው እየተናቁ እና እየተገላመጡ ቆሺታቸው እያረረ ጊዜ እየጠበቁ ያሉበት ሁኔታ ይታየኛል።

**እናመሰግናለን።**

እኔም አመሰግናለሁ።

# የፖለቲካ ለውጥ ዘይቤና የፖለቲከኞነት ዕሳቤ



ሰሎሞን ተሰማ ጂ.
(solomontessemag@gmail.com/
semnaworeq.blogspot.com)

### መግቢያ ፩

በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመን ነው፤ አንድ ጎደኛ ሰውዬ ልቀ ለመግባት ፈለገና አንድ መቶ ያህል የአንድ ሳንቲሞች (ሰልዲዎች) ሰብስቦ ወደ ሱቅ ሄደ። ባለሱቁ ደግሞ ያልተለመደ ዓይነት የግብይት ጥያቄ ሆነበትና ሰልዲዎቹን አልቀበልም አለ። ነገሩ ወዲያውኑ ከቢሉ የአንድ ብር ኖት አጠማዱ ላዩ ላይ ‹‹ሳምልጠው እንዲከፈል ሕግ ያስገድዳል!›› የሚለውን ጽሑፍ ለባለሱቁ እያሳየው ተከራከረ። ባለሱቁም መልስ አደርጎ፤ ‹‹ሕሱኽ ታዲያ ለወረቀቱ ብር እንጂ ለአንድ ሳንቲሙ የሚሠራ አልመሰለኝም!?›› ሲል ተከራከረ። ነገሩ በዚሁ፤ ‹‹ቆይ! አሁን አንተ ይኼ ሳንቲም የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት መንግሥት መገበያያ ገንዘብ ነው ብለህ ታምናለህ አታምንም?›› ሲል ሽንጡን መገዝዞ አጠትቶ ትንቦ ተከራከረው። የዚህን ጊዜ ባለሱቁ ተገልብጦ፤ ነገር ሆኖ የመጣበት ሰው ኑሮ ለባሽ (ጆሮ ጠቢ) ወይም በዘመኑ አባባል ‹‹ተናግሮ-አናጋሪ›› ይሆን እንዴ ብሎ ሰጋ(ል)። መጨረሻ ላይ፤ ‹‹ወዳጄ! እኔ ፖለቲካ አላውቅም፤ ፖለቲካም አታናግረኝ። መግባት የፈለግኸውን ነገር ገዝተህ ጥርግ በልልኝ›› አለው። (‹‹መሳንት›› መጽሔት።)

### መግቢያ ፪

የፖለቲካንና የታሪክን ዘይቤ ለመሸፈን የሚያግዝ ባለሙያ ሁሉ ችላ የማይለው አንድ ወሳኝ ቃል ‹‹ለውጥ›› የሚለው ነው። ታሪክ፣ በማኅበራዊ ኑሮ እና በልዩ ልዩ ተሰጥኦዎች፣ በዘመናት መካከል የሰው ዘር በዓለም ላይ የሚያደርጋቸውን እንቅስቃሴዎች እና የፈጸማቸውን ለውጦች ያለ ወሳኔ የሚያውሳት ዓይነተኛ ዓላማው ነው። ለውጡን ደግሞ ከሥር-ከሥሩ እየተከታተለ የሚያተጋው ነገሩ ‹‹ፖለቲካ›› ይባላል። የሰው ሕይወት ሁሉ ጊዜ የሚንቀሳቀስና የሚያድረግ የ‹‹ለውጥ›› ጅረት ነው። ስለዚህ፣ አንድ የታሪክ ጸሐፊ የአንድን ሕዝብ ታሪክ እና ፖለቲካ ለመጻፍ ሲነሣ፣ በእርግጠው ዘይቤ (በታሪክ) ፈንታ የተተነነውን አዲሱን ዘይቤ (ፖለቲካውን) ማወቅ ይገባዋል። በእዲሱ ዘይቤ ምክንያት፣ ሰው የወሰጠውንና የውጭውን ሁኔታዎች ለውጦ ፊቱን የሚያደበበት ኃይል መኖሩም ፈጽሞ ችል ሊባል አይገባውም። የ‹‹ፖለቲካ ለውጥ›› የምንለው እጋዘ፤ ከሥር መሠረቱ የሚናደ አለመሆኑንና የማይለወጥም አንድ ሰው ‹‹ነገር›› እንዳለ ማወቅም የተገባ ነው።

### ሐተታ ፖለቲካ -ውለውጥ!

ብዙ ኢትዮጵያውያን ፖለቲከኛ መሆን አይደለም፤ ፖለቲካ ለመናገርም ይፈሩ ነበር። አሁንም ብዙዎች ይፈራሉ። ይህንንም የሚያረጋግጡ በርካታ አባባሎች አሏቸው። ለአብነትም፤ ‹‹ፖለቲካንና ኤሌትሪክን በሩቁ ነው!..፤ ‹‹ፖለቲካ ማለት ሸርሙጣ ነው!›› ይላሉ። አልፎ አልፎም፤ ‹‹አጅሬ!? ጎደኛ ፖለቲከኛ አይደል እንዴ!?›› ሲሉ ይደመጣሉ። እነዚህ ዐረፍተ ነገሮችና አባባሎች ትክክለኛውን የፖለቲካ ትርጉም የሚያሳጡን ናቸው፤ ፖለቲካን ከአጭበርባሪነት፣ ከአምታችነት፣ ከአፈ-ጮሌነት (ከምላሰኝነት)፣ ከጭካኔነት፣ ከነገር ፍንፍንነት (intrigue)፣ ከምሾነትና ከጠብ-መንገር ሆኜነት (ከባለብረትነት) ጋርም ማቆራኘት የሚዘወተር ጉዳይ ሆኗል።

‹‹ፖለቲከኛ››ነት መንግሥትን ከመስደብ፣ ባለሥልጣናትን ከመተቸት እና ከመንቀፍ፤ የመንግሥት ድርጅቶችን ከማንቋሸሽ እና ከማብጠልጠል የበለጠ ትርጉም ያለው የማይመስላቸው ብዙ ‹‹ፖለቲከኛ ነን›› ባዮች አሉ። በቅርቡ አንድ ወዳጄ ያሉኝ ነገር ከዚህ ሐሳብ ጋር ይቀየማል፤ ባለፈው ፓርላማ (ማለትም ከ1998-2002 ዓ.ም ድረስ) ለአምስት ዓመታት ያህል የፓርላማ አባል የነበረን አንድ ምሁር ጠቅሰው፤ ‹‹አሁን እሱ ፖለቲከኛ ነኝ ይላል እንዴ!?›› አሉኝ። ‹‹እና ምንድነው ብለው ያስባሉ?›› አልኳቸው። ጥያቄዬን ቀበል አድርገው፤ ‹‹እኔማ ምን አውቃለሁ፤ ተሳዳቢ ነው'ንጂ! የሰየሱት ተሳዳቢው! ለነሱ ይህንንም የሚሉት ራሳቸው - የተከበሩት ፖለቲከኛና የፓርላማ አባላቶቹ ናቸው!›› ሲሉ አጣረሩ።

ይህ ከሆነ ዘንዳ፤ ‹‹ፖለቲካ ማለት ምንድነው?›› ‹‹ፖለቲከኛነትስ›› ምን መሆን አለበት? ‹‹ፖለቲካስ ዘይቤ አለውን?›› ወይስ እንዲያው እንደአጀሬ ነገር-ተንኳኙ እና እነ እያ ሚራ-ፈጥርቁ ሁሉ ‹‹ፖለቲከኞች ናቸው›› ሊባል ነው? በዚህ ጽሑፍ ሥር እነዚህን እና ተያያዥ ጥያቄዎችን ለመመለስ ጥረት እናደርጋለን። በቅድሚያ ግን የፖለቲካን ዘይቤ (ፖለቲካንና የፖለቲካን ጥበብ) ለመበየን ጥረት እናድርግ። ‹‹ፖለቲካ ወይም የፖለቲካ ጥበብ›› ማለት ስለመንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር የሚጨነቅና የሚጠበብ መስክ ነው። የፖለቲካ ሳይንስ በበኩሉ፣ ስለመንግሥትና ስለሕዝብ የሁለትዮሽ ግንኙነት የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ ነው። ሁለቱ ጎራዎች እንደያም ሆነው በተቀናጀና በተጣመረ መልኩ ወደ ፊት መራመድ እንደሚችሉ የሚታተትበትም ዘዴ ነው። የፖለቲካ ጥበብ ሦስት ተዛማጅ ጉዳዮችን ያካትላል። እነርሱም፡- 1ኛ) የሰውን ልጅ ፍጥረተ-ባሕርይ እና ተግባሮቹን፤ 2ኛ) የሰውን ልጅና የሌሎችን ፍጥረታት ግንኙነት በተመለከተ፤ እና 3ኛ) የሰውን ልጆች የርስበርስ ግንኙነት በተመለከተ ያሉትን ችግሮችና መፍትሔዎች በማጥናት፣ በመመርመርና እንደ አስፈላጊነቱም ለማረም በመጀልና በማስቻል ክህሎት ላይ የሚያጠነጥን የጥበብና የሳይንስ ዘርፍ ነው።

ከላይ ያነሳናቸውን ሦስት ጉዳዮች ከመተንተናችን በፊት፣ የፖለቲካን ጥበብ በቅጡ ለመረዳት በሁለት ክፍሉ ማየት ያስፈልጋል። በቀድሞው የተጓዳኝ የዩኒቨርሲቲ ውስጥ የፖለቲካ ሳይንስ መማሪያ የነበሩት፣ ዶክተር አማረ ተክሌ፣ በ1960 ዓ.ም እንዳስረዱት፣ የፖለቲካ ጥበብ የመጀመሪያው ክፍል አጠቃላይ የፖለቲካን ፍልስፍና፣ አሳቦችንና ሕጎችን (Basic Philosophical Assumptions and General Laws) የሚይዝ ነው። ሁለተኛው ክፍል ደግሞ፣ ስለመንግሥት አቋም፣ ስለሕዝብ አስተዳደር ሥርዓትና ሕግጋቱም አጠቃለሉ የሚይዝ ክፍል ነው። ጥሩ ፖለቲከኛ የሆነ ሰው (የሚሆን ሰው) እነዚህን ሁለቱን መረዳትና ጠንቅቆ ማወቅ አለበት። አንዱን ክፍል ከሁለተኛው ነጥሎ መመሥረት አይገባ ይመዘባል። ሁለቱም ክፍሎች የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው። ወይም የአንድ በር መዝጊያ የፊትና የኋላ መልኮች ማለት ናቸው።

የመጀመሪያውን ክፍል በምሳሌ ማስተንተን ያስፈልጋል። እንዳንድ ፈላስፎች የሰውን ልጅ እኩይ፣ አረመኔ፣ ጉደኛ እና በጣሙ-ሰብዕ አድርገው ያቀርቡታል። ሚሂዎቹ ደግሞ የሰውን ልጅ ግብረ-ገብነት ያለው፣ በሕግና በጎሊና የሚገዛ፣ ፈሪኃ-እግዚአብሔር ያለው ‹‹ፍጡር›› እንደ ሆነ አድርገው ያቀርቡታል። የግል ራሱን አምሳያ (self-image) ወይም የግል ብቤውን (ወንድመንና እህቱን) በሞሳል የሚገድል ‹‹ፍጡር›› ነሐም ሰው ብቻ መሆኑን ያረጋግጣሉ። ግፈኛውን ፍጡር እና ክእንስሳትም ሁሉ የባሰውን እንስሳ ‹‹ሰው››ን ለመግዛት ‹‹ስለፈለገም፣ የኃይል አገዛዝ (Government By Physical Force) መመሥረት እንዳለበት ያስተምራሉ። በአንጻሩም፣ ለሕግና ለጎሊና ለሚገዛው (ወይም ፈሪኃ-እግዚአብሔር) ላለው ሕዝብ ደግሞ ተስማሚው የማስተዳደሪያ ፖለቲካዊ ጥበብ፣ ሕዝቡን በማግባባትና ሐሳቡን በማስለወጥ ዘዴ (Government by Persuasion) መሆን እንዳለበት ያስረዳሉ።

እዚህ ላይ፣ ‹‹ኢትዮጵያውያን በየትኛው የመንግሥታዊ ሥርዓት ሥር (በኃይል አገዛዝ ሥር ወይስ በማግባባትና ሐሳቡን በማስለወጥ ዘዴ ነው) እየተዳደሩ ያሉት?›› ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው። ጥያቄውን ለመመለስ ከመሞከራችን በፊት፣ ሌላ ሊጠየቅ የሚገባ ተዛማጅ ጥያቄ አለ። ይህም፣ ‹‹የኢትዮጵያውያን የሕይወት ፍልስፍናና የዓላማቸው ኑሮ ዓላማቸው (Ethiopians' Purpose in Life) ምን ይመስላል?›› የሚለው ነው። መጠየቁ ግዴታም ነው። የኢትዮጵያውያን የሕይወት ዓላማቸውና ግባቸው ምን ነበር? የመንግሥታቶቻቸውና የማኅበራዊ ኑሯቸው ግብስ ምን ይመስል ነበር? የሚሉትን ጥያቄዎች እናንሣ። መልሱም ቀላል አይደለም። መሠረታዊ የኢትዮጵያ ታሪክ ንባብ ያለው ሰው ግን አይስተውም።

ኢትዮጵያውያን ለብዙ መቶ ዓመታት የኖሩት በኃይማኖተኛነት ነው። የይሁዲነትም ሆነ የክርስትናን ኃይማኖቶች ሲቀበሉ ፈጥነዋል። ቤተ-ምኩራቦችንና አብያተ-ክርስቲያናትንም ለመሥራት ከመጀመሪያዎቹ የነበሩትን ሕዝቦች ውስጥ ይጠቀሳሉ። ኢትዮጵያ፣ እስልምናንም ለመቀበልና መስጊዶችንም ለመሥራት ቀዳሚዋ ናት። የቤተ-ክርስቲያን ሊቃውንትም፣ ‹‹የሰው ልጅ የሕይወት ተልዕኮውና ግቡ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጸጋ ለመውረስ እንጂ፣ ዓለማዊ ኑሮን ተንፈላሰና ተደላድሎ ለመኖር ብሎ አይደለም!›› እያሉ ሰብከውላታል። መንግሥታቱም (አገዛዞቻቸውም)፣ ርዕሰ-ብሔሮቻቸውንና የፖለቲካ ስብከቶቻቸውን ከቤተክርስቲያን አስተምህሮቶች ጋር በማስማማት እና በማቀናጀት ለበርካታ ምዕት ዓመታት ኖረዋል። ለዚህም አገልግሎታቸው፣ የ‹‹ሊያ መንግሥትን›› ደርሻ ተጋርተው ነበር። ኤድዋርድ ጊበን (Edward Gibbon) እንዳለው፣ ‹‹ኢትዮጵያውያን በራቸውን ጠርቅመው ወደ ፈጣሪያቸው ሲማጠኑ፣ ዓለምን ረስተው፣ ዓለምም መልሶ ረሳቸው።›› ይህ ትናንትና ነው። ቢያንስ-ቢያንስ ከዐፄ ቴዎድሮስ ዘመነ-መንግሥት በፊት ነው።

ከዚያ በኋላ ግን ነገሮች ተቀይረዋል። ኢትዮጵያውያን ድንበሮቻቸውንና በራቸውን ብቻ ሳይሆን፣ ልባቸውን ከፍተው የውጭውን ዓለም ማየት ጀምረዋል። ከዐፄ ቴዎድሮስ ዘመን ጀምሮም የሕዝቦችን ባሕርያዊ-ፍጥረት እየተቀየረ ሄዷል። ፈሪኃ-እግዚአብሔር ቀስ በቀስ ተናውሟል። ለኢትዮጵያውያን በዚህ ዓለም አሸሉ ድረስ፣ ጥናው ቀም-ነገር ‹‹ቁሳዊ ሀብት›› ነው የሚል አስተሳሰብ መስፈን ጀምሯል። ኢትዮጵያውያን፣ ሀብትን ለማከማቸት እና ኑሯቸውን ለማደላደል የሚያስችላቸው መንግሥት መምረጥ እየፈለጉ ሄደዋል። ጥረው ግረው ያፈሩትን ሀብትና ንብረት ዋስና ጠበቃ ሆኖ የሚያስጠብቅላቸው ሀገረ-መንግሥት (State) እንዲኖራቸው ሽተዋል። ለዚህም በአፅፈታው፣ የገዢዎቹ የአገዛዝ ሥልት እየተጣበ መሄዱም ይታያል። የሕዝቡ መብቱን በሰላት እና በምህዳ ያለመጠየቅ አቅም ላይ የውጭው ዓለም የሥልጣኔ ጉጉት ታክሎበት፣ ሕዝባዊ አመጾች በየሰፈሩው ተከስተዋል። የገዢዎቹ አመጽ በቢሌ፣ በጎጃም እና በትግራይ ተከታታዮች ናቸው። የአገዛዙም ምላሽ ተመጣጣኝ ሳይሆን ቀርቷል። በዚያም ላይ፣ የባንዳዎቹ እና የከተማሊዎቹ፣ የመሳፍንቶቹና የመኳንንቱም ቀጥር እንደ አሸን በመፍላት ደረጃ ላይ መሆኑም ተስተውሏል። ይህ ሁሉ የሆነው በ20ኛውና 21ኛው መንክዘመና ኢትዮጵያ ነው። የገዢዎቹም ተመጣጣኝ ያልሆነ ቅጣትና የአልሁ ርምጃ ሕዝቡ፣ ‹‹ፖለቲካንና ኤሌትሪክን በሩቁ››፤ ‹‹ፖለቲካ ማለት ሸርሙጣ ነው!›› እንዲል አስገድዶታል።

እስቲ የሰውን ልጅ ፍጥረተ-ባሕርይና ተግባሮቹን እንዳንሳ። ከዚያም ባሻገር የኢትዮጵያውያንን ታሪካዊ ባሕርይ እና ዝንባሌ ምን እንደሚመስል እናያለን። አሁን ወደ ሁለተኛው ተግባራችን እናልፋለን።

ፖለቲካ ሰለው የሚያተኩርበት ነጥብ፣ የሰው ልጅና ሌሎች ፍጥረታት ያላቸውን ግንኙነት መሠረት አድርጎ ነው። ፖለቲካ ከአፈር፣ ውኃ፣ እፅር እና እሳትን፣ እንዲሁም በዙሪያችን ከሰፈሩን ሕዋዊ አካላት ጋር ስላለን ግንኙነት የመረዳት ዘዴ ነው። ከዚኢ እና ከመን ጋር ይሰየውማል። ባለብት ዘላለም አይኖሩም። ይባስ ብሎ፣ የእግዚአብሔርም ኅልውናት ሳይቀር በፖለቲካ ውስጥ ይዋንታል። ‹‹እግዚአብሔር የለም!›› የሚሉም ማርክሲስቶች እስከ መነሣት ደርሰው ነበር። ‹‹ያለው፣ ቁስ አካላዊነት ነው!›› ያሉት ፖለቲከኞቹ ናቸው። ለእነዚህ ኅዝቦች፣ የአየር መዛባትና ድርቅ፣ የርዕደ-መሬት እና ፀናሚ መንሽ ‹‹የተፈጥሮ መዛባት እንጂ›› ሌላ አይደለም። የጠፈር ላይ እሽቅድምድሙና የአህጉር አቋራጭ መሣሪያዎች ፋብሪካ እና ቀጥጥር፣ የሰው

ወደ ገጽ 24 ዞሯል





# ሕገ-መንግሥቱ፤ ለኅብረ-ብሔራዊነትም ቦታ ይስጥ!



ግርማ ካሳ
(muziky68@yahoo.com)

የኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት ተግባራዊ መሆን ከጀመረ 24 ዓመታት አልፈውታል። እስከ አሁን ድረስ በሒደት የተሻሻለ/ የተለወጠ ነገር አላየንም። የብዙ አገራት ሕገ-መንግሥቶች በየጊዜው ይሻሻላሉ። ሕገ-መንግሥቶች የእግዚአብሔር ቃል አይደሉም ፤ የሚሻሻሉ ሠነዶች ናቸው ((ፈረንጆቹ ‹‹live documents›› ይሏቿል)።

ሕገ-መንግሥቱ በውስጡ ጥሩም የሆኑ አንቀጾች ያሉት እንደ መሆኑ በአብዛኛው የሚደገፍ ሕገ-መንግሥት ነው። ነገር ግን ሕገ-መንግሥቱ በተለይም «ብሔር ብሔረሰብ እና ሕዝቦች» በሚለው ዙሪያ፣ በፌደራል አወቃቀር ዙሪያ፣ እስከ መገንጠል የራስን ዕድል በራስ በመወሰን ዙሪያ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ፣ እንዳንዶቹም ተግባራዊ ሊሆኑ የማይችሉ ነገሮችን ያቀተተ፣ ችግሮች ያሉበት ሕገ-መንግሥት ነው።

በሕገ-መንግሥቱ የሰፈሩ አንቀጾችን ካለመረዳት የተነሣ፣ በሕገ-መንግሥቱ ላይ ያሉትን ችግሮች መጠቆም፣ ሕገ-መንግሥቱን እንደ መጣስ አድርገው የሚመለከቱ አንዳንድ ወገኖች ይኖራሉ። የሕገ-መንግሥቱ የመጨረሻ አንቀጽ፣ አንቀጽ 105፣ ሕገ መንግሥቱ ሊሻሻል እንደሚችል በግልጽ ያስቀምጣል። አሁን ያለውን ሕገ መንግሥት አክብሮ፣ ሕገ መንግሥት ካሉት መሠረታዊ ችግሮች እንዲጠራ፣ ማሻሻያ እንዲደረግበት መሞከር ሕገ-መንግሥታዊ ነው።

በሕገ-መንግሥቱ አንድ መቶ አምስት አንቀጾች ሲኖሩ፣ «ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች» የሚሉት ቃላት በብዛት ሲጠቀሱ እናያለን። ሕገ-መንግሥቱ በመግቢያው ላይ «እኛ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች» ብሎ ነው የሚጀምረው።

እነዚህ በተደጋጋሚ የሚጠቀሱ ቃላት በብዛት የመጠቀሳቸውን ያህል፣ ምን ማለት እንደ ሆኑ ብዙዎቻችን ግልጽ መረዳት ያለን አይመስለኝም። ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ሲባል ምን ማለት ነው? የፌደራል ክልል ማለት ነው? ብሔር ከብሔረሰብ፣ ብሔረሰብ ከሕዝብ፣ ሕዝብ ከብሔር በምን ይለያያሉ? ሁሉም አንድ ዓይነት ትርጉም ካላቸው፣ አንዱን ቃል ብቻ ለምን መጠቀም አላስፈለገም?

ሕገ-መንግሥቱ የአገሪቱ የበላይ የሕግ ሠነድ እንደ መሆኑ፣ የእነዚህን ቃላት ትርጉም ከዚሁ ከሕገ-መንግሥቱ ላይ መፈለጉ ተገቢነት የሚሰጠው ነው። «ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች» ሲል ሕገ-መንግስቱ ማንን ማመላከቱ እንደ ሆነ ሰላሳ ስምንት አንቀጾችን ከወረድን በኋላ ነው በአንቀጽ 39፣ ንኡስ-አንቀጽ 6 ላይ አጠር ያለ ትርጉም ሲሰጥ የምናገኘው። «በዚህ ሕገ-መንግሥት ውስጥ "ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ህዝብ" ማለት ከዚህ ቀጥሎ የተገለጸውን ባህርይ የሚያሳይ ማኅበረሰብ ነው። ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንጸባርቅ ባህል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸው፣ ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸው፣ የጋራ ወይም የተዛመደ ህልውና አለን ብለው የሚያምኑ፣ የሥነ-ልቦና አንድነት ያላቸውና በአብዛኛው በተያያዘ መልክዓ ምድር የሚኖሩ ናቸው» ይላል ንኡስ አንቀጹ።

አንዳንዶች በብሄርና በብሄረሰብ መካከል ያለውን ልዩነት በሕዝብ ብዛት አንጻር የሚያዩ አሉ። ለምሳሌ አማራን፣ ትግሬን፣ ሶማሌን፣ ኦሮሞን እንደ ብሄሮች በማየት አገው፣ ኩናማ፣ ማጂን እንደ ብሄረሰብ ያዩዋቸዋል። በሕገ መንግስቱ በተሰጠው ትርጓሜ ግን ብሄር ከብሄረሰብ፣ ብሄር ከሕዝብ፣ ብሄረሰብ ከሕዝብ፣ ያላቸውን ልዩነቶች አናይም። ለሁሉም ተመሳሳይ ትርጓሜ ነው ሕገ መንግስቱ የሰጠው።

ታዲያ እነዚህ ቃላት በሕገ-መንግሥቱ አንድ ዓይነት ትርጉም ካላቸው፣ ለምን ብሔር ወይም ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ የሚለውን ቃል መጠቀም አልተፈለገም? ሦስቱንም አባባሎች የተለያዩ ሐሳቦችን የሚያመላክቱ ከሆነ ደግሞ ሕገ-መንግሥቱ ለምን በአንድ ዓይነት መንገድ ተረጎማቸው? ይህ እንግዲህ በሕገ-መንግሥቱ የሚታይ አንድ ትልቅ ችግር ነው።

አንቀጽ ስምንት የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ባለቤት የሆኑት ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እንደሆኑ ይደነግጋል። በሌላ አባባል ሕገ-መንግሥቱ ከብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ውጭ ሊኖር የሚችል ኢትዮጵያዊ እንደ ሌለ አድርጎ ነው የሚቀጥረው። በዚህ ዙሪያ ያሉትን መሠረታዊ ችግሮች ለማሳየት እንሞክር።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሺኅዎች ዓመታት አብሮ የኖረ እንደ መሆኑ ተዛምዷል፣ ተዋልዷል። በስሜን ጎንደር፣ በምዕራብና በደቡብ ትግራይ፣ በስሜን ወሎ አማራና ትግሬ ተደባልቋል። በጎጃም፣ በወሎ፣ በሸዋ፣ ኦሮሞውና አማራው ተደባልቋል። በሐረርጌ ሶማሌው ከኦሮሞ ተዋልዷል። በሀሥር ሚሊዮን የሚቆጠሩ በተለይም በተለያዩ ትላልቅ ከተሞች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ከብዙ ብሔር፣ ብሔረሰቦች የመጡ ኅብረ- ብሔራዊ ናቸው። አሁን ባለው የብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝብ አተረጓጎም ከአንድ ያለፈ ብሔር ብሔረሰብ ውጭ የሚመደቡበት ሁኔታ የለም። እንዱን ጥለው ሌላውን መምረጥ ይኖርባቸዋል። በሌላ አባባል ሕገ-መንግሥቱ ለብዙ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች አባልነት እውቅና አይሰጥም። ይህ ሕገ-መንግሥቱ ያለበት ሌላው ትልቁ ችግር ነው።

በኢትዮጵያ የሚሰጡ መታወቂያዎች ላይ ብሔር የሚጠቀስበት ቦታ አለ። ያ ቦታ ካልተሞላ መታወቂያ ሊሰጥ አይችልም። አንድ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ወረቀት እንዲሰጠው ከተፈለገ የአንድ ብሔር አባል መሆን አለበት። አማራ ወይም ኦሮሞ ወይም ትግሬ ወይም አንዱን ብሔር መምረጥ የግድ ይላል። ይህ ትልቅ ስሕተት ነው። መታወቂያ ላይ ስም፣ የትውልድ ቦታ፣ ዕድሜ፣ አድራሻ እስከ ተጠቀሰ ድረስ ብሔር የመጠቀሱ አስፈላጊነት አይታየኝም።

ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ፣ እሷ ሚኒስትሮቻቸውን ሲያርላማው ሲያስተዋውቁ አማራ፣ ኦሮሞ ትግሬ ማለት ስላሳባቸው፣ ኅብረ-ብሔርነቱን የሚፈልግ ኢትዮጵያዊ ከወዲሁ ይገለላል። ስለዚህም ሕገ-መንግሥት የብሔር ብሔረሰብ መብቶችን አስጠብቆለሁ ብሎ፣ የኅብረ-ብሔሮችን መብቶች ረግጧል።

እንደኔ እንደኔ፣ ሕገ-መንግሥቱ የብሔር ብሔረሰቦችን መብቶች በጠበቀ መልኩ የዜጎችን ኅብረ-ብሔራዊ ባሕርዩንም እንዲያንጸባርቅ መደረግ አለበት። ኦሮሞነት፣ ትግሬነት፣ ጉራጌነት፣ አማራነት ወዘተ. ሊከበርና እውቅና ሊሰጠው እንደሚገባው ሁሉ፣ ኅብረ-ብሔራዊነትም ሊከበር ይገባል። ዜጎች ከብዙ ብሔር ብሔረሰብ የተውጣጡ በመሆናቸው፣ ብኢትዮጵያዊነታችን ነው መታወቅ የምንፈልገው። ኢትዮጵያዊነት ዘራችን ነው፣ ካሉ፣ መብታቸው መከበር አለበት። በዚህ ዙሪያ ሕገ-መንግሥቱ ትልቅ ማሻሻያ ሊደረግበት ይገባል ባይ ነኝ።

ሕገ-መንግሥቱ ብሔር ብሔረሰብን የሁሉ ነገር መሰኪያ ማድረጉ ስሕተት ነው። ሁሉም ነገር በብሔር ብሔረሰብ ሒሳብ ማስላቱ መቆም ያለበት ይመስለኛል።

ሕገ-መንግሥቱ የአገሪቱ የበላይ

## ዜና

*በአዲስ ገጽ*

### የተቃዋሚ ፓርቲ አመራር አባላትን ጨምሮ አንድ ጋዜጠኛ ለእስር ተዳረጉ

የተቃዋሚ ፓርቲ ከሆኑት መሃል የሰማያዊ ፓርቲ አምስት አባላቱ ባለፍነው ሳምንት የታሰሩ ሲሆን፣ የፓርቲው ልሳን የሆነችው የ‹‹ነገረ ኢትዮጵያ›› ዋና አዘጋጅ ጋዜጠኛ ጌታቸው ሽፈራው ለእስር ተዳርጓል። የኦሮሞ ፌደራላዊ ኮንግረስ በዙሉ ደግሞ ሁለት አመራር አባላቱ ታስረዋል።

የሰማያዊ ፓርቲ የቀድሞ ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ዮናታን ረጋሳ እንዲሁም የፓርቲው አባላት የሆኑት አቶ ዳንኤል ተስፋዬ፣ አቶ ኤርሚያስ ፀጋዬ፣ አቶ ፍሬው ተክሉ፣ አቶ ቴዎድሮስ አስፋው መታሰራቸውን ለማወቅ ተችሏል። የፓርቲው ድርጅት ጉዳይ ኃላፊ የሆኑት አቶ ጋሻው መርሻ የታሰሩት የፓርቲው አባላት በፓርቲው ውስጥም ሆነ በማህበራዊ ድረ-ገፅ ላይ ንቁ ተሳትፎ የነበራቸው መሆናቸውን ለ‹‹አዲስ ገጽ›› ገልፀዋል። አምስቱም የፓርቲው አባላት በማዕከላዊ እንደሚገኙና ከእነዚህም መሃል በተያዘበት ወቅት አቶ ኤርሚያስ ፀጋዬ፣ አቶ ፍሬው ተክሉና አቶ ቴዎድሮስ አስፋው ድብደባ እንደደረሰባቸው ከቤተሰቦቻቸው መስማታቸውን አቶ ጋሻው አያይዘው ገልፀዋል። የፓርቲው ልሳን የሆነችው ‹‹ነገረ-ኢትዮጵያ›› ዋና አዘጋጅ ጌታቸው ሽፈራው እና የፓርቲው አባል ዳንኤል ተስፋዬ በፌደራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አራዳ ምድብ ችሎት ቀርበው ፖሊስ የ28 ቀን የጊዜ ቀጠሮ ጠይቆባቸው ፍ/ቤቱ ፖሊስ ማስረጃውን እንዲያቀርብ ቀጠሮ ለጥር 14/2008 ዓ.ም ሰጥቷል።

በሌላ በኩል ከእስር ከተፈቱ ዓመት እንኳ

### የ‹‹የህይወት መንገድ›› ይመረቃል

በጀራሲ አክሊሉ ረታ ወልደጋይ የተዘጋጀው ‹‹የህይወት መንገድ›› የተሰኘ መጽሐፍ ነገ ታህሳስ 24 ቀን 2008 ዓ.ም ከ9:00 ሰዓት ጀምሮ ጋራድ ሕንፃ 3ኛ ፎቅ፣ ያልማ ካፌና ሬስቶራንት አዳራሽ በይፋ ይመረቃል።

# ያልተገሩ አስተሳሰቦች



በቃሉ አጥናፉ ታዬ (ዶ/ር)

በአንድ ነገር ላይ የሰለጠኑ እንስሶች በሰለጠኑበት ነገር ላይ ተመሳሳይ ምላሽ ሊሰጡ ወይም ሊያሳዩ ይችላሉ። የሰው ልጅ ግን በአንድ ጉዳይ ላይ በእኩል መጠን ቢሰለጥንም በሰለጠነበት ነገር/ጉዳይ ላይ እኩል ግንዛቤ ሊኖረው አይችልም። ነገሮችን የምንረዳበት መጠን ልዩነት አለው። ስለዚህ ልዩነት ተፈጥሮአዊ፣ ልዩነት ሰዋዊ ነው። ልዩነት የዲሞክራሲያዊ ስርዓት ባህሪ ነው።

የህወሃት/ኢህአዴግን የፖለቲካ ስርዓት ቅኝትን መቃወም በአገር ጉዳይ ላይ ያገባኛል ከሚል ዜጋ የሚጠበቅ የሀሳብ ልዩነት ነው። ይህ የሀሳብ ልዩነት ወይም መቃወም ግን በፖለቲካ ስርዓቱ ተቀባይነት የለውም። መቃወም ወይም የተለየ ሀሳብ ማራመድ ለዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ እና ሂደት የራሱ ድርሻ ሊኖረው የተቃርኖ አስተሳሰቦች ገንቢ ትችት ስለሚይዙ ለስርዓቱ ጠቀሜታ ነበራቸው።

ህወሃት/ኢህአዴግ ከስልጣኑ በላይ ስለምንም ነገር ማሰብ ስለማይፈልግ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን እንቅስቃሴ ስልጣኑን ያለሙኛል የሚል እሳቤ የተጠናወተው ስለሆነ የሚቃወም ወይም በስርዓቱ ላይ የተለየ አስተሳሰብ ያነገቡ ግለሰቦችን እንደ አሸባሪ ወይም ወንጀለኛ ይፈርጃል፤ ከዚህ ይልቅ ግን የተቃዋሚዎችን ትችት ለአስተዳደራዊ ግብዓትነት ሊጠቀምበት በተገባ ነበር። እንዲሁም ከተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ወይም ስርዓቱን ከሚተቹ ዜጎች አስተሳሰብ አንፃር ስርዓቱ የቆመበትን የፖለቲካ ዘውግ እንዲመረመር ዕድል ይሰጥ ነበር። መቃወም ወይም የተለየ አስተሳሰብ ማራመድ ለስልጣን ብቻ ተደርጎ መታየቱ ስህተት ነው።

ከህወሃት/ኢህአዴግ የፖለቲካ ስርዓት በተቃርኖ ያሉትን አባላት ተቃዋሚዎች በሙሉ የጥፋት ኃይሎች፣ የልማት እንቅፋት፣ ፀረ ሰላም፣ የውጭ ጉዳይ አስፈፃሚዎች፣ አሸባሪ፣ ነፍጠኛ፣ ትምክህተኛ፣ ጠባብ አመለካከት፣ የደርግ ስርዓት ናፋቂዎች እያሉ በመፈረጅ የአገሪቱን ችግር መፍታት አይቻልም። ይህም አባባል «ጨለምተኛ ቀመኝ» ይሰኛል። ትምክህተኛ እና ጠባብ አመለካከት ማን ኖረው እና ነው እነዚህ ቃላት ለተቃዋሚዎች የሚሰነዘሩት። ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ፀረ-ሰላም፣ ፀረ-ልማት ሊሆን አይችልም። የአገርን ልማት፣ ሰላም፣ ዕድገት የማይመኝ ኢትዮጵያዊም የለም። የአገርን ልማት፣ ሰላም፣ ዕድገት ለማጠልሸት የሚንቀሳቀስ ኃይልም የለም። ሆኖም ግን ህወሃት/ኢህአዴግ በአገሪቱ ላይ ከሚያራምደው ስርዓት ይልቅ ለአገሪቱ የተሻለ ስርዓት/ፕሮግራሞችና ፖሊሲዎች/ እናሰፍናለን የሚሉ የተለያዩ የተቃዋሚ ድርጅቶች አሉ። የእነዚህ ድርጅቶች እይታ፣ የጠራ የፖለቲካ አስተሳሰብ፣ ገንቢ ትችቶች፣ ፖሊሲ እና ፕሮግራሞች በቅን ልቦና ከመመርመር ይልቅ በተቃዋሚዎች ላይ ጭፍን ፍረጃ ወይም ጥላቻ ጤናማ አስተሳሰብ አይደለም።

ሰው የህወሃት/ኢህአዴግን የፖለቲካ ስርዓት የሚቃወመው ወዶ አይደለም። አዕምሮው አስገድዶት ነው። አገሪቱ የወረደችበትን የዝቅጠት ቁልቁለት እንኳን ግምት ውስጥ ሳናስገባ ሞት፣ ስደት፣ የፍትህ እጦት፣ ረሀብ፣ አድሉአዊነት በሰፈነበት ስርዓት ውስጥ ዝም ብሎ መቀመጥ ለአዕምሮ ሰላም አይሰጥም፤ ለአዕምሮ ሰላም ይነሳል። የስደተኛው ብዛት የስርዓት ችግር እንዳለ ያመለክታል፤ ሰው ወዶና ፈቅዶ አይደለም ከአገሩ የሚሰደደው፤ የተሻለ ኑሮ ፍለጋ ህይወቱን ለማቆየት ግድ ብሎት ነው። በአረብ አገሮች የሴት እህቶችን እሮሮ፣ በሊቢያ የታረዱ ወንድሞችን ደም፣ በደቡብ አፍሪካ የተቃጠሉ ወንድሞቻችን በደል፣ በኬንያ፣ በታንዛንያ፣ በየመን እና በተለያዩ አገሮች እስር ቤቶች የታጎሩ ኢትዮጵያውያንን ነፍሶች እስኪ ለአፍታ አስቡት። በቤንሻንጉል ጉምዝ፣ በጉራፈርዳ፣ በደኖ፣ በቴፒ እና በሌሎች ክልሎች በአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ላይ የደረሰውን እና እየደረሰ ያለውን ሰቆቃ እናስበው፣ በኡጋዴን፣ በጋምቤላ፣ በአፋር የደረሰውን ጭፍጨፋ እናስታውሰው፣ በተያያዥ በግፍ የተገደሉ ኢትዮጵያውያንን እናስባቸው፣ አሁን በቅርቡ እንኳን በኦሮሚያ የወደቁ እና የቆሰሉ ወንድም እና እህቶቻችንን በምናባችን እናስታውሳቸው፤ የሀሳብ ነፃነታቸውን በመጠቀማቸው እና በመፃፋቸው እስር እና ግድያ የተፈረደባቸውን ኢትዮጵያውያንን በደል እስኪ እናስታውሰው። ረሀብ፣ የኑሮ ውድነቱ፣ አድሉዓዊነቱ፣ ዘረኝነቱ፣ እነዚህን ሁሉ የበደል ክምችት እያየን እንዴት ዝም እንበል? እነዚህ ነገሮች እንዳይፈፀሙ መከላከል ባንችል፤ አቅም ቢያጥረን ቢያንስ እንዴት መቃወም ይሳነን? እነዚህን አስከፊ በደሎች የፈፀመውን እና መከላከል ያልቻለውን ስርዓት መቃወም ምንድን ነው ነውሩ? ከምን ላይ ነው ስህተቱ? የቱ ነው በደሉ? የቱ ነው ጥፋቱ? እነዚህ ከዚህ በፊት የተዘረዘሩትን ኢ-ሰብዓዊ እና ኢ-ፍትሐዊ ድርጊቶችን አይቶ እና አይቶ ዝም ማለት ህሊናቢስነት ነው። ነፍስን ማቆሸሽ መንፈስንም ማርከስ ነው። እነዚህ ድርጊቶች ደግመው እንዳይፈፀሙ የተፈፀሙትንም «ለምን?» ብሎ አለመቃወም እንደ እውነቱ ሆዳምነት ነው። ከህሊና ጋርም መፋታት ነው።

ታላቁ የህንድ የነፃነት ታጋይ ማህተመ ጋንዲ በአንድ ወቅት እንዲህ ብሎ ነበር «የአንድ መንግስት ታላቅነት የሚመዘነው ለእንስሳቱ በሚያደርገው ወይም በሚያሳየው እንክብካቤ ወይም አያያዝ ነው።» እንዳለ ይነገራል። ጋንዲ የኢትዮጵያ ህዝብ በአሁኑ ሰዓት የተያዘበትን አያያዝ ቢመለከት ምን እንደሚል መገመት አያዳግትም። የህወሃት/ኢህአዴግ መንግስት እንኳንስ ለእንስሳት ክቡር ለሆነው ለሰው ልጅ የሚያሳየው ንቀት እና ጤናማ ያልሆነ አያያዝ በውጭ/በምዕራባውያን አገሮች የሚገኙ እንስሳት ከባለቤቶቻቸው ከሚያገኙት እንክብካቤ ወይም አያያዝ ያነሰ ነው። ሰዎች እንደ ውሻ ከቆሻሻ ገንዳ ምግብ የሚመገቡበት አገር ነች ኢትዮጵያ፤ የምግብ ፍርፋሪ በጉርሻ መጠን የሚሸጥበት አገር ነች ኢትዮጵያ፤ ሰዎች ያለፍርድ፣ ያለፍትህ የሚገደሉበት፣ የሚታሰሩበት፣ የሚሰደዱበት፣ የሚገለሉበት አገር ነች ኢትዮጵያ፤ አፈር ጭሮ የሚያድረው ገበሬ በቃህ አይደለም(አገርህ አይደለም ተብሎ የሚፈናቀልበት፣ የሚገደልበት፣ ሰብዓዊ መብቱ የሚጣስበት አገር ነች ኢትዮጵያ። ዜጎች በችሎታቸው ሳይሆን በብሔር ማንነታቸው ያለብቃታቸው ስልጣን ይዘው ገዥዎች [illegible] የሆኑባት አገር ኢትዮጵያ ይህን መቃወም የቱ ላይ ነው ግድፈቱ?

በግብረ-ገብነት እና በእምነት ስለተቃኘ ስብዕና እና ማህበረሰብ በገዘፈን ኢትዮጵያውያን ላይ የሚደርሰውን በደልና ግፍ ቢያንስ አለመቃወም ግርምትን ይፈጥራል። ይህንን ሁሉ ኢ-ፍትሃዊ ተግባራትን «ለምን?» ብሎ የጠየቁትን፣ የተቃወሙትን፣ ከእነዚህ በደሎች ፈፃሚዎች ጋር ተባባሪ ያልሆኑትን፣ የተለየ አስተሳሰብ ወይም ተቃርኖ ያላቸውን ዜጎች አሸባሪ፣ ትምክህተኛ፣ ጠባብ አመለካከት፣ ፀረ-ሰላም፣ ፀረ-ልማት ወዘተ እያሉ መፈረጅ ሰዋዊ የሆነውን የፍትህ ስርዓት ያልተከተለ የብይን አሰጣጥ ሂደት ነው።

እንደራሱ አስቦ እንደ ህሊናው ፈቅዶ ራሱን በሰብዓዊ ሚዛን ለሚመረምር ዜጋ ይህን ስርዓት መቃወም ፍፁም ጤነኝነት ነው። እደግመዋለሁ መቃወም ጤነኝነት ነው፤ መቃወም ወንጀል አይደለም። ሰው ወዶ ሳይሆን የሚቃወመው ህሊናው አስገድዶ ነው። ከሆዱ ጋር ሳይሆን ከህሊናው ጋር ይኖር ዘንድ፤ ፍትሃዊ፤ ኢ-ሰብዓዊ የሆኑ ድርጊቶችን ይቃወማል። ስጋዊ ምቾቱን አደጋ ላይ ጥሎ ለህሊናው መታዘዝ ስላለበት ጤናማ ሰው ኢ-ሰብዓዊ ወንጀሎችን ይቃወማል።

ስለሆነም ህወሃት/ኢህአዴግ የተቃውሞ ድምፆችን ከማፈን ይልቅ፣ ለተቃውሞ ድምፆች ምክንያት የሆኑትን ኢ-ሰብዓዊ ድርጊቶችን ማቀብ ግድ ይለዋል። እንዲሁም የተቃውሞ ድምፆችን እና አስተሳሰቦችን ሊያስተናግድበት የሚችል ምህዳሩን ማስፋት ተገቢ ይመስለኛል። ይህን ለማድረግም የአስተሳሰብ ተሃድሶ ያስፈልገዋል።

በጥቃቅን ነገሮች ላይ ልዩነትን እየፈጠርን በየዕለቱ ከምንራራቅ፣ የውይይት ምህዳሩ ሰፍቶ በአገራዊ ጉዳዮች ላይ እየተስማማን፣ እየተደማመጥን፣ ሀሳቦችን እየጸመርን በውይይት እየቀነስን የአገሪቱን ችግሮች መፍታት መልካም ነው። ያለበለዚያ ኢ-ፍትሃዊና ኢ-ሰብዓዊ ድርጊቶች በዚሁ ከቀጠሉ ውጥረቱን እያባባሱት ይሄዳሉ እንጂ መፍትሔ ሊሆን አይችልም። ከቀላዊ እና ከአመክንዮዓዊ አስተሳሰቦች ተፃራሪ ተላቀን ውጥረቶችን ፈተን ነገሮችን መለወጥ የተሻለ ነው። እኛ በምናስበው እና በፈቀድነው መንገድ ብቻ እንጂ መራመድ የተለያዩ አስተሳሰቦችን እና የተቃውሞ ድምፆችን እናፍናለን በማለት እና በማፈን የአገሪቱን ችግር መፍታት አይቻልም።

በሬ ወለደ ዜና ሁለት አሃዝ የምጣኔ ሀብት እድገት አድገናል፤ በየአምስት ዓመቱ ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ተካሂዶ በቅርቡ እንኳን 99.6% እና 100% አንድ ፓርቲ አሸንፏል፤ ህዝባዊ ቅቡልነት ያለው ወገናዊ ፓርቲ ነው ኢህአዴግ እያሉ የሚያንቆለጳጵሱ አጋፋሪዎች፣ ስርዓቱን ከነግንባሩ የሚያሞካሹት ዜጎች እንደመናገራቸው መጠን ስርዓቱ የፈፀማቸውን በደሎች የሚዘግቡ እና የሚቃወሙ ዜጎችም አስተሳሰብ ሊከበር ይገባል።

በአጠቃላይ በህወሃት/ኢህአዴግ ስርዓት ካገነነው ርዕዮተ ዓለም በተቃርኖ የሚገኙ ሀሳቦች በሙሉ የሚደመጡበት፣ የሚሸጡበት፣ የሚዳበሩበት፣ ስርዓት ሊሆን ይገባል። የተለያዩ ወይም አዳዲስ አስተሳሰቦች የሚፈጠሩበት፣ ያለውን ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሁነቶች የሚተቹበት፣ ተቃዋሚዎችም ስርዓቱን ባለመደገፋቸው ምክንያት የማይገደሉበት፣ የማይታሰሩበት፣ የማይሰደዱበት፣ የማይገለሉበት፣ የማይፈናቀሉበት ዘመኑን የዋጀ ስርዓት ሊሆን ይገባል እንጂ እንደ አዳኝ አውሬ በአስተሳሰብ የተለዩ ዜጎች ወይም ተቃዋሚዎችን በማሳደድ የዚህች አገር ችግር በፍፁም አይፈታም።





# የነጻነት አሜኬላ



ኪያ ዓሊ

የአምባገነን ሥርዓቶች የምጽአት ቀን እንዲደርስ፣ የጭቁን ሕዝብ ሁሉ ምኞት ነው። እነዚህ ሕዝቦች፣ ምኞታቸውን እውን ለማድረግና የናፈቁትን ነጻነት ለመጎናጸፍ፣ ከገዢዎቻቸው ጋር ብርቱ ትንቅንቅ አድርገዋል። ፕ/ር ጂን ሻርፕ "From Dictatorship to Democracy" በሚለው መጽሐፋቸው ላይ እንደ ገለፁት፣ ከ1980 (እ.ኤ.አ) ወዲህ የብዙ አገራት አምባገነን መንግሥታት በሰላማዊ አመፀኞችና ታጋዮች ድል ተንኮታኩተዋል። አምባገነን የመንግሥት ሥርዓት ሰለባዎቻቸው ከነበሩት ውስጥ እስቶንያ፣ ላቲቪያ፣ ፖላንድ፣ ምሥራቅ ጀርመን፣ ቼኮዝሎቫኪያ፣ ስሎቬንያ፣ ማዳጋስካር፣ ማሊ፣ ቦሊቪያ እና ፊሊፒንስ ይጠቀሳሉ። ምንም እንኳ ጨቋኝ አገዛዞች ባይወገዱባቸውም፣ የኔፓል እና በርማ (ምያንማር) ነጻነት ናፋቂዎች፣ የተቃውሞ ድምፃቸውን በማሰማት የመንግሥታቸውን አስከፊ ገጽታ ለዓለም አጋልጠዋል፤ የሰላማዊ ትግልን አተገባበርም ከፍተኛ ዋጋ ከፍለው ከፍተኛ ዋጋ ያለው ልምድ አስተላልፈዋል።

በተመሳሳይ መልኩ ሩት(ruth)፣ ያኢር(yair) እና ቢትሪዝ (beatriz) "Taking to the streets: Theory and evidence on protests under authoritarianism" በሚለው የጋራ ስራቸው ላይ እንደገለጹት "ከቅርብ አስርት አመታት ወዲህ በአለም ዙሪያ ያሉ ህዝቦች የአንድ ሰው የረጅም ጊዜ የአገዛዝ ስርአት እንዲያበቃ ወደጎዳናዎቻቸው ሆ ብለው በመውጣት ተቃውሟቸውን ሲያሰሙ ተስተውሏል። ከነዚህም መካከል በ1988 ሜክሲኮ፣ በ1989 በቻይናና ምስራቅ አውሮፓ፣ በ2000 መጀመሪያዎቹ ላይ በሰርቢያ፣ ጆርጂያ፣ ዩክሬን፣ ኪርጊስታን፣ በ2007 በሚያንማር እንዲሁም ከተወሰኑ አመታት በፊት በኢራን፣ ቲዩኒዝያና በግብፅ የተካሄዱት ይገኙበታል። ከእነዚህ ውስጥ አብዛኞቹ ያለምንም መሪ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሰዎች በአንድነት ወደአደባባይ በመውጣት ያደረጉት የአደባባይ የተቃውሞ ሰልፎች ሲሆኑ እነዚህ ሰልፎችም የተቀጣጠሉት ምርጫን፣ የኑሮ ውድነትን፣ መብትንና ጭቆናን ተቃውመው ነው" በማለት የፕ/ር ጂን ሻርፕን ሀሳብ ተጋርተዋል።

እንግዲህ ከላይ በተጠቀሱት ሀገሮች ውስጥ የሚኖሩት ህዝቦች የተቃወሟቸው ነገሮች በሙሉ የኢትዮጵያ ህዝብም የሚቃወማቸው ነገሮች በመሆናቸው ከእነርሱ ጋር የምንጋራው ነገር መኖሩ አያጠራጥርም። ነገር ግን አብዛኞቹ በሰላማዊ ትግል ውስጥ ያለፉት ሀገራት ነጻነታቸውን ሲጎናጸፉ እኛ ግን እንደ ቻይና የኢህአዴግን ባህሪ ለአለም ከማጋለጥ ሳናልፍ ቆይተናል። እናም የዚህ ትውልድ አባላት የሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቻቸውን ለማስከበር በተለያዩ ወቅቶች መስዋዕትነት ቢከፍሉም እስከአሁን ግን በሰላ ቀንበሩን የተመኘነውን ማግኘት አልቻልንም። ስለዚህም ዋና ዋና ምክንያት ናቸው ብዬ ያመንኩትን የሚከተሉትን ነው።

## እረኛውን ምታ መንጋው ይበተናል?

ብዙ ጊዜ የነጻነት ጥያቄዎች በሚያስተጋቡበት ወቅት በቅድሚያ የገዢዎች ግፍና ጭካኔ ጎልቶ ቀማሽ የሚሆኑት ከፊት ሆነው ህዝቡን የሚመሩ ግለሰቦች ናቸው። ይህም «እረኛውን ምታ መንጋው ይበተናል» ከሚል እሳቤ የመነጨ ይመስለኛል። በተለይ ምርጫን ተከትሎ ከሚፈጠር ግርግርና በዚህ ሳቢያ ከሚነሱ አለመግባባቶች ጋር በተያያዘ ጂን ሻርፕ ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፍ ላይ "አምባገነኖች ከስልጣን መንበራቸው ላይ የሚያወርድ ምርጫን ማድረግ አመክንዮአዊ ባለመሆኑ በአምባገነን ስርአት በምትተዳደር ሀገር ውስጥ የሚደረጉ ምርጫዎች እውነተኛ ሳይሆኑ ዴሞክራሲያዊ ሆኖ ለመታየት ብቻ ሲባል የሚከናወኑ ናቸው። ስለዚህ ወሳኝ የፖለቲካ ለውጥ የማምጣት አቅም የላቸውም። በመሆኑም በ1990 በበርማና (ምያንማር) በ1993 በናይጄሪያ እንደ ሆነው ምንም እንኳ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በውድድሩ ያሸነፉ ቢሆንም ገዢዎች ግን አሸናፊነታቸውን ችላ በማለት የአሸናፊው ፓርቲ አመራሮች ላይ ዛቻና ማስፈራሪያ በመፈጸም እስርን በሚጠቀም መንገድ እንዲገቡ ጫና ሲፈጥሩባቸው ይስተዋላሉ። እንዲሁም አሸናፊዎቹ የህግ ሽፋንን በመጠቀም ህጋዊ የቅጣት ውሳኔ በማስተላለፍ የሞት ፍርድ እስከመስጠት ይደርሳሉ» በማለት ሁኔታውን በተግባር መልኩ ገልጿል።

በዚህ ዓይነት ሁኔታዎች በምን መልኩ መጓዝ እንዳለባቸው መመሪያ የሚያስተላልፉ አመራሮች ባለመኖራቸው፣ የተጀመሩ የለውጥ እንቅስቃሴዎች ባይጠፉም ሌላ ብቃት ያለው ከፊት ሆኖ የሚመራ ግለሰብ ወይም ቡድን እስከሚፈጠር ግን ተዳክመው ለመቆየት ይገደዳሉ። በተጨማሪም አምባገነን መንግስታት የሚከተሉትን የ«እረኛውን ምታ መንጋው ይበተናል» አካሄድ ተከትለው አመራሮች ላይ የሚደርሰው እንግልት፣ ወከባ፣ እስራት እንዲሁም ለሞት የሚዳርጋቸው አስከፊ ሁኔታዎች ተደማምረው የነጻነት ጥያቄ ለማንሳት እርሱን በሚያነሳሱት እቅድና በሚያስተላልፉት መመሪያ ላይ ብዥታ መሆን፣ የድል ጸዳል ለማማተም እንቅፋት ከሆኑ ምክንያቶች ውስጥ በዋናነት ተጠቃሽ እንዲሆን አድርጓታል።

ይህንን ሁኔታ ከሀገራችን የፖለቲካ ታሪክ ጋር ስናገናኘው ተመሳሳይ ሆኖ እናገኘዋለን። በተለይ ምርጫ 97ን ተከትሎ በመንግስትና በህዝብ መካከል በተከሰተው አለመግባባት ለተፈጠሩ የንብረት ውድመትና የሰው ህይወት መጥፋት ሙሉ ሀላፊነቱን በወቅቱ በምርጫው አሸናፊ የነበሩት የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች እንዲወስዱ ተደርጎ ወደወህኒ መወርወራቸውን ስናስታውስ ሁኔታው ይበልጥ ግልጽ ሆኖ ይታየናል። ከዚህም ወዲህ ከሽብርተኝነት ወንጀል ጋር በተያያዘ ተከሰው በእስር እየተቀጡ ያሉትን እንደ እንዷለም አራጋው በቀለ ገርባ (በቀለ ገርባ የእስር ዘመኑን አጠናቅቆ የተፈታ ቢሆንም በቅርቡ በኦሮሚያ ክልል ከተነሳው ግርግር ጋር በተያያዘ እርሱና ሌሎች የፓርቲ አመራሮች በቁጥጥር ስር ውለዋል) የመሳሰሉ ፖለቲከኞችን በምሳሌነት ማቅረብ ሀሳቡን ይበልጥ ያጠናክረዋል።

ነገር ግን ይህ የ«እረኛውን ምታ መንጋው ይበተናል» ስልት በፖለቲካ አመራሮች ላይ ብቻ የሚደርስ ሳይሆን የነጻነትን ንቃተ-ህሊና በማዳበር በኩል ጉልህ ሚና አላቸው ተብለው የሚገመቱ የሚዲያ ባለሙያዎችም ላይ ያነጣጠረ ነው። ከዚህም መካከል ጋዜጠኞች በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ ሲሆን፣ ኢህአዴግ በትረ ስልጣኑን ከጨበጠበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን ስንት ጋዜጠኞች እንደ ተገደሉ፣ ስንት ጋዜጠኞች እንደ ተሰደዱና ለእስር እንደ ተዳረጉ ስንመለከት ጉዳዩ ስር የሰደደበት ጥልቀት ምን ያህል እንደ ሆነ እንገነዘባለን። በተለይ ደግሞ በአለም አቀፍ ደረጃ ሽብርተኝነትን አጥብቀው የሚቃወሙ ሀገራት የሚሰጡዋቸው ተጓዳኝ ፈቃዶች ጋዜጠኞቹ በጽኑ መታሰር እንደማይገባቸው የሚወተውቱ መሆናቸውና ሲጋለጡ የሚሰነዝሩባቸውን ሽልማቶች ስናይ የሚሰጣቸው ጋዜጠኞቹ ሽብርተኛ ሳይሆኑ «እረኛውን ምታ መንጋው ይበተናል» ስልቶች እንደ ሆኑ እንረዳለን።

ይህም መንገድ የብዙሀኑ ድምጽ ተደማጭ የሆኑትን ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመመስረት በሚደረገው ጥረት ላይ የጎላ ሳንካ በመሆን ሂደቱን ወደ ኋላ ይጎትተዋል። የኋላ ኋላ ግን የቱንም ያህል ቢዘገይ ይህንን የተፈለገ ህዝብ ግለሰቦች በተናጠል መልኩና ብቃት ባለው አመራር የሚመራ የነጻነት እንቅስቃሴ ጫፍ ውጤት ማስገኘቱ ባያጠራጥርም፣ ነገር ግን ነጻነታችንን ለመጎናጸፍ ግዴታ ከፊታችን የሚቆም ቡድን ወይም መሪ አያስፈልገንም በማለት በተጠቀምነው ወይም ድምፃችንን ያሰሙልናል ብለው በሚያምኑባቸው አካላት ብቻ መንግስትን በመሞገት ፈንታ፣ በመሪያቸው ላይ እንደ ተዘረጋ ህዝብ ሀገራት ህዝቦች፣ እራሳቸው ድምፃቸውን ለማሰማት ወደ አደባባዮች መውጣታቸው አይቀሬ ይሆናል። ለዚህም በቅርቡ በኦሮሚያ ክልል የተፈጠረው ክስተት ከዚህ በላይ ለሁኔታው አስረጂ ነው ብዬ አምናለሁ።

## የመረጃ እጥረት

በግልጽ እንደሚታየው በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ሰፊ ተደራሽነት ያላቸውን ሚዲያዎች ለብቻው በመቆጣጠር ስለስራቸው መንገዶች፣ ከድህነት ቀንበር ተላቀው በህዝብ ሙቀት ስለተሰጡ ልማታዊ ባለሀብቶችና አርሶ አደሮች፣ በጥቃቅንና አነስተኛ በመደራጀት ህይወታቸውን ስለለወጡ ሰዎች፣ በአጠቃላይ ስለሀገሪቱ ልማትና እድገት በተጋነነ መልኩ በመስበክ በስልጣን ላይ ለመቆየት የሚያስችለውን ፕሮፓጋንዳ ያለማቋረጥ እያሰራጨ ይገኛል። ከተማሪዎች እንቅስቃሴ ጀምሮ ሽንጡን ገትሮ ስለሚከራከርላቸው የብሄር ብሄረሰቦች መብት መከበርም፣ የብሄር ብሄረሰቦችን ቀን የደመቀ የበአል አከባበር በማሳየት ሊያሳምን ሌት ተቀን ይተጋል።

የፍትህ፣ የማንነት ጥያቄ፣ የነጻነት፣ የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር፣ መንግስት በሃይማኖታችን ጣልቃ አይግባ የሚሉና መሰል ጉዳዮችን ለሚያነሱ አካላትና ግለሰቦች ደግሞ ህገወጥና ህገመንግስቱን በሀይል ለመናድ የተነሱ በማለት በሚሰሩ ዶክመንተሪ ፊልሞች (ለዚያውም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት በሌሉበት) አሸባሪነት የተላበሰ መልእክት ሰጥቶ ያስተላልፋል። በመሆኑም በተለያዩ ስፍራዎች ያሉ ሰዎች ስለሚጋሩን ትክክለኛ ችግርና ጥያቄ የማወቅ እድላችንን የመነመነ ነው ብል ስህተት አይሆንም።

በዚህም ሳቢያ በአንድ አካባቢ ያሉ ሰዎች ሌላ አካባቢ ስላሉ ሰዎች ትክክለኛ እውቅና ስለማይኖራቸው፣ ለሚያቀርቡት ተቃውሞ ተገቢነት ተቀብለው በተቀናጀ መልኩ እንዲያስቡ እንቅፋት ሆኖባቸዋል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሩት እና ያኢር ከላይ በተጠቀሰው ስራቸው ላይ አምባገነን አገዛዙን ለመቃወም አቅም ያላቸው ዜጎች ድምፃቸውን ለማሰማት በሚነሳሱበት ወቅት፤ ደጋግመው ቆም ብለው የሚያስቡበትን ሀሳብ ተግባራዊ ሲያደርጉ "አንደኛ አምባገነኖች የተቃውሞ ድምጾችን ጆሮ ለማደንቆር ዘወትር ማስፈራሪያና ፕሮፓጋንዳ ስለሚጠቀሙ አንዱ ዜጋ ለሌላው ዜጋ ስለመንግስት ያለው እውነታ ላይ የሚደርሰው መረጃ ያልተሟላ በመሆኑ ግለሰቦች ትክክለኛ ውሳኔ እንዳይወስኑ ሲያደርግ፣ ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ህዝቦች ሆ ብለው በአንድነት ካልተነሱ ለረጅም ጊዜ በስልጣን ላይ የቆየ አምባገነን ለመጣል አስቸጋሪ ስለሚሆንና የተቃውሞ እንቅስቃሴ ተሳታፊዎች ደግሞ በተቃውሞ እንቅስቃሴ ውስጥ ሲሳተፉ እስራት፣ የአካል መጉደል እንዲሁም ህይወታቸውን ጭምር መስዋዕት አድርገው የሚከፍሉት ዋጋ ስላለ፣ በአጋጣሚ አይሆኑም ብለው በሚያምኑት እንቅስቃሴ ላይ ከመሳተፍ ይቆጠባሉ። በዚህም ምክንያት በተቃውሞ እንቅስቃሴ ላይ የሚሳተፉ ሰዎች ቁጥር ጥቂት ስለሚሆን በአገዛዙ ላይ ጫና ለመፍጠር ያላቸው አቅም ውሱን ይሆናል። እናም ወደትግል ከመግባታቸው በፊት ሌሎች ሰዎችም የትግሉን እንቅስቃሴ ለመቀላቀል ፍላጎት እንዳላቸው ማረጋገጥ ይፈልጋሉ" በማለት የተሟላ መረጃ አለማግኘትን በሚገባ ገልጸውታል።

በዚህም መሰረት ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሰላማዊ ትግል አማራጭን ለማራመድ መወሰናቸው፣ የተቃውሞ ሰልፍ እንዳይካሄድ በመንግስት በኩል ያለው ጫና፣ በመገናኛ ብዙሀን ላይ የሚደረገው አፈና የህዝብ ትክክለኛ እና እውነተኛ መረጃ ወደ ህዝቡ እንዳይደርስ የሚያደርጉ እንቅፋቶች ናቸው። በዚህ መሰረት ጠንካራ ባለ መልኩ ነፃ የተመሰረቱ እንደሆነ የመረጃ እጥረትና ፕሮፓጋንዳ የህዝብን መረጃ የማግኘት ነጻነት በመጋፋት የነጻነት ጉዞዋ መሆናቸውን እንረዳለን።

በመሆኑም ለእነዚህ እንቅፋቶች ተገቢውን መፍትሄ በጊዜ ካላገኘን አሁን ባለንበት የአገዛዝ ስርአት ስር ለተራዘመ ጊዜ መቆየታችን አይቀሬ ይሆናል። መቼም ኢህአዴግ የዘራው ችግሮች መፍቻ ቁልፍ የምናገኝበትን መንገድ አልጋ ባልጋ ያደርገዋል ብሎ የሚጠብቅ የዋህ ይኖራል ብዬ አላስብም። እናም እንቅፋቶችን አስተውለን ቢሆን የመፍትሄውን ቁልፍ በእጃችን ለማስገባት ሁላችንም የበኩላችንን እንጣር።

# <<በኢትዮጵያ ምሁራን ዘንድ በጣም የአድርባይነት መንፈስ አለ>>

አቶ በቀለ ገርባ /የኦፌኮ ምክትል ሊቀመንበር/

**በጸረ-ሽብርተኝነት አዋጁ ተከስሰው በፍርድ ሂደት ከሶስት ዓመት ከግማሽ በላይ በማዕከላዊ፣ በቃሊቲና በዝዋይ እስር ቤቶች አሳልፈዋል፡፡ የእስር ጊዜዋውን ጨርሰው ከዝዋይ ከወጡ በኋላም፤ ቀደም ሲል ወደነበሩበት የተቃውሞ የፖለቲካ ዓለም ሲቀላቀሉም <<ልረፍ፣ ልቀመጥ>> ሳይሉ ነበር፡፡ ከሀገር በመውጣት በአሜሪካን ሀገር ቆይታ በማድረግ፣ በሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ በተጋበዙባቸው የተለያዩ መድረኮች ላይ ንግግርና የተለያዩ ቃለ-ምልልሶችን አድርገው በቅርቡ ወደሀገራቸው ተመልሰዋል፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የውጪ ቋንቋዎች የሙያ ዘርፍ መምህር እና የኦሮሞ ፌደራሊስት ኮንግረስ (ኦፌኮ) ተተዳሚ ምክትል ሊቀመንበር የሆኑት አቶ በቀለ ገርባ የዚህ ዕትም <<የአዲስ ገጽ>> መጽሄት እንግዳ አንግዳችን ናቸው፡፡ እናንያ ሶረና ኤልያስ ገብሩ ከአቶ በቀለ ጋር በመገናኘት በጉዳዩ ሊተገበር ታቅዶ ስለነበረውና ላለፈው አንድ ወር ያህል በተለይ በተለያዩ የኦሮሚያ ክልል ከባድ ህዝባዊ ተቃውሞና ቀጣን በመቀስቀስ የበርካታ ንጹሃን ዜጎችን ሕይወት እስከመቀጠፍ ስለደረሰው <<የአዲስ አበባና የኦሮሚያ ልዩ ዞን የተቀናጀ የጋራ ማስተር ፕላን>> በባለፈው ሳምንት ዕትማችን የመጀመሪያው ክፍል ቀርቦ ነበር፡፡ የቃለምልልሱን ሁለተኛ እና የመጨረሻ ክፍል እንዲህ አቅርበነዋል፡፡ አቶ በቀለ ገርባም በአሁን ወቅት ለድጋሚ እስር ተዳርገው በማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ በእስር ላይ ይገኛሉ፡፡**

**<<አዲስ አበባን ማስፋት ኢትዮጵያን ማጥበብ ነው>> የሚሉ ወገኖችም አሉ፡፡ በዚህም ላይ የእርስዎ ምላሽ ምንድን ነው?**

እንዲህ የሚሉትን ሰዎች ትንታኔ፣ እኔ በደንብ አልተረዳሁትም፡፡ አዲስ አበባን በተመለከተ የእኛን አንደበት እና አመለካከትን ብናገር እመርጣለሁ፡፡ አዲስ አበባ ብትሰፋ፣ ሕዝቦች ተፈቃቅረው ከዚህ ቀደም ይኖሩ በነበረበት ሁኔታ፣ ለሁሉም የተመቻቸችና የተረጋጋች ከተማ ብትሆን በጣም ደስ ይለኛል፡፡ አዲስ አበባ የሚያስፈልጋትን፣ ከክልሎች ወይንም ደግሞ ከአካባቢው ካሉ አገራቶች ከተሞች እና ገጠሮች አግኝታ ብታድግና ሕዝቡ የተሻለ ኑሮ ቢኖር፣ ሌላው በአካባቢ ያለውም ህዝብ ተጠቃሚ እንደሚሆን በትክክል እንገነዘባለን፡፡ እኛ የምንጠላውና አጥብቀን የምናወግዘው፣ በአንድ ሕዝብ ጉዳት ላይ የተመረኮዘ ልማት መሰል ጥፋትን ነው፡፡ <<ይሄ አያስኬድም፣ ጥሩ አይደለም፡፡ በዓቱ ሰላምንና አውነተኛ እድገትንም አያመጣም>> ብለን እናምናለን፡፡

አዲስ አበባ ማዕከል ናት፡፡ መሀሉን የያዙ ዙሪያ ግዛውን ይይዛል፡፡ መሀሉ ከተበላሸ ዙሪያ ግዛው መበላሸቱ አይቀርም፡፡ ይሄ ደግሞ የኢኮኖሚም የፖለቲካም ማዕከል ነው፣ የዕውቀትም ማዕከል ነው፣ የሥልጣኔም ማዕከል ነው፣ የሁሉ ነገር ማዕከል ነው፡፡ ስለዚህ አዲስ አበባ ላይ የሚደርስ ችግር ሌሎችንም የአገሪቱን ክልሎች የሚያጠፋ መሆኑን እኔ በበኩሌ እጋራዋለሁ፡፡ስለዚህ ይሄን የምንመኘው ነገር አይደለም፡፡ ለሀገሪቱን መልካምና በጎ የሆነ ሰላም፣ መልካም ኑሮ፣ ለሃገራችንም ደግሞ አንድነትና ከዚህ በፊት ይዘን የመጣነውን በጋራ ማንኘት፣ በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ አንድነታችንን አዳብረን ሁላችንም እንደሀገርና እንደህዝብ የምንቀጥልበት መንገድ ቢኖር ነው በአሁን ጊዜ የምንመኘውና የምናጠው፡፡የምንታገለውም ለዚሁ ነው፡፡ መንግስትንም የምናስጠነቅቀው ለዚሁ ነው፡፡ ህዝቡም ደግሞ ወደኋላ ነገር ሳይሄድ ብሶቱንና ተቃውሞውን በሰላማዊ መንገድ ብቻ እንዲገልጽ የምናበረታታውም ለዚሁ ነው፡፡ ህዝቡም በየቦታው በሰላም እየወጣ ወደ ቤቱ የሚመለሰው በዚህ ምክንያት ነው፡፡

**ይሆን የኦሮሞ ህዝብ ንቅናቄ፣ የሌላው ብሔር ተወላጅ በምን መልኩ ሊረዳው ይገባል ይላሉ? ለሌላው የሚያስተላልፉ ጥሪስ አለ ...**

አሁን በአንዳንድ ቦታዎች ላይ፣ ለምሳሌ፣ የሌላውን ብሔር ተወላጆች ሃገሬው እየጠራ፣ መቃወሚያ እየሰጡ፣ <<እንደዚህ አድርጉ፣ እንደዚህ በሉ>> የኦሮሞ ተወላጆች ላይ ለማንሳሳት የሚያደርጉት ጥረት አለ፡፡ ነገር ግን፣ አንዳንድ ቦታ የምንሰማው፣ ህዝቡ ይህንን የማይቀበል መሆኑን በግልጽ እየገለጹ፣ ነው፡፡ይሄንን በእውነት እኛ በአድናቆት እና በትልቅ ክብር ነው የምንመለከተው፡፡ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ያሉ የማናቸውም ብሔር ተወላጆች፣ ከማንም አርሞ ባላነሰ መብታቸውን እንዲጠቀሙና እንዲከበርላቸው፣ የመዘዋወር፣ ሀብት የማፍራት፣ የመኖር፣ ስራ የመስራት መብታቸውም እንዲከበርላቸው የምናስበው ለፖለቲካ ፍጆታ ሳይሆን ከልባችን በማመን ነው፡፡

ስለዚህ በመሬዎች ለሀተትና ወትዋችነት ህዝቡ ወዳልተፈለገ ግጭት እንዳይሄድ አበክረን እንገልጻለን፡፡ መሪዎች ይመጣሉ፣ ይሄዳሉ፡፡አንደዚህ ይመጣል ያልፋል፡፡ ህዝቦች ግን እንድ ላይ ይኖራሉ፣ ወደፊትም አብረው ይቀጥላሉ፡፡ስለዚህ ለልጆቻችን የማይሆን ዓለም ትተን እንዳንሄድ፣ ቁርሾ በመካከላችን ጥለን እንዳንሄድ፣ በመተሳሰብ፣ በመከባበር እና ያለንን ደግሞ ተካፍለን ፍትሃዊ የሆነ የሀብት ክፍፍል አድርገን፣ መልካም የሆነ አስተዳደር ራሳችን በምንመርጠው መንግሥት አማካኝነት መንግስት መስርተን በጋራ አብረን የምናርበት ነገር ላይ ማተኮር አለብን፡፡

በመሰል ነገሮች ውስጥም <<አንዱ እንደዚህ ነው፣ ሌላው እንደዚህ ነው>> ብሎ በጅምላ የመፈረጅና የመሰየየት፣ በስፋ የመተያየትና የመተጣጣት ነገር እንዳይኖር ሁሉጊዜ ይሄን ማስብና ወደፊት ማዋት እንዳለብን፣ ግጭት ውስጥ እንዳንገባም ጥንቃቄ እንድናደርግ መምከር እንዳለብን መናገር እፈልጋለሁ፡፡

**አሁን ካሉት ጋራም ሊያያዝ የሚችልና እንደማጠቃለያም ልንወስደው የምንችለው፤ አሁን በተለያየ አካባቢ ህዝብ በፊት ተነስቶት ነገሮችን አያከናወነና ትግሉን እያካሄደ ነው፡፡በዚህ መሀል ንብረቶች፣ ወጣቶች፣ ሀገናትና ነፍሰ-ጡር ሴት ጭምር ተገድለዋል፡፡ ለአካል ጉዳተኝነት የተዳረጉም ብዙ እንዳሉ የተለያዩ ሰሚል ሚዲያ ላይ የምናያቸው ነገሮች አሉና በእነዚህ ጉዳዮችስ ፓርቲያችሁ ምን አይነት አቋም ይወስዳል? እነዚህ የኦሮሞ ህዝብ ላይ ጉዳት ያደረሱ የአገዛዙ መሳሪያዎች በህግ አግባብ ሊጠየቁ አይገባም ወይ? የሚሰውንና ህዝቡስ አሁን ላይ መሪ ከማጣት እየወሰደ ያለውን እርምጃስ በምን መልክ ነው የምትረዱት?**

እኛ አሁን የህዝቡን ታጋሽነት በጣም አድርገን እናደንቃለን፡፡ ህዝቡ እየተከላከለበት በሰላማዊ መንገድ እየታገለ ነው፡፡ አንዳንድ ቦታዎች <<እንፈልጋችሁም>> ብለው የራሳቸውን አስተዳደር እየመሰረቱ ነው፡፡ ራሳቸው በመረጧቸው ሽማግሌዎች መተዳደር የጀመሩበት አንዳንድ ቦታዎች እንዳሉም ይሰማል፡፡ በሌሎች ቦታዎች ደግሞ ሌላ ነገር ሊከተል ይችል ይሆናል፡፡ ዋናው ነገርና ጥሩ ነው ብዬ የምለው፣ እስካሁን ድረስ በብሔር ብሔረሰቦች መካከል የተፈጠረ ችግር የለም፡፡ ወደፊት ደግሞ <<ወደዚህ ችግር ያመራል>> ተብሎ የሚታሰብ ስጋት እስካሁን አልታየም፡፡ ይሄ መሆኑ ጥሩ ነው፡፡ በሌላ በኩል ይህንን ችግር ያስከተሉ ሰዎች፣ ህጻናትን የገደሉ ሰዎች፣ ንብረት ያጠፉ ሰዎች ወይንም ደግሞ ይህንን ስርዓት በመደገፍ በሰዎች ላይ ግፍ የሚፈጽሙ ሰዎች በህግ ፊት መቅረብ እንዳለባቸው እናምናለን፡፡ ህግ ፊት መቅረብ አለባቸው፡፡ ይሄ ማንንም ዘር ወይም የፖለቲካ ድርጅት የሚመለከት ሳይሆን ማንም በማለስብ ደረጃም ቢሆን በህዝብ ላይ ወይም በሰው ላይ ጥቃት የፈፀመ ወይም የሰው ነፍስ ያጠፋ ሰው በህግ አግባብ መታየት እንዳለበት እናስባለን፣ እንናገራለንም፡፡

በዚህ አጋጣሚ ግን በመከላከያ ሰራዊት፣ በፖሊስ ሰራዊትና በደህንነት ውስጥ ያሉ ወንድሞቻችን ቆም ብለው እንዲያስቡ፣ ከመግደል እንዲታቀቡና ማንም መብቱን ከመጠየቅ ወደ ኋላ ከማለት እንደማይቀር እንዲያውቁ እፈልጋለሁ፡፡ህዝቡ የጠየቀው ሌላ ሳይሆን መብቱን ነው፡፡ የሚሞተው ደሃው ህዝብ ነው፣ እየገደለ ያለው ደግሞ ከደሃ አብራክ የተገኘ ፖሊስና ወታደር ነው፡፡እናም <<እባካችሁ! ወንድሞቻችሁን አትግደሉ፣ ራሳችሁ እየተራባችሁ ለእናንተም ጭምር እየታገለ ያለን ህዝብ አትግደሉ! እጃችሁንም ኢታቆሽሹ! ቢታሪክም ራሳችሁን ተወቃሽ አታድርጉ! እባካችሁ እጃችሁን ሰብስቡ! በሰላማዊው ህዝብ ላይ ጠብመንጃችሁን አታዙሩ፣ ይህንን ህዝብ አትግፉ! ወደፊት ቢታሪክ ተጠያቂ እንዳትሆኑ አሁኑኑ ትዕዛዞቻችሁን እርምጃ ወስዱ!>> የሚል መልዕክት ልናስተላልፍላቸው እንወዳለን፡፡

**ከዚህ ቀውስ ለመውጣት መፍትሄ ብለው የሚሰጡት ነገር ምንድን ነው? በተጨማሪ ደግሞ በዚህ ስርዓት ውስጥስ መፍትሄ ሊመጣ ይችላል ብለው ያስባሉ?**

ሥርዓቱ እጅግ በጣም የደከመ፣ ራሱንም እንደገና እንደሥርዓት ማቆም የሚችልበት ደረጃ ላይ ያለ አይደለም፡፡ በጣም ያረጀ ሥርዓት ነው፡፡ የተፈበረከው ግፍና በደል እጅግ በጣም ብዙ ነው፡፡ ምናልባት የፖለቲካ ፓርቲዎችና ሀገሬቸውን የሚወዱ በውጭም በሀገር ውስጥም ያሉ ሰዎች አንድ የሽግግር መንግስት ሊያቋቁሙ የሚችሉበት ሁኔታ መታሰብ ያለበት ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም አሁን ያለው ሁኔታ ራሳቸው ሊያስተዳድሩ የሚችሉበት ሁኔታ ሆኖ አይታይም፡፡ ህዝቡንም እንደምታየው ከሆነ፣ እምነት ኖሮት በዚህ መንግስት ስር ለመተዳደር ፍቃደኛ የሆነ አይመስለኝም፡፡ ነገር ግን፣ ይሄን ሁሉ እያችሉ፣ ይሄ ሀገር ወደ ቀውስ ሳይገባና ሌላ ችግር ሳይከሰት ምናልባት አንድ የሽግግር መንግስት ቢቋቋም መልካም ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ ይህም ችግሮችን የሚፈታ ይመስለኛል፡፡

**የማስተር ፕላኑ ጉዳይ ተግባራዊ እንዳይሆን ምን መደረግ አለበት ብለው ነው የሚያስቡት?**

ማስተር ፕላኑማ አሁኑኑ ነው መቆም ያለበት፡፡ ለኦሮሚያና በተለይ አሁን ዋናኛ ጥያቄ ለሆነው ጉዳይ፣ እኛም እንደ ፓርቲ፣ እኔም እንደአንድ የኦሮሞ ተወላጅ፣ መናገር የምፈልገው ነገር ቢኖር፣ ማስተር ፕላኑ መቆም እንዳለበት ነው፡፡ የማስተር ፕላኑ ትግበራ መቆም አለበት፡፡በኦሮሚያ እና በአዲስ አበባ መካከል ትናንት እና በሽግግር ወቅት የነበረው ድንበር በትክክል ወደዚያ ድንበር መመለስ አለበት፡፡ ከዚያ በኋላ የተሰሩ ማናቸውም ግንባታዎች በኦሮሚያ አስተዳደር ክልል ውስጥ መሆን አለባቸው፡፡ ይህ ካልሆነ ህዝቡ ተቃውሞውን እስከመጨረሻው የሚያቆመው አይሆንም፣ እኛም እንዲያቆሙ አናበረታታም፡ ስለዚህ ዋናው ነገር፣ ማስተር ፕላኑ አሁኑኑ መቆም እንዳለበት ነው የኛ እምነት፡፡መንግስት ይህንን እተገበራለሁ ብሎ የሚቀጥል ከሆነ የህዝቡን አመፅና የህዝቡን መነሳሳት ወይም በሰላማዊ መንገድ ተቃውሞውን እንዲቀጥል መንገድ መክፈት ብቻ ነው የሚመስለኝ እኔ፡፡

**ስለዚህ በዚህ የተነሳ የፌደራል ሥርዓቱ እየተናደ ነው ማለት እንችላለን?**

የፌደራል ስርዓቱማ እየተናደ ሳይሆን በትክክል ...በትክክል ንደውታል፡፡ እንዱ በተለይ የፌደራል መንግስት የራሱ መሬት የለውም፡፡ ራሱ በሌለው መሬት ላይ ደግሞ ሊያቅድ አይችልም፡፡ አሁን ግን ይሄ መንግስት ራሱ ቀበሌ ድረስ ያለውን ነገር ራሱ አቅዶ ይሰጣል፡፡ ይሄ ሊሆን አይችልም፡፡ እንደዚህ ከሆነ <<ራስን በራስ ማስተዳደር>> የሚባል ነገር የታለ?! እራሱ የማያቅድ ከሆነ፣ እራሱ ግብር የማይሰበስብ ከሆነ፣ እራሱ የማያዝንል ከሆነ፣ መሪዎቹን ራሱ የማይሾም የማይሽር ከሆነ፣ ምኑ ነው ፌደራል መንግስት ተብሎ የሚጠራው?! ስለዚህ ፌደራሊዝሙን ካፈረሱትኮ ቆይተዋል፡፡ እኛ የኦሮሞ ፌደራሊስት ኮንግረስ፣ ትክክለኛ የሆነ የፌደራሊዝም ህዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩበት፣ ነገር ግን በጋራ ደግሞ አንድ ትልቅ ሀገር መስርተው በሰላም የሚኖሩበት ሥርዓት እንዲፈጠር ነው የመጨረሻ ትግላችን፡፡

**ለችግሩ መነሻ የአህዴድ ሚና እንዴት ነው የሚታየው? አህዴድስ ለክልሉ ወይስ ለህወሃት ወግኗል ማለት እንችላለን?**

አህዴድ ችግር ሊሆን የሚችል ድርጅት አይደለም፡፡ ችግሩን የሚያስከትል ድርጅት አለ፡፡ አህዴድ ምን እንደሚታሰብ እና ምን እንደሚታቀድ የማያውቅ ድርጅት ነው፡፡ የሆነ ቦታ ይታሰባል፣ ይታቀዳል፣ ይመከራል፣ ይወሰናል ከዚያ በኋላም <<ተግብሩት!>> ይባላል፡፡ ከዚያ በኋላ <<በዚህ መንገድ ስሩት!>> ተብሉ ይነገረዋል፣ በዚያ መሰረት ይሰራል፡፡ ስለዚህ ይሄ ድርጅት ችግር ፈጣሪ ተብሎ ሊወሰድ የሚችል አይደለም፡፡ <<ስራ>> የተባለውን የሚሰራ ድርጅት ነው፡፡ ቁጭ ብሉ የተቀመጠ፣ ማንንም ሊወክል የማይችል፣ በራሱ ማንምንውን እንኳ ማስከበር የማይችል ድርጅት ስለሆነ እኛ ችግር ፈጣሪም አድርገን አንቆጥረውም፡፡

**እውነተኛ የፌደራል ስርዓት ሳይኖርስ ማስተር ፕላኑን መተግበር ቢቆም ለውጥ ይመጣል ብለው ያስባሉ?**

ለውጥ ላይመጣ ይችላል፡፡ ነገር ግን፣ እውነተኛ የፌደራል ስርዓት በሰላም፣ በፍቅርና በመግባባት የሚመጣ ነገር መሆኑ ይሰማኛል፡፡

**እኛ ጥያቄዎቻችንን ጨርሰናል፡፡ እርስዎ ቢጨመር የሚሉት ነገር ካለ ....**

እኔ ማስተላለፍ የምፈልገው መልዕክት ቢኖር፣ የተወሰኑ ኢትዮጵያውያን ስለዚህ ሀገር ህዝቦች ሁሉ፣ በአንድ በተወሰነ የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የሚደርሰውን ችግር፣ ምንም እንሱን እንደማያገባቸው አድርገው ወስደው፣ ዝምታን መርጠው፣ ቁጭ ብለው፣ ተመልካች ሆነው ያሉበት ሁኔታ እጅግ በጣም አሳዛኝ ነው፡፡ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ቢሆኑ ምንም ነገር እንዳልተደረገ፣ ምንም ነገር እንዳልሆነ፣ ነገሩ ምንም የማያገባቸው እንደሆነ ሁሉ፣ ዝም ብለው ዝምታን መርጠው ቁጭ ማለታቸው ራሳቸውንም ትዝብት ላይ ይጥላቸዋል፡፡ በፖለቲካ በመጀመሪያ የተነሱበትን ዓላማ የሚያስንስባቸው ሆኖ ነው የሚታየው፡፡ ስለዚህ በሀገሩ ውስጥ የሚታየውን ዝምታ እኔ በበኑ አልመለከተውም፡፡ በምሁራን ዘንድ ያለው ዝምታ በጣም አስፈሪ ነው፡፡

አንዱ ፈላስፋ እንደተናገረው፣ አያንዳንዱ ሰው ለሚናገረው ነገር የሚጠየቀውን ያህል ባለመናገሩም ደግሞ ያን ያህል ተጠያቂ ይሆናል፡፡ አለመናገር አደገኛ የሆነ፣ መንግስትን የልብ ልብ ሰጥቶ እዚህ ያደረሰ ሲሆን በተለይ በኢትዮጵያ ምሁራን ዘንድ በጣም የአድርባይነት መንፈስ አለ፡፡ ስለዚህ ይሄ ሊቀረፍ ይገባል፡፡ በኃይማኖት ተቋማትም ያለው ዝምታና ከዚህ መንግስት ጋር አንዳንድ ጊዜ የማበር ያህል በራሴ እየሰጡ የሚገኙ ኃይማኖተኞች ጭምር <<ይሄ ነገር ተገቢ አይደለም፣ አይገባም፣ ህዝብ እየተበደለ ነው፡፡ እባካዱ ሊስተካከል ይገባል>> ብለው አለማለታቸው የኃይማኖት ተቋማቱን ትዝብት ላይ የሚጥላቸውና ተጠያቂ የሚያደርጋቸው መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

ህዝብ <<አንድ ቀን ተምረው ለመብታችን ይከራከሩልናል>> ብሎ የሚልባቸው የተማሩ የተባሉ ምሁራን፣ በመንግስት ጉያ ውስጥ ገብተው ከመንግስት ጋር እየወገኑ፣ ሕዝብንና የህዝብ ልጆችን እየተበደሉ ዝምታን መምረጣቸው፣ እውነታን አለመጋፋታቸው፣ አለመናገራቸውና አለመዘገባቸው በታሪክ እንደሚያስጠይቃቸው አውቀው አሁኑኑ እርምጃ መውሰድ መጀመር አለባቸው፡፡ ስለዚህ ስለሀገር ጉዳይ <<ያገባናል!>> የሚሉ ምሁራን አሁን ላይ መፈጠር አለባቸው፡፡

ጋዜጠኞችም ደግሞ እውነት ላይ ቆመው፣ ለማንም ሳይሆን በእውነት ለሰው ልጆች መብት መከበር ተቆርቋሪነታቸውን ማሳየት እንደሚኖርባቸው፣ ከወገናዊነት በጸዳ መልኩ የጋዜጠኝነት ሥነ-ምግባርን ጠብቀው ለህዝቡ አስተያየት ማቅረብ እንዳለባቸው ማሳሰብ እፈልጋለሁ፡፡ ...በመጨረሻም፣ እናንተ ስለሰጣችሁኝ እድል በጣም አመሰግናለሁ፡፡

**እኛም እናመሰግናለን፡፡**





## ዜና

## አነበፍቃዱ ኃይሉ ለጥር 27 ተቀጠሩ

በፌደራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ከተመሰረተባቸው የሽብርተኝነት ክስ በነፃ የተሰናበቱት ጦማሪ አጥናፍ ብርሃኔ፣ ናትናኤል ፈለቀ፣ አቤል ዋበላና በከፍተኛ ፍ/ቤት ክሱን እየተከታተለ የሚገኘው አቶ በፍቃዱ ኃይሉ ረቡዕ ታህሳስ 20 ቀን 2008 ዓ.ም በፌደራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ቀረቡ፡፡

ፍ/ቤቱ መዝገቡን ለታህሳስ 20 ቀን 2008 ዓ.ም ቀጥሮት የነበረው በአቃቤ ሕግና በተከሳሾቹ በኩል የሚደረገውን የቃል ክርክር ለመስማት ነበር፡፡ በዕለቱ አራቱም ጦማሪያን በፍ/ቤት የተገኙ ሲሆን፣ በሌለችበት በስር ፍ/ቤቱ በነፃ የተሰናበተችው ወ/ሪት ሶልያና ሽመልስን በሚመለከት አቃቤ ሕግ <<ፖሊስ ሊያገኛት አልቻለም>> ሲል ከፍ/ቤቱ ለተነሳለት ጥያቄ ምላሽ ሠጥቷል፡፡ ጦማሪ ናትናኤል ፈለቀ ፍ/ቤቱን ተዘጋጅተው ለመቅረብ ተለዋጭ ቀጠሮ እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል፡፡ ናትናኤል፣ <<ሁለቱ ጓደኞቼ መጥሪያው በጭራሽ አልደረሳቸውም፡፡ እኔም መጥሪያው የደረሰኝ ትላንት ነው፡፡>> ሲል ተደምጧል፡፡

ከተከሳሾቹ መሃል ጦማሪ አጥናፍ ብርሃኔ እና አቤል ዋበላ መጥሪያው እንዳልደረሳቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ በፌደራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ክሱን እንዲከላከል ብይን የተሰጠው ጋዜጠኛ እና ጦማሪ በፍቃዱ ኃይሉ በዚህ መዝገብ ሥር የቃል ክርክር እንዲያደርግ ተጠርቷል፡፡ ይህን በማስመልከት የተከሳሹ ተከላካይ ጠበቃ የሆኑት አቶ አምሃ መኮንን፣ የበፍቃዱ ኃይሉ በዚህ መዝገብ እንዲጠራ መደረጉን በሚመለከት <<ሥነ-ሥርዓታዊ አይደለም!>> ሲሉ ለ<<አዲስ-ገጽ>> ገልጸዋል፡፡

የፌደራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በተከሳሾቹና በአቃቤ ሕግ መሃል የሚደረገውን የቃል ክርክር ለመስማት ተለዋጭ ቀጠሮ ለጥር 27 ቀን 2008 ዓ.ም ሰጥቷል፡፡

## ኤልያስ ገብሩና አምሳሉ ገ/ኪዳን ለየካቲት 18 ተቀጠሩ

በመጋቢት 2006 ዓ.ም በዕንቁ መፅሔት ላይ በመፅሔቷ አምደኛ ሀሣሲ አምሳሉ ገብረኪዳን <<በመንግስት ላይ ያሉ ሐውልቶች የነማንና ለእነማንና ናቸው?>> በሚል ርዕስ ተዘጋጅቶ የቀረበውን ስሁፍ ተከትሎ <<በሀገሪቷ ሕዝቦች መካከል ፀብና ቁርሾ እንዲፈጠር ግጭፍ ያልሆነ የማነሳሳት ተግባር>> የሚል ክስ የቀረበባቸው 1ኛ ተከሳሽ ጋዜጠኛ ኤልያስ ገብሩና 2ኛ ተከሳሽ ሀሣሲ አምሳሉ ገብረኪዳን ሰኞ ታሕሳስ 18 ቀን 2008 ዓ.ም ሰባራ ባቡር በሚገኘው የፌደራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አራዳ ምድብ ችሎት ለ14ኛ ጊዜ ቀረቡ፡፡

ፍ/ቤቱ መዝገቡን ለታህሳስ 18 ቀን 2008 ዓ.ም የቀጠረው የተከሳሾቹን መከላከያ ምስክሮች ለማድመጥ የነበረ ቢሆንም፣ ተከሳሾቹ ጠበቃቸው የነበሩት አቶ ተማም አባቡልጉ የጥብቅና ፍቃድ መታገዱንና አግዱ እንዲነሣላቸው ያቀረቡት ደግሞኝ አለመታየቱን ጠቁመን፣ ጠበቃ ለማቆም ጊዜ ስለሚያስፈልጋቸው እንዲሁም መከላከያ ምስክሮቻቸውን አሟልተው ለማቅረብ ተለዋጭ ቀጠሮ እንዲሰጣቸው ፍ/ቤቱን ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱ የተከሳሾችን መከላከያ ምስክሮች ለማድመጥ ተለዋጭ ቀጠሮ ለየካቲት 18 ቀን 2008 ዓ.ም ሰጥቷል፡፡ በማረሚያ ቤት ለሚገኙ የተከሳሾቹ መከላከያ ምስክሮች መጥሪያ እንደሚሰጥ ፍ/ቤቱ ገልጿል፡፡

ጋዜጠኛ ኤልያስ ገብሩ 12 መከላከያ ምስክሮች ማዘጋጀታቸውን ለ<<አዲስ-ገፅ>> ገልጿል፡፡ ከምስክሮቹ መካከልም ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማርያም፣ ጠበቃ ተማም አባቡልጉ፣ አቶ ፍቃዱ ማኅተመወርቅ፣ ጋዜጠኛ ተመስገን ደሣለኝ፣ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋና ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬ እንደሚገኙበት ጋዜጠኛው አስረድቷል፡፡ ሰዓሊ አምሳሉ ገብረኪዳን በበኩሉ ስድስት ያህል የታሪክ ባለሙያዎችን ለምስክርነት አዘጋጅቷል፡፡ በአምሳሉ ለምስክርነት የተጠሩት፣ ፕ/ር ባሕሩ ዘውዴ፣ አቶ አበባው አያሌው ፣ ፕሮፌሰር ሽፈራው ደሳለኝና ዶ/ር ውዱ ጣፈጠ ይገኙበታል፡፡

የፌደራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አራዳ ምድብ ችሎት ጥቅምት 29 ቀን 2008 ዓ.ም ጋዜጠኛ ኤልያስ ገብሩና ሀሣሲ አምሳሉ ገብረኪዳንን የቀረበባቸውን ክስ እንዲከላከሉ ብይን ማስተላለፉ ይታወሳል፡፡

# የራስ መድኃኒት ሸጦ፤ የራስ በሽታ መግዛት



ጀርብ ቾርታው

ከወዳጄ ጋር ሻይ ቡና ለማለት አንድ ሻይ ቤት ጎራ ብለናል። እኔ ምፈልገውን አገባር እንዲያዝ ጋብዘሁት። «ሻይ ይሁንልኝ!» አለ ወዳጄ። «ሌላ ነገር ወሰድ እንጂ!?» አልኩት። «ምን ልውሰድ?» ሲለኝ፤ «ወተት፤ ማኪያቶ፤ ለውዝ…» እያልኩ ዘረዘርኩ። እርሱም ቀበል አድርጎ፤ «አይ! እኔኮ ወተት አልወድም!» አለኝ። «እንዴ! ያውም ገበሬ፤ ኢትዮጵያ ተወልደህ? ግን ይሁን እሺ፤ ሌላ ነገር ጠጣ። አልኩለ? ምናልባት የሐበሻ አረቄ?» አልኩት። ፈጠን ብሎ፤ «እሱን እንኳ እሺ - ብጠጣሁ!» አለኝ። «አረቄ» ያልኩት ለቀልድ ያህል እንጂ እውነት ካፊው አረቄ የሚሸጥበት ሆኖ አይደለም፤ በኋላ ማኪያቶውን እንዲያግዛው እንዲያግዘው አዘባውት።

ከላይ እንደ መግቢያ የጫጨርኳትን ምልልስ ማቅረቤ ለጽሑፌ መነሻ ፍንጭ ያገኝሁበት ስለሆንችኝ እንጂ፤ ብዙ ወግ ልጠርቅላችሁ ፈልጌ አይደለም። እና፤ አስተናጋጁ ትእዛዛችንን ተቀብሎ ከሄደ በኋላ፤ ከወዳጄ ጋር አንድ ቃል ሳንለዋወጥ ለደቂቃዎች ቆየን። በሰዓቱ የማብሰለስለው ስለሀገሬ ነበር፤ ሐሳቤ አገራዊትን አጫረብኝ። ለምን?

እንደ እኔ፤ እየኖርን ያለነው «የራስ መድኃኒት ሸጦ፤ የራስ በሽታ በመግዛት ነው። ለገበያ ስለሚቀርቡ ምርቶች አለማለሉ፤ በእኛ ልእኛ የተሰሩ ምርቶችን እናጣጥልና ብእውሮፓ ስታንዳርድ የተሰሩት የተባሉ እቃዎችን በውድ ዋጋ ለመግዛት በምገዛያው እንሽለፍለን። እኛ አውሮፓውያን አይደለን! የአውሮፓ ደረጃ የለን! ታዲያ ስለምን ለእኛ በእኛ የተሰሩ፤ የተሰሩቱ ምርቶችን አንሸምትም ቢባል ምላሹ «ከራስ መድኃኒት ይልቅ የሰው በሽታ ይበልጣል» ላይሆን ይቀራል!?

በሀገራችን ለሀገራቸው ከምቱት ጦሊ ቴዎድሮስ ይልቅ፤ የማያውቁ ጀኔራል ናፒየር በደንብ ይታወቃል። በማይጨው ጦርነት እንደ ቶሎ ከረገፉት ወድ የኢትዮጵያ ልጆች፤ ጦርነቱን ከመሩ ራሶች፤ ፊታውራሪዎች፤ ደጃዝማቾች… ይልቅ የእንግሊዝ ጀኔራሎች በደንብ ይታወቃሉ። ከአርበኞች ይልቅ ባንዳዎች በደንብ ይታወቃሉ። ታዲያ ይህ «የራስ መድኃኒት ሸጦ፤ የራስ በሽታ መግዛት» ካልተባለ ምን ሊባል ይችላል?

በኢትዮጵያ ላይ የአውሮፓውያንን የአስተዳደር ሥርዓቶች ለመትከል የሚሮነውን ያህል (ያውም እንደ ወረደ)፤ የሩሲያን ማርክሲዝም-ሌኒኒዝም ምድሪቱ ላይ ለመጫን የታገልነውን ያህል፤ የአሜሪካን ካፒታሊዝም ግላቶችን ውስጥ ለማስረጽ የታገልነውን ያህል፤ የቻይናን ፖሊቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አስተሳሰብ የእኛ አፈር ላይ ‹እንዲያብብ› የታገልነውንና እየታገልን ያለነውን ያህል፤ ለሀገራችን - ለኢትዮጵያ - የገዳ ሥርዓት ምን ሠራን? ምንም። ለእኛ ያልተዘጋጀ፤ በእኛ ልክ ያልተሰፋ፤ የሀገራችንን ትምህርት፤ ባህል፤ እምነት፤ አስተሳሰብ… ‹የማያውቁ› ሥርዓቶችንና አመለካከቶችን - እስከ ቅርፊታቸው - እናመጣና እዚህ እንዲተከሉ ሀገር እንሸጣለን፤ ለቅርፊቶቹም ክቡር የሆነውን የሰው ልጅ ሕይወት እንገብራለን፤ ገበርናል፤ እርስ በርስ ተፋርደናል፤ ወንድም ወንድሙን ገድሎ እናቱን ‹ልጆቸን ገደልኩልሽ! እልል በይ!› ይላል። ለሰው የተዘጋጀ ካባሰለትን ብለን ማንነታችንን፤ ባህላችንን አጥተናል። ታዲያ ይህ ‹የራስ መድኃኒት ሸጦ፤ የራስ በሽታ መግዛት› አይደለምን?

ከቅዱስ ያሬድ ውልደት፤ ትምህርት፤ ሥራ… ከማውራት ይልቅ፤ ስለ ሞዛርት፤ ቤትሆቨን ውልደት፤ ሥራ፤ ትዳር … ተዘርዝሮ ይነገረናል። ስለ ዘርአ ያዕቆብ፤ የዘርአ ያዕቆብ ተማሪ ወልደ ኢትዮጵያዊ የሕይወት ታሪክ፤ ፍልስፍና… እንዴው በትንሹም ቢሆን ከማስተማር ይልቅ፤ ስለ አውሮፓውያን ፈላስፎች ፍልስፍና እጅግ ዝርዝር ነገር ያስተምሩናል። በሁለተኛ የትምህርት ተቋማት ውስጥ (በውጭ ቋንቋዎች ትምህርት ክፍል) ፈረንሳይኛ፤ እንግሊዝኛ፤ ጀርመንኛ፤ ጣሊያንኛ፤ ዐረብኛ (በቅርቡ ማንዳሪን!?) ከመጀመሪያ እስከ ዶክትሬት ዲግሪ ድረስ ይሰጣል። ወደ እኛው ግዕዝ የመጣን እንደሆነ፤ ምን አለፋችሁ - ዝም-ጭጭ ብሎ ይሸለፋል። በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ተዉት! ከቤተ-ክህነትም ሊጠፋ የተቃረበ! የተቃረበ እየመሰለኝ ነው! እንግዲህ ‹የራስ መድኃኒት ሸጦ፤ የራስ በሽታ መግዛት› ከዚህ በላይ ምን አለ?

እንዲህ አባቢ ሆኖብን እንጂ፤ የእኛ ግዕዝ ከማን - ከየትኛው ቋንቋ - ያንሳል? ከማንም አያንስም! ለምን ጀርመኖች አይመስክሩም! በአገራቸው የኛኑ ግዕዝ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ያስተምሩታል!

እንዴው በዚህ ላይ ለማከልና ለመጠየቅ ያህል፤ የንሰም ሥልጣኔ ሲነሣ አውሮፓውያኑ ግሪክና ሮም ይጠቀሳሉ። የአፍሪካም ሲነሣ ኢትዮጵያ እና ግብጽ አሉ። ግን አሁን እያስተማርን ያለነው የእኛን የሥልጣኔ ዘመን ያቀፈ ነው? እዚህ ጋር ማንሣት አስፈላጊ ላይሆን ይችላል፤ ግን ባሳው ‹የራስ መድኃኒት ሸጦ፤ የራስ በሽታ መግዛት› አባዜያችን የት እንደ ደረሰ ማሳያ ይሆንልናል።

በ7ኛ ክፍል የማኅበራዊ ሳይንስ ትምህርት ላይ ስለ ጥንታዊ የአፍሪካ ሥልጣኔ የሚያወሳ ርዕስ አለ። ከርዕሱ ሥር ስለ ግብጽ፤ ሱዳን፤ ማሊ፤ ዚምባብዌ ወዘተ. የሚያወሱ ጽሑፍ አለ። ግን ስለ ጥንታዊት ኢትዮጵያ የሚያወራ አንድም ነገር የለም። ይህ ብቻ አይደለም፤ 8ኛ ክፍል ማኅበራዊ ሳይንስ ትምህርት ላይ ስለ ዓለም ሥልጣኔ ዝርዝር ጉዳይ ያወራና ስለ ኢትዮጵያ ጥንታዊም ሆነ ዘመናዊ ታሪክ ምንም የሚነግረን ነገር የለም። እንግዲያስ? ስለሀገሩ የማያውቅ፤ የራስ መድኃኒት የተሸጠበትና የራስ በሽታ የተገዛበት የ16/17 ዓመት የዘመናዊ ክፍል ተማሪ አፈራን ማለት አይደል?

ተማሪዎች ስለአፍሪካ አንድነት ድርጅት አመሠራረት ያውቃሉ። የቀድሞዎቹም ያውቃሉ። አሁን እኛ እያስተማርን ያለነው ግን ለምን ተመሠረተ የሚለውን ነው። ይሁን፤ እሱም ጥሩ ነው። ግን ዐፄ ኃይለሥላሴ የነበራቸውን የመሥራችነት ሚና ትኩረት ሰጥቷል? ይልቅ በደንብ የሚያወሳው ድርጅቱ ግዜረት ሲሆን የድርሻቸውን ስለተወጡትና የጎበረቱን መቀመጫ ወደ ሀገራቸው ለመውሰድ ስለጣሩት የቀድሞ የሊቢያ ፕሬዚዳንት ሙሐመድ ጋዳፊ ሚና ነው። ወገኖቼ! ታዲያ ይህ ‹የራስ መድኃኒት ሸጦ፤ የራስ በሽታ መግዛት› አይደለምን?!

በመጨረሻ፤ የራስን አውርዶ የሌላን መስቀል፤ የራስን አዋርዶ የሌላን ማክበር፤ የራስን መቃብር አዋርዶፋ የሌላን ማማ ላይ መስቀል ያዋርዳል። ያስንቃል። ክብር ያሳጣል። የራስ መድኃኒት እንጂ የራስ በሽታ ቤሊደት ያጠፋል። ማንነትን ያሳጣል። ምድብ የሌለው ጎራ ውስጥ ይከተናል። የራስ መድኃኒት ሸጦ፤ የራስ በሽታ ከመግዛት ቢታቸሁ ይበለን። አሜን! አሜን!

## የፖለቲካ ለውጥ……..

ከገፅ 18 የዞረ

ልጅ ከሌሎች ፍጥረታት ጋር ያለው ግንኙነት አከል ነው። ያልታወቁ በራሪ አካላትን (Unidentified Flying Objects - UFOs) በተመለከተ የአሜሪካን መንግሥትና ሌሎችም ኃያላን መንግሥታት የሚያራምዱት አቋም፤ የቢሁ ፖለቲካ አካል ነው። በሀገራችንም ቢሆን፤ የሥጋወ-እግዚአብሔርነት አስተሳሰብ እና የፖለቲካ አካሄድ የቢሁ ክፍል መገለጫ ነው። «እግዚአብሔር መንግሥትን ይሠይማል ወይም ይሽማል!» ተብሎ መታመኑ አሁንም ቢሆን ጨርሶ አልጠፋም።

ለመሆኑ «መንግሥት» ማለት ምንድነው? ከየትስ መጣ? ይኸን ጥያቄ የምንመልሰው ወደን አይደለም። «መንግሥት ማለት፤ ማኅበራዊ ኑሮን በሰላይነት እንዲመራ የተዘጋጀ/የተቋቋመ አካል ነው።» ብለው የሚገልጹ ሊቃውንት አሉ። በሌላ ወገል፤ መንግሥትን ከሰው ፍጥረት ጋር የተወሳሰበ ምስጢር ያለው ተቋም አድርገው የሚገልጹ ሊቃውንትም አልጠፉም። ከእነርሱም መካከል፤ የመጨረሻዎቹ ዘመን ጥናና ፈላስፎች ተጠቃሽ ናቸው። ሁለቱም መንገዶች በመንግሥትን አስፈላጊነት ይስማማሉ። ልዩነታቸው ያለው፤ «ማን ይምራ? ወይም ማን ፖለቲካኛ ይሁን?» የሚለው ጥያቄ ሲነሣ ነው። የማኅበራዊ ሊቃቹ፤ «ችሎታ ያለው ይምራ!» ወይም «ብልሕግበ የተመረጠ ይምራ!» ሲሉ፤ «መንግሥትነት ከፈጣሪ ጋር የተወሳሰበ ምስጢር አለው!» የሚሉት ደግሞ፤ «እግዚአብሔር የመረጠው ይምራ!» ይላሉ። ስለዚህም፤ በመሪዎቹ አሠያየም ላይ ይለያዩ እንጂ፤ «መንግሥት» በሚባለው ኃይሉ-አካል ላይ ይስማማሉ።

ሕዝብንና መንግሥትን የሚያቆራኝ አንድ ነገር አለ፤ እርሱም ሕግ ነው። «ምን ዓይነት ሕጎች ቢደነገጉ ሕዝቡን በፍትሐዊ አኳኋን ማስተዳደር ይቻላል?» የሚል ጥያቄም መነሣቱ አይቀሬ ነው። «የሕገ-ፍጥረቱ የተለያየ አስተሳሰብ እና ተግባራትን የሚከተለው ሰው፤ ለምን የመንግሥትንና የማኅበረሰቡን ሕጎች ያከብራል?» የሚለውም ጥያቄ መነሣቱ አይቀሬ ነው። ሕዝቡ ለሕጎቹ የሚገዛው፤ ከሌሎች መሠሎቹ ጋር ያለውን የጋራ ተጠቃሚነትና ዋስትና አስከብሮዩት (Social Contract) አስከተሰማው ድረስ ነው። ወይም ደግሞ፤ ከሰው ባሕሪይ-ፍጥረት ጋር እንደዚ የእግዚአብሔር ፈቃድ (Will of God) ስለሆነ ነው፤ ብሎ ከተቀበለ ብቻ ነው። አለበለዚያ ያምጻል። ፖለቲከኞቹ በሕግ የደነገጉበትን አለመቀበልም ብሎ ያምጻል። ያንንም የማድረግ ተፈጥሯዊ መብት እንዳለው ቢያውቅም፤ የፖለቲካ ምህዳሩ ግን አይፈቅድለትም። ሕዝቡ ግን የእንቢታን መንገድ ይከተላል። እንቢታዎቹም ከውስጥ ሲነሡ፤ የ‹ፖለቲካ ለውጥ› የሚቀንሱን ይዘትና ተፈጥሮም አላቸው።

አዋቢል አብሬን ማንሳት አለብን፤ እርሱም፤ «ጥሩ ሕጎች ከጥሩ መንግሥት ይወጣሉ፤ መጥፎ ሕጎችም የመጥፎ እና የመሠሪ መንግሥት ትዝብቶች ማሳያ ናቸው!» የሚለው ነው። መጥፎ መንግሥት፤ የዜጎችን የሀብትና ንብረት የማፍራት መብት ገድበሕቶ፤ ዜጎች በስቃ ድህነት ውስጥ እንዲኖሩ ያደርጋል። የክፉ መንግሥት ሹማምንት፤ «ዜጎች እየራባቸውና ጠኔ እያጠቃቸው ሲኖሩ፤ የክፉም መንግሥት ልድሜ ይረዝማል!» ተብሎ ስለሚታመን፤ መጥፎ-መጥፎ ሕጎች እንዲወጡ ሌት-ተቀን ይተጋሉ፤ የሚል ወገኖች በብዛት ይደመጣል።

አንድ ጭብጥ እናንሣ፤ ከላይ እንደ ገለጽነው፤ «ፖለቲካ፤ አጠቃላይ የፖለቲካን ፍልስፍና አሳቦችን እና ሕጎችን (Basic Philosophical Assumptions and General Laws) የሚይዝ ብቻ ሳይሆን፤ ስለ መንግሥት አቋም፤ ስለ ሕዝብ አስተዳደር ሥርዓትና ሕጎቹንም አጠቃልሎ ማስቀንና መረዳትን ይጠይቃል። ጥሩ ፖለቲከኛ ማለት በተሊዝነቶችን መስከት መጥፎ የሚያደብና የሚቃወማቸውን ሁሉ የሚያጣበሰርፍ ፍጡር አይደለም። የነገሮቹን የፍርድ ቤቶች አመራርና የቦዮታ ጓደኞቹንም አጠቃቀር ጭምር በንሥር ዐይናቹ የሚያይ መሆን አለበት። «ይህን መሠል ፖለቲከኞች ሆይ፤ ነ! ኢትዮጵያውያንንም አገልግሉ! የኢትዮጵያንም ሀገረ-መንግሥት ታደጉ» ብለ ጽሑፌን እቋጫለሁ።

ስለፖለቲካዊ ሕጎች በናገጣ አንድ የተለመደ

ከየእንቅመሰጡው ቸር ወሬ ያሰማን!

## የተረሳው መንገድ……..

ከገፅ 10 የዞረ

በስሜት ጥልቀትም ሆነ በድግግሞሽ ብዛት እያሻሻላችሁ እንድትቀጥሉበት በምታምኑት አምላክ ስም እማፀናችኋለሁ።

አንድ ሰው (ዜጋ) በደሉን መንግስት ወይም ሕዝብ ወይም ፈጣሪ ይበቀልለታል። መንግስት በዳይ ሲሆን ደግሞ ሕዝብ ወይም ፈጣሪ ይበቀልለታል። ሕዝብ የሚበቀለው በፈጣሪ አማኝ ከሆነ ለፈጣሪ በመንገርና ለቢያ ለተጎዳው ወገኑ ፍትሕ እንዲሰጠው ወይም በዳዩን እንዲቀኝለት ወይም በዚህ ረገድ የራሱንም ሚና እንዲያሳየው በመማፀንና በልቡናው በተነገረው (በታየው) መሠረት በመፈፀም ሲሆን ሌላው ደግሞ ከሕሊናው ተማክሮ ተገቢ ነው (ሰኔም/ሰማንም ቢሆን ይሻል) ያለውን መሠረት አድርጎ ለተበዳዩም ተመጣጣይ እንዲሆን በማገዝ (በማድረግ) ይሆናል። እነዚህን አንድ ላይ ወይም እያፈራረቀ እንደሁኔታውና ችሎታው በመንፈስም፤ በስሜትም፤ በአካልም፤ በሃሣብም፤ በድርጊትም፤ በቁስም፤ በሥነ-ልቡናም ከተበዳዩ ጋር በመቆምና በነዚህ ሁሉ መንገዶች ደግሞ በዳዩን በመፋለም ብቻ ነውና የፈለገው ሊሳካ የሚችለውና በዚህ መልኩ መፈፀም ይህንን ስሌት የፈለገ ሁሉ ግዴታው ይሆናል።

እስካሁን ያሳግብ የተበደሉትን ሁሉ እንዲክስ በዳዮችን ደግሞ በመሬት ላይ እንዲቀጡና ላደረጉት ሁሉ ተመጣጣኙን አግኝተው እንዲያሳያችሁ ፈጣሪያችሁን (የምታምኑበትን) ከዚህች ቅፅበት ጀምራችሁ መጠየቅ ጀምሩ፤ መፀለይ እንጀምር። ይህም የአጠቃላዩ ግብና አካሄድ አንድ አካል (በራሱ ምግብ) ሊሆን ይችላል። ፀሎታችንንም «ጌታዬ ሆይ በዚህች ሀገር ፍትሕ እንዲሠፍን፤ ሁሉም እንደእምነቱ አቋሙና ሃሣቡ ሆኖ እንዲበለፅግ፤ የሚሆንበትን አካባቢ ሕግና አስተዳደር አብጅልን፤ ወይም እንድናበጅ ልቦና ስጠን፤ ጭቆናን ቅበርልን፤ ወይም እንድንቀብር አብቃን፤ አንድነትን፤ ፍቅር፤ መተሳሰብና መተጋገዝ፤ እኩልነትና ነፃነትን ፍትሕን እንጂ ሌላ አትስጠን እስካሁን እንጂ ሌላ የማንቀበልና ይህንንም ሳናሟላ የማንመለስ አድርገን፤ ለሁላችንም በቋሚነትና በዘላቂነት በማይጠቅም ጉዳይና ድርጊት ላይ ወይም ይህንን ከሚያሳስ ወይም ከሚያሠናክል ወገን ጋር በፍፁም የማልሰለፍ አድርገኝ፤ ተሠልፈም ከሆነ ከዚህች ቅፅበት ጀምሮ እንድነጠል ብርታቱንና ጥንካሬውን ስጠኝ፤ ለሁሉም የሚጠቅመውን ወገን ብርታት ስጠው፤ ድርጊቱን ወይም ሁኔታውን ደግሞ በፍጥነት ከስተው ወይም እንዲከስት ለማገዝ የምችልበትን መንገድ አሣየኝ አቅምና ብርታት በሁለይም ፍላጎቱን አስድርብኝ። በዳዮችን አዳምጣቸው እንዲዳኙ፤ ለማድረግ የምችልበትን አቅምና መንገድ ብርታት አሣየኝ፤ የተጎዱትን ፍትህ፤ ብርታትና መፅናናትን ስጣቸው፤ ስጠኝ በሥልጣናቸው ተመክተው ንፁሓንን የጎዱትን ደግሞ ልቦና ስጣቸው፤ ካልሆነም ንፁሓንን እንዳይበድሉ መተባበርን አቅም፤ ሀብት፤ ሥልጣን፤ ወይም ሌላም ጉልበታቸውን፤ ምንሳቸውን፤ ስውቀታቸውን፤ ብልሃታቸውን ንሳቸው። ይህንን ለመፈፀምም ተገቢውን ሚናዬንና አስተዋፅኦዬን የምወጣና የማበረክት አድርገኝ። ምንም የማይሳነህ ጌታ አቅምም ብልሃትም፤ ብልጠትም፤ ችሎታም፤ ስልጣንም አለህና በምንሰህ ሕዝቡን (ደሃ) የሚበድሉትን፤ የሚያስለቅሱትን፤ የሚያፈናቅሉትን፤ ፍትሕ የሚያጓድሉትን፤ እውነትን የሚደብቁትን ለሚከዱትን፤ ሃገር፤ የሃገር ሃብትና ዕድልን ያለአድልኦ ለሁሉም እንዲሆን፤ የማያደርጉትን፤ በትዕቢት የተወጠሩትን፤ ትህትና የሌላቸውን ሁሉ አስተዳዳሪ እንዳይሆኑብን ከሆኑም እንዲከሱልን አድርግልን፤ ለዚህም ማበርከት ያለብኝን ተገቢውን አስተዋፅኦ እና ሚና አሳይተህ ያን እንድወጣ አብቃኝ፤ ወይም ማድረግ እንድንችል አብቃን፤ ሀገራችንንየሁላችን እንጂ በተለይ የማንም ብቻ እንዳትሆን አድርገን፤ ጥላቻን የጥርጣሬ ፍርሃትን፤ ሴራን፤ ትዕቢትን አስወግድልኝ።

ከወዳጆች ጋር አለተባበርም የማልተባበር አድርገኝ። እምነት፤ መተማመንና ዕውቀት ስጠኝ። ፍቅር፤ አንድነት፤ ሰናት፤ ብርታትና መተግበር ስጠኝ፤ ለዕቅ፤ ዕውነት፤ የሚቆም አድርገኝ። ጨቋኝም፤ ተጨቋኝም አታድርገኝ፤ ሁለቱም ፈተናዎች ናቸውና የሁሉም ኢትዮጵያዊ በደል የእኔም በደል ነው፤ ያንን በደል ለማስቀረት ሁሌም የምቆም አድርገኝ፤ የምንፈልገውን ተገቢውን ለሁሉም የሚሆነውን አሳውቀኝና ለዚያ አቁመኝ፤ እንድሠራ አድርገኝ። ከዛሬ ጀምሮ ጨቋኝም ተጨቋኝም እንዳልሆን ሳብቃኝኝ አምላክ ክብርና ምሕጋና ይድረስህ፤ የጭቆና ሽክርክሪት በእኔ ላይ እንዲያበቃ ላደረግህ አንተ ትልቅነት ተገቢ ወይም የተገባ ይሁን አሜን!!» ብለን በሎታችንን እናብቃ።

ይህ ምሣሌ (ማሣያ) ሲሆን ስለዚህ ምሳሌን ያልነውን የመሠለንን ሰፊን ለፈጣሪያችን መንገር (መለመን) እንችላለን።

ችግራችን የሉጂክ ብቻ አይመስለኝም፤ መድረታችንንና ፍርሃታችንን አምላክ መቀበል ያለመቻልም ይመስለኛል። ሉጂክ ኋላ ይመጣል። እናም ራርተናል ብለን እንመን። መራራታችንን፤ መጠራጠራችንን፤ ያለመተማመናችንን እንመንና ምትኩን እንጠይቅ እናም ገዢን (ሠውን በመለመን የፈለግነው ካልመጣ ፈጣሪን መለመን ተገቢ ይመስለኛል። ፈጣሪንም ለምንን ከጨረስን በኋላ የጠየቅነው ካልሆነም ወይምሕና ከሆነም ቀጥሎ የምንፈልገውን በእርግጠኝነት እናገኛለን። ይህም እሱ ወይም እኛ ለራሳችንና ለሁላችንም፤ ራሳችንና ራሳችን ብቻ የቀረን/ ያለን ስለሆን ራሳችን ለራሳችን ወይምሕና ለሁላችንም እንድንቆምና መቆም እንዳለብን ያደርገናል ወይም ያ ይገባናልና ነው። ለራሳችን ለሁላችንም በግልም ቢጋራም መቆም ወይም የፈለግነውን ለምንን ካልሆነም እስንድደን የመቀበልን ተገቢነት ለመወሰን የቀረን እንዱ ይህ ይመስለኛል።

## አዲሱ ዐዋጅና……..

ከገፅ 11 የዞረ

ተናግረናል! ሰሚ ግን የለም! በሕግ መመሪያ የተቀመጠው የመንግስት ዲፕሎማቶች ተደሚ ስራ ባሉበት ሀገር የሚገኙ ሕጋዊም ሆኑ ሕገወጥ ዜጎች የሚደርስባቸውን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት እየተከታተሉ ማስቆምም፤ ጥሰቱም እንዳይደርስባቸው መከላከል ነው፤ ግን እየሆነ ያለው እዚህ አይደለም። የሕጉ-ወጦችን ቀርቶ በኮንትራት ሰራተኛና አስራ ስምንት የመጡ ዜጎችን መብት ማስከበር አልቻሉም! ‹እንኳንስ ዘንበብሽ… › እንዲሉ፤ አይደለም ከፍተኛ ቀጥር ያላቸው ዜጎች መጥቀው፤ ያሉትን ዜጎች መብቶች የሚያስጠብቁ ተወካዮች አለመኖራቸውን ባለፉት ወራት ደጋግሜ የማነሳው፤ ሀሥር ዓመት በሳኡዲ ጤና ጥበቃ አንድ ኮሚቴ የተፈጋገጠውን የበላቲና መሐመድ አብድልአዚዝ ጉዳይ ማሳያ ይመስለኛል።

በህክምና ስህተት በአራት አመቱ ለተላል ህክምና ገብቶ ላለፉት 10 አመታት የአልጋ ቁራኛ ስለሆነው መሐመድ አብድልአዚዝ የሚሟገት አልተገኘም። ይህን ጆሆፍ ሰጆፍ መሐመድ ከክሬቡት ክፍል ወደ ማይመጥን ክፍል ሲዛምር በህክምናው ረገድ በቂ ክትትል እንደተቋረጠበት ከቤተሰቡ መረጃ ደርሶኛል። ይህ እንግዲህ በመብት ጥበቃው ረገድ እየተሰራ ያለ ስራም ሆነ ከሀሳቡ ያለው የመንግስት ተወካይ አለመኖሩን ካሳያቸሁ መልክም ነው። ወደ ኮንትራት ሰራተኞች ጉዳይ ፊታችንን ካዞርን የምናገኘው እውነት ይህው የመብት ማስጠበቅ ክሽፈት ይሆናል።

በሪያድና በጅዳ የሚገኙት የኢምባሲ እና የቆንስል ተወካዮቻችን የቪዛ ውል ማስፈጸሚያ ገንዘብ እየሰበሰቡ ባደፉት የኮንትራት የስራ ውል ላይ የተጻፉት ስምምነቶች የዜጎች ይዞታ የመከታተልና የማስፈጸም ኃላፊነትን ሲጠበ አላየንም! ሌላው ቀርቶ ህጉ ተግባራዊ ሲደረግ የሰው ኃይል ጭማሪ ይደረጋል ቢባልም፤ እንኳንስ አዲስ መጥቶ ላለትም በሙቶ ሽንዎች ለሚገመት ነዋሪ በቂ ግልጋሎት የሚሰጡ ስልጡን ዲፕሎማቶች የሉንም። ህጉ ጸድቆ ወደ ተግባር ሲገባም የሚመጡትን ሰራተኞች ለማስተናገድ በቂ የሰው ኃይል በሪያድ ኢምባሲና በጅዳ ቆንስል መስሪያ ቤቶች አለመኖራቸውን በቦታው ያለን የምናውቀው ሐቅ ነው! በአዲሱ ህግ የሚላኩት ሰራተኞች ቢያንስ እስከ ስምንተኛ ክፍል የተማሩትን ብቻ እንደሚያካትት ከመነገሩም ባለፈ፤ ሰራተኞች ማግኘት ስላለባቸው በቂ ስልጠናና ተዛማጅ ቅድመ-ዝግጅት እየሰሆን የሚታወቅ ነገር የለም።

ከዚህ ቀደም ድህነትና የኑሮ ውድነቱን ተከትሎ በልጆቻቸው ህይወታቸውን ለመለወጥ የቋመጡ ወላጆች በደላሎች ቀቢጸ-ተስፋ ተታለውና የተሳሳተ የእድሜና የትምህርት መረጃና የመታወቂያ ወንድ አቅርበው ከሃገር እንዲወጡ የተሰራውን ስራ የሚከላከል ዘዴ ስለመዘየዱ የሚታወቅ ነገር የለም። አለም አቀፍ የሰራተኛ ህግንና ሰብአዊ መብት ማስከበሪያ ድንጋጌዎችን ባገናዘበ መልኩ ሰራተኞች ስለሚከፈላቸው ክፍያ፤ ስለጤና፤ ስለረፍት ሰአታቸውና ስለ መሳሰሉት መሰረታዊ የኮንትራት ሰራተኞች እንግዚዚ ጥያቄዎች በጸደቀው ህግ ላይ ምን እንደሚመስሉ አልተገለጸም።

በህጉ ከዚህ በፊት በመንግሥት ፈቃድ የወሰዱ ኤጀንሲዎች ከዚህ በፊት ለሻጋገሯቸው ዜጎች ኃላፊ ይሆኑና ሁኔታ፤ አድራሻና ያሉበትን ሁኔታ በዝርዝር መረጃ አላቀረቡም። በሳኒቻው ሰራተኞች ላይ ለተፈጸመውና እየተፈጸመ ላለው በደል ተጠያቂው አልታወቀም፤ የቀሩት መብት ጥበቃ እንዴትና በምን መልኩ ይፈታል የሚለው መልስ ያገኘ አይመስልም። እልፍ አእላፍ የኮንትራት ሰራተኞች አሁን ያሉበት ይዞታ በውል ሳይመረመርና ሳይታወቅ ባለበት ሁኔታ የተዘጋውን መንገድ ለመክፈት የጸደቀው ህግ ያከፈራል። በጸደቀው ህግ ጠቃሚ ውይይት ተደርጎ ቢባልም፤ በአረብ ሀገራት ያሉትን ዜጎች ጨምሮ የዲያስፖራ ተወካዮች እንኳ እንደ ባለድርሻ አካላት በረቂቁ ህግ ተሳትፎ ሳያደርጉ ህጉ በተወካዮች ምክርት መጽደቁ ‹ሕሰዝብቡሰው› ቢያርጉ፤ በአረም ይመስሉ እንዲል የአባቶች ተረት፤ የጎፈት ስለቦዎችን መስጥፊት አድርጎ ጥቂቶች ተጠቃሚ የሚሆኑበት ህግ መጽደቁ አግባብ አይደለም፤ ጆሮ ያለው ይስማ!

ቸር ያሰማን!

# የ‹‹መባ›› አፍራሽ ስጦታዎች



ዮሐንስ ሞላ

### መባ (ፊልሙ)

"መባ" የ"ረቡኒ"ዋ ቅድስት ይልማ ፊልም መሆኑን በሰማሁ ቅጽበት ነበር የማይበትን ቀን ቆርጬ ሲኒማ የተገኘሁት:: "ረቡኒ" ላይ ካሳየችው ጥሩ ነገር አንጻር፣ 'መባ ላይ ምን አምጥታ ይሆን?' ከሚል ከፍተኛ ጉጉትና ጥበቃ ጋር ነበር ጀምሬ የጨረስኩት:: ሆኖም ግን፣ እንደተለመዱት 'ፊልሞቻችን' ሆኖ ነው ያገኘሁት:: የተፈረፈሩ የቴክኒክ ብቃቶችን እዚህና እዚያ፣ በየፊልሙ ሊያጋጥሙን እንደሚችል ሁሉ፣ መባም የራሱን ጥሩ ነገሮች አያጣም:: የመጠበቅ (expectation) ጣጣም ተጨምሮበት፣ ፊልሙ ይዞኝ እንዳልቀየና እንዳሰለቸኝ ልግለጽና፣ ከዋናው ጉዳዩ ጋር ልቀራረብ::

### መባ (ዋና ገጸ ባህርይው)

መባ የህክምና ዶ/ር ነው:: ሲኖር ሲኖር... በደረሰበት የአእምሮ ህመም ምክንያት ወደ ቤተሳይዳ የአእምሮ ህክምና ሆስፒታል ሄዶ ታክሞ፣ እንግዳም ወጥቶ እንደነበረ፣ ያልተቀረፈው የጀርባ ታሪኩ ያወሳል:: የሞያም ነገር ተጨምሮበት፣ ሌሎች ታማሚዎችን በመርዳት የተሰማራ፣ የሰው ህመም የሚያመው ትሁት ጎልማሳ ነው:: መባ ከሲት እስክ ደቲት የሚዘምርለት ደጋፊ ባለሞያ ነው:: ለታካሚዎቹ "መባ ሲመሰስ ነው::" የሚሰው ወሬ በራሱ ሰርግና ምላሽ ሆኖላቸው በዝማሬና በሆታ የሚጠቁት 'መሪ' ነው:: ከነበሩበት ባርነት ነጻ እንዲያወጣቸው ተስፋ የሚሹበት 'መሲሀ'፣ ዶ/ር መባ!

ከተመለሰ በኋላ "መባ... መባ..." ተብሎ የተደነከረለት፣ ሲያዩት ብቻ እግሮቹ ስር ወድቀው የሚታዘዙለት ዓይነት ነው:: በሰመ የተቀመሩ ዝማሬዎችን በኅብረት ያቀንቅኑለታል:: በመምጣቱ ተስፋቸው የለመለመ ታካሚዎች አሉ:: በወዳጁ በ30 ብር አልተሸጠም እንጂ፣ 'ስቀለው ስቀለው' ተብሎ ቀራንዮ አደባባይ አልዋለም እንጂ፣ ዶ/ር መባን በ"መባ" ፊልም እንደ ኢየሱስ ነው የተሳለው ብንል ማጋነን አይሆንም:: አስተምህሮዎቹም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃና ያላቸው ናቸው:: ሕይወቱ ካለፈ በኋላም ራዕይው በደንብ ተበክሮ፣ ታካሚዎቹን ከህክምና ተቋሙ ባንድ ጊዜ የማስወጣት (deinstitutionalization) ተቋማዊ እርምጃን አስወስዷል:: ፊልሙ ሲገባደድም፣ አብዛኛውን የሥነ-ልቡና ህሙም ትወክላለች የምታስብለው ዶ/ር ቢባ በተራዋ ታካሚ ሆና ተቋሙ ውስጥ ስትታከምና፣ የዶ/ር መባ መንፈስ ሲገዘግዘባት ይታያል::

ሰዎች ቱግ ብለው ሲናገሩት ዶ/ር መባ በትህትና ለዛብር ይመልሳቸዋል:: እጠገቡ ያለ ታማሚ ሌማ ከሩ ተፈትቶ ካየ፣ ገቶ ብሎ ያስርለታል:: የሆስፒታሉ መደበኛ ሀኪሞች ታካሚዎችን ሲናገሩ ቁጣ የተቀላቀለበት ከሆነ፣ እርሱ ቆም ብሎ ያስረዳቸዋል:: ታማሚን "ትንሽ ቀን እኔ ጋር ትቆይና ልያት" (ምሀረትን) እስከማለት የሚደርስ ጥንካሬም አለው:: ሆኖም ግን መባ አነጋሚ ነው:: በዚህ የተነሳ ወይም በልበ-ስሱነቱ ሊሆን ይችላል፣ ታካሚዎቹ የቀድሞ ታሪካቸውን ሲናገሩ ሆዱ ይንቦጫቦጫል:: ሜንታው ህመማቸውን መሸከም ከብዶት ይንገዳገዳል:: ሲረዳቸው ቀጭ ብሎም እርዳታ ያሻዋል:: ከዚህ ባለፈ ሌላ የሚረዳት ታካሚ (ምሀረት)፣ ከእርሱ ጋር የፍቅር የሚመስል ግንኙነት ለመጀመር

እንደተወሰወሰች በሚመስል መልኩ ስትቀርበው፣ እርሷን ለመጠበቅ ያህል እንኳን አይጠብቃትም:: - "ተ[illegible]ት ከኔ ጋር" ይላል እንጂ:: 'እርስዎ ልክ ነገር ቢኖር ነው' እንዳይባል፣ አሳሳሉ አያስገምተውም:: እንደ መልከጼዴቅ ነው!

### ገጸ-ባህርይ አሳሳልና መቼት

የአእምሮ ታማሚዎቹን የዘባ ጆልና መሳቂያ አድርጎ በተሰመደው መልኩ የመሳል ነገር




አለ:: ውስጥአቸው ፍጹም እርጋታ የራቀው፣ በገወጥ የተሞላ፣ እና ስለህመማቸውና ሀኪሞቻቸው በማውራት ብቻ የተሞላ አድርጎ ይስላል:: ይሄ በቅርብ ከሚታየው ነባራዊ ሁኔታ የራቀ ከመሆኑ ባሻገር፣ ኅብረተሰቡ ለአእምሮ ህክምና ጣቢያዎችና ታማሚዎቹ ያለውን አመለካከት የሚያጠለሽና መገለልን ሊሰብክ የሚችል ዓይነት ነው:: ስፖርት ሲሰሩ፣ እንደ ህጻን ኩቀ እስክ ቆሎ ምልክቶችን በሰውነታቸው ይሰራሉ:: ምናልባት "መሳቂያ ይሁኑ" ተብሎ የገባ ነገር ይሆናል እንጂ፣ ይሄ ለህጻናት ወይም ለተለዩ የአእምሮ ታማሚዎች እንጂ፣ ለግዜ ሙሉ ታማሚ የማይመስል ነገር ነው:: ግቢው እግርኳ አካባቢ፣ ሊያስዋኝ የሚችል የተኛ ኩሬ አለ:: ምናልባት ምህረት ከመባ ጋር እንዲተዋወቁ በተከለለበች ጊዜ፣ እንድትዋዘብትና ሌሎቹ ታካሚዎች ተሯሩጠው ገብተው እንዲያወጧት ብቻ የተመረጠ ቦታ ይመስላል:: ደግሞም ውጣው ለፊልሙ ትዕይንት (scene) ተጨማሪ ግብአት ሊሆን ይችላል፣ የአእምሮ ህክምና ተቋም ውኃ ያለበት ቦታ ላይ ለመገንባት ግን ወይ ማድየለሽ አስተዳደር፣ አለያም የፊልም ባለሞያ መሆንን ብቻ የሚጠይቅ ይሆናል::

ፊልሙ የሚያቀንቅነው የህክምናን ዘዴ

መቀየርና፣ ከ50 ዓመታት በፊት የነበረን የጽኑ አእምሮ ህሙማን ማቆያ ተቋማት የማፍረስ ፖሊሲ ዙሪያ ቢሆንም፣ ፊልሙ ላይ ምንም የጊዜ መቁጠሪያ ዓ/ም ስላልተጠቀሰ (እንደ "ከ40 ዓመት በፊት" ዓይነት) ፊልሙን በአሁን ጊዜንት ሲመዘን ጎዶሎ ያደርገዋል:: ያኔ የነበረውን እንቅስቃሴ ማሳየት ነው የፈለገው እንዳይባልም፣ ሁኔታውን በሚመስል መልኩ አልተረጸውም:: ለምሳሌ፣ የጽኑ አእምሮ ታማሚዎቹ ድምጾች የታፈኑ ጨኸቶች ስለሚሆኑ እርስ በርስ በዙድን መዋልን ሳንጠብቅ እንችላለን:: የሚኖሩበት ሁኔታም ያኔ ችግር ተብሎ እንደተነሳው የተፋፈገ አይደለም:: ምናልባት፣ እንደ በየፉ መሜታት እና ጆሮ አልይዘ መቅጣት ዓይነት የአካላዊ ጥቃቶች ሲፈጸሙ ማሳየቱ ከሆነው ወቅት ጋር ያቀራርበው ይሆናል:: ሆኖም ግን፣ በዚህ አገርና ዘመን የአእምሮ ህክምና ተቋማት የሚደረግ አይደለምና ባለን ጥቂት ተቋማትና ባለሞያዎች ከብራነክ ሲሆን ይችላል:: ችግሩ ኢ-ልብወለዳዊ ሆኖ እንደሚፈጸም የተደረሰበት ነው ከተባለም፣ የሰብአዊ መብት ጥሰት ነውና በወንጀል ዶሴ እንጂ በፊልም ጽሁፍ አይደለም መታየት ያለበት::

### በነገራችን ላይ... "መባ" ቅጂ (copy)፣ ወይስ ኦርጂናል?

'መባ' ብዙ ነገሩ ከቶም ሻድያክ "ፓች አዳምስ" ጋር ይመሳሰላል:: ይሄ ሆን ተብሎም፣ አጋጣሚም ሊሆን ይችላል:: ሆኖም ግን ተወዳጁ "ረቡኒ"ም ከስዊት ኖቬምበር ጋር መመሳሰሉንና በዚህ የተነሳ ብዙ ተብሎ እንደነበርም ይታወሳል:: ከፊልም ላይ ቅመሞችን (elements) ወስዶ፣ የራስ ታሪክ ላይ መዘራትም ሆነ፣ ከታሪኩ ጨልፎ፣ የራስ ቅመሞችን (elements) መቀየር ሁሉም ጥበብ ቢሆንም፣ ቅጂ ቅጂ ነው:: ከሰው ፍርድ ቢሸሹም፣ ከኅሊና አያመልጥም:: ቅድስት ግን ታህሳስ 16/2008 ላይ ከ-ታዲያስ አዲስ ጋር ባደረገችው ቆይታ ስለኦርጂናልነቱ ተጠይቃ "ጥሩ ፊልም በተሰራ ቁጥር ኮፒ ነው ባይባል ደስ ይለኛል:: ኮፒ ከሆነ ይታወቃል:: ...ኮፒ ነው መባል የጥሩ ስራ መገለጫ እየሆነ መጥቷል::" ስላለች እንተወው::

### የጽኑ አእምሮ ህሙማን ማቆያ ተቋማትን የማፍረስ ፖሊሲ (Deinstitutionalization)

እ.ኤ.አ. በ1950 ገደማ የተጀመረ፣ የጽኑ የአእምሮ ህሙማን እና ተፈጥሯዊ የአእምሮ እክል (mental retardation) ተጠቂዎችን ከትልልቅ ማቆያ ተቋማት በማስወጣት፣ ተቋማቱን ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል የመዝጋት ፖሊሲ ነው:: ይህም፣ በወቅቱ በህመም ሲሰቃዩ ለነበሩ ሰዎች እና ከዚያ በኋላ የታማሚዎቹን ጎስም ለተቀላቀሉ፣ የነበረው ጥቅምና ጉዳት በብዙ ባለሞያዎች ተተንትኖ ተመዝግቧል:: በወቅቱ የነበረው የታማሚዎች አያያዝ ችግር፣ የወጪ ቅነሳ፣ እና ክሎርፕሮማዚን (ቶራዚን) የተባለው የመጀመሪያው የአእምሮ ህመም መድኃኒት (antipsychotic) መፈጠር ጋር ተያይዞ፣ ሰዎች ማኅበረሰቡ ውስጥ ሆነው መድኃኒቱን ቢጠቀሙ፣ በሽታቸውን ለማከም ይችላሉ ተብሎ መታመኑ፣ ፖሊሲውን በማርቀቅ እና በመተግበር ረገድ አንኳር ሚናዎችን ተጫውተዋል::

እንደማሳያ:- እ.ኤ.አ. በ1955 በአሜሪካ አገር ውስጥ ከነበረው 164 ሚሊዮን አጠቃላይ የህዝብ ብዛት፣ 558,230 ያህል ጽኑ የአእምሮ →





ታካሚዎች በሕዝብ ሆስፒታሎች ውስጥ ነበሩ:: በአንጻሩ ደግሞ በ1994 ከነበረው 260 ሚሊዮን የአሜሪካ ህዝብ መካከል፣ 486,620 ያህሉ ሆስፒታሎች ውስጥ ይታከሙ ነበር:: የቁጥሩ ለውጥ በግልጽ እንደሚያሳየው፣ በፊት ሆስፒታል ውስጥ ሆነው እንክብካቤ ሊያገኙ ይችሉ የነበሩ የጽኑ የአእምሮ ህሙማን አሁን ማኅበረሰቡ ውስጥ አሉ:: - እንደማንኛውም ሰውኛም፣ ይባስ የራሱ ፈተናዎችና ዕድሎች እንደሚኖሩት ይጠበቃል::

የዘርፉ እና የማኅበረሰብ ሳይንስ ባለሞያዎች፣ ፖሊሲው ያመጣውን ጥቅምና ጉዳት በሁለት ጎራ ቆመው ይከራከራሉ:: አንዳንዶች፣ 'በትልልቅ ተቋማት ውስጥ የአእምሮ ታማሚዎች ይያዙ የነበሩበት ሁኔታ፣ የሰው ልጆችን ክብር የሚነካ፣ ለተለያዩ አካላዊና ወሲባዊ ጥቃቶች የሚያጋልጥ፣ አካላዊ ቅጣቶች ተበይነው የሚተገበሩበት፣ ነጻነትን የሚገፍ፣ የአእምሮና የመንፈስ ደህንነት ሰላምን የማያስከብር፣ እና ሆን ብሎ፣ ሰዎችን መሳቂያ መሳለቂያ የሚያደርግ ስለነበረ ፖሊሲው መፍትሄ አምጥቷል' ይላሉ:: ተቋማቱ፣ ጥገኝነትን፣ ልግምተኝነትን እና ስንፍናን እንዳበረታቱ አክለው ያስረዳሉ::

ሌሎቹ ደግሞ፣ "ፖሊሲው ታካሚዎቹን ከተቋማቱ ስለማስወጣት እንጂ፣ ቀጥሎ መድኃኒት ስለማግኘት አለማግኘታቸው ግድ እንዳልሰጠው፣ በኅብረተሰቡ ውስጥ በስኬት እንዲኖሩ ለማገዝ አቅጣጫዎችን እለመቀየሱና፣ ስለመልሶ ማቋቋም አገልግሎቶች አለማሰቡ፣ የከፋ ተስፋ መቁረጥና መገለል ውስጥ ከቷቸው ነገሩን አባብሶታል" ይላሉ:: ፖሊሲው መተግበር ከጀመረ በኋላም፣ ታካሚዎቹ ከማኅበረሰቡ ጋር ሲቀላቀሉ፣ ያለባቸው ህመም በአልኮልና በተለያዩ አጾች ተባብሶ በሚያደርሷቸው ጥፋቶች ተከሰሰው ወህኒ ይወርዳሉ በማለት፣ ከጥቃቶችን የገዳ ጥቃቶች አንስቶ እስከ ትልልቅ አገራዊ ወንጀሎች ጀርባ የአእምሮ ጤና ክፍተት መግባት ያለበት ጉዳይ መሆኑን ይናገራሉ:: ከዚህ ጋር ተያይዞ፣ 1/3ኛ ጎዳና አዳሪዎች የአእምሮ ታካሚዎች እንደሆኑ ይነገራል:: "ስራ መቅረት፣ ራስን የማጥፋት ሙከራዎች፣ ከሰዎች ጋር አለመግባባትና መገለልም ከፈተናዎቹ መካከል ይጠቀሳሉ:: ከዚህ በተጨማሪም፣ ፖሊሲው ብዙዎችን ጎዳና ላይ ጥሏቸዋል፣ ካሰቤና ሽፋን አስቀርቷቸዋል፣ በተለየ ዓለም ውስጥ መገለልን አስተናግደዋቸዋል" ይላሉ ተከራካሪዎቹ::

የታሪክ መዛግብት እንደሚያስረዱትም፣ ያኔ በዓለማቀፍ ደረጃ የነበረው የተቋማቱ ሁኔታ ከዓለም በታዋቾች ጋር የሚመሳሰል ነበር:: በ1970 (እ.ኤ.አ) በበጀት እጥረትና በመድኃኒቶች ተስፋ ሰጪነት ምክንያት አብዛኞቹ ተቋማት ሲፈርሱ፣ ብዙ ታማሚዎች በቤት እጦትት ወይም በእስር ተቋማት ውስጥ ቆይተዋል:: የሁለቱ ጎራዎች ክርክር ባለበት፣ ከ1973 ጀምሮ፣ ከማፍረስ ይልቅ፣ ትልልቆቹን ተቋማት ወደ ማኅበረሰብ መንከባከቢያዎች በመቀየር እንዲተገበር እንቅስቃሴዎች ተጀምረው ለውጦች ታይተዋል:: የሥነ-ልቡና ታካሚዎች ኅብረተሰብ (psychiatric community) ከማቋቋም ይልቅ፣ ኅብረተሰቡን የሥነ-ልቡና ድጋፍ ሰጪ (community psychiatrists) እንዲሆን ማድረግ የሚለውም እንደመፍትሄ የተጠቆመ ነው::

### ያለበት ሁኔታ...

(ዓለማቀፍ)

እንደ የዓለም ጤና ድርጅት 2001 (እ.ኤ.አ) ሪፖርት በዓለም ላይ፣ ከ4 ሰው አንዱ በህይወት ዘመኑ የሆነ ጊዜ ላይ፣ በአእምሮ ወይም በነርቭ ቀውስ ጥቃት ይደርስበታል:: 450 ሚሊዮን ሰዎች በአእምሮ ህመምና የባህርይ ነውጥ የተነሳ እየተሰቃዩ ይኖራሉ:: ይህም የአእምሮ ጤና ችግሮችን፣ ከዋና ዋና የጤና ችግሮችና የአካል ጉዳት መዘዞች ተርታ ይመድባቸዋል:: ህክምናዎች ቢኖሩም፣ 2/3ኛ ያህሉ የበሽታቸው

ዓይነት ተለይቶ ቢታወቅም፣ ታማሚዎቹ የህክምና እርዳታ አይፈልጉም:: ይህንን ችግር ከሚያባብሱ ነገሮች መካከልም፣ ማግለል፣ መድልዎ፣ እና ችላ መባል ይገኙበታል:: "መገለል ባለበት የሰዉ ግንዛቤም እናሳ ይሆናል:: ግንዛቤው ባልሰፋበትም መገለል ይበዛል::" ይላሉ አሰላሳዮች::

"አንዳንድ የአእምሮ ጤና ችግሮችን መከላከል እንችላለን:: አብዛኛው የአእምሮና የባህርይ ቀውስ ደግሞ በተመጣጣኝ ወጪ መታከምና መዳን ይችላል:: የጤና ችግር ያለባቸው ሰዎች ውጤታማ ሆነው በመኖር የማኅበረሰብ ዋና አካላት መሆን ይችላሉ::" ይላሉ:: የጥናት ውጤቶች እንደሚያስረዱትም፣ ከ80 በመቶ በላይ የስኪዞፍሬኒያ ታካሚዎች መድኃኒታቸውንና ህክምናቸውን ከጨረሱ በኋላ አያገረሽባቸውም:: 60 በመቶ የሚሆኑ በድብርት የሚሰቃዩ ሰዎች በመድሃኒት እና በሳይኮ ክትትል ሊያገግሙ ይችላሉ:: 70 ከመቶ የሚሆኑ የመጣል በሽታ (epilepsy) ያለባቸው ሰዎች አስፈላጊው ህክምና ቢደረግላቸው መዳን ይችላሉ::

### (አገራዊ)

የእኛ ሰው፣ ጤናማነውንም አእምሮ የማሳመም አቅም አለው:: ቢጋራ እንደመኖራችን፣ እርስበርስ መተያየታችንም ይበዛልና አሽሙሩም ተራቱም አተማዲ ነው:: የኑሮ ሁኔታውና የማኅበራብሀዊው አኗኗርም አለ:: ባሁሉ የአእምሮ ህመምን ከእርኩሳን መናፍስት ጋር ስለሚያያይዙ አስፈላጊውን ህክምና ለማግኘት መንገዶች ተሉ አይከፈቱም:: መንገዶቹ በሚገኙበት አጋጣሚም ማኅበረሰቡ እግዳይ ነው:: ከጊዜ ወዲህ ጥቂት ለውጥ ቢታይም፣ ብዙ ከአእምሮ እክል ጋር የተወለዱ ህጻናት ቤት ውስጥ ይደበቃሉ እንጂ፣ ትቤት ለመላክ አቅሙም አግራጩም ብዙ አይደለም::

ታማ ሰፈር ውስጥ ከሚታይ ሰው ይልቅ፣ ሆስፒታል የሚመላለሰው ላይ የበለጠ አይንና እፍ ይበዛበታል:: በዚህ የተነሳ የተጋላጭነት መጠኑን ለማጥናት ቀላል አይሆንም:: ስለዎም ለአዕምሮና ለባህርይ ቀውስ ሀኪም የሚያማክረው ከስንት አንድ ጊዜ ነው:: አንድ ለእናቱ የሆነውን አማኑኤል ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ብዙዎች አግልለው ነው የሚመለከቱት:: ከስሙም "እብድ ሆስፒታል" ይባላል:: ሆኖም ታካሚዎች ግቢው ውስጥ የሚተክሏቸውንና የሚንከባከቧቸውን አበቦች፣ የሚቀቧቸውን ግድግዳዎች እና የሚያዘጋጇቸውን የሥነጽሁፍና የስነ ጥበብ ዝግጅቶች በንመለከት አመለካከታችን ይለውጣል:: የአእምሮ ህክምና ሆስፒታል ውስጥ ይዝናናል፣ አትክልት ይተከላል፣ የእደ ጥበብ ሞያ ይደረጃል፣ ኪነ ጥበብ በውሎ ይከውናል:: እዚያ ጆሮ መያዝም ሆነ ሌላ ዓይነት ቅጣት የለም!

### ተጠቂው የኅብረተሰብ ክፍል

ከአእምሮ ህመም ጋር በተያያዘ ተጋላጩና፣ እንክብካቤውን ባለማግኘት የሚጠቃው ደሀው ነዋሪ ነው:: በዚህ የተነሳም የአእምሮ ጤና ሀገትፍ፣ የማኅበረሰብ ሀገትፍ ይሆናሉ:: በአእምሮ ጤና ዙሪያ የሚሰሩ የኪነጥበብ ስራዎችም በአዎንታም ሆነ በአሉታ፣ በፖሊሲ ዙሪያ የሚታሰቡ ስለሚሆኑ ሊታሰብባቸው ይገባል:: ታካሚዎች ላይ ስለሚደርሱ ጥቃቶች ሲወራ፣ ህክምናውን እንዲያቋርጥ ማስገደድም ራሱን የቻለ ጥቃት ነው::

"መባ"ላይ፣ ወደ መጨረሻው... የስኪዞፍሬኒያ ታካሚዋ ምህረት፣ መጀመሪያ "እኔ እብድ አይደለሁም" ማለቷን ባቆመች ጊዜ፣ "እዚህ ላንቺ የሚሆን መድኃኒት የለንም::" ሲሏት (ስኪዞፍሬኒያ ታመው የዳኑ ዙሪያችን ያሉ ሰዎች መኖራቸውን ልብ ይሏል::)፣ "እኔ እኮ እብድ ነኝ ብላ ህክምና እንደሚያሻት ስትገልጽ ትታያለች:: ብዙም ሳይቆይ፣ ታካሚዎቹን ሁሉ ነድቷቸው፣ ከግቢ አስወጥቶ "ሁላችሁም ተሸሏችኋል:: ሂዱ! መባ የሰጣችሁን ለጎለም ስጡ::" ብሎ በሩን ከውጭ ሲዘጋባቸው፣ ፍላጎታቸውን አውቆ እና ቤተሰብ

አማክሮ አይደለም:: ስለወደፊት አማራጮቻቸውና ስለሚገቡበት ቦታም አልተጨነቀም::

### 'ራስ ሳይጠና ጉተና'

ፊልም ለኪነጥበባዊ ውበቱ ብቻ ተብሎ ሊሰራ ይችላል:: ደግሞ አገራዊና ማኅበራዊ ጉዳይ ሲያነሳ በእግባቡና ነባራዊ ሁኔታን ከግምት እንዲከት ይጠበቃል:: ሳያውቁ የሚነሱ ከሆነ፣ ምክሩ "ከመጠምጠም መማር ይቅደም" ነው የሚሆነው:: የፊልም ስራ ባለሞያ እንደሚያሻው ሁሉ፣ ህክምናውም ባለሞያ ያሻዋል:: ይህንን ማንሳቴ፣ ዳይሬክተሯ ቅድስት ይልማ አማኑኤል ሆስፒታል ሄዳ ከባለሞያ ጋር ስለደረገችው ቆይታ ስለሰማሁ ነው:: ሲጀመር፣ እዚያ የሄደችው ለማማከር ሳይሆን፣ የሆስፒታሉን Electroconvulsive therapy (ECT) ለመጠቀም ትብብር ጥየቃ ነበር:: ያናገራት ባለሞያ ስለስክሪፕቷ አንዳንድ ነገሮችን አውርቷት፣ 'መስተካከል ያሉባቸው ነገሮች አሉ:: በሞያው ያለውን እስተያየት እንድንሰጥሽ የፊልሙን ጽሁፍ ብትሰጪንም እንተባበርሻለን::' ሲላት፣ "ከ70% በላይ ተረጸው ሄዷልና የምቀይረው ነገር የለም" ብላ ነበር የመለሰችለት:: (ለኛ ታህሳስ 18/2008 ከሸገር 102.1 ታዲያስ አዲስ ጋር በነበራት ቆይታ ግን "መባን ለመስራት ወደ 6 ወር አካባቢ አማኑኤል ሆስፒታል ነበርኩ:: እኔ ብቻ ሳይሆን ተዋንያኑም እዛ ነበሩ::" ብላ ተናግራለች:: እስካሁን፣ ይሄ ሆስፒታሉ ከሚያውቀው ጋር እንደሚጣረስ ነው ያረጋገጥኩት::)

'ከዚህ ባሻገር፣ ኪነ ጥበብ ኅብረተሰብን ከአገልግሎቶች ጋር የሚያገናኝ ድልድይ ነው:: በአእምሮ ጤና ዙሪያ እኛ አገር ብዙ ስራዎች አልተሰሩም:: ታማሚዎቹን ከሰውነት ተራ የወጡ አድርጎ መቁጠርና እየተከተሉ መንጓጓተል፣ ደግሞ መሸሽና መሮጥ የሚስተዋሉ የየእለት ክስተቶች ናቸው:: ታዲያ ይሄኔ ነው፣ "መች የጸደቀውን ዛፍ ነው፣ ልንቆርጠው መጋዝ የምንስራለት?" ብሎ መጠየቅ የሚገባው:: ተቋማቱን ማጠናከር፣ ለተጠቃሚዎች ግንዛቤ ማስፋትና ከኅብረተሰቡ ጋር ማቀራረብ፣ ከአንድ 'ተራማጅ' ሀሳብ ካላ፣ ተራማጅ የሆነ የኪነጥበብ ባለሞያ ቡድን የሚጠበቅ ነው:: ለማንኳሰስና ለማራራቅ ግን፣ ማኅበረሰቡ በቂና የጠነከረ የማግለል ልማድ አለው::

### 'በጎን ለማድነቅ ፍየሏን ማረድ' ለምን?

ፊልሙ የተሰራበት ዓላማ፣ "ተቋማትን ማፍረስን ስለማቀንቀን አይደለም" ካልን፣ "ፍቅርን ስለመስበክ" ይሆናል:: ይህንንም ያጠናከረልን በንድ፣ የዶ/ር መባ ፍጹማዊነትና ፍቅርን ሰባኪነት፣ ስለፍቅር ፍቱን መድኃኒትነት የሚናገር የዶ/ር ካትሪን ሀምሊን ጥቅስ በፍሬም ተስትሎ መታየቱና፣ ዶ/ር ቢባ በተራዋ ታማሚ ሆና "ምንም ዓይነት የጎን ጉዳት (side effect) የሌለው መድኃኒት ፍቅር ብቻ ነው::" ብላ ስትናገር፣ ፊልሙ ማስረጽ የፈለገው ዋና ጉዳይ ፍቅር እንደሆነ እንገነዘባለን::

በርግጥ ፍቅር ጥሩ ነው:: ሆኖም፣ ፍቅር በሕክምና እና በሰዎች የመታከም መብት ዋጋ አይሰበክም:: ዶ/ር ካትሪን ሀምሊን ስለፍቅር ፍቱን መድኃኒት ሲሰብኩ፣ በፊስቱላ የተጠቁ ታካሚዎቻቸውን ፍቅር ሰጥተው ብቻ ከነቁስልና ስበራ ልባቸው እየሳኳቸው አይደለም:: ከዋቀሚሱበት ለቅመው ሲያመጧቸው እንጂ በር ከፍተው "ሂዱ ከዚ! ለእናንተ መድኃኒት የለም:: በፍቅር ኑሩ::" ብለው ተቋማቸውንም አልዘጉም:: ይልቅስ 'አስፈላጊውን ቀዶ ጥገና፣ እንክብካቤና ድጋፍ ለማድረግ፣ እርሾው ፍቅር ነው' ሲሉን፣ በፍቅር ተስበው መጥተው፣ ተጠቂዎችን በፍቅር ጠርተው የእኛን ትልቅ የቤት ስራ እየሰሩልን ነው እንጂ::

ከምላ ጎደል ስናየው፣ "መባ" የሚሰጠን ስጦታ ጊዜውንና የአገራችንን ሁኔታ የዋጀ አይደለም::

ሰላም!

# የታዳጊ ፕሮጀክት ነገርና እኛ አሳፋሪዎቹ



ፍርድያውቃል ንጉሤ
(firdyawkal@gmail.com)

### መንደርደሪያ

ባለፈው ኢትዮጵያ ባዘጋጀችው የሴካፋ ውድድር ላይ በመጀመሪያው ጨዋታ ብሔራዊ ቡድናችን በሩዋንዳ አቻው መሸነፉ ይታወሳል። ይህ ውጤት ከተመዘገበ ከሰዓታት በኋላ ታዲያ አንድ ወዳጄ በ‹‹ፌስቡክ›› ገጹ ላይ ‹‹አሁን የግድ ታዳጊዎች ላይ መሥራት አለብን!›› የሚል የስላቅ አረፍተ ነገርን ብቻ ጻፈ። የሚገርመው ይህን የርሱን የስላቅ አባባል ተከትሎ በርካቶች ፈርጀ ብዙ የሆኑ የበሰሉና የጠለቁ አስተያየቶችን ሰጥተዋል።

ለዓሬው ጽሑፌ ይህን አጋጣሚ እንደ መግቢያ የተጠቀምኩት፣ ለርከ፣ በተለይ ብሔራዊ ቡድኖቻችን በተሸነፉ ማግስት፣ የሚደመጥ፣ ግን ዘወትር በተግባር የማንተገብረውን የታዳጊ ፕሮጀክት ጉዳይን የዛሬ ርዕሴ ስላደረኩኝ ነው።

እዎ! ሁሉም ሙያተኛና የፌደሬሽኑ አመራሮች ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ የሚለፍፉት፣ ነገር ግን ለትግበራው ጊዜ ‹ወዘኑ› የሚሉበትን የታዳጊ ፕሮጀክት እስከ ዛሬ አለመተግበራችን፣ ያለብንን ብሔራዊ ስንፈት ቅልብጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው።

### እጀማመሩ

ከአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ውስጥ ከሰላሳ በመቶ በላይ የሚሆነው ከ18 ዓመት በታች መሆኑን ጥናቶች ይጠቁማሉ። ኢትዮጵያ ተአምርን መሥራት የሚችል የሰው ኃይል ሀብት ባለቤት ብትሆንም፣ እኛ ለምጀ ግን እስካሁን ታዳጊዎች ከሲጋራት ለድሜያቸው ጀምሮ እያኮተኮትን ለማሳደግ አልቻልንም፣ በዚህም ምክንያት ሀገሬች በየሙያ መስኩ አስተማማኝ የሆኑ ተተኪ የሰው ኃይል ማፍራት እንዳትችል ሆናለች። በተለይ በስፖርቱ መድረክ፣ እኛ ዘወትር በስሜት በምንቃትትበት በእግር ኳሱ ብቻ ሳይሆን፣ በሩጫውም፣ በውርወራውም ሆነ በዝላይ እንዲሁም በቦክስ እና የኳስ ጌሞች በሚባሉት በነ ቮሊቦል፣ ቅርጫት ኳስ እና እጅ ኳስ፣ ከፍተኛ የተተኪ እጥረት አለ፣ ይህም ሁኔታ እጅግ አሳሳቢ የሆነ ደረጃ ላይ ደርሷል።

በኢትዮጵያ በተለይ በስፖርቱ መስክ የታዳጊዎች ሥልጠና በ1973 መጀመሩን ጥናቶች ይጠቁማሉ። በወቅቱ ይህ ሥልጠና ከአወቃቀሩ ውጭ ከሕዝብ ድጋፍ አለማግኘቱና በፋይናንስ ችግር ተዘፈ ሥልጠና ባለመሰጠቱ፣ ይህ ታዳጊዎችን ማእከል ያደረገ ፕሮጀክት እንደ ተጠበቀው ፍሬያማ ሊሆን አልቻለም።

በወቅቱ ይሰጥ የነበረው ሥልጠናም በዓመት ለሁለት ወሮች ብቻ ነበር። የሰለቀው ዓላማ ታዳጊዎች በረፍት ጊዜያቸው ካልባሌ ቦታ እንዲርቁ ማድረግ እንጂ፣ እግር ኳሱን አሳድጎ ተተኪ ማፍራት አልነበረም፣ እናም በቀጣይ ጉዞ በተወሰኑ ተጨዋቾች ብቻ - ያለተተኪ - ለመጓዝ ተገደን ነበር።

### 1990 - ወርቃማው ጊዜ

1990 ለኢትዮጵያ እግር ኳስ ታላቅ ዕሴትን ያጎናፀፈ መልካም ዓመት ነው ብል ከማንም አይቀመርብኝም። እዎ! በዚህ ዓመት ሀገር አቀፍ በሆነ መልኩ መሠረት ያለውና ዛሬም ድረስ በሳቂ እሽሩ ማሳረፍ የቻለ የታዳጊዎች ፕሮጀክት የእግር ኳስ እንቅስቃሴ ተጀምሮ ነበር።




እዎ! በሀገሪቱ በሚገኙ ክልሎችና የከተማ መስተዳድሮች ውስጥ ዓመት ሙሉ የተሰጠው ይህ የታዳጊዎች ፕሮጀክት ሥልጠና፣ በአስተማማኝ መልኩ ለሶሥር ዓመት ይዘልቃል ተብሎ ታስቦ ነበር። በፕሮጀክቱ በየዓመቱ እስከ 6,800 ታዳጊ ወጣቶችን ለማሠልጠን ታስቦ ነበር፣ ሥልጠናውንም ለመስጠት የታቀደው በዕድሜ እርከን በመከፋፈል ነበር (ከ13 ዓመት በታች፣ ከ15 ዓመት በታች፣ ከ17 ዓመት በታች፣ እና ከ20 ዓመት በታች)።

የሀገራችንን እግር ኳስ አንድ እርምጃ ወደ ፊት ማራመድ የቻለው ይህ የታዳጊዎች ፕሮጀክት፣ የታሰበለትን ያህል ዐሥር ዓመት መዝለቅ ባይችልም፣ በአምስትና ስድስት ዓመታት ውስጥ ትልቅ ሀገራዊ ፋይዳን አበርክቷል። ለዚህ ደግሞ ማረጋገጫ ማቅረብ ካስፈለገ ማቅረብ ይቻላል። እዎ! ኢትዮጵያ ከ31 ዓመታት በኋላ ለአፍሪካ ዋንጫ እንድትበቃ ያስቻሉት ተጨዋቾችን በጠቅላላ በዚህ የታዳጊዎች ፕሮጀክት ውስጥ ሠልጥነውና ተጫውተው ያለፉ ናቸው!

የሚገርመው በ1991 ደብረ-ማርቆስ ላይ ተሰናድቶ በነበረው ሀገር-አቀፍ የታዳጊ ፕሮጀክቶች ሻምፒዮና ላይ ምርጥ ብቃት ያሳዩ 23 ተጨዋቾችንና አንድ የውድድሩ ምርጥ አሠልጣኝ ወደ ስዊድን ሄደው ከእኛ ከተሻሉ ሀገራት የልምድ ተሞክሮ እንዲቀስሙ ለማስደረግ ውጥን ነበር (ውጥኑ ግን አልተሳካም)።

### ከዛ በኋላስ?

ይህ 1990 መባቻ ላይ የተጀመረው የታዳጊ ፕሮጀክቶች ሥልጠና በሀገራችን በአራቱም አቅጣጫዎች ተፋፍሞ መቀጠሉን ቀጥሎ ነበር፣ ግን ለዘላቂነት ሊበቃ አልቻለም። በተለይ ያኔ የነበረው የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌደሬሽን አመራር ከተቀየረ በኋላ፣ እሊጋ ወራሹ አመራር ይህን መልካም ውጤት እየተመዘገበበት የነበረውን ሥራ ይበልጥ አፋፍሞ መቀጠል ሲገባው፣ በደንታ-ቢስነት ፕሮጀክቱን አከሰመው።

ይህ የታዳጊዎች ፕሮጀክት ሥልጠና እንዲጀመር ሲደረግና ከተጀመረም በኋላ ነገሮች እሊጋ በእሊጋ አልነበሩም፣ ለማስጀመር ብርቱ ጥረትና የጠየቀ ነበር። ለምሳሌ፣ የታዳጊዎቹ አሠልጣኞች በሙሉ ለትራንስፖርት፣ ለላብ መተኪያና ለማንቃቂያ ተብሎ ይከፈላቸው የነበረው ወርሃዊ ክፍያ 100 ብር ብቻ ነበር፣ ፕሮጀክቱ ወደ ትግበራ የገባው፣ በፕሮጀክቱ ተሳታፊዎች መልካም ፍላጎት እና ፍቃደኝነት ላይ ተመርኩዞ እንጂ፣ በነገሮች መመቻቸት አልነበረም።

የትላንቱ እውነታ ይህ ሆኖ ሳለ፣ ዛሬ በፌደሬሽኑ አመራሮች ዘንድ መሰል ቁርጠኝነትን ማጣት እና ባለሙያዎችን አነሣሥቶና የጋራ ራእይን ሰንቆ ያን መሰል ሥራ ዳግም መሥራት አለመቻሉ - አለመቻሉ ቀርቶ አለመሞከሩ በራሱ - እጅግ የሚሳዝን ነው። ከትላንቱ እውነታ በተለየ፣ ዛሬ ያን ዓይነት ፕሮጀክት ለመተግበር የሚያስችሉ ነገሮች አሉ፣ እኛ ግን ወሬ ብቻ ሆነን ቸልተኞች ሆነናል! ሀገራዊ ኃላፊነትን ከመሸከም ይልቅ፣ በየዶ ሜዳ - በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ - እንጮኻለን፣ እንጯጯሃለን!

ግን ቸልተኛ የሆንነበት ምክንያት ምንድን ነው? ምንስ እስከንሆን ነው የምንጠብቀው? ዘወትር ተቀርቅሬ ይመስል በየመድረኩ አንዱ ‹ታዳጊዎች፣ ታዳጊዎች› ብቻ እያልን የምንለፍፈው እስከ መቼ ነው? ስለምንድን ነው ተግባራዊ እርምጃ መራመድ ያቃተን? የተጠናወተንን ደንታ-ቢስነት የምናስወግደውና በቆራጥነት ወደ ፍሬያማ ሥራ የምንገባው መቼ ነው? ... እነዚህን ጥያቄዎች ሁላችንም መመለስ ይኖርብናል። እሰቃለሁ።





# የአገዛዙ የበቀል ጅራፍ



አዩኤል ፍሰሐ

እውቁ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋችና ምሁር ፕሮፌሰር መሥፍን ወልደማርያም፣ አገዛዙን፣ ‹‹ከሦስት ትውልድ ጋር የተጣላ፣›› ሲሉ መግለጻቸውን አስታውሳለሁ። ፕሮፍ፣ ‹ከብርቱካን እናት፣ ከልጇ ጎሊይ እና ከራሷ ብርቱካን ጋር የተጣላ› አገዛዝ ሲሉ ነበር ‹የአንድነቷ› ብርቱካን ሚደቅሳ እንስተው አገዛዙን የኮነኑት። እንድ ግልጽ ሐቅ አለ፣ የሀገሪቱን በትረ-ሥልጣን የያዘው የሕወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ፣ ከአንድ ግለሰብ ጋር ‹ሲጣላ› የሚወስደው የበቀል እርምጃ በተጣላው ግለሰብ ላይ ብቻ የተወሰነ አይደለም፣ ከግለሰቡ አልፎ ወዳጆቹ፣ ጓደኞቹ፣ ዘመዶቹ ወዘተ. የበቀል ጅራፉ ግርፋት ሰለባዎች ይሆናሉ፣ ታዲያ ይህን ሲያደርግ ምን እያደረገ እንዳለ እንኳ ልብ አይለውም፣ ልብም ለማለት አይፈቅድም፣ የበቀል ጅራፉ ሰለባ የሆነ ሰው እንዲህ ዓይነቱ ግርፋት የሚደርስበት የተለየ እስከፊ ወንጀል ፈጽሞ በመገኘቱ አይደለም፣ ከአገዛዙ የተለየ አስተሳሰብ በመያዙ እንጂ!

እንደ አገዛዙ፣ በሀገሪቱ ውስጥ በያዘው የተለየ የፖለቲካ አመለካከት የታሰረ ሰው የለም። እውነታው ግን ሌላ ነው፣ ያለችውን ሚጢጢ የፖለቲካ ምኅዳር ተጠቅመው፣ የያሚቸውን ሕጋዊ የፖለቲካ አጀንዳዎች ለማራመድ የሚንቀሳቀሱ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጅቶች አባሎች በዚሁ በተፈቀደ የፖለቲካ ተሳትፎ ምክንያት ለእስር ተዳርገዋል። ለሰብዓዊ መብቶች መጠበቅና መከበር የሚሟገቱ ዓለም አቀፍ ተቋማት በሚያወጧቸው ሪፖርቶች ውስጥ፣ ኢትዮጵያ፣ ዜጎችን በፖለቲካ አመለካከት ልዩነት ብቻ ለእስር ከሚዳርጉ አገራት ዝርዝር ውስጥ ቀዳሚ ነች።

> ‹‹ለሰብዓዊ መብቶች መጠበቅና መከበር የሚሟገቱ ዓለም አቀፍ ተቋማት በሚያወጧቸው ሪፖርቶች ውስጥ፤ ኢትዮጵያ፣ ዜጎችን በፖለቲካ አመለካከት ልዩነት ብቻ ለእስር ከሚዳርጉ አገራት ዝርዝር ውስጥ ቀዳሚ ነች››

በኢትዮጵያ፣ ከአገዛዙ የተለየም ሆነ የራሳቸውን ሐሳብ በማራመዳቸው ምክንያት ለእስር የተዳረጉ ግለሰቦች መኖራቸውን ራሱ መንግሥት እምኖ የተቀበለው እውነታ ነው ብዬ አምናለሁ። ‹‹ጋዜጠኛ በጋዜጠኝነቱ ብቻ አይታሰርም!›› ብሎ የለፈፈ መንግሥት፣ ባለፈው ዓመት በሀገሪቱ የግል ፕሬስ ታሪክ ውስጥ የራሱን አሻራ ያሳረፈውን ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ የሶስት ዓመት እስር ፈርዶበታል። ጋዜጠኛውን ተጠያቂ ለማድረግ እንደ ማስረጃ የቀረበው ጋዜጠኛ ደሳለኝ የጻፋቸው ጽሑፎች ናቸው። እንግዲህ አንድ ሰው በያዘው የተለየ አስተሳሰብ ብቻ ለእስር ሊዳረግ እንደሚችል ጋዜጠኛ ደሳለኝ አንድ ማሳያ ነው።

ጠ/ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ በአል-ጀዚራ (የእንግሊዘኛ ስርጭት) "Talk to Aljazeera" ፕሮግራም ቀርበው፣ ጋዜጠኛ ማርቲን ፎኢስ ስለዞን ዘጠኝ ጦማሪያንና ጋዜጠኞች እስር በጠየቃቸው ጊዜ፣ ‹‹በጦማሪነታቸውም ሆነ በጋዜጠኝነታቸው ምክንያት አልታሰሩም። የአንድ አሸባሪ ቡድን አባል በሆኑ ሰዓት ግን ወዲያውኑ ጦማሪ/ጋዜጠኛ ይሆናሉ!›› ሲሉ ነበር የመለሱት። እንደ ጠ/ሚኒስትሩ (እና እርሳቸው ተረድተውታል ብዬ እንደ ተረዳኋቸው)፣ ጦማሪነት/ጋዜጠኝነት ሽፋን እንጂ ከጀርባው ሌላ ድብቅ ዓላማ አለ። ቃለ-ምልልሱ ከተካሄደ ከወሮች በኋላ ግን ከእነዚህ ታሳሪ ጦማሪያንና ጋዜጠኞች መሀል አምስት ያህሉ የቀረበባቸው ክስ ተቋርጦ ከእስር ሲለቀቁ፣ ቀሪዎቹ ደግሞ የቀረበባቸውን ክስ መከላከል ሳያስፈልጋቸው በነጻ ተሰናበቱ። አሁንም ከአገዛዙ የተለየ ሐሳብ ማራመድና ለመግለፅ መሞከር ለእስር እንደሚዳርግ የነዞ ዘጠኝ ጦማሪያን/ ጋዜጠኞች ምስክር ናቸው። ሁለት ማሳያዎችን ብቻ የጠቀስኩት ሌሎች ታሳሪ-ንጹሁዜጎችን አንድ ሁለት እያልኩ መዘርዘር ስላቃተኝ አይደለም፣ ልጥቀስ ብል መጽሔቷ የፈቀደችልኝ ገጽ ስለማይበቃኝ እንጂ!

የሕወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ፣ ከእርሱ የተለየ ሐሳብ እንሥተው የሚሞግቱትን ሰዎች፣ ራሱ በሚያወጣቸው ሕጎች ሽፋን ማጥቃት ሥራዬ ብሎ ከተያያዘው ከርሟል። አገዛዙ ጥርስ የንከሰባቸውን ዜጎች፣ እንደፈቀደው በሚዘውራቸው ‹የፍትሕ ሥርዓት› አስፈጻሚዎች ክስ እየፈበረከ ወህኒ ቤት ወርውሮ በእስር ካማቀቀ በኋላ በነጻ ማሰናበት፣ ክስ ማቋረጥ፣ ለወራትና ዓመታት በቀጠሮ እያንጓላ ቀይቶ ማሰር ወዘተ. እርግጥ የሚያንጸባርቀው የፖለቲካ ታካቲኩ ይመስላል።

አገዛዙ ሊያጠቃ የፈለጋቸውን ዜጎች አጥቅቶ ሲያበቃ፣ ‹የአገሪቱ ፍርድ ቤቶች ገለልተኞች ናቸው። በአሸባሪነት ተጠርጥረው ክስ የተመሠረተባቸው፣ ነጻ ከሆኑ በነጻ ይለቃሉ፣› በማለት ይደሰኩራል። ፍርድ ቤቱ በቀጠሮ አንግላቶ ነጻ ብሎ የሚያሰናብታቸው ተከሳሾችም ሆኑ ሌሎች ክዛድ ሲቃይ ደርሶባቿል። በእነርሱ ላይ ሀያሬ ተግባር የፈጸሙ ‹መርማሪዎች›፣ ለፈጸሟቸው የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችም ሆነ ለተላለፏቸው ሕጎች ተጠያቂ ተደርገው ፍርድ ቤት ሲቀርቡ አላየንም! አገዛዙ እንደሚለው ፍርድ ቤቶች ገለልተኞች ከሆኑ፣ ‹ተከሳሾች› በእነዚህ ‹መርማሪዎች› ላይ አቤቱታ በሚያቀርቡ ሰዓት ስለምን ጠርተው አይጠይቋቸውም? መልሱ ግልፅ ነው።

አገዛዙ ትችት ይፈራልና የተቹትን ያቂምባቸዋል፣ ሲበቀላቸውም ይፈልጋል። ለበቀሉ እርሱ ‹ደንንነት›፣ ‹መርማሪ› ብሎ የሰየማቸው ‹‹መለስተኛ አግዜሮች›› መሣሪያዎቹ ናቸው፣ የበቀል ጅራፉንም በራሱ ዜጋ ላይ ያሳርፋል። ፍርድ ቤቶችም የግል መገልገያው ናቸው። በዘመኑ ሕወሓት/ኢሕአዴግ ‹‹ወደ ማዕከላዊ እንዳንመለስ!›› የሚሉ ዳኞችን አይተናል። የአረና ፓርቲ አመራር አባል አቶ አብርሃ ደስታ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት 19ኛ ወንጀል ችሎት ቀርቦ ቅሬታውን ሲያሰማ፣ ከችሎቱ ሦስት ዳኞች አንደኛቸው - ቃል በቃል - እንደዛ ነበር የተናገሩት።

የሕገ-መንግሥቱ አንቀፅ 25፣ ‹‹ሁሉም ሰዎች ሕግ ፊት ዕኩል ናቸው›› ቢልም፣ በተግባር የአገዛዙ ሰዎች ከሕግ በላይ እንደ ሆኑ፣ የሳይናው ዳኛም ሆነ የሌሎች የአገዛዙ ሹማምንት ንግግሮች/ድርጊቶች ይናገራሉ። የሕግ ባለሙያው ጠበቃ ተማም አባቡልጉ በኢትዮ-ምሕዳር ጋዜጣ ላይ (የታኅሣሥ 16 ቀን 2008 ዓ.ም ዕትም)፣ ‹‹ሰው የሌለውን አይሰጥም!›› በሚል ርዕስ እንድ መጣጥፍ አስፍረው ነበር። በመጣጥፋቸው ሕግ እየጣሱ ባሉ የሕወሓት/ኢሕአዴግ አባላት ላይ እርምጃ እንደማይወሰድና አንቀጹ መሬት ላይ እየተተገበረ እንዳልሆነ ሲያስረዱ እንዲህ ይላሉ፦

‹‹ኢሕአዴግ ወንጀል የፈጸሙ አባላቶቹን እንደማንኛውም ዜጋ ለፍርድ ባለማቅረቡ ብቻ የሕገ-መንግሥቱን አንቀፅ 25 (የዕኩልነት መብት) ጥሷል። ይህ አንቀጽ ደግሞ ሀገሪቷ የአስቸኳይ ጊዜ ዐዋጅ ታውጆባት እንኳ አፈጻጸሙ የማይታገድ የሕገ-መንግሥቱና የሥርዓቱ ምሰሶ ነው። ምክንያቱም ዕኩልነት ዜግነት በመሆኑና ሕግም፣ መንግሥትም፣ ሥርዓትም፣ ሀገርም ያስፈለጉት ለዚሁ በመሆኑ፣ ዜግነትና ዜጋው ከሌሉ አስቸኳይ ጊዜ ዐዋጅ የሚታወጅለትን ነገር መንግሥትም፣ ሕግም፣ ሥርዓትም፣ መኖራቸው ትርጉም አልባትርጉም የሚይሰጥ ወይም ወለፈንድ (Absurd) ስለሚሆን ነው።››

እንግዲህ እውነታው የሕግ ባለሙያው እንደገለጹት ነው፣ የአገዛዙ ባለሥልጣናት እንዳሻቸው በሚዘውሯቸው ሚዲያዎች በመቅረብ ሕዝቡን ለማደናገር ዘወትር ላይ ታች ይላሉ። በኢትዮጵያ አንድ ዜጋ በፖለቲካ አመለካከቱ እንደማይታሰር፣ አንድ ጋዜጠኛ በጻፈው ጽሑፍ ለእስር እንደማይዳረግ ይለፍፋሉ። ሐቁ ግን ሌላ ነው!

የአገዛዙ ቂም-በቀለኝነትና እስከ ምን ድረስ እንደ ሆነ የምንረዳው የገደላቸውን ዜጎች ስም ሲያጠፉ ስንሰማ ነው። ከሕዝብ ጉያ የወጡ የሕዝብ ልጆችን ገድሉ፣ ‹‹በሕዝብ ላይ ጉዳት ሊያደርሱ ሲሉ ተመጣጣኝ እርምጃ ተወሰደባቸው›› ይላሉ። በዚህ አካሄዱ ሥልጣን ላይ ሩብ ክፍለ ዘመን ሊያስቆጥር አምስት ወራት ብቻ ናቸው የቀሩት። የእኔ ጥያቄ፣ አገዛዙ በዚህ መልኩ እንዲቀጥል እስከመቼ ነው የምንፈቅድለት? በዜጎች ላይ እየፈጸመ ያለው ግፍ የእኛን ጓዳ ዘልቆ እስኪገባ ለምን እንጠብቃለን? አገዛዙ በወንድምና እህቶቻችን ላይ የሚፈጽመውን አሲቃቂ ብርቻር፣ እስራት፣ እስገዳጅ የግፍ ስደት፣ ወዘተ. በአይናችን እያየን ለምን እንዳላየና እንዳልሰማ እንሆናለን? ለፍርሃታችን ‹‹ትዕግሥት›› የሚል ዳቦ ስም እየሰጠን ያለንስ ስንቶቻችን ነን? ...

ያሉንን ልዩነቶች ለጊዜው ወደ ጎን ብለን፣ በአገዛዙ ላይ ካልተነሣን ግድያው፣ ድብደባው፣ እስሩ፣ የግፍ ስደቱ ወዘተ. ይቀጥላል። ይህ ሁላ እንዲቀም ማድረግ የምንችለው እኛና እኛ ብቻ ነን። ይህን ልብ ልንል ይገባል! ከላይ የጠቀስኩትን የጠበቃ ተማም አባቡልጉ ጽሑፍ መደምደሚያ እስፍሬ ለዛሬ ላብቃ፦

‹‹ሰው የሌለውን አይሰጥም። ከሰጠም ያለውን ነውና መስጠት የሚችለው፣ ከኢሕአዴግ እና ኢሕአዴግን ከመሰሉት ግን [የሚለጠን የድብደባ፣ የርሸና፣ እና የእነዚህን መሰል ድርጊቶች ቅይጥ መሆኑን መረዳ ይኖርብናል]። ቀጋና እሾህንትም ስብዕናቸው ነውና እሱ ካለና ባለበት ሁሉ ነጻነት፣ ሰላም፣ እርጋታ፣ ዕኩልነት፣ ሚዛናዊነት፣ መረጋጋት፣ መብቶች በፍፁም ሊኖሩ አይችሉም። ልብ ያለው ልብ ሊለው የሚገባው ይህንን ነው!››

# ክፍት የሥራ ቦታ፤ አዲስ አበባ መኖር



አዶንያስ ልሣንወርቅ

አዲስ አበባ ውስጥ ሰማይ ከምድር ሳይለቀቅ ራሱን ከሌሊጋ ምኞት ላይ በማዋለቅ ታክሲ መጠበቅ ይጠበቅብዎታል። ሆኖም እርስዎ ስለጠበቁ ሳይሆን፤ ስለታደሉ ብቻ ታክሲ ያገኙ ይሆናል። ታክሲ ሲጠብቁ ታዲያ አንድ ሰዓት ቢቆሙ አይማረሩ። ጌታም እነሆ «በቶሎ እመጣለሁ» ብሎ ይኸው ሁለት ሺ ዓመት ሞልቶታል። እርስዎ አንድ ሰዓት ቢጠብቁ ይሞታሉ!?

አስረግጬ የምነግርዎ፤ ታክሲው መምጣቱ አይቀሬ መሆኑን ነው። ከእርስዎ የሚጠበቀው ታክሲው የሚመጣበትን ጊዜ መርሳት ብቻ ነው። ደግሞምኮ የምርጥ ምርጥ አትሌቶች አገር ውስጥ ነው የተወለዱት። በዚያ ላይ የጠዋት ሩጫ ለጤና ብቻ ሳይሆን፤ ለሀሳብ ብቃትም ይመከራል። ሮጥ ሮጥ እያሉ ታክሲ ይጠብቁ።

ታክሲው ከመጣ እሰየው፤ ታክሲው ውስጥ ይገባሉ። ካልመጣም እንደ ጀመሩት በሶምሶማዎ ገፍተው መሥሪያ ቤትዎ ይደርሳሉ። ግፋ ቢል እንደ መጀመሪያው የማራቶን ሯጭ ፌዲፒደስ ልብዎት ፈንድቶ ቢሞቱ ነው። ይህ ደግሞ ወደ ቤቱ ለመግባት ሲሟሟጥ ሳይሆን፤ ወደ ሥራ ለመግባት በትጋት ሲሮጥ የሞተ የመጀመሪያው ልማታዊ ሰማዕት ሠራተኛ ያደርግዎታል - እና ይስ ይበልዎት።

ደግነቱ ታክሲው መጣ። አቅሙ ያለምንትም ቢሆን ገዱታትሪው ያለ ምንም ይሉኝታ አይኖትን በጨው አየነው ግባት ይለሱ። እርስዎስ ቢሆን ኪስዎ ይዘማ ስለሆን አደልዋንዶ በታክሲ የሚሄዱት!? ግን ይሉኝታ በጨው የሚለቅ ቢሆን ኖሮ አምሊ ጨው የሰስ ከዘበት ሁሳ ሳይፈራረጥ በታረደ ነበር፤ ያን ሁሉ አገር ማር ያሰፍን ባለቤቱንማ አሳሳፍረውም፣ ብሎ። ነገር ግን ይሉኝታ በጨው ሳይሆን በማማት ይለቃል። ድህነት ይሉኝታ ቢስ ያደርጋል። ክርስቶስ፤ «እናንተ የዓለም ጨው ናችሁ» ቢለም፤ ትውልዱ ግን ከጨው ይልቅ ማር ወዷል። ኑሮን በጨው ሳይሆን በ«ተማምሬት አጣፍጣለሁ» ብሎ ታምሬት ገጸታን 20 ዓመት አስፈረደበት። አዳም ፍሬ የበላው ዛሬ ቢሆን «ጥረህ ግረህ ብላ» ብሎ እግዚአብሔር ባልፈረደበትም ነበር። ዛሬ ዛሬ ጥሮ ግሮ መብላት እርግማን ሳይሆን ምርቃት ነው። ጥሮና ግሮ (ጾሮ) መብላት ያቃተው ስንቱ በየቦታው አለ።

ወደ ጉዳያችን ስንመለስ፤ ወደ ታክሲው በለው ሲገቡ እግርዎትና እጅዎት ከገፊያው ብርታት የተጥግ በአየር ላይ ሲወራጨና ሲውለበለብ ቢታዩ፤ በዓይብ መምኛ ገንዳ ውስጥ የገቡ እንጂ ታክሲ ውስጥ ብቻ የገቡ አይመስሉ ይሆናል። ይምሰሉዋ! ከራሳሽ! ሰሆነት ሰው አይጨልቅ። አይሆት! ታክሲ ሲጋፉ መንገድ ያንከባበቡትን ከብር መኪና ገዝተው ወይም ምንር ቤት ገዝተው ተዘርጋ እየተባሉ በአጥየፍ ያስመልሉታል።

የገቡበት ታክሲ ውስጥ አጠገብ የተቀመጡ ሪየም አየውንት ተልባ የመሰለ ጥቁር በዘፍ እግራቸውን እንሥተው ደንገት እግርዎ ላይ ቢያስቀምጡ ምክም አይቀየሟቸው። ምናልባት በሸታቸው የሚለቁቸው እግራቸው የሰው እግር ሲያነው ይሆናል። ይልቁንም ያኔ ልጅ እያሉ ቆረጠሙኝ ባሉ ቁጥር በዚያ የልጅ እጅዎት ደክም እስኪሉት ድረስ በቅባት የሚያሹላቸውን፤ በሆዲያን የዮድት ጠባሳ ያሸበረቀውን የአርበኛውን የአያቶችን እግር እያስታወሱ ይታገሷቸው፤ ለአድዋና ማይጨው ድሎች ምክንያ ይሁን እንጂ ዛሬ ቻይና ሳይሆን ጣሊያን በሠራው መንገድ ላይ እየሳቁ ሳይሆን እየተሳቀቁ በዚሁ ነበር። እንዲው ግን ቻይና ኢትዮጵያዊ ሆነ እንዴ?

> "የማይለምን ማን አለ? ሰዉ ሰዉን ይለምናል። ሰዉ መንግሥትን ይለምናል። መንግሥት ሰዉን ይለምናል። መንግሥት መንግሥትን ይለምናል። እግዜር ሰዉን ከኃጢያታችሁ ተመለሱ እያለ ይለምናል፤ ሰዉም እግዜርን እባክህ ይኼንን አድርግልኝ እያለ ይለምናል። የልመና ኔትወርክ ያልጠለፈው ማን አለ!? አንዱ ሌላውን ለማኝ ይላል። ግን ማን ያውቃል? የመንግሥት-ሰማይ መግቢያ ትኬት የሚያስቆርጥዎት እነዚህ ደሆች ቢሆኑስ

አያቴ ታሪክ ሲሠሩ እኔ የአያቱን ታሪክ እያወራሁ ጠጅ ይጋዝዙ ነበር። ዝነኛ ሰው አገራችን በመጣ ቁጥር ለምን ሴቶቻችሁ ሲያምሩ ይላል? የሴቶቻችን ጭኖች እንጂ የጉሬቻችን ጫና መች ያሳይልናል። ሚሊ አዋሚ ሲመጡ የቤሌን ውበት እንጂ የጨርቆስን ውበት ማን አሳያቸው?

አይ ለድልዎ! ከተቀመጡበት የታክሲ ወንበር በስተቀኝ ልጅ ያዘለች እናት ደግነት የሚገዘዝበትን ገጸታዎን አስተካክላ ሊሆን ይችላልና እጇ ወደ ኋላ መድረስ ስለሚቀተው ያዘለችውን የልጇን ገጥሞ እንዲጠርዝላት እርዳታዎን ልትጠይቅ ነው። ይህም ቢሆን ክፋት አይደለም፤ ይተባበሯት። ሉክሳሴ ግድብ ሳምፓው ያመለጡትን አስተዋጽኦ የትውልዱን ገጥሞ በመገደብ ያበረክቱ ይሆናል።

የተሳፈሩበት ታክሲ ግን ይገርማል! ገና የመንገዱት ወገብ ላይ ሳይደርሱ ደግነት ሩጫውን ጨርሻለሁ ብሎ ወገቡን እንሽክት ያደርጋው? ይሆን ለዚህ ነው። ለላ ታክሲ ይይዙሉ። ተገፍተው የት ሊደርሱ!? መስደብ ካማርት ደግሞ እንዴ ቀና ብለው ታክሲው እናት ላይ የተጻፉትን ጽሑፎች ማንበብ ነው፤ «መብትዎ እኛ ጋር ሲመጡ ነው ትዝ የሚለዎት?»፤ «አመልዎን ቤትዎ»፤ «እኛ ላይ ከሚጎመጉሙ ለምን ሳዋና ካፌ ውስጥ አይከራከሩም!?»... ምን አለፋዎ! ብሶት የወለዳቸው ጥቅሶች በሽ ናቸው። እ! እ! ስድብ ከጆሮ ሐዋ ወደ አፍ ሳይቀየር መውረድ ይሸሉታል።

ታክሲ ሰመያዝ ወረዳና ለላ ሰልፍ ጋር ደረሱ። እሰይ ዝርጋ! ይሄኛው ሰልፍ ደግሞ የተጥመለመለ - ረዥም ነው። ረዥም ዕድሜ ለሌለው ሕዝብ ረዥም ሰልፍ ምን ያደርግለታል? ሰልፉን እንደ መልካም አጋጣሚ የወሰዱ የአገሬው ለማኞች በልዩ ልዩ ሥልት ልመናቸውን አሚጡፈጥፍ የሰልፉ ማጀቢያ መሆናቸው ነው። አቸፍ ማዘብል የተማኙዋቸው ጉርድ ሬቶች፤ ድፍጥጥ አፍንጫዎች፤ አሸመር የሚናኙ የሚመስሉ ጠማማ እጆች፤ ያለው ዳብልቡል ሆዶች፤ በትክ መቶም ተሰናችው የቴአትር ቤት ተወዛዋዥ የመሰሉ ተንቀጥቃጭ ወገቦች... ፊት ለፊቱ እየተመላለሱ ሽብረብ ይላሉ።

የማይለምን ማን አለ? ሰዉ ሰዉን ይለምናል። ሰዉ መንግሥትን ይለምናል። መንግሥት ሰዉን ይለምናል። መንግሥት መንግሥትን ይለምናል። እግዜር ሰዉን ከኃጢያታችሁ ተመለሱ እያለ ይለምናል፤ ሰዉም እግዜርን እባክህ ይኼንን አድርግልኝ እያለ ይለምናል። የልመና ኔትወርክ ያልጠለፈው ማን አለ? አንዱ ሌላውን ለማኝ ይላል። ግን ማን ያውቃል? የመንግሥተ-ሰማይ መግቢያ ትኬት የሚያስቆርጥዎት እነዚህ ደሆች ቢሆኑስ? መንግሥተ-ሰማይ ከገቡ በኋላ ይኼንን ሁሉ ችግር የማየት ዕድል የት ያገኙና? በዚያ የመላእክትና የቅዱሳን ምስጋና እንጂ የድሆችን ርሃብ የመስማት ዕድል የለውም!

እና ለአንዱ ለማኝ ሳንቲም እንደ ሰጡ ሌላው ለማኝ ተንደርድሮ ፊቶ ይቆማል። ከመጡት ውስጥ አንዱ አንካሳ ነው። የሰፈርን አንካሳ ተሴን አስታወሱት። ተሰማን ተሴ ካሉት ይበሽቃል። ተሰማ ብለው ከሚመርቁት ተሴ እያሉ ቢሰድቡት ይመርጣል። ሰዉ ሙሉ ስሙን የሚጠራው ነገር ሲፈልገው ይመስለዋል። ተሴ ታዲያ በሰፈሩ ብቸኛው ባለ አንድ እግር ነው። የተሴ አባት ደግሞ የዛሬን አያድርገውና የሰፈሩ ሕዝብ በአንዳንድ መኪናዎች፤ በዘቡ ባጃጅ እና በአድር ድንኳን ከመግዛቱ በፊት ብቸኛው ባለ መኪና ነበሩ። ታዲያ የሰፈሩ ሰው ባገባ ቁጥር የተሴን አባት ፔጆ መኪና ተሰፍሮ አድርገን ነበር። እንዲያውም ከሚያገባት ልጅ እሺ ማለት ይልቅ የተሴ አባት መኪናቸውን ለሰርጉ ቀን እሺ ማለታቸው ያሳስበው ነበር።

ተሴ አይሠራም። አይለምንም። ባለመሥራት እና ባለመለመን መሀከል ያሉ የምስጢር ክሮችን በልቡ ጠብቋቸዋል። ማን ያውቃል? ሊሞት ሲል ብቻ ለልጁ ምስጢሩን አውርሶት ይሞት ይሆናል። ከዚያ ውጭ ተሴ እንዴት እንደሚኖር ማንም የሚያውቅ የለም። አንድም ቀን ሳምንቱ በመሽ ቁጥር መጠጣት ግን የግሉ ነው። ሰኞ ሰኞ ሰኞ ሰኞ እንዲህ ሊሆን ብቻ ምርጋቸሁ ካንዲሶቹን ታትፈውለት የቁራማ እግሩ ሱሪ እንደ ባንዲራ እየተውለበለበ በአንድ እግሩ ብቻ እንዣባየ እንዣባየ እያለ ወደ ቤቱ ይገባል። በዚያው እግሩ እንዣባየ እንዣባየ እያለ አልጋው ላይ ይወጣል፤ አሁንም እንዣባየ እንዣባየ እያለ ሚስቱ ላይ ይወጣል። ይኸው አሁንም ገና ከሚሽት እንዣባየ እንዣባየ እያለ የሚያስጠምቁ ልጁ የተገኙ ፈዳሽ ወመኔ ልጅ ለሰፈሩ አበርክቷል።

ተሴን በማስ የሚገርፋት ብቸኛው ሰው የዛባሌው እድር ጡሩንባ ነፊ ጋሽ አየሌ ብቻ ናቸው። ጋሽ አየሌ ተሴን ሲመሽ ባገኙት ቁጥር፤ «ተሰማ! ሰዉ በሁለት እግሩ በቢ ይገባል፤ አንተ በአንድ እግርህ ታመሽለህ!» ይሉታል። አንድ ቀን ግን ተሴ ጠብቆ የልቡን አደረሰ።

በዚያ ቀን ተሴ ከጋሽ አየሌ ጋር ሆኖ ሲጠጣ ዕኩለ ለሊት ይሆናል። ጋሽ አየሌ ተሴን፤ «ስንት ሰዓት ሆነ?» ብለው ይጠይቁታል። ተሴም ወሸቱን፤ «ለ12 ሩብ ጉዳይ» ይላቸዋል። ያያይዙና፤ «ግን እኮ አሁን ነጋ! እንደኛውን ለምን ኑ ኑ አድርገህ ቤት አትገባም? ከምቀ ኢሊጋህ ላይ ተንከባለህ ጡሩንባ ከምትነፋ?» ይላቸዋል። ጋሽ አየሌ ጥንብዝ ብለው ሰክረው ነበር፤ እውነትም የጌታ መሰዲቸው በሰላሉ ሌሊት ስድስት ሰዓት ላይ ጡሩንባ አንፍቶ ለተበለው ሕዝብ የሊቀመንበሩን ሞት አረዱ፤ ድርጊታቸውም እስከወዲያኛው ከሥራቸው አሰናበታቸው።

(ይቀጥላል)





# ሰባራ ታሪክ፤ ሰባራ ትወና (በተከታታይ የቴሌቪዥን ትወናዎች)



ደረጀ ታደሰ

ሰዎች ለመዝናናትም ሆነ አንዳች ቁም-ነገር ለመሸመት ብለው ሳምንት እየጠበቁ ከሚታደሟቸው የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ውስጥ ተከታታይ ድራማ ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል። ኅብረተሰቡም ትኩረት ሰጥቶ ይከታተላቸዋል። ባለሙያዎቹም የታዳሚዎችን ፍላጎት ለማሟላት በሚመስል መልኩ በርካት ያሉ ሥራዎችን ይዘው ቀርበዋል።

ዛሬ በኢብኮ እና በኢቢኤስ የሚተላለፉ ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማዎች በድምሩ ሰባት ይሆናሉ። በዚህ ቁጥርና ምልከታ ውስጥ «ቤቶች» አልተካተተም፤ የድራማው ዓይነት ሲትኮም (Sitcom) በመሆኑ።

ሲትኮም ድራማ ደግሞ በዜልርይው በሳምንቱ አዳዲስ ርዕሰ ጉዳዮችን በማንሳት ፍፃ (አስቂኝ) በሆነ መንገድ የሚቀርብበት ነው። በዚህ የተከታታይ ድራማ ዓይነት ወጥ የሆነ የታሪክ ፍሰት አይኖርም። ግን በድራማው በአጃቢነት ከሚገኙትና አጭር ቦታ ካላቸው ገጸ-ባሕርያት ውጭ ያሉት ዋና ዋና ገጸ-ባሕርያት አይቀየሩም። ቀሪዎቹ ሰባት ድራማዎች ተከታታይ (Serial) በሚባለው የድራማ ዓይነት ሥር የሚመደቡ ናቸው። ተከታታይ (Serial) የቴሌ. ድራማ ከፍተኛ ተያያዥነትና ሒደት ባለው ታሪክ፤ እጅግን በተሟላ ሔራዎች ተሰናስሎ ትይዩም-ተከተላዊ ፍሰቱን ጠብቆ የሚጓዝ የድራማ ዓይነት ነው። እና ልክ እንደ ሲትኮም፤ አሸኒ ገጸ-ባሕርያቱ እንጂ ዋና ዋናዎቹ አይቀየሩም።

ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማ ከሚቀርብበት መንገድ አንፃር ሲታይ፤ ሰፊውን የኅብረተሰብ ክፍል የማዳረስ አቅሙ ከፍተኛ ነው። በቴሌቪዥን አማካኝነት በየቤቱ የሚደርሱ በመሆኑ የያዘውን መልዕክት ለሚመለከተው ሁሉ የማድረስ ዕድሉ ሰፊ ነው። ለዚህም ነው በአሜሪካ የመጀመሪያዎቹ ተከታታይ ድራማዎች (በብዛት በሬዲዮ ይቀርቡ ነበር) የሳሙና ሽያጭን ከፍ ለማድረግ ሲባል ተቀነባብረው ይቀርቡ የነበረው። ከዚህም አንፃር ሶፕ ኦፔራ (Soap Opera) በሚል ይጠራሉ።

በአሜሪካን ወርቃማው የቴሌቪዥን ዘመን ከሚባለው ጊዜ (ከ1947-48 እ.ኤ) በኋላ ከ1952 (እ.ኤ) አንስቶ በሲቢኤስ ቴሌቪዥን በኩል ይቀርብ የነበረው «The Guiding Light» የተሰኘው ሶፕ ኦፔራ ከርዝመት አንፃር ቀዳሚው ነው። ይህ ድራማ ቀደም ሲል በሬዲዮ ይቀርብ የነበረ ቢሆንም፤ ወደ ቴሌቪዥን ከመጣበት ከ1952 (እ.ኤ) ጀምሮ እስከ ተጠናቀቀበት መስከረም 18፣2009 (እ.ኤ) ድረስ 15762 ክፍሎችን የያዘ ነበር።

ወደ ሀገራችን ስንመለስ፤ የተከታታይ (Serial) የቴሌቪዥን ድራማዎች ዕድሜ ከሁለት ዐሥርት ዓመታት የሚበልጥ ነው። በተለይ «ገመና» (የመጀመሪያው) ከቀረበበት ዘመን ወዲህ በቁጥር በርከት ብለው ይታያሉ። «ሰው ለሰው» ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማም ከርዝመት አንፃር ቀዳሚውን ስፍራ እንደሚይዝ ይገለፃል።

ቀጥለን በአሁኑ ሰዓት በሀገራችን በመቅረብ ላይ ከሚገኙት ሰባት ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማዎች ውስጥ (ማለትም «መለከት»፣ «ሚዜሜ»፣ «ብኩ ሥራ»፣ «ዳና»፣ «ወሰፈን»፣ «ምጋቾች» እና «በቀናት መካከል») የተወሰኑትን በምሳሌነት እያነሣን ከታሪክ ነገሩ፤ ከፍሰት እና ከይዘት እንዲሁም ከትወና አንፃር እንመለከታለን።

አንድን የድራማ ክፍል በሳምንቱ ለማድረስ ያለውን ውጣውረድ አልፎ ሥራውን ለታዳሚ ማድረስ ቀላል ነገር አይደለም። ተዋንያኑን አሰማምዶ፤ ቀረፃ ቦታ አስፈቅዶም ሆነ ተከራይቶ፤ የቡድን አባላትን ሰብስቦና አቀናጅቶ፤ አልባሳትና የቀለሳበ ችግሮችን ተወጥቶ፤ ቢሮክራሲያዊ አሠራሮችን ተሻግሮ እንዲሁም ኤዲቲንግ አጠናቅቆ ማቅረብ በርግጥም ይህ ነው የሚባል የፈረም እንዳልሆነ በሌላት ሀገር በቀላሉ የሚታይ አይደለም። እነዚህ ችግሮች እንዳሉ ሆነው ቢያንስ ቢታረቅ፤ በትወና እና ብዙ ቴክኖሎጂ በማይጠይቁ የገሃድች ሒደቶች ተጠቅሞ የተሻለ ሥራ መሥራት የባለሙያው ድርሻም ኃላፊነትም ነው።

ከላይ የተጠቀሱት ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማዎች በአብዛኛው ተመሳሳይ የሆነ ችግር ይታይባቸዋል። በአንድ ሰው የተጻፉና የተዘጋጁ እስኪመስል ድረስ፤ አንድ ዓይነት ችግርን መጋራታቸው ግር የሚያሰኝ ነው፤ ግን እውነት ነው። አንዱና ዋናው (አብዛኞቹ የሚጋሩት) ችግር፤ በደራሲ ሜልዶ ገብቶ የሚመሩ ሕይወት እና ማንነት ያላቸው ገጸ-ባሕርያት ስፋ ብለው መታየታቸው ነው። በምናብ ዓለም የምንቀርጻቸው ገጸ-ባሕርያት የራሳቸው የሆነ ከፋብን ማንነትን ምሉዕ በሆነ መንገድ ተላብሰው መቀረፅ እና በድርሰቱ ውስጥም በዛው መንገድ መጓዝ ይኖርባቸዋል። ነገር ግን ከዚህ የድርሰት ድንጋጌ ፍጹም ባፈነገጠ መልኩ የድራማዎቹ ደራሲያን በገጸ-ባሕርያት ሕይወት ያለ ምንም ምክንያትና መብት ጣልቃ እየገቡ እንዳሻቸው ሲዘውሯቸው ይስተዋላል። ለአብነት ያህል፤ ከ«ሚዜሜ» ግሩም፤ ከ«መለከት» አዳራታና ፍሥሐ፤ ከ«ምጋቾች» ክበበ የተሰኙትን ገጸ-ባሕርያት መጥቀስ ይቻላል። እነዚህ ገጸ-ባሕርያት ለሚያደርጉት ነገርና ለሚወስዱት እርምጃ በቂ የሆነ ምክንያት ሳይኖር፤ ብቻ በሆነ አጋጣሚ ውስጥ መገኘት ሲኖርባቸው፤ ከማንነታቸው የመነጨ በማይመስል ድርጊት ውስጥ መግባታቸው በርግጥም ደራሲያኑ በብዕራቸው ቀጥቅጠው ሥር አውለው እንዳሻቸው የሚዘውሯቸው ገጸ-ባሕርያት መሆናቸውን በግልጽ አረጋግጡ።

ለድራማው ታሪክ ሒደትና ለሚፈሰው ጥምረት ምንም ፋይዳ የሌላቸው ትዕይንቶችን መጨመር ሌላው የጋራ ችግራቸው ነው ብዬ አምናለሁ። በመሠረቱ ለታሪኩ ሒደት ምንም የማይጨምር፤ ተቀርጾ ቢጠፋ አንዳች የማያጎድል ትዕይንት በተደጋጋሚ ይታያል። ትዕይንትና ድርጊት ይቅርና፤ በአንድ ክፍል ቀረፃ ውስጥ እንኳ የምትኳትት እያንዳንዷ ነገር መነሻም ሆነ መድረሻ ምክንያት ሊኖራት ሲገባ፤ ትዕይንትን የሚያህል ሰፊ ክፍል ያለ ምክንያት ሲያስገቡ ይታያል። ችግሩ ከአማተርና ጀማሪ ደራሲ እንኳ የማይጠበቅ ቢሆንም (አዘጋጆቹ ስሕተቱን መድገማቸው እንዳለ ሆኖ) «በዓለም አቀፍ ደረጃ» በሚተላለፉ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች ያውም በተከታታይ ድራማነት መቅረባቸው ችግሩ ከደራሲው ተሻግሮ በአዘጋጁ አልፎ ዝምታ ጋሚው እስከ ድረስ የሚዘልቅ መሆኑን ያሳያል።

ከተወሰኑ ክፍሎች ወዲህ ትንሽ መሻሻል ቢያሳይም፤ «ምጋቾች»ም የዚህ ችግር ተጠቂ ነው። በተጨማሪ «መለከት»፣ «ሚዜሜ» እና «ዳና» በሰፊው የሚጋሩት አንድ ክፍተት ነው። ይህም የድራማዎቹን የሰዓት ቆይታ ከድርሰት ሕግጋት በሚሻልስ መልኩ ለማርዘም ሲባል ሆን ተብሎ የተደረገ ነው - በእኔ እይታ። ከ«ሚዜሜ» ድራማ አንዳ ማሳያ እንጥቀስ፤ ግሩም የተባለው ገጸ-ባሕርይ ከሚስቱ ጋር በሪብ ሀገር ሄዶ ከዘሪዎቹ ጋር የሚያደርገውን ቆይታ የሚያሳየውን ትዕይንት እንውሰድ፤ የትዕይንቱ ጥቅም ምንድን ነው? ይህ ትዕይንት ለታሪኩ ሒደት ያለው አስተዋፅኦ የቱ ጋር ነው ያለው? ተቀርጾ ቢጠፋ ምን ያጎለ? እንግዲህ እነዚህ ጥያቄዎች መልስ ካላቸው ጥሩ፤ ካልሆነ ግን ትዕይንቱ ያለ ምክንያት መግባቱንና አላስፈላጊ መሆኑን ያመለክታል።

### ጉዘት

በተመሳሳይ ድራማዎቹ ከጉዘት (Tempo) አንፃር ሰፊ ክፍተት አለባቸው። እጅግ የቀዘቀዘና በዝግታ የሚጎተትም ታሪክ በሁሉም ድራማዎች ላይ የሚታይ ችግር ነው። ተመልካች ለአፍታም ቢሆን ከቴሌቪዥን መስኮት ሳይነቀል እንዲከታተል የሚያደርግ አቅም ይጎድላቸዋል። እንደ ሬዲዮ በድምፅ ብቻ ብንሰማቸው እንኳ «ይህ ቀረብኝ» ብለን የምንቆጭባቸው ዓይነት አይደሉም።

### ትወና

ከትወና አንፃር ድራማዎቹን ስንመለከት፤ በአብዛኛው ጥሩ ሆነው አናገኛቸዋለን። በተለይ ልምድ ያላቸው ተዋንያን በተሻለ ብቃት ይተውናሉ። ሁሉም ባይባልም፤ በጀማሪዎቹ ላይ ግን ሰፊ ክፍተት ይታያል። ከድምፅ አውጣጥ እስከ አካላዊ እንቅስቃሴ የሚደርስ የሚደርስ መሠረታዊ ያለታወቁ ታል። «አስተወን ነው» ዓይነት ስሜቱ ትወና ተዋናዮ ብቻ ሳይሆን፤ አዘጋጆቹም ሥራውን በአግባቡ እንዳልተወጡ ያሳያል። «ብኩ ሥራ»፣ «በቀናት መካከል»፣ «መለከት» እና «ሚዜሜ» የሚስተዋልባቸው የትወና ችግር ልምድ ያላቸው ተዋንያን ጭምር የሚጋሩት ነው።

### መልዕክት

ድራማዎቹ የተመለከቱ ዕድሜ ገደብ ደረጃ (PG) ያልወጣላቸው ናቸው። በተለይ በሕፃናትና ታዳጊዎች ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ትዕይንቶችን በዘፈቀደና በማንአለብኝነት ያቀርባሉ። ከሕጻናቱ ጋር ሰብሰብ ብሎ ለሚታደም ኢትዮጵያዊ ወላጅ የማይመጥኑ ትዕይንቶች ከሚታዩባቸው ድራማዎች አንዱና ሰፊ ድርሻ ያለው «መለከት» ነው። ለዚህ ደራሲው፤ አዘጋጁ፤ ፕሮዲውሰሩና እና ተዋንያኑ ተጠያቂ ተወቃሾች ናቸው። ይህን የሚያቀርበው የቴሌቪዥን ጣቢያም ሆነ ያፀደቀው ዝምጋሚ አካል ለችግሩ መፈጠር ከመቻቻት መንገድ አንፃር ከተጠያቂነት አይተርፉም።

### በመጨረሻ

ዛሬ በቴሌቪዥን የሚቀርቡት ተከታታይ ድራማዎች በአንድ ክፍል አንድ ጉዳይ ገልጦ በጠንካራ ምክንያት በመጫር ምን ሊሆን ይችላል የሚል ጥያቄ ፈጥሮ የመግዛ ክፍተት ይታይባቸዋል። ገጸ-ባሕርያት ቆመው አልያም ተቀምጠው ሲያወሩ፤ እንደ ወሬ ወዲህና ወዲያ ሲያመላልሱ የሚታዩ ናቸው። ይህም ጥበባዊ ፋይዳቸው ገቶ ያለ እንዲሆን ያደርጋቸዋል።

በአለበት፤ በኢቢኤ የሚተላለፉትን ድራማዎች ዝምታም ያሳለፈው ኮሚቴ (በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቴአትር አርት ትምህርት ክፍል የተወጣጡ ናቸው) ከላይ የቀረቡትን ችግሮች ለምንና እንዴት እንዳለፏቸው ግልፅ አይደለም። በበኩሌ በዘርፉ ካላቸው እውቀትና ልምድ አንፃር ችግሮቹን ሳይረዱ ቀርተው እንዳልሆነ አምናለሁ።

ያም ሆነ ይህ፤ ሁሉም የድርሻውን በአግባቡ ቢወጣ፤ ለጥበብ ያለውን ታማኝነት ጥያቄን ክፍተቶችን በመድፈን ቢያሳይ፤ ለዘርፉ ዕድገት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ቀላል አይሆንም። በዚህም ቢያንስ ከሰባራ ታሪክና ትወና ተላቅቀን፤ የተሻለ ሥራ መሥራት እንችላለን። ጥበብ ገንዘብ ማግኛ ሳይሆን፤ ኅብረተሰቡን አገልጋይ የሚያሳውቅ ዓይነተኛ መንገድ መሆኑን አምነን በአግባቡ እንጠቀመው።

መልካም ጊዜ!

# ዝምታ ሰላም አይደለም! ፕሮፓጋንዳም ዕድገት አይሆንም!



ግርማ ሠይፉ ማሩ
girmaseifu32@yahoo.com;
www.girmaseifu.blogspot.com

**“በተፈጠረው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ <<ሀገር አለን፣ መንግሥት አለ>> ብለው በሰላም ሐሳባቸውን ለመግለፅ ወጥተው ሳይመለሱ የቀሩ ዜጎች ደምና ሕይወት በተራ የፎረም ፕሮፓጋንዳ ስብሰባ በሚሰጥ የአቋም መግለጫ የሚፈወስ አይደለም። በዚህች ሀገር ሕዝብን ያማከለ ልማትና እድገት እንዲኖር ካስፈለገ፣ ዜጎች ሃሳባቸውን በመግለፃቸው የሀይወት መስዋዕትነት መክፈል ማቆም ይኖርባቸዋል። ለእስከ ዛሬው የተከፈለው መስዋዕትነትም ተገቢውን ማካካሻ በማድረግ ብሔራዊ እርቅ እንዲሰፍን መስራት ይኖርብናል**

ሰሞኑን በማኅበራዊ ሚዲያዎች ላይ ተሳትፎ የሚያደርገው ሰው ጤና መሆኑን መጠራጠር የግድ ብሎኛል:: እንዴ ውጭ ሀገር ሆኖ እንደ እርሱ ካላትራራህ ይለኛል:: ለሌው ማንነቱ እንዳይታወቅ መሸሸ እየጻፈ ይፎክርና እንደ እኔ ፎጋሮ ይለኛል:: ለማንኛውም ሁላችንም እንዲቀማችን፣ እንደ ችሎታችንና ምናልባትም እንደ ድፍረታችን ደረጃ ለምናደርገው የነጻነት ትግል ክብር ብንሰጠው ጥሩ ይመስለኛል:: ሲመስለኝ ፈሪ መሆንም መብት ነው! ሰው እንዴት ለምን ትፈራለህ ይባላል?! ባይሆን ፈሪ እንደ እኔ ፍሩ ቢል ነው እይ ሲባል የሚገባው:: በእኔ እምነት የዚህች ሀገር የወደ ፊት ዕጣ-ፈንታ ሊወሰን የሚገባው በሐሳብ ክርክርና በዚሁ በሚገኝ የበላይነት ብቻ መሆን አለበት:: ለዚህም ነው፣ ሁሉም የማይስማማበት ቢሆን እንኳ «የእኔ ሐሳብ ይህ ነው» ብሎ ለመግለፅ የምወደው:: ይህን አካሄድ ያለመወደድ መብት ቢሆንም፣ «የእኔን ውደድ» ብሎ ማስገደድ አይቻልም::

ይህን ከሰሞኑ የማኅበራዊ ሚዲያዎች የጽሑፍ ምልልሶች መነሻ አድርጌ ካልኩኝ፣ ለዛሬ ጽሑፌ መነሻ ያደረግኩት ለአንድ ሳምንት በማኅበረ ቤት ወሰ እንዳይቀር «ሊመከርበት» የከረመው የሁለተኛው ዙር የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድና የሰሞኑ «የተቀናጀ ማስተር ፕላን እንዳሉ» በሚል መነሻ በኦሮሚያ ክልል የተቀሰቀሰው ንቅናቄ፣ በጎንደር የተፈጠረው ግጭት፣ እንዲሁም ድርቅ መነሻ ሆኖ የተከሰተው ርሃብ እንደምታ ምን ሊመስል እንደሚችል በአጭሩ የግል እይታዬን ለማስቀመጥ እሞክራለሁ::

ነገሮቻችን አፍረት የሚባል ነገር እንደሌለባቸው የሚያስታውቀው የመጀመሪያውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ በቤት ማጠናቀቃቸውን ሲነግሩን እፍረታቸውን እንኳ ዓይናቸ ያለማድረጋቸው ብቻ ሳይሆን፣ በምክር ቤት ውስጥ ለተሰበሰቡት እጅ በማውጣት ደግመው ለሚከፈላቸው ሳይሆን በሚዲያ ለሚከታተላቸው ሕዝብም ያላቸውን ንቀት የሚያሳይ ነው:: በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ በዋናነት ከተቀመጡት ግቦች የተሳካ የሚባል አንድም ነገር የለም እንዳይባል (ጥራት በሌለው ትምህርትና ጤና የቁጥር ስኬት መኖሩ አይካድም)፣ ከዚህ በስተቀር መብራት 10 ሺ ሜጋ ዋት ብለው ሰባት ሺ ያለመድረሳቸው፣ ባቡር 2395 ኪ.ሜ ታቅዶ እስከ አሁን ስራ ያልጀመረውን የአዲስ አበባ ድሬዳዋን ብንወስድ 700 ኪሎ ሜትር እንደማይሞላና ይህም ዕቅዱ የውሸት ሀገብ ማግለያ እንደ ነበር ነው:: በግብርና ዘርፍ በዛሁ ሚሊዮን የውጭ ምንዛሬ ያስገኛል የተባለው ዕቅድ የተያዘለት፣ የተማለሙሽ መንግስት በውጭ ምንዛሬ ስንዴ መግዛት ውስጥ መግባቱ ይታወቃል:: ባለፈው አምስት ዓመት «ከፍተኛ የእድገት ምጣኔ አስመዝግቧል» የተባለው ግብርና ነው ብለው ሚሊየነር እርሶ አደር ብሎ መሸለሙን ሳይጠናቀቅ በድርቅ ተሳክቶ 15 ሚሊዮን የሚጠጋ ህዝብ የሚላስ የሚቀመስ ማጣቱ መሬት የያዘ ሀቅ ነው:: እነዚህ ለማሳያ የቀረቡትና ሌሎችም ራሳቸው ያመኑት የውጭ ንግድ ዘርፍ ያለመሳካት ተጨምሮ ከመረቀትና ቶስራ ያላለፈው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ በቤት አጠናቀናል ይሉናል:: ይህ እቅድ አልተሳካም የሚሉት ምን ቢሆን እንደ ነበር ግን ሊነግሩን አልቻሉም:: ቢሆንም በቤት ተጠናቋል እያሉን ነው:: በአንድ ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ትምህርት እንማራለን ማለታቸው የሚታወስ ቢሆን፣ እቅዱ ግን ለትምህርት መቅሰሚያ ነው አላሉንም ነበር::

ቀጣዩ ዕቅድ በሚመለከት በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመን ከነበረው ሁኔታ በባሰ በጀምሩ የታየው እጅግ አሳሳቢ ጉዳይ ደግሞ በኦሮሚያ እና በጎንደር አካባቢ የዜጎችን ህይወት እስከመቅጠፍ የደረሰው ህዝባዊ እንቅስቃሴ ሲሆን በመላ ሀገሪቱ የተከሰተውም ድርቅ መነሻ ያደረገው ርሃብ እንዱ ነው:: ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ ሲገለፅ የነበረው ነገር «የጥያቄ/ትዝምታ መኖር»፣ የሰላም ምልክት እንዳልሆነ» ነበር:: የተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት በኢትዮጵያ ካለው ዘርፍ ያለው ቋንቋ መሠረት ያደረገ ፌዴራሊዝም፣ እንዲሁም በተለያየ ወቅት የነበሩ የእርስ በእርስ ግጭቶች፣ እሁንም በሀገሪቱ ለመድበለ ፓርቲ እንዳይመሠረት ገዢው ፓርቲ የዘጋው በር፣ ሀገራዊ መግባባት ለመፍጠር የሚያስመስል ከተለያየ መስመር የሚቀርቡ ብሔራዊ ዕርቅ ጥያቄዎች ወዘተ ...ተገቢው ምላሽ ያለማግኘታቸው በሀገራችን ዘላቂ ሰላም ለማምጣት አስቸጋሪ እንደሆንም ተገልጿል:: ዘላቂ ሰላም በሌለበት ደግሞ እድገት የሚባል ነገር ሊታሰብ የሚችል አይደለም:: በቅርቡ በኦሮሚያ አካባቢ በተፈጠረው እንቅስቃሴ ምክንያት ወደ ሀገር ውስጥ መዋዕለንዋይ ካፈሰሱ ግንባር ቀደም የሆነው የዳንጎቴ ሲሚንቶ ፋብሪካ ላይ እንዲፃፍ ነበር የተባለው አደጋና ሌሎች ችግሮች ለሌሎች በዚህ ሀገር ኢንቨስት ለማድረግ ለሚፈልጉ ኢንቨስተሮች መልዕክቱ ምን ሊሆን እንደሚችል ግልፅ ነው:: ከፍተኛ የውጭ መዋዕለ ንዋይ ፍሰትን ያለት ሀገራችን እስከ አሁን ያለውን ያህል የውጭ ገንዘብ ለማግኘት በሚቀጥለው አምስት ዓመት የምትችልበት ሁኔታ አይኖርም የሚል ግምት አለኝ:: ይህ ደግሞ የሚሆነው የውጭ ኢንቨስተሮች መረጃ የሚያገኙት ከኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ሳይሆን ዓለም አቀፍ ባለሞያዎች ከሚሰጡት ትንታኔ ነው:: መንግስት እንደሚለው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች የሚሰጡት መግለጫ እና የሚያወጡት ሪፖርት ዋጋ ቢስ አይደለም:: እነዚህ ባለሀብቶች የት ሀገር ቢሄዱ በሰላም እንደሚሰማሩና የተሻለ ትርፍ እንደሚያገኙ መረጃ የሚያገኙበት ምንጭ ነው::

የውጭ ኢንቨስተሮች ብቻ አይደለም ከአሁን በኋላ የሀገር ውስጥ ባለሀብትም ቢሆን ዘላቂ ሰላም በሌለበት ሁኔታ ኢንቨስት የሚያደርጉበት ሁኔታ እጅግ ዝቅተኛ ነው የሚሆነው:: ከዚህ በፊትም ሲያደርጉ ከነበረው ያነሰ ይሆናል ማለቴ ነው:: ከዚህ በፊትም ቢሆን ቀላል የማይባሉ ኢትዮጵያውያን ከሀገራቸው ውጭ መሥሪያትን በተለይ በምሥራቅና ደቡብ አፍሪካ ሀገሮች አካባቢ ምርጫቸው እንደሚያደርጉ ይታወቃል:: አሁን ያለው ሁኔታ ደግሞ የከፋ ጊዜ ነው:: ባለፈው የዘኪያዎችና ንግድክ ባለሥልጣን ሹም በመሰሉና ሲታሰሩ ከሀገር ተሰናብተው የወጡ ነጋዴዎች ያሳዩትን የደስታ ምንጭ ትዝ ይለኛል:: ትንንሾቹ ሲታሰሩ ለውጥ የሚመጣ መሰሏቸው!

በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ውስጥ መንግሥት እጁን በማስረዘም በከፍተኛ ደረጃ ኢንቨስትመንት ውስጥ ይሳተፋል:: ይህ የመንግሥት ተሳትፎ ደግሞ መሠረት ያደረገው ከውጭ መንግሥታትና ዓለም አቀፍ አበዳሪዎች ከሚገኝ ብድር እንደ ሆነ ይታወቃል:: በሀገር ውስጥ የተፈጠረው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ በግልፅ ወጥቶ ከመታየቱ በፊትም ሀገሪቱ ያለባት የብድር ጫና ከፍተኛ መሆኑን ሪፖርት እያደረጉና ጥንቃቄ እንዲወሰድ ሲመከሩ ነበር:: በዚህ ሁኔታ ላይ እንደ ከዚህ ቀደሙ ከፍተኛ ብድር ይሰጣሉ የሚል ግምት መውሰድ የዋህነት ነው:: ይልቁንም ይህን አጋጣሚ ተጠቅመው ብድሮቹን ከማግኘት በፊት እንዳንድ የማሻሻያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ግፊት ያደርጋሉ:: አሁን በግልጽ እያየነው ያለው እውነትም ዜጎች በረሃብ አደጋ ላይ ሆነው እያለ እርዳታው በቁጥ ቁጥ የሆነበት ሁኔታ «በምግብ ራሳችንን ችለናል» የሚለውን መንግሥት ከወደቡ ጎንበስ ብሎ እስኪለምን ድረስ እንደ ሆነ ይታወቃል:: በቅርቡ እንደሰማነው ቶሎ ከሆነ ደግሞ መንግሥት በራሱ አቅም ርዳታ እንደሚሰጥ ነው:: ውጤቱን አብረን የምናየው ይሆናል::

የረሃቡን ጉዳይ ካነሳን «ኤል ኒኖ» ወቅታዊ ክስተት በሰሆን ማለፉ አይቀርም፤ ጥሩ የሚሄደው ጠባሳ ግን በአንድና ሁለት ዓመት የምንወጣው አይደለም:: ለእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ትግበራ 15 ሚሊዮን ሕዝብ ከዚህ ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆነው አምራች ዜጋ ምንም ሚና የለውም ሊባል አይችልም:: ይህ ሕዝብ ለዕድገት እሴት ከመሆን ይልቅ ለሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የመቋቋሚያ ዝቤው ነው የሚሆነው:: የጠፉብትን እንስሳት ተክቶ ወደ ትርፍ እና ቁጠባ ለማምራት በዚህ አምስት ዓመት ውስጥ አይችልም:: ይህ ደግሞ በእድገት ላይ የራሱ ሚና ይኖረዋል:: መንግሥት ይህም ሆኖ ግን እድገታችን እንደተለመደው በአስማት «በሁለት አሃዝ እድገት» ማለቱ አይቀርም:: የንብስ ወከፍ ገቢያችንም እንዲሁ ይጨምራል::

ለዚህ ቀጣዩ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ አሁን ሀገሪቱ ካለችበት ያልተረጋጋ ሁኔታ፣ እዚህም እዚያም የሚከሰቱ ግጭቶችና ግጭቶችን መንግሥት የሚፈታበት ኃይልን መሠረት ያደረገ አካሄድ ለሀገሪቱ እጅግ አስፈሪ የሆነው የውጭ ኢንቨስትመንት በሚጠበቀው ያህል ሊመጣ አይችልም:: የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችም ቢሆኑ ተሳትፎቸው በአጭር ጊዜ ውጤት ከሚያመጡ ንግዶች ሊዘል አይችልም፣ ቢኖርም በተለመደው አዲስ አበባና አካባቢዋ ብቻ ይሆናል:: ይህ በአንዲህ እንዳለ፣ አሁን ከፍተኛ አደጋ ተጋርጦ ያለው የዜጎች የሚላስ የሚቀመስ ማጣት አጠቃላይ ሀገራዊ አቅምን በሚፈትን መልኩ ለልማት የሚውልን ገንዘብ ወደ እለት ደራሽ እርዳታ እንዲውል ከማድረጉም በላይ አጭር ለማይባል ጊዜ የሚቀጥል የማቋቋሚያ ወጪን ይጠይቃል::

እነዚህ በጥሜይ ፈታኝ ሁኔታዎች ሲሆኑ በተለይ በተፈጠረው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ «ሀገር አለን፣ መንግሥት አለ» ብለው በሰላም ሐሳባቸውን ለመግለፅ ወጥተው ሳይመለሱ የቀሩ ዜጎች ደምና ሕይወት በተራ የፎረም ፕሮፓጋንዳ ስብሰባ በሚሰጥ የአቋም መግለጫ የሚፈወስ አይደለም:: በዚህች ሀገር ሕዝብን ያማከለ ልማትና እድገት እንዲኖር ካስፈለገ፣ ዜጎች ሃሳባቸውን በመግለፃቸው የሀይወት መስዋዕትነት መክፈል ማቆም ይኖርባቸዋል:: ለእስከ ዛሬው የተከፈለው መስዋዕትነትም ተገቢውን ማካካሻ በማድረግ ብሔራዊ እርቅ እንዲሰፍን መስራት ይኖርብናል:: ሀገራችን የጋራችን ሃሳባችን የጋራችን ነው::

ቸር ይግጠመን!






# ደጀኔ ብሩ
## ባህላዊ ሕክምና አገልግሎት

ሐኪም ደጀኔ ብሩ ይባላሉ:: ለረጅም ዘመናት በባህል ህክምናቸው በስፋት ይታወቃሉ:: በዘመናዊ ሕክምና ሊድኑ ያልቻሉ በርካታ በሽታዎችን በአጭር ጊዜ የመፈወስ አቅምና ችሎታ አላቸው:: ለረጅም ጊዜ ባደረጉት የህክምና አገልግሎት ለአያሌ ወገኖች ፈውስ ሰጥተዋል:: በዚህ ባህላዊ ሕክምናቸው እየተፈወሱ ላሉ ወገኖች ከፍተኛ እርካታ እንደሚሰማቸው ይናገራሉ::

ስንፈተ ወሲብ ለ7 ተከታታይ ቀናት በትክክል ከተጠቀሙ ሙሉ በሙሉ ፈውስ የሚሰጥ መድኃኒት አለን::ለአስማት ማርከሻና ለአልማዝ ባለጭራ በሽታ ሙሉ በሙሉ የሚያድን ፈውስ የሚሰጥ የባህል መድኃኒት አላቸው: :መድኃኒታቸው ከሆድ ውስጥ በሚመነጭ ደዌ የተነሳ በአፍ ውስጥ የሚፈጠር መጥፎ ጠረንን የሚያስወግድና በተጨማሪም መጥፎ የአፍንጫ ጠረን የሚያጠፋ የባህል መድሃኒት አላቸው::

አብዛኞቹ መድኃኒታቸውን መውሰድ ከጀመሩበት ዕለት ጀምሮ ሚፈወስ እንደሚችሉ ሚረጋገጡን የሚገልፁት ሐኪም ደጀኔ ከእነዚህም ወስጥ ለጨብጥ ፤ለልክፍት ፤ለጆሮ ሰብ ፤ለሌት አልጋ ላይ ሽንት ለሚያመልጣቸው ፤ለጨጓራ ፤ ለሚርት ፤ ለራስ ምታት ፤ ለወባ ዕለቱን ፈውስ ይገኝላችዋል:: ከዚህም በተጨማሪ ለወሲብ ድክመት ችግር፣ ለለምጥ፣ ለኪንታሮት፣ ለነቀርሳ ፤ ለወፍ(ለጉበት)፣ ለችፌ፣ በደረቁና እየቆሰሉ ለሚያሳክክ ለሚጥል(ኤፒሊፕስ)፣ ለጆሮ መግል፣ ለቋቁቻ፣ በሆድ ውስጥ በሚፈጠር ለጆሮ መግል፣ ለቋቁቻ፣ በሆድ ውስጥ በሚፈጠር ደዌ የአፋቸው ና የአፍንጫቸው ጠረን ለሚሸትባቸው፣ ለጭንቀትና ለድብርት ፤ ለሪህ በሽታ መድኃኒቱ በትንሹ ለ3 ቀን ቢበዛ ለ7ቀን በተከታታይ ከወሰዱ ይፈወሳሉ:: በተጨማሪም ለአስማት ማርከሻ እንዲሁም የብዙዎች ችግር የሆነው የአስም በሽታ እንደ እድገት ደረጃው ደለያያል የሚሉት ሐኪም ደጀኔ ብሩ ለአፍንጫ ሳይነስ በ7ቀናት ፤ በአፍንጫ ወደ ጉሮሮ እየወረደ ላለ በ15 ቀናት፣ ደረት ላይ ለደረሰው በ21 ቀናት በባህል መድኃኒታቸው ሙሉ ለሙሉ እንደሚያድኑ ያረጋግጣሉ::

ማየት ማመን ነው እና መጥተው ይጎብኙን!!

የስራ ሰዓት:-
ዘወትር ከሰኞ እስከ ቅዳሜ
ጠዋት ከ2-7 ሰዓት
ከሰዓት -ከ9 እስከ 12 ሰዓት

### በተጨማሪ
የአስም ወይም የፕሮንካይት መድኃኒት አዘገጃጀት፣ የአፍንጫና የሳይነስ፣ የቆዳ ካንሰር፣ መጥፎ የአፍ ጠረን መድኃኒት አዘገጃጀት፣ መጥፎ የአፍ ጠረን ፤ የጨጓራ በሽታ፣ የጉበት በሽታ፣ የምግብ መመረዝ፣ የአልማዝ ባለጭራና ሌሎች ፈዋሽ መድሃኒት አዘገጃጀት የምስክር ወረቀት ከኢትዮጵያ አእምሮ ፅ/ቤት የተሰጠን መሆኑን በደስታ እንገልፃለን::

ስልክ :-0911-201273 /0913/040515 ፖስታ 180708